# «መጻሕፍተ ብሉያት»

## ፫ቱ

**እሉ እሙንቱ**

- ኦሪት ዘሌዋውያን
- ኦሪት ዘኍልቍ
- ኦሪት ዘዳግም

ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

አንድምታ ትርጓሜ

አሳታሚ ፡፡ - ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
፲፱፻፺፱ ዓ.ም
አዲስ አበባ፡፡

አዲስ አበባ
፲፱፻፺፱ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## መግለጫ

### «መጻሕፍት አምላካውያት»

**ልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን «እንዲህ ብለህ ጻፍ፤ እንዲህ ብለህ ተናገር » እያለ ድምጹን እያሰማ ፣በራዕይ እየገለጠ ፣ በልቡና እየቀረጸ እንዲጻፉ በማድረጉ፤ «መጻሕፍት አምላካውያት» ተብለዋል::(ዘፀ ፴፬ :፳፯ ፣ ዘዳ. ፴፩ :፲፱፣ ኢሳ.፰ ፣ ፩፣ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፪ )**

በመሆኑም በቅድሚያ ወደ ሀገራችን የገቡና በሀገራችን ቋንቋ በግእዝ የተተረጐሙ መጀመሪያዎቹ የኦሪት መጻሕፍት እንደሆኑ በቃልም በጽሑፍም የተረጋገጠ ነው ፤ እነዚህም መጻሕፍት :- አምስቱ ብሔረ ኦሪት ተብለው ይጠራሉ፤ ብሔረ ኦሪት ሲባልም አንቀጸ ኦሪት፣ ወይም አንቀጸ ሕግ ለማለት እንደሆነ ግልጥ ነው ፤ አምስቱ ብሔረ ኦሪት የሚባሉትም ከዘልደት እስከ ዘዳግም ያሉት መጻሕፍት ናቸው፤ ሁሉም በነቢዩ ሙሴ የተጻፉ መሆናቸው በቤተ አይሁድና በቤተ እስራኤል ይታመናል::

ከዘፀአት እስከ ዘዳግም ሕግ ያሉት አራቱ መጻሕፍት በአንድ ሺህ አምስት መቶ /፩ሺህ፭፻/ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ገደማ እስራኤል ከግብጽ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ሙሴ እስካረፈበት ዘመን ድረስ በአርባው ዓመታት ውስጥ የተነገሩና የተጻፉ ናቸው፤ መጀመሪያው መጽሐፍ ኦሪት ዘልደት /ዘፍጥረት/ ግን የተነገረ ከዚያ በፊት ሲሆን የተጻፈውም እንደ ሌሎቹ መጻሕፍት በሙሴ እንደሆነ ከጥንት ጀምሮ ይታመናል::

ከክርስትናበፊት በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ያለው የአምልኮት ሥርዐትና የመሥዋዕት አቀራረብ፣ የሰንበት አከባበርና የመሰለው ሁሉ በሀገራችን ተሠርቶበታል፤ ከክርስትናውም በኋላ አምስቱ መጻሕፍት ለሐዲስ ኪዳን ትንቢትና ታሪክ ፣አምሳልና መርገፍ እንደ መሆናቸው ከመሥዋዕቱና ከሥርዐተ አምልኮቱ በቀር ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሕጋቸውና ትእዛዛቸው ፣እንደዚሁም ትምህርታቸው ዛሬም እንደ ተጠበቀ ነው::

አምስቱ ብሔረ ኦሪት ከሚለው ስያሜ ሌላ «ስምንቱ ብሔረ ኦሪት » የሚል ስያሜ በቤተ ክርስቲያናችን አለ ፤ ስያሜው የተወ

www.ethiopianorthodox.org

ረሰው ከሰብዓ ሊቃናት ነው፤ይኸውም የኢያሱ ፣የመሳፍንትና የሩት መጻሕፍት በአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ላይ ተደምረው ነው።

ከዚህም የተነሳ በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት ሦስቱ መጻሕፍት ማለትም ኦሪት ዘኢያሱ፣ ኦሪት ዘመሳፍንት፣ ኦሪት ዘሩት ተብለው ይጠራሉ፤ነገር ግን ሦስቱ መጻሕፍት የታሪክ መጻሕፍት እንጂ እንደ አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ የኦሪት ወይም የሕግ መጻሕፍት አይደሉም ፤ በዚህ ይዘት ኦሪት ዘኢያሱ ሲባል መጽሐፍ ዘኢያሱ ወይም መጽሐፈ ኢያሱ ለማለት እንደሆነ ግልጥ ነው ።

ሦስቱ ከአምስቱ ጋር ተደምረው ስምንቱ ብሔረ ኦሪት መባላቸው ግን አይሁድ ከአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ቀጥሎ እነዚህን ሦስት መጻሕፍት ተቀብለው ስለያዟቸው እና የታሪክ ይዘታቸውም ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ታሪክ ጋር ተከታታይነት ስላላቸው ነው ፤ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የሰጣቸው ተስፋ ከግብፅ ምድር የእስራኤል መውጣት ብቻ አልነበረም፤የተስፋው ፍጻሜ ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን መግባታቸው ነበር / ዘፍ.፲፪ ፡ ፪-፫ ፤ ፲፭ ፡ ፲፰-፳፩/ ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣትም ምድረ ርስትን ከመውረስ ተነጥሎ አይታይም፤ በመሆኑም መጽሐፈ ኢያሱ ምድረ ርስት ለነገደ እስራኤል እንዴት እንደ ተከፈለች ስለሚያብራራ የርስቱንም አከፋፈልና አመዳደብ ሥርዐት ስለሚናገር ከመጻሕፍተ ሙሴ ጋር ተያይዞ በመከብበ ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ተብሏል።

የመጽሐፈ መሳፍንትና የመጽሐፈ ሩት ታሪክም አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ እንደተጻፉበት ዘመን የእስራኤል ልጆች ንጉሥ ሳያነግሡ እግዚአብሔር አምላካቸውን ንጉሣቸው አድርገው ይኖሩ በነበረበት ዘመን /መሳ.፲፰ ፡ ፩ ፤ሩት ፩ ፡ ፩/ ስለተፈጸመ እንደ መጽሐፈ ኢያሱ ከአምስቱ መጻሐፍተ ኦሪት ተደምረው ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ወይም ስምንቱ መጻሕፍት ተብለዋል።

## ✠ ዘሌዋውያን

ኦሪት ዘሌዋውያን አምስቱን የመሥዋዕት ዐይነቶች / ዘሌዋ. ምዕ. ፩ ፡ ፭/ ሥርዐተ ክህነትን፣ የተቀደሱ በዓላትንና የተለያዩ ሕጎችን ያስረዳል ።

## ✠ ዘኁልቊ

ኦሪት ዘኁልቊ እስራኤል ወደ ተስፋዪቱ ሀገራቸው ለመግባት አርባ ዓመታት በሲና ምድረ በዳ መንከራተታቸውን፣ አንድ ጊዜ በሲና፣ /ምዕ.፩/ ሁለተኛ ጊዜ ከሞአብ ሜዳ / ምዕ. ፳፮/ መቆጠራቸውንና ከሃያ ዓመት ዕድሜ በላይ ያለው እስራኤላዊ ሁሉ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ወደ ተስፋዋ ሀገር /ምድር/ እንዳይገባ በእግዚአብሔር መወሰኑን ይናገራል። / ምዕ. ፲፬ ፡ ፳፱ - ፴/።

## ✠ ዘዳግም

ኦሪት ዘዳግም ከግብጽ የወጡት ከሃያ ዓመት በላይ የነበሩት አበው በምድረ በዳ ከሞቱ በኋላ ወደ ከነዓን እንዲገቡ ለተፈቀደላቸው ውሉድ፣ ሙሴ በሦስቱ መጻሕፍት በዘፀአት፣ በዘሌዋውያንና ዘኁልቊ የተመዘገበውን ታሪክ፣ ሕግና ትዕዛዝ ከማስጠንቀቂያ ጋር በድጋሚ መናገሩን የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው፤ የሙሴን ሞትና በሙሴ ፋንታ የአመራሩን ኃላፊነት ኢያሱ መረከቡንም ይገልጣል።(ምዕ. ፴፬ ፡ ፰)።

ይሁን እንጂ ከብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍት ፦

፩. ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ፪. ትንቢተ ኤርምያስ፣ ፫. ትንቢተ ዳንኤልና አሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት፤ ፬. መጽሐፈ ጦቢት ፭. መጽሐፈ ዮዲት ፣ ፮. መጽሐፈ አስቴር ፣ ፯. መጽሐፈ ኢዮብ፤ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ በቆየው የአንድምታ ትርጓሜ በቅደም ተከተል በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅታችን አሳታሚነት ታትመው እንዲወጡ እና በተከታታይም ቀሪዎቹ የብሉያት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በቀጣይነት እየታተሙ ለሚያስተምሩ መምህራን፣ለሚማሩ ደቀ መዛሙርት የአባቶችን እምነትና ታሪክ ማወቅ ለሚፈልጉ ምእመናን እየታተሙ እንዲከፋፈሉ በገባነው ቃል መሠረት ሦስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ማለትም ኦሪት ዘሌዋውያን ዘኁልቊ እና ዘዳግም በአንድምታ ትርጓሜ ታትመው መቅረባቸውን ስናበስር መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል ።

ቀሪዎቹም የመጻሕፍተ ብሉያት አንድምታ ትርጓሜ በቅደም ተከተል ተዘጋጅተውና ታትመው ለመፍቀርያነ መጻሕፍት እንደሚቀርቡ እምነታችን ጽኑእ ነው ልዑል እግዚአብሔርንም «ወይኩን ፈቃድከ » እያልን እንለምነዋለን።

«በስመ እግዚአብሔር ፡መሐሪ፡ ወመስተሣህል »

አባ ጳውሎስ

ፓትርያርክ፣ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፣

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ው ጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| 1. ኦሪት ዘሌዋውያን | ፩ - ፻፳፫ |
| 2. ኦሪት ዘኁልቊ | ፩ - ፪፻፲፮ |
| 3. ኦሪት ዘዳግም | ፩ - ፻፯ |




## መቅድም

ዜና ዘሌዋውያን ሲል ነው ፤ የኦሪትን ትርጓሜ በኦሪት ዘልደት ተናግሯል፣ በሌዊ ሌዋውያን ተብለዋል፣ የሌዋውያንን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፣ ሌዋውያን ሲሠሩት የሚገባቸውን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፣ ሌዋውያን የሚላቸው እንደ ቀሳውስት እንደ ዲያቆናት ያሉትን ነው፤ ይህ አርእስት ነው፣ ይህንም አርእስት ፫፻ት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ ሰጥተውታል እሱ ግን ነገሩን "ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ ብሎ" ይጀምራል።

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወጸውዖ እግዚአብሔር ለሙሴ ወተናገሮ እምውስተ ደብተራ ዘመርጡል፣

እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ተነጋገረው፣ እስካሁን እንደ መቃረቢያ ያለች የራሱ ድንኳን ነበረችው፣ በዚያች ይነጋገረው ነበር፣ አሁን ግን በደገኛዪቱ በደብተራ ኦሪት ይነጋገረዋል፤

፪፤ ወይቤሎ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአይድዖሙ፣

ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ተነጋገረው፤

እመበ ብእሲ እምኔክሙ ዘአብአ መባአ ለእግዚአብሔር እምእንስሳ፣

ከናንተ ለእግዚአብሔር ከእንስሳ ወገን መባ የሚያገባ ቢኖር፤

ወእምአልሕምት ወእምአባግዕ ታበውኡ መባአክሙ፣

እንስሳ ያለውን ይተረትራል፤ ከላም ከበግ ወገን መባችሁን ታገባላችሁ፤

፫፤ ለእመ ለሠዊዕ መባኡ እምአልሕምት ተባዕተ ንጹሐ ያመጽእ ኀበ ኆኀተ ደብተራ ዘመርጡል፣

ያምጽእ ሲል ነው፣ በኦሪት ካልአይ አንቀጽ ትእዛዝ እየ ሆነ ይፈታልና፣ አስተውል፣ እስካሁን የሚያገቡት መባ ለመሥዋዕት አልነበረም፣ እንግዲህ ወዲህ የሚያመጡት ግን ለመሥዋዕት ነውና ለሠዊዕ አለ፣ የሚያገቡት መባ ለመሥዋዕት ከሆነ ከላም ወገን ቀንዱ ያልከረከረውን፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን፣ ጠጉሩ ያላረረውን ፣ አኅረቂ ያይደለ

www.ethiopianorthodox.org

ውን ወይፈኑን ወደ ደብተራ ኦሪት ያቅርብ።

ወያበውኦ ሥጦወ ቅድመ እግዚ አብሔር፤

እግዚአብሔር ወዶ እንዲቀበ ለው አድርጎ ያቅርበው ፤ነውር የሌለው ከሆነ እግዚአብሔር ይቀበለዋልና።

፬፤ ወያነብር እዴሁ ላዕለ ርእሱ ለዝክቱ ላሕም ዘአምጽኦ ለሠዊዕ ከመ ይሠጠዎ ወያስተሥሪ ሎቱ ኃጢአቱ በእንቲአሁ፤

እግዚአብሔር ይቀበለው ዘንድ ኃጢአቱንም በሱ ምክንያት ያስተሠርይለት ዘንድ ሊሠዋው ያመጣው ሰው በላሙ ላይ እጁን ይጫንበት፤ ኃጢአቴ ባንተ ምክንያት ይሠረይልኛል ሲል፤ አንድም ሊቀ ካህናቱ እጁን ይጫንበት፤ የዚህ ሰው ኃጢአቱ ባንተ ምክንያት ይሠረያል ሲል።

፭፤ ወይጠብሕዎ ለውእቱ ላሕም ቅድመ እግዚአብሔር፤

ላሙን በእግዚአብሔር ፊት ይረዱት ማለት በቤተ እግዚ አብሔር ይሠዉት፤

ወያመጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ለሊ ሆሙ ካህናት ወይክዕውዎ ላዕለ ምሥዋዕ ዓውዶ ኀበ ኆኀተ ደብ ተራ ዘመርጡል፤

ከአሮን የተወለዱ ካህናትም ራሳቸው ደሙን አምጥተው በደብተራ ኦሪት ደጅ ባለ በም ሥዋዑ ዙሪያ ይረብርቡት (ይርጩት)፤ ያቀረቡትን ለሊ ሆሙ አሳቸው።

፮፤ ወይጠብሕዎ ወይፈልጡ መለ ያልይሁ ዘዘዚአሁ፤

አርደው አዋራርደው ብልቱን በየዘርፉ ይለዩት።

፯፤ ወይወድዩ እሳተ ደቂቀ አሮን ካህናት ላዕለ ምሥዋዕ ወይዌጥሑ ዕፀወ ላዕለ እሳት፤

ከአሮን የተወለዱ ካህናትም ከመሠዊያው ላይ እሳት አን ድደው በእሳቱም ላይ እን ጨት ረብርበው።

፰፤ ወይዌጥሑ ደቂቀ አሮን ካህ ናት ዝክተ ዘገመዱ ርእሶኒ ወስ ብሖኒ ላዕለ ዕፀው ዘላዕለ እሳት ዘዲበ ምሥዋዕ፤

የአሮን ልጆች ካህናትም ያረ ዱትን ያወራረዱትን ራሱንም ስቡንም በመሠዊያው በነደ ደው እሳት ባለው እንጨት ላይ ይረብርቡት።



፱፤ ወንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ የሐፅቡ በማይ ወይወዲ ካህን ኵሎ ዲበ ምሥዋዕ፤

ሆድ ዕቃውንና ስኰናውን በውሃ ይጠቡት፤ ካህኑ ሁሉ ንም በምሥዋዑ ላይ ያድ ርግ።

መሥዋዕት ውእቱ ወቍርባን ዘመ ዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤

ይኸውም እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው መሥዋዕት ቍር ባን ነው።

፲፤ ወእመሰ እምአባግዕ ውእቱ መባኡ ለእግዚአብሔር እመኒ በግዕ ወእመኒ መሐስዕ ለሠዊዕ ተባዕተ ንጹሐ ያመጽኡ፤

ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መሥዋዕት ግን ከበግ ወገን ቢሆን ሙክትም ጠቦትም ቢሆን ነውር የሌለበት ተባት አምጥተው።

፲፩፤ ወይጠብሕዎ በገቦ ምሥዋዕ ዘመንገለ መስዕ ቅድመ እግዚ አብሔር፤

በመስዕ በኵል ባለ በም ሥዋዑ አጠገብ በእግዚ አብሔር ፊት ይረዱት።

ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ካህ ናት ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ፤

የአሮን ልጆች ካህናቱም ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ዙርያ ይርጩት።

፲፪፤ ወይመትርዎ ካህናት በበመ ለያልይሁ ርእሶኒ ወስብሖኒ ወይዌ ጥሕዎ ላዕለ ዕፀው ዘዲበ እሳት ዘላዕለ ምሥዋዕ፤

ካህናቱም ራሱንም ስቡንም በየብልቱ ለይተው በመሠዊ ያው አጠገብ በነደደው እሳት ባለው እንጨት ላይ ይረብ ርቡት።

፲፫፤ ወንዋየ ውስጡ ወእገሪሁ የሐፅቡ በማይ ወያመጽእ ካህን ኵሎ ወያነብሮ ላዕለ ምሥዋዕ፤

ሆድ ዕቃውን፤ ስኰናውን በውሀ ይጠቡት፤ ካህኑም የታ ጠበውን ሁሉ አምጥቶ ከም ሥዋዑ ላይ ያድርገው።

ለቍርባን መሥዋዕት ውእቱ ወመ ዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበ ለው መሥዋዕት ቍርባን ነውና ራሱ ይሠዋ አለ፤ መካነ ራስ አእምሮ ነው፤ አው ቃችሁ ኃጢአት አትሥሩ፤ ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተ ሠርይላችኋለሁ ሲል፤ ስቡ ይሠዋ ማለቱ ስብ ትርፍ ነው፤ ከሕገ እግዚአብሔር ትርፍ የምትሆን ኃጢአት አትሥሩ

www.ethiopianorthodox.org

ሲል መላው አካሉ ይሠዋ ማለቱ በሕዋሳታችሁ ሁሉ ኃጢአት አትሥሩ፣ ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላ ችኋለሁ ሲል፤

፲፬፤ ወእመሰ እምአዕዋፍ ያበውእ መሥዋዕቶ ቍርባነ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው መሥዋዕት ከአዕዋፍ ወገን ቢሆን ግን፤

ያመጽእ እመ አኮ እማዕነት ወእመ አኮ እምርግብ ቍርባኖ፣

አዕዋፍ ያለውን ይተረትራል፣ ሁለት ርግብ፣ ቢታጣ ሁለት ዋኖስ ያምጣ ፤ አንድም ሁለት ርግብ ሁለት ዋኖስ ቢታጣ፣ አንድ ርግብ አንድ ዋኖስ ያምጣ፤

፲፭፤ ወያመጽእ ካህን ኀበ ምሥ ዋዕ ወይመትር ክሣዶ ወያነብሮ ላዕለ ምሥዋዕ፣

ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥ ዋዕት ከዋኖስም ከርግብ ወገ ንም ቢሆን ካህኑ ተቀብሎ ወደ ምሥዋዑ ወስዶ አንገ ቱን ገዝግዞ በመሠዊያው ላይ ያኑረው፤ አንድም እግዚአብ ሔርን ሊያገለግል የተሾመው ሰው ወደ መሠዊያው አቅርቦ አንገቱን ይገዝግዘው፤

ወያንጸፈጽፍ ደሞ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ፣

ደሙን ከመሠዊያው እግር ያንጠፍጥፈው፤

፲፮፤ ወያሴስል ንዋየ ውስጡ ምስለ ፀጉሩ ወያነብሮ በገቦ ምሥዋዕ ዘመንገለ ጽባሒሁ ኀበ መንበረ ሐመድ፣

ሆድ ዕቃውን ግን ከጠጉሩ ጋራ አመድ በሚፈስበት ዐዘ ቅት በመሠዊያው አጠገብ በም ሥራቅ በኩል ያፍስሰው፤

፲፯፤ ወይሰብሮ እምክነፊሁ ወኢ ይመትሮ፣

አንገቱን ቆልምሞ ከክንፉ ያገ ናኘው እንጂ ጨርሶ አይቍረ ጠው፤

ወያነብሮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ በዲበ ዕፀው ዘላዕለ እሳት፣

በምሥዋዑ አጠገብ በነደደው እሳት ባለው እንጨት ላይ አድርጎ ያቃጥለው፤

ቍርባን ዘመሥዋዕት ውእቱ ወመ ዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፣

ይኸውም እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው በጎ መሥዋዕት ቍርባን ነው፣ ይህም ምሳሌ ነው፣ ዋኖስ የኦሪት፣ ርግብ የወንጌል፣ዋኖስ የሚገኝ በም ድረ በዳ ነው ፤ ኦሪትም የተ



ሠራች በምድረ በዳ ነውና፣ ርግብ የምትገኝ በቤተ ክርስ ቲያን ነው ፤ ወንጌልም መሠ ራቷ በቤተ ክርስቲያን ነውና ፤ አንድምሥርየት በወንጌል ተፈ ጸመ ሲል ርግብን አንገቱን ገዝግዞ ይተወው፣ አይቍረጠው ማለቱ በኦሪት ፍጹም ሥር የት አልተሠጠምና ፤ ክንፉን አይስበረው ማለቱ ፤ የሁለቱን ወንበዴዎች ጭን ጭናቸውን ሲሰብሯቸው የጌታን አልሰበ ሩትምና ::

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወእመሰ ህየንተ ነፍስ ቍርባነ ወመሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ያመ ጽእ ሥንዳሌ ይኩን ቍርባኑ፣

ዋኖስ ርግብ ቢታጣ ግን ስለ ሳም ፈንታ የሚሠዋው የእህል መሥዋዕትም ቢሆን ለእግዚ አብሔር የሚቀርበው የተፈ ተገ ፍሬያማ ሥንዴ ይሁን ፤ ባቄላ ዐተር ሽንብራ አይሁን፤

ወይክዑ ላዕሌሁ ቅብዓ ወይወዲ ዲቤሁ ስሒነ፣

የሚጤስ ነውና በዘይት የታ በቀ ቁንዶ በርበሬ ይጨም ርበት፤ አንድም ነጭ ዕጣን ይጨምርበት፤

፪፤ ወይወስድ ኀበ ደቂቀ አሮን ካህናት፣

ከአሮን ወደ ተወለዱ ካህና ትም ይውሰደው፤

ወይዘግን እምኔሁ ካህን ምልዓ ሕፍኑ እምሥንዳሌ ምስለ ቅብዑ ወኵሉ ስሒኑ፣

እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ሰው በዘይትና በዱ ንዶ በርበሬ ከተሸው ስንዴ እጅ ያህል ቈርሶ ያጢስለት፤

ወይወድዮ ለተዝካር ላዕለ ምሥዋዕ መሥዋዕት ውእቱ ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ የሚሆን መሥዋዕት ነውና (ለመታሰቢያ ሊሆን) ካህኑ በመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

፫፤ ወዘተርፈ እመሥዋዕት ለአሮን ወለደቂቁ ቅዱስ ለቅዱሳን እመሥ ዋዕቱ ለእግዚአብሔር፣

“እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔርና እመሥዋዕት አንድ ወገን፣” ለእግዚአብሔር ከቀረበው ከተ ለየው መሥዋዕት የቀረው ከሕዝቡ ለተለዩ ለአሮን ልጆችና ለአሮን ነውና፤

፬፤ ወእመሰ አባእከ ቍርባነ ለመ ሥዋዕት ብሱለ በእቶን ኅብስተ ሥንዳሌ ናዕተ ልውሰ በቅብዕ፣

www.ethiopianorthodox.org

ለመሥዋዕት የምታቀርበው በዘይት የታበቀ የተለወሰ ድፎ ቂጣ ቢሆን ግን፤

፭፤ ወለእመ መሥዋዕተ ቴጉን ቍርባንከ ሥንዳሴ ልውስ በቅብዕ፤ ወናዕተ ይኩን፣

ቍርባንህም በብረት ምጣድ የበሰለ (የተጋገረ) መሥዋዕት ቢሆን በዘይት የተለወሰ የስንዴ ቂጣ ይሁን፤

፮፤ ወትፌትቶ፣

ፈትተህ (ቈርሰህ) አጢሰው፤ አንድም ሽና ይሁን፤

ወትክዑ ላዕሌሁ ቅብዐ፣

ለእግዚአብሔር የሚጤስ ነውና፤ ዘይት ጨምርበት፤

፯፤ ወለእመ ብሱል በመቅጹት መሥዋዕትከ ሥንዳሴ በቅብዕ ይትገበር፣

በምንቸት የተቀቀለ (የበሰለ) መንካኮ (ገንፎም) ቢሆን በዘይት የተለወሰ ይሁን ፤ አንድም ቆንጥረህ አጢስለት፤

፰፤ ወታመጽእ መሥዋዕተከ ዘገበርከ እምዝንቱ ለእግዚአብሔር ወያቀርቦ ካህን ኀበ ምሥዋዕ፣

ለእግዚአብሔር ካዘጋጀኸው ከዚህ መሥዋዕትህ ወደ ካህኑ አምጣ፣ ካህኑም ወደ መሠዊያው ያቅርበው፤

፱፤ ወይነሥእ ካህን እመሥዋዕት ለተዝካር ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ፣

እግዚአብሔርን ሲያገለግል የተሾመው ሰው ወደመሠዊያው አቅርቦ ለመታሰቢያ የሚሆነውን በመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው ሆኖ የሚቀርብ መሥዋዕት ነውና፤

፲፤ ወዘተርፈ እመሥዋዕት ለአሮን ወለደቂቁ ቅዱስ ለቅዱሳን እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር፣

"እመሥዋዕትና እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ዘተርፈና ቅዱስ አንድ ወገን" ለእግዚአብሔር ከቀረበው መሥዋዕት የቀረው ከሕዝቡ ለተለዩ ለአሮንና ለልጆቹ ነው፤

፲፩፤ ወኵሎ ዘታመጽኡ ለሠዊዕ ለእግዚአብሔር ኢትግበሩ ብሑአ እምኵሉ ብሑእ፣

ለእግዚአብሔር ለመሠዋት የምታመጡትን ሁሉ ከመጻጻ አታድርጉ፤

ወእምኵሉ መዓር ኢታምጽኡ ለሠዊዕ ለእግዚአብሔር ለቍርባን፣



ለቍርባን ሲሆን ለእግዚአብሔር ለመሥዋዕት ከመዓር ወገን አታምጡ፣ መጻጻውን አትሠዉ ማለቱ መጻጻ የቆየ ነው፣ የዘገየ ኃጢአት አትሥሩ ሲል (ኃጢአት አይዘግይባችሁ ሲል ነው)፣ መዓር አታቅርቡ ማለቱም ንህብ የማትቀስመው የላትም፣ እናንተም ዘመደ ኀጣውእን አትሥሩ፤ ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ነው፤

፲፪፤ ወባሕቱ ለዓሥራት ታበውኡ እምኔሁ ለእግዚአብሔር፣

ነገር ግን ከሱ ለእግዚአብሔር ከዓሥር አንዱን አግቡ፤

እስመ ለመሥዋዕትሰ ኢትሠውዑ እምኔሁ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር በጎ አድርጎ ሊቀበለው ከሱ አትሠዉምና ከዓሥር አንዱን አግቡ፤

፲፫፤ ወኵሉ ቍርባነ መሥዋዕትክሙ በጼው ይትገበር ወኢይትኃደግ ጼው እንዘ ትሠውዑ ለእግዚአብሔር ውስተ ኵሉ ቍርባን ክሙ ትወድዩ ጼወ፣

"ወኵሉ ቍርባነ መሥዋዕትክሙ በጼው ይተገበርና ውስተ ኵሉ ቍርባንክሙ ትወድዩ ጼወ ያለው አንድ ወገን ነው›› መሥዋዕት አድርጋችሁ በምታቀርቡት ሁሉ ጨው ጨምሩበት፣ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ከሆነ ‹‹ያለጨው አይቀርብምና ጨው የሌለበት አልጫ ይባላል›› እናንተም አልጫ ኃጢአት አትሥሩ፤ ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ነው፤

፲፬፤ ወእመሰ አባእከ መሥዋዕተ እምቀዳሜ እክልከ ለእግዚአብሔር ሐዲስ ቅልወ ንጹሐ ወልቱመ ፣

መጀመሪያ ከደረሰው እህልህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀርባለሁ ብትል ግን የተለቀመ የተፈተገ አዲስ እህል ይሁን፤

፲፭፤ ወታበውእ መሥዋዕተ እምቀዳሜ እክልከ ወትክዑ ላዕሌሁ ቅብዓ ወትወዲ ላዕሌሁ ስሒነ ፣

መጀመሪያ ከደረሰው እህልህ ለመሥዋዕት አቅርበህ ቍንዶ በርበሬ፤ አንድም ነጭ ዕጣን ጨምርበት፤

ወያበውያ ካህን ለውእቱ እክል ምስለ ቅብዑ ወኵሉ ስሒኑ ለተዝካር፣

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ሰው በዘይትና በቍንዶ በርበሬ የተለወሰውን መሥዋዕት ተቀብሎ ለመታሰቢያ ሲሆን ያቅርበው፤

መሥዋዕት ውእቱ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር የሚጤስ መሥዋዕት ነውና ።

## ምዕራፍ ፫
## ጉባኤ

፩፤ ወእመሰ መሥዋዕተ መድኃኒት ውእቱ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር ፤

ከአባር ከቸነፈር የሚድኑበት ስለሆነ መሥዋዕተ መድኃኒት አለው ድኅነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር መሥዋዕቱ ቢሆን ግን፤

ለእመ እምአልሕምት አምጽአ እመኒ ተባዕተ ወእመኒ አንስተ ንጹሐ ለያምጽእ ቅድመ እግዚአብሐር፤

ያቀረበው ከላም ወገን ቢሆን ወንድም ቢሆን እንስትም ብትሆን ቀንዱ ያልከረከረውን ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ጠጕሩ ያላረረውን ‹‹አጥራቂ ያይደለውን›› ለእግዚአብሔር ያቅርብ፤

፪፤ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ፤

የሚሠዋው ሰው እጁን በላሙ ራስ ላይ ይጫንበት ኃጢአቴ ባንተ ምክንያት ይሠረያል ሲል ፤

ወይጠብሕዎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ካህናት ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ፤

በደብተራ ኦሪት ደጅ ሠውተው ከአሮን የተወለዱ ካህናት ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ዙሪያ ይረብርቡት፤ ይርጩት ፤

፫፤ ወያበውኡ እመሥዋዕተ መድኃኒት ቍርባነ ለእግዚአብሔር ስብሖ ዘይገለብቦ ለከርሡ ወኵሎ ስብሐ ዘውስተ ከርሡ ፤

ድኅነት ከሚገኝበት መሥዋዕት ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሞራውን በሆዱ ውስጥ ያለውን ስቡንም ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርገው ያቅርቡ ፤

፬፤ ወክልኤሆን ኵልያቶ ወስብሖ ዘላዕሌሆን ዘውስተ ፀራኢቱ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ምስለ ኵልያቲሁ ያመጽኡ ፤

ሁለቱን ኵላሊቱን በጭቅናው ውስጥ ያለውን ስቡን



ለምለም ጉበቱን ከኵላሊቱ ጋራ አንድ አድርገው ያቅርቡ፤

፭፤ ወያበውኡ ደቂቀ አሮን ላዕለ ምሥዋዕ ዲበ ዕፀው ዘላዕለ እሳት፤

ከአሮን የተወለዱ ካህናት ከመሠዊያው እሳት ባለው እንጨት ላይ ያኑሩት ፤

መሥዋዕት ውእቱ መዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤

በጎ መዓዛ አድርጎ ሊቀበለው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነውና ፤

፮፤ ወእመሰ እምአባግዕ ቍርባኑ ወመሥዋዕተ መድኃኒቱ ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር ድኅነት የሚገኝበት መሥዋዕት ከበግ ወገን ቢሆን ፤

እመኒ ተባዕተ ፤ ወእመኒ አንስተ ንጹሐ ያመጽእ ፤

ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ቀንዱ ያልከረከረውን ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ጠጕሩ ያላረረውን ያቅርብ ፤

፯፤ ወእመሰ መሐስዐ አባግዕ ቍርባኑ ያመጽእ ቅድመ እግዚአብሐር፤

ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው መሥዋዕት የበግ ጠቦት ቢሆን ግን፤

፰፤ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሰ ቍርባኑ ፤

የሚሠዋው ሰው እጁን በበጉ ራስ ላይ ያኑር ፤ ኃጢአቴ ባንተ ምክንያት ይሠረያል ሲል፤

ወይጠብሖ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደቂቀ አሮን ካህናት ደሞ ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ፤

በደብተራ ኦሪት ደጅ ይሠዋው፤ ከአሮን የተወለዱ ካህናትም ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ዙሪያ ይርጩት፤

፱፤ ወይነሥእ እመሥዋዕተ መድኃኒት ቍርባነ ለእግዚአብሔር ፤

ድኅነት ከሚደረግበት መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርጎ ቢያቀርብ፤

ስብሖ ወሐቌሁ ፍጹመ ምስለ ስመጢሁ ይመትሮ ወኵሎ ስፀሖ ዘይገለብቦ ለከርሡ ወኵሎ ስብሖ ዘውስተ ከርሡ ፤

ስቡን ዳሌውን ከሽንጡ ጋራ ይለየው፤ ከሆድ ዕቃው ውስጥም የሚገኘውን ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሞራውን ሁሉ ይለየው ፤

፲፤ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሖ ዘጸራዒቱ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሁለቱን ኵላሊቱን ከጭቅናው የሚገኘውን ስቡን ግልገል ጉበቱን ከሁለቱ ኵላሊት ጋራ ይለየው ፣ ‹ሐተታ› ሐሞት ያለ በጉበት ነው፣ ቍጣም የሚነቃ ከሐሞት ነው፤ ከሰውነታችሁ አንቅታችሁ ተቆጥታችሁ ኃጢአት አትሥሩ ፣ ኃጢአት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ነው ፤ ‹ኵላሊት ነቅዓ ሐልዮ ነው ከልባችሁ አንቅታችሁ ኃጢአት አትሥሩ ሲል መሥዋዕት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል፣ ዳሌ ከጭቅናው ጋር የተያያዘ ነው፣ ነቅዓ ዘርም ነው፣ ከሰውነታችሁ አንቅታችሁ መላልሳችሁ ኃጢአት አትሥሩ፤ መሥዋዕት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ፣ ሽንጥ ከሰውነት ጋር የተያያዘ ነው ‹አስተጋባኢም ነው› በሕዋሳታችሁ ሁሉ ኃጢአት አትሥሩ ሲል መሥዋዕት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ይህን ሁሉ ለይቶ ያጢሰው አለ ፤

፲፩፤ ወይወድዮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ፣ ቍርባን ውእቱ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ቍርባን ነውና ፤ ካህኑ በመሠዊያው ላይ ያኑረው ፤

፲፪፤ ወእመሰ እምአጣሊ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር ወያመጽእ ቅድመ እግዚአብሔር፣

ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው መሥዋዕት ከፍየል ወገን ቢሆን ግን ፤

፲፫፤ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ ፣

የሚሠዋው ሰው እጁን በራሱ ላይ ያድርግ፣ ኃጢአቴ ባንተ ይሠረያል ሲል፤

ወይጠብሕዎ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይክዕዉ ደሞ ደቂቀ አሮን ላዕለ ምሥዋዕ በዓውዱ ፣

ልዩ በሆነች በደብተራ ኦሪት ደጅ በእግዚአብሔር ፊት ይሠውት ከአሮን የተወለዱ ካህናትም ደሙን ተቀብለው በመሠዊያው ዙሪያ ይርጬት፤

፲፬፤ ወይነሥእ እምኔሁ ቍርባነ ለእግዚአብሔር ስብሐ ዘይገለብባ ለከርሡ ወኵሎ ስብሐ ዘውስተ ከርሡ ፣

ከተሠዋው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ቍርባን የሚ



ሆን ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስቡን፣ በሆዱ ውስጥ የሚገኘውን ሞራውን ሁሉ፤

፲፭፤ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወኵሎ ስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘፀራዊቱ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ ፣

‹‹ይነሥእ ወይመትሮ ሲል ነው›› ፣ ሁለቱን ኵላሊቱን በኵላሊቱና በጭቅናው ውስጥ ያለውን ስቡን፣ ለምለም ጉበቱን ከኵላሊቶቹ ጋር አምጥቶ ያጢሰው፤ ‹ሐተታ እንዳለፈው ፤

፲፮፤ ወያነብሮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ መሥዋዕት ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ፣

በጎ መዓዛ ሁኖ የሚቀርብ መሥዋዕት ነውና ካህኑ ተቀብሎ በመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

፲፯፤ ወኵሉ ስብሕ ለእግዚአብሔር ሕግ ዘለዓለም ውእቱ በኵሉ መዋዕሊክሙ በኵለሄ በኀበ ትነብሩ ፣

በኵለሄና በኵሉ መዋዕሊክሙ አንድ ወገን፣ ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት ስብ ሁሉ በምትኖሩበት ዘመን የዘለዓለም ሕግ ነው፤

ኵሎ ስብሐ ወኵሎ ደመ ኢትብልኡ፣

‹ሰ› የቀረው ነው፤ ስቡን፣ ብርንዶውን ግን አትብሉት፤ አንድም በቁሙ ደሙን አትብሉ፣ አርግተው ቆልተው ይበሉታልና።

## ምዕራፍ ፬

## ጉባኤ

፩፤ ወተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

ለያዕቆብ ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው፤

፪፤ ወበሎሙ ነፍስ ለእመ አበሰት እምኵሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር በኢያእምሮ ዘኢትከውን ለገቢር ወገብረት አሐተ እምኔሁ ፣

የሰው ሰውነት እግዚአብሔር ጠብቁ ብሎ ካዘዘው ትእዛዝ ወጥታ ሊሠሩት የማይገባውን ባለማወቅ ሠርታ ብትበድል ፣ አታድርግ ካለው አንዱቱን ብትሠራ፤ አንድም ለእመ አበሰት በአእምሮ አውቃ ሠርታ ብትበድል ፤

፫፤ ወእመኒ ሊቀ ካህናት ዘቅቡዕ አበሰ እምሕዝብ ፣

‹‹ዝቅቡዕ እምሕዝብ ›› ሲል ነው ፣ ከሕዝቡ ተመርጦ የተሾመው ሊቀ ካህናቱ

www.ethiopianorthodox.org

ቢበድል፤ አንድም ሊቀ ካህናቱ ከሕዝቡ ተለይቶ ቢበድል፤

ያመጽእ ህየንተ አበሳሁ ዘአበሰ ላሕመ ንጹሐ እምአልሕምት ለእግዚአብሔር በእንተ ኃጢአቱ፣

‹‹በእንተ አበሳሁና በእንተ ኃጢአቱ ›› አንድ ወገን፣ እግዚአብሔርን ስለበደለበት ኃጢአቱ ከላም ወገን ነውር የሌለበትን ወይፈኑን ለእግዚአብሔር ያቅርብ ፤

፬. ወያመጽኦ ለውእቱ ላሕም ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ እግዚአብሔር ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሰ ላሕም፤

ሊሠዋው ያመጣውን ላም በእግዚአብሔር ፊት ወደ ደብተራ ኦሪት አቅርቦ እጁን በራሱ ላይ ይጫንበት፣ ኃጢአቴ ባንተ ይሠረያል ሲል፤ አንድም ባንተ ምክንያት እከብራለሁ ሲል ፤

ወይጠብሖ ለውእቱ ላሕም ቅድመ እግዚአብሔር ፣

የቀረበውንም ላም በእግዚአብሔር ፊት ይሠዋው ፤

፭፤ ወይነሥእ ካህን ዘቅቡዕ ወፍጹም በእዴሁ እምደሙ ለውእቱ ላሕም ወያበውኦ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፣

ተቀብቶ የከበረ ካህኑም የላሙን ደም በእጁ ተቀብሎ ወደ ደብተራ ኦሪት ያግባው፤

፮፤ ወይጠምዕ አፃብዒሁ ውስተ ደሙ ወይነዝኅ እምውእቱ ደም ስብዓ ቅድመ እግዚአብሔር ላዕለ መንጦላዕተ ቅድሳት፣

ጣቱን ከደሙ ነክሮ ከዚያ ደም በድንኳኑ መጋረጃ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጭ፤ በፍጹም ትጋት ኃጢአት እንዲሠረይ ለማጠየቅ፣ ሐተታ እግዚአብሔር የማይለየው ስለሆነ ቤተ እግዚአብሔርን ቅድመ እግዚአብሔር ይለዋል ፤

፯፤ ወይወዲ ካህን እምደሙ ለውእቱ ላሕም ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን ዘያነብሩ ቅድመ እግዚአብሔር ዘሀሎ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፣

እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ካህን ከደሙ ዘግኖ (ታፍኖ) በደብተራ ኦሪት ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት የሚያኖሩትን ዕጣን ከሚቀመጥበት ከአቅርንተ ምሥዋዑ ላይ ይጨምረው ማለት ይርጨው ፤

፰፤ ወይክዑ ኵሎ ደሞ ኀበ መንበሩ ለምሥዋዕ ዘቍርባን ዘኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፣



በደብተራ ኦሪት ደጅ ቍርባን የሚጤስበትን የመሠዊያውንም መቀመጫ ይርጨው፤

፱፤ወኵሎ ስብሖ ለውእቱ ላሕም ዘበእንተ ኃጢአት ያሴስል ወእም ስብሕ ዘይገለብብ ንዋየ ውስጡ ወኵሎ ስብሖ ዘውስተ አማዑቱ ፣

ኃጢአት የሚያስተሠርይ የላሙን ስብ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍን ሞራውን ባንጀቱ ውስጥ የሚገኘውን ስብ ፤

፲፤ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘፀራዒቱ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትር ፣

ሁለቱን ኵላሊቱን በበላያቸው ያለ ስቡን በጭቅናው ያለ ስቡን ግልገል ጉበቱን ከሁለቱ ኵላሊት ጋር ለይቶ ያጢሰው ፤

፲፩፤ ወበከመ ያመጽኡ ዘላሕመ መድኃኒት ወይወድዮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ ዘቍርባን ፣

ድኅነት የሚደረግበትን የላሙን ስብ እንዲለዩ ይህንንም እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ካህን ቍርባን ከሚቀርብበት ከመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

ወማዕሶሂ ለውእቱ ላሕም ወኵሉ ሥጋሁ ምስለ ርእሱ ወምስለ ሰኰናሁ ወከርሦ ወካዕሴሁ፣

ለመሥዋዕት የቀረበውን የላሙን ቍርበቱንና የተረፈውን ሥጋውን ከራሱና ከሰኰናው ጋር ሰንበሩንና ፈርሱን፤

፲፪፤ ወይወስዱ አፍአ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ኀበ ይክዕዉ ሐመደ ወያውዕይዎ ላዕለ ዕፀው በእሳት ውስተ ምክዓወ ሐመድ ፣

ይህን ሁሉ ከከተማው በውጭ አውጥተው እንጨት ረብርበው አመድ በሚያፈሱበት በንጹሕ ቦታ በእሳት ያቃጥሉት፣ ‹ሐተታ› አፍኣዊ ኃጢአት አትሥሩ ሲል፣ በንጹሕ ቦታ መሆኑም ኃጢአት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ ይቅር እላችኋለሁ ሲል ፤ አንድም ጌታ ከከተማ በአፍኣ ተሰቅሎ፣ ዓለምን ለማዳኑ ምሳሌ ነው፣

፲፫፤ ወእመሰ ለኵሉ ተዓይን ዘደቂቀ እስራኤል ተስሕቶሙ ወተረስዓት እምአዕይንቲሆሙ ቃል ለተዓይን፣

(ለኵሉ ተዓይንና ለተዓይን አንድ ወገን)፣ የያዕቆብ ልጆች ከሚሆኑ ወገኖች ጠብቁ ብሎ

www.ethiopianorthodox.org

ያዘዘው ሕግ ከዓይነ ልቡና ቸው ቢዘነጋቸው ግን፤

ወገብሩ እምኵሉ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር ዘኢይከውን ለገቢር ወእምዝ ነስሑ፤

እግዚአብሔር ካዘዘው ትእዛዝ ወጥተው ሊሠሩት የማይገባውን ቢሠሩ ከሠሩትም በኋላ ተፀፅተው ንስሐ ቢገቡ፤

፲፬፤ ወተዓውቀቶሙ ኃጢአቶሙ እንተ አበሱ ያመጽኡ ትዕይንቶሙ ላሕመ እምአልሕምት ንጹሐ በእንተ ኃጢአቶሙ ወያመጽእዎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

ወያመጽኡና ያመጽእዎ አንድ ወገን ነው፤ የሠሯት ኃጢአትም ብትታወቃቸው፤ የእስራኤል ወገኖች ስለሠሩት ኃጢአት ከላሞቻቸው ወገን ነውር የሌለውን ወይፈኑን ወደ ደብተራ ኦሪት ያቅርቡ፤

፲፭፤ ወይወድዩ ሊቃናተ ይእቲ ትዕይንት ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ላሕም እደዊሆሙ በቅድመ እግዚአብሔር ወይጠብሕዎ ቅድመ እግዚአብሔር ለውእቱ ላሕም፤

በእስራኤል ወገን ላይ (በእስራኤል ከተማ) የተሾሙ ካህናትም ለመሥዋዕት ባቀረቡት በላሙ ራስ ላይ በእግዚአብሔር ፊት እጃቸውን ይጫኑበት ፤ ላሙንም በእግዚአብሔር ፊት ይሠዉት፤ (ሐተታ) ቅድመ እግዚአብሔር ማለቱ ቡሩክ እግዚአብሔር ብሎ እንደ መባረክ ነው፤

፲፮፤ ወያበውእ ካህን ዘቅቡዕ እምደሙ ለውእቱ ላሕም ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፤

ተቀብቶ የተሾመው ካህኑም ከላሙ ደም ወደ ደብተራ ኦሪት አግብቶ፤

፲፯፤ ወይጠምዕ አፃብዒሁ ካህን ውስተ ውእቱ ደም ወይነዝኅ ስብዓ በቅድመ እግዚአብሔር ቅድመ መንጦላዕተ ቅድሳት፤

ከዚያ ደም በጣቱ ነክሮ የድንኳኑን መጋረጃ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው፤ በፍጹም ትጋት ኃጢአት እንዲሠረይ ለማጠየቅ፤

፲፰፤ ወይወዲ እምደሙ ካህን ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር ዘውስተ ደብተራ ዘመርጡል፤

እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ካህን ከደሙ ዘግኖ (ታፍኖ) በደብተራ



ኦሪት ውስጥ ካለው ከአቅርንተ ምሥዋዑ ላይ ያድርግ፤

ወኵሎ ደሞ ይክዑ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን ዘሀሎ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

የቀረበውንም ደሙን ከእግረ ምሥዋዑ ያፍስሰው፤ (ምሥዋዑን ዘቍርባን) ቍርባኑን ኀበ ኆኅተ ደብተራ አለው ፤ ቍርባኑ ከምሥዋዑ፤ ምሥዋዑ ከደብተራ ኦሪት ደጅ አይለይምና፤

፲፱፤ ወኵሎ ስብሖ ያሴስል እምኔሁ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ፤

ለ የቀረው ነው፤ ስቡን ግን ከመሥዋዕቱ ለይቶ ከመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

፳፤ ወይገብሮ ለውእቱ ላሕም በከመ ይገብርዎ ለላሕም ዘኃጢአት ወያስተሠሪ ሎሙ ካህን ወይትኃደግ ሎሙ፤

(ያስተሠሪ ሎሙና ይትኃደግ ሎሙ) አንድ ወገን፤ እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተሾመው ካህን መሥዋዕተ ኃጢአቱን እንዲሠዉ ኃጢአታቸው ይሠረይላቸው ዘንድ ያን ወይፈን ይሠዋው ፤ ይህም ኃጢአት የሚያስተሠርይላቸው ነውና፤

፳፩፤ ወይወስድዎ ለውእቱ ላሕም አፍኣ እምትዕይንት ወያውዕይዎ በከመ ያውዕይዎ ለቀዳማዊ ላሕም ዘኃጢአት እስመ ዘኃጢአተ ትዕይንት ውእቱ፤

የሕዝቡን ኃጢአት የሚያስተሠርይ መሥዋዕት ነውና፤ የቀደመውን መሥዋዕተ ኃጢአቱን እንዲያቃጥሉት ይህንንም ከከተማ ወደ አፍኣ ወስደው ያቃጥሉት፤ ቀዳማይ አለው አስቀድሞ ተናግሮታልና፤

፳፪፤ ወእመሰ መኰንን አበሰ ወገብረ አሐተ እምኵሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር አምላክከሙ ዘኢትከውን ለገቢር በኢያእምሮ ወነስሐ፤

በሕዝቡ ላይ የተሾመው ዳኛው ግን ቢበድል ከፈጣሪያችሁ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥቶ ሊሠሯት የማትገባ ኃጢአትን ባለማወቅ ሠርቶ ንስሐ ቢገባ፤

፳፫፤ ወተአውቀቶ ኃጢአቱ እንተ አበሰ ባቲ ያመጽእ ቍርባኖ ሐርጌ እምአጣሊ ንጹሐ፤

www.ethiopianorthodox.org

የበደለባት ኃጢአት ብትታወቀው ቍርባን አድርጎ ከፍየሎች ወገን ነውር የሌለበትን ሙክት ያምጣ፤

፳፬፤ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ፤

እጁንም በሙክቱ ራስ ላይ ያኑር፤ ኃጢአቴ ባንተ ምክንያት ይሠረይልኛል ሲል፤

ወይጠብሕዎ ውስተ መካነ ነበ ይጠብሑ ዘይሠውዑ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ዘኃጢአት ውእቱ፤

ስለ ኃጢአት ማስተሥረያ የሚቀርብ ነውና በእግዚአብሔር ፊት፤ ቀድሞ በሚሠዉበት ቦታ ይሠዉት፤

፳፭፤ ወይወዲ ካህን እምደም ዘበእንተ ኃጢአት በአፃብዒሁ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን፤

ካህኑ ስለ ኃጢአት ሥርየት ከሚፈሰው ደም በጣቱ እየጠለቀ፤ ዕጣን በሚታጠንበት ጽና ቀንዶች ላይ ይጨምር፤

ወኵሎ ደሞ ይክዑ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን፤

የቀረውን ደም ግን ቍርባን ከሚያቀርቡበት ከእግረ ምሥዋዑ ያፍስሰው፤

፳፮፤ ወኵሎ ስብሖ ይወዲ ላዕለ ምሥዋዕ በከመ ስብሐ መሥዋዕት ዘመድኃኒት፤

ድኅነት የሚገኝበትን የመሥዋዕቱን ስብ እንዲያጤሱት ስቡን ሁሉ በምሥዋዑ ላይ ያጢሰው፤

ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ወይትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ፤

ይትኃደግና ያስተሠሪ አንድ ወገን፤ ካህኑም ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል፤

፳፯፤ ወእመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ እምሕዝበ ምድር በኢያእምሮ

በዓለም ካሉ ከሕዝቡ ተለይቶ አንድ ሰው ባለማወቅ ቢበድል፤

ወገብረ አሐተ እምትእዛዘ እግዚአብሔር ዘኢትከውን ለገቢር፤

እግዚአብሔር ካዘዘው ትእዛዝ ወጥቶ ሊሠሯት የማትገባ አንዲት ኃጢአት ቢሠራ፤

፳፰፤ ወነስሐ ወተዐውቀቶ ኃጢአቱ እንተ ገብረ ያመጽእ ጠሊተ እምአጣሊ አንስተ ንጽሕተ በእንተ ኃጢአቱ ዘገብረ፤

የሠራውም ኃጢአት ታውቆት ንስሐ ቢገባ ስለ ሠራው ኃጢአት ከፍየሎች ወገን



ነውር የሌለባትን ሴት ፍየል ያምጣ፤ የወንዱን ተናግሮ ነበርና የሴቲቱን አመጣ፤ (ሐተታ) ስለምን ሴት ፍየል ይሠዋ አለ ቢሉ፤ ኃጢአት የተገኘ ከሴት ነው፤ ከሴት የተገኘ ኃጢአት አትሥሩ፤ ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል፤

፳፱፤ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሳ ዘአምጽኣ በእንተ ኃጢአቱ፤

ስለ ኃጢአቱ ባመጣት ፍየል ራስ ላይ እጁን ያኑር ባንቺ ምክንያት ኃጢአቴ ይሠረይልኛል ሲል፤

ወይጠብሕዋ ለይእቲ ጠሊት ዘበእንተ ኃጢአት ውስተ መካነ ነበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት፤

ስለ ኃጢአት ያቀረቧትንም ፍየል ቀድሞ መሥዋዕቱን በሚሠዉበት ቦታ ይሠዉዋት፤

፴፤ ወይነሥእ ካህን እምደማ በአፃብዒሁ ወይወዲ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን፤

ካህኑም ከደሟ በጣቱ ጠልቆ ዕጣን በሚታጠንበት በአቅርንተ ምሥዋዑ ላይ ይጨምረው፤

ወኵሎ ደማ ይክዑ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን፤

የቀረውን ደሟን ግን ቍርባኑ ከሚቀርብበት ከእግረ ምሥዋዑ ያፍስሰው፤

፴፩፤ ወይመትር ኵሎ ስብሐ በከመ ይመትሩ ስብሐ ዘበእንተ መድኃኒት፤

ድኅነት የሚገኝበት የመሥዋዕቱን ስብ እንዲለዩ ስቧንም ይለዩት፤

ወይወድዮ ካህን ላዕለ ምሥዋዕ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ ሲቀበለው ካህኑ በመሠዊያው ላይ ያኑረው፤

ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ወትትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ፤

(ይትኃደግና ያስተሠሪ አንድ ወገን)፤ ካህኑም በስቡ ምክንያት ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ይሠረይለታል፤

፴፪፤ ወእመሰ በግዐ አምጽአ ቍርባኖ በእንተ ኃጢአቱ አንስተ ንጽሕተ ያመጽእ፤

ስለ ኃጢአቱ ቍርባን አድርጎ በግ ቢያመጣ ግን ቀንዷ

www.ethiopianorthodox.org

ያልከረከረውን ጥፍሯ ያልዘረ ዘረዙን ሐጕሯ ያላረረውን ሴት በግ ያምጣ፣ (ሐተታ) እንዳለፈው፤

ምዕራፍ ፬ ቁጥር ፳፰ ተመልከት፤

፴፫፡ ወይወዲ እዴሁ ላዕለ ርእሳ ዘበእንተ ኃጢአቱ፣

ስለ ኃጢአቱ ባቀረባት በግ ራስ ላይም እጁን ያኑር፤ ኃጢአቱ ባንቺ ምክንያት ይሠረይ ልኛል ሲል፤

ወይጠብሕዋ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘይሠውዐ፣

የሚሠዉዋትን በግ ቀድሞ መሥዋዕቱን በሚሠዉበት ቦታ ይሠዉዋት፤

፴፬፡ ወይነሥእ ካህን እምደማ በአጻብኢሁ ወይወዲ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ዘዕጣን፣

ካህኑም ከደሟ በጣቱ ጠልቆ ዕጣኑን በሚያጥኑበት በጽናው ቀንዶች ላይ ይጨምረው፤

ወይክዑ ኵሎ ደማ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘቍርባን፣

የቀረውን ደሟን ግን በቍርባኑ መሠዊያ መቀመጫ ያፍስሰው፤

፴፭፡ ወይመትር ኵሎ ስብሐ በከመ ይመትር ስብሐ በግዕ ዘመሥዋዕተ መድኃኒት፣

ድኅነት ሊደረግበት የተሠዋውን የበጉን ስብ እንዲለዩ ስቧን ይለየው፤

ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ቍርባን ለእግዚአብሔር፣

ለይቶ በእግዚአብሔር ቍርባን መሠዊያ ላይ ይጨምረው፤

ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ ወይትኃደግ ሎቱ፣

ያስተሠሪ ሎቱና ይትኃደግ ሎቱ አንድ ወገን፣ ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ይሠረይለታል።

## ምዕራፍ ፭

፩፡ ወእመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ ዘሰምዐ ኮነ ወሰምዐ ቃለ ወአምሐልዎ፣

አንድ ሰው አሥራት አስቀርቶ ማለት ከአሥር አንድ የሚከፍለውን አስቀርቶ ሌላም ገንዘብ አስቀርቶ አምጣ ቢሉት የለኝም ብሎ ከማለ በኋላ በምስክር ቢረታ



እርሱም አላበጀሁም ብሎ ንስሐ ቢገባ ፤ የዚህን ፍርድ ባንድ አምስት ጨምሮ ስድስት አድርጎ ይክፈል ብሎ ባሥራ አምስተኛው ቍጥር ያመጣዋል፤

ወየአምር ወርእየ ለእመ ኢያይድዓ ኃጢአተ ይከውኖ፣

እያወቀ፣ እየሰማ ካልተናገረ ዕዳ ይሆንበታል፤

፪፡ ወእመቦ ብእሲ ዘገሠሠ እምኵሉ ርኩስ፣

ከርኩስ ወገን ሊነኩት የማይገባውን የነካ ቢኖር፤

አው ምውተ አው ብልዐ አርዌ ዘኢኮነ ንጹሐ፤

የሞተውን፣ ንጹሕ ያይደለውን አውሬ የነከሰውን የነካ፤

አው በድነ እንስሳ ርኩስ አው በድነ ዘይትሐወስ ርኩስ ወዘአልዓለ እምኔሁ ርኩስ ውእቱ፣

የከብት ውዳቂን ተሐውሶ ያለውን ማለት ደመ ነፍስ ያልተለየውን ከዚህ ሁሉ የነካ ሰው የረከሰ ነው፤

፫፡ አው ዘገሠሠ እምርኩስ ሰብእ፣

ከሰው ርኩሰት የነካ ዕጣለት፤ ከሴት ያደረውን፣ ዝንየት ያገኘውን፣ የነካ የረከሰ ነው፤ የዚህንም ፍርድ ፤ በ፲፭ኛው ምዕራፍ፤ በ፪ኛው ቁጥር ያስጣዋል፤

ወእምኵሉ ርኩስ ወዘአልዓለ እምኔሁ ይረኵስ፣

ከረከሰው ሁሉ የነካ ይረክሳል፤

ወእመኒ እንዘ ኢየአምር ወእምዝ ተዓውቆ ወነስሐ፣

ሳያውቅ አድርጎት፣ ካደረገው በኋላ ቢታወቀው፣ ምንም ቢያዝን ቢፀፀት ይረክሳል፤

፬፡ ወእመኒ ብእሲ መሐለ ወነበበ በከናፍሪሁ ለገቢረ እኩይ አው ለገቢረ ሠናይ በእንተ ኵሉ እምከመ መሐለ እንዘ ኢየአምር፣

ክፋውንም ቢሆን በጎውንም ቢሆን አደርጋለሁ ብሎ ባንደበቱ ከተናገረ በኋላ ሳያውቅ ቢያፈርስ፤

ወእምዝ ተዓውቆ ዘአበሰ በአሐዱ እምዝንቱ፣

ካፈረሰው በኋላ የበደለው በደል ከታወቀው፤ ከበደሉ ባንዱ አዝኖ ተፀፅቶ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወአይድዐ ኃጢአቶ ዘአበሰ ባቲ፣

የበደለባትን ኃጢአቱን ከተና ገሬ፤

፮፡ ያመጽእ ለእግዚአብሔር በእንተ ኃጢአቱ ዘእንበለ በግዕት ንእስተ ንጽሕተ እምአባግዕ፣

ስለ በደለበት ኃጢአቱ ነውር የሌለባትን እንስት በግ ለእግዚአብሔር ያቅርብ፣ (ሐተታ) በጎውን ነገርስ ይሁን ክፉውን ነገር አደርጋለሁ ብሎ ቢያፈርስ ዕዳ ይሆንበታልና ፣ (በእንተ ኵሉ አለ) ቢሉ ክፉውንስ አደርጋለሁ ብሎ ቢያፈርስ ዕዳ አይሆንበትም፣ በጎውን ሲያይ (በእንተ ኃጢአቱ) ብሏል፤ አንድም በጎውን ነገር አደርጋለሁ ብሎ ቢያፈርስ ክፉውን ነገር አደርጋለሁ ብሎ (ቢያደርግ) ዕዳ ይሆን በታልና ይሠዋ አለ፤

አው ጠሊተ እምአጣሊ፣

በግ ቢታጣ ከፍየል ወገን እንስት ፍየል መርጦ ያቅርብ፤

ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ ዘአበሰ ወትትኃደግ ሎቱ፣

ካህኑም ስለ በደለው በደል ያስተሠርይለታል፤ ኃጢአቱም ትሠረይለታለችና ያመጽእ ብለህ እሠር፣

፯፡ ወእመሰ አልቦ ውስተ እዴሁ ወኢየአክል ለሤጠ በግዕ፣

በግ ፍየል በእጁ ባይኖር በእጁ ያለ ገንዘብ ለበግ ለፍየል መግዣ ባይበቃው፤

ያመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ፤ አው ክልኤተ ዕጕለ ርግብ ለእግዚአብሔር አሐደ በእንተ ኃጢአቱ ወአሐደ ለመሥዋዕት፤

ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት ርግብ አንዱን ስለ ኃጢአቱ አንዱን ስለ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቅርብ፤ አንድም ሁለት ዋኖስ ሁለት ርግብ ቢታጣ አንድ ዋኖስ አንድ ርግብ ያቅርብ ፤

፰፤ ወያመጽእ ኀበ ካህን ወይቀውም ወየሐርዶ ካህን ክሣዶ ወኢያወቅዮ ርእሶ ፣

ወደ ካህኑ አምጥቶ ይቁም፣ ካህኑም አንገቱን አርዶ ራሱን አይቍረጠው፤

፱፤ ወይነዝኀ ደሞ ውስተ አረፍተ ምሥዋዕ ፣

ደሙን በመሠዊያው ዙሪያ ይርጨው ፤



ወዘተርፈ ደሞ ያንጸፍጽፍ ላዕለ መንበረ ምሥዋዕ እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ውእቱ ፣

የቀረውን ደሙን ግን ስለ ኃጢአት የተሠዋ ነውና በመሠዊያው እግር ያፍስሰው፤

፲፤ ወለካልዑኒ ይገብሮ መሥዋዕተ በከመ ሕጉ፣

ሁለተኛውንም እንደ ሕጉ እንደ ሥርዓቱ ይሠዋው ፤

ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ እንተ አበሰ ወትትኃደግ ሎቱ፣

‹‹ትትኃደግና ያስተሠሪ አንድ ወገን ›› ስለ ኃጢአቱ ካህኑ ያስተሠርይለታልና ፤

፲፩፤ ወእመሰ አልቦ ውስተ እዴሁ ኢየአክል ለዘውገ ማዕነቅ አው ለክልኤ ዕጕለ ርግብ ፣

ዋኖስ ርግብ በእጁ ባይኖር በጁ ያለውም ገንዘብ ለዋኖስ ለሁለት ርግብ ዋጋ ባይበቃው፤

ያመጽእ ቍርባኖ በእንተ ኃጢአቱ ስንዳሴ ዐሥራተ እድ ዘመሥፈርተ ኢፍ፣

‹‹በእንተ ኃጢአቱና በእንተ ኃጢአቱ አንድ ወገን›› ስለ ኃጢአቱ ኢፍ የሚባል መሥፈሪያ ዓሥረኛ እጅ ቍርባን አድርጎ ያቅርብ፣ (ኢፍ የሚይዝ አሥር ላዳን ነው) ላዳን ስንዴ ያምጣ ሲል ነው፤

ወኢይወዲ ውስቴቱ ቅብዓ ወስኂነ እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ውእቱ ፤

ስለ ኃጢአት የቀረበ መሥዋዕት ነውና ዘይት ቍንዶ በርበሬ አይጨምሩበት፣ ቍንዶ በርበሬ ዘይት የሌለበት አልጫ ይባላል፤ አልጫ ኃጢአት አትሥሩ ሲል፣ መሥዋዕት ብትሠሩም ከተመለሳችሁ አስተሠርይላችኋለሁ ሲል ነው ፤

፲፪፤ ወያመጽእ ኀበ ካህን ወይዘግን እምኔሁ ካህን ምልአ ሕፍኑ በእንተ ተዝካሩ፣

ያቀረበው ሰው ወደ ካህኑ ያምጣው፤ ካህኑም ከቀረበው ዳቦ እጅ ታህል ዘግኖ (ቆርሶ) ለመታሰቢያ ሲሆን ፤

ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ በላዕለ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር እስመ ዘኃጢአት ውእቱ ፣

ለእግዚአብሔር ቍርባን በሚቀርብበት በመሠዊያው ላይ ይጨምረው ፣ የኃጢአት መሥዋዕት ነውና ፤

፲፫፤ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ኃጢአቱ እንተ አበሰ በአሐዱ እምእሉ ወይትኃደግ ሎቱ፣

www.ethiopianorthodox.org

ካህኑም ስለበደለው በደል በስንዴውም ቢሆን በርግቡም ቢሆን ከእሲህ ባንዱ ያስተሠርይለታል፣ ኃጢአቱም ይፋቅለታል ፤

ወዘተርፈ ይከውን ለካህን ከመ መሥዋዕተ ስንዳሴ ፣

የቀረው እንደ ስንዴው መሥዋዕት ለካህኑ ይሁን ፤

፲፬፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤

፲፭፤ ብእሲ ለእመ ረሲዓ ረስዓ ወአበሰ በኢያእምሮ ላዕለ ቅድሳተ እግዚአብሔር ፣

ለእግዚአብሔር የተለየውን ሳያውቅ አስቀርቶ የበደለ ሰው ቢኖር ፤

ያመጽእ በእንተ ኃጢአቱ ወንስሓሁ ለእግዚአብሔር ሐርጌ ንጹሐ እምአባግዕ ዘሤጠ ሰቅሎን ብሩር በሰቅል ቅዱስ በእንተ ዘነስሐ ፣

‹‹በእንተ ንስሐሁና በእንተ ዘነስሐ›› አንድ ወገን ፤ እግዚአብሔርን ስለበደለበት ኃጢአቱ ከበግ ወገን ነውር የሌለውን በቤተ እግዚአብሔር አዋቂ ‹‹ሚዛን›› የተመዘነ ዋጋው ሦስት ብር የሆነ ሙክት ለእግዚአብሔር ያቅርብ ፤

፲፮፤ ወይፈዲ በዘአበሰ ላዕለ ቅድሳት ፣

ለእግዚአብሔር በተለየው በቀደመው ገንዘብ ላይ አራጣ ይክፈል ፤

ወይዌስክ ላዕሌሁ ኃምስተ እዴሁ፣

‹‹ወሰምዐ ቃለ ወአም ሐልዎ›› ያለውን አመጣ ፤ ምዕ ፭ ቍ. ፩ ምሎ በምስክር ቢረታ ፣ እሱም አላበጀሁም ብሎ ንስሓ ቢገባ አምስት ትርፍ ስድስተኛ ዓይነት አድርጎ ይስጥ ፤

ወይሁቦ ለካህን ወያስተሠሪ ሎቱ በውእቱ ሐርጌ ዘንስሓሁ ወይትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ ፣

የሚከፍለው ሰው ወስዶ ለካህኑ ይስጠው ፤ ካህኑም ስለኃጢአቱ ባቀረበው ኃጢአቱን ያስተሠርይለታል፤ ትርፍ ገንዘብ በመስጠቱም ኃጢአቱ ይሠረይለታል፤

፲፯፤ ወብእሲ እመ አበሰ ወገብረ አሐተ እምትእዛዘ እግዚአብሔር ዘኢይከውን ለገቢር በኢያእምሮ ወተዐውቆ ወነስሐ በእንተ ዘኮነቶ ኃጢአተ ፣



እግዚአብሔር ካዘዘው ትእዛዝ ወጥቶ ባለማወቅ አንዲት ኃጢአት የሠራ ሰው ቢኖር፣ ኋላም የሠራው ኃጢአት ታውቆት ይችውም ዕዳ ስለሆነችበት ንስሓ ቢገባ፤

፲፰፤ ያመጽእ ሐርጌ እምአባግዕ ንጹሐ ዘሤጠ ሰቅሎን ብሩር በእንተ ንስሓሁ ኀበ ካህን ፣

ስለ ሠራው ኃጢአት ከበጎች ወገን ዋጋው ሦስት ብር የሆነውን ሙክት ወደ ሊቀ ካህናቱ ያቅርብ ፤

፲፱፤ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በእንተ ረሲዖቱ ዘረስዓ ወበእንተ ዘኢያእመረ ወይትኃደግ ኃጢአቱ ፣

‹‹ያስተሠሪና ወይትኃደግ አንድ ወገን››፤ ካህኑም ሳያውቅ ዘንግቶ ስለ በደለው ያስተሠርይለት ፤

እስመ ነስሐ ቅድመ እግዚአብሔር፣

በእግዚአብሔር ፊት ንስሓ ገብቷልና ፡፡

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤

፪፤ ብእሲ ለእመ አበሰ ወአስተተ ወተኀየየ ትእዛዘ እግዚአብሔር ፣

‹‹አስተተና ተኀየየ›› አንድ ወገን፣ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ ንቆ አቃሎ የበደለ ሰው ቢኖር ፤

ወሐሰዎ ለካልኡ በዘአማኀፀኖ ፣

አደራ የሰጠውን ወንድሙን ቢክደው ፤

አው በዘተሳተፎ አው ዘሄዶ አው ዘዐመፆ ለካልኡ ፣

በእሽሙር የገዙትን ማለት ባንድነት የገዙትንም ቢሆን ፤ ወዙ የነጠባበትን፤ ደሙ የፈሰሰበትን ገንዘብ ቢክደው፤ አንድም አንዱ አንዱን በግፍ ቢበድለው ፤

፫፤ አው እመ ረከበ ዘገደፉ ወሐሰወ በእንቲአሆሙ ፣

አንዱ የጣላትን ገንዘብ አግኝቶ ስለነሳቸው ቢክደው ፤

ወመሐለ በዓመፃ በአሐዱ እምእሉ ዘይገብር ሰብእ ዘኢይከውን ለገቢር ወለአብሶ ቦሙ ፣

በነሱ ለመበደል ሊሠሩት የማይገባውን ሲናገሩት ከምጣው አንዱን ሠርቶ በሐሰት የማለ ሰው ቢኖር ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወእምከመ አበሰ ወእምገ፤ ነስሐ ወአግብአ ዘነሥአ ወሄደ አው ዘዓመፀ ወገፍዐ ፤

ከበደለ በኋላ ባገኘው በቀማ ውም ገንዘብ ቢሆን ፤

አው ማኅፀነ ዘአማኅፀኖ ካልዑ አው ዘረከበ ዘገደፉ ፤

ወንድሙ አደራ ባስጠበቀው ወድቃ ባገኛትም ገንዘብ ቢሆን ተፀፅቶ ንስሐ ቢገባ ፤

፭፤ እምኵሉ ዘመሐለ በእንቲአሁ በዓመፃ ወአግብአ ርእሰ ንዋዩ ፤

ከተናገረው ገንዘብ ሁሉ ወስዶ በሐሰት ከማለ በኋላ አለ ብኝ ብሎ የወሰደውን ገንዘብ ቢመልስ ፤

ይወስክ ኃምስተ እዴሁ ላዕሌሁ ወያግብእ ለበዓለ ንዋይ በዕለተ ዘለፍዎ ፤

ምስክሮች ከመሰከሩበት፤ ዳኞች ከፈረዱበት በኋላ አምስት ትርፍ ስድስተኛ ዐይነት አድ ርጎ ለባለገንዘቡ ይስጥ ፤

፮፤ ወያመጽእ በእንተ ንስሓሁ ለእግዚአብሔር በግዐ ንጹሐ እምአባግዕ ዘሤጠ ሰቅሎን ብሩር፤

ስለ በደለው በደል ከበጎች ወገን ቀንዱ ያልከረከረውን ጠጕሩ ያላረረውን ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ባንድ ወቄት የተገዛውን በግ ለእግዚአብ ሔር ያቅርብ ፤

፯፤ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ሊቀ ካህናቱም በእግዚአብሔር ፊት ያስተሥርይለት ፤

ወይትኃደግ ሎቱ በበይነ አሐዱ እምእሉ ዘገብረ ወነስሐ በእንቲአሁ፤

‹በእንቲአሁ› ኃጢአት ስለ መሥራቱ ‹‹በበይነ አሐዱ›› ስለመጸጸቱ ከግብራቱ ሁሉ ተለይቶ ይሠረይለታልና ፤ አንድም በመሥዋዕቱም ቢሆን ትርፍ በመስጠቱም ቢሆን ኃጢአቱ ይሠረይለታልና ፤

፰፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

## ጉባኤ

፱፤ አዝዞሙ ለአሮን ወለደቂቁ ወበሎሙ ፤

አሮንንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ፤

ከመዝ ውእቱ ሕጉ ለመሥዋዕት፤



የመሥዋዕቱ ሥርዓት እን ዲህ ነው አለ ፤ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ነው ፤

ውስተ ምሥዋዕ ተኃድግዎ እስከ ይጸብሕ እንዘ ትነድድ እሳተ ምሥዋዕ ላዕሌሁ ፤

የመሠዊያው እሳት እስኪነጋ ድረስ በበላዩ እየነደደ በመሠ ዊያው ላይ ተዉት በላቸው፤ ‹ሐተታ› ስቡን በምሥዋዑ ላይ አቅልጠው ምሥዋዑን እሳት እንዳይጐዳው ፈቅ አድ ርጎ በጕድጓዱ ሲነድ ያድ ራል ፤

፲፤ ወይለብስ ካህን ልብሰ አጌ ወቃሰ ዘአጌ ላዕለ ሥጋሁ ፤

ካህኑም የነጭ ሐር ቀሚስ ለብሶ የነጭ ሐር ሰናፊል አግብቶ ፤

ወያሴስል ውእተ ሐመደ ዘበልዓት እሳተ መሥዋዕት እምውስተ ምሥ ዋዕ ወያነብሮ ቅሩበ ምሥዋዕ፤

የመሥዋዕቱ እሳት የበላቸ ውን ያን አመድ ከመሠዊ ያው ጠርጎ በመሠዊያው አንጻር ያኑረው ፤

፲፩፤ ወያሴስል ውእተ አልባሲሁ ወይለብስ ካልአ ልብሰ ወይወስድ ሐመደ አፍኣ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ፤

የለበሰውን ነጭ ሐር አውልቆ ሌላ ተርታ ልብስ ለብሶ ፤ አመዱን ከከተማው በአፍኣ አውጥቶ በንጹሕ ቦታ ያፍስሰው ‹‹ሰናፊሉን ሲያይ አልባስ ብሎ አበዛ›› ፤

፲፪፤ ወእሳትሰ ትነድድ ውስተ ምሥዋዕ በኵሉ ጊዜ ወኢትጠፍእ፤

እሳቲቱ ግን በነግህም በሠርክም ትንደድ እንጂ አትጥፋ፤

ወያነድድ ዕፀወ ላዕሌሁ ካህን በበነግህ ወይዌጥሕ ላዕሌሁ ዘመሥዋዕት ወይወዲ ውስቴቱ ስብሐ ዘመድኃኒት ፤

ካህኑም ጧት ጧት በመሠ ዊያው ላይ እንጨቱን ይጨ ምር፤ በእንጨቱም ላይ ሊጤስ የቀረበውን ሥጋ ያኑር፤ ድኅ ነት ሊደረግበት የተለየውንም ስብ ጨምሮ ያጢሰው ፤

፲፫፤ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለመ ሥዋዕት ዘያበውኡ ደቂቀ አሮን ውስተ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብ ሔር ፤

እግዚአብሔር እንዳልተለየው ለማወቅ ፤ አሁንም አሁንም ቅድመ እግዚአብሔር ይላል፤ የአሮን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ወዳለው መሠዊያ የሚያ

www.ethiopianorthodox.org

ቀርቡት የመሥዋዕቱ ሥር ዓት ይህ ነው፤

፲፬፤ ወይነሥእ እምኔሁ በሕፍኑ እምስንዳሌ ዘመሥዋዕት ቅድመ እግዚአብሔር ምስለ ቅብዑ ወም ስለ ኵሉ ስኂኑ ዘሀሎ ውስተ መሥዋዕት ፤

እግዚአብሔር ወደ ሲቀበለው ካቀረበው ዳቦ እጅ ያህል ቆርሶ ከዘይቱ ጋር ለቍርባን ከቀረበው ከተጣፈጠው ቊንደ በርበሬ ፤ አንድም ነጭ ዕጣን ጨምሮ፤

፲፭፤ ወይወድዮ ውስተ ምሥዋዕ እስመ ቍርባነ ዝክሩ ለእግዚአ ብሔር ውእቱ ወመዓዛ ሠናይ ፤

በጎ መዓዛ ያለው ለእግዚአ ብሔር የመታሰቢያ ቍርባን ነውና በመሠዊያው ላይ ያጢሰው ፤

፲፮፤ ወዘተርፈ እምኔሁ ይበልዑ አሮን ወደቂቁ ወናዕተ ይበልዕዎ በመካነ ቅዱስ ውስተ ዓፀደ ደብተራ ዘመርጡል ፤

ከዚህ የቀረውንም አሮንና ልጆቹ ይብሉት፣ ሲበሉትም በደብተራ ኦሪት ዙሪያ በከበረ ቦታ ቂጣውን ይብሉት፣ ‹ሃያ ክንድ› አርባ ክንድ አለና ዓፀደ ደብተራ አለ ፤

፲፯፤ ወኢያብሕእዎ ለአብስሉ ፤

ለሰውነታችን ይስማማን፣ ተረፈ መሥዋዕቱን ለመጋገር እያኮ ምጥጡት ማለት አያቡኩት፤

ክፍሎሙ ውእቱ ዝንቱ ዘወሀ ብክዎሙ እመሥዋዕቱ ለእግዚአብ ሔር ቅዱስ ለቅዱሳን ፤

የከበረው መሥዋዕት ለከበሩ ለካህናት ስለሆነ ለእግዚአብ ሔር ከሚቀርበው መሥዋዕት የሰጠኋቸው ዕድል ፈንታ ቸው ይህ ቂጣ ነውና አያ ቡኩት ፤

ከመ ዘበእንተ ኃጢአት ወዘበእንተ ንስሐኒ ፤

ስለ ኃጢአትና ስለ ንስሐ የቀረበው መሥዋዕት ለካህ ናት ይሁን ብሎ እንዳዘዘ ፤

፲፰፤ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ ሕግ ውእቱ ዝንቱ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ ፤

በዘመናችሁ ሁሉ ይህ የዘለ ዓለም ሥርዓት ነውና ፤ ከካ ህናት ወገን ወንድ ወንዱ ይብላው ፤

ወእመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ኵሉ ዘገሠሠ ይትቄደስ ፤

‹‹ኵሉ ይበልዖ›› ካለ ብሎ ማንም እንዳይበላው ፤ ይህን



የሚመገብ ሰው ሁሉ ከኃ ጢአት ንጹሕ እንደ ሆነ አውቆ፤ አንድም ንጹሕ ሁኖ ይብላው ፤

፲፱፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤

፳፤ ዝንቱ ውእቱ ዘአገውክዎሙ ለአሮን ወለደቂቁ እምዘ ያመጽኡ ለእግዚአብሔር ፤

ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ከሚያ ቀርቡት መሥዋዕት ለአሮን ለልጆቹ የሰጠኋቸው ሥር ዓት ይህ ነው አለ፣ ‹ወደፊት ያመጣዋል› ፤

እምአመ ዕለተ ተቀብዐ ዓሥራተ እድ ዘመስፈርተ ኢፍ ስንዳሌ ፤

ተቀብቶ ከከበረበት ቀን ጀምሮ ለሊቀ ካህናቱ የሚሰጠው ያንዱ ቀን መሥዋዕት ኢፍ የሚ ባል መስፈሪያ ፲ኛ ነው፣ የኢፍ ፲ኛም አንድ ላዳን ነው፤

መሥዋዕትሰ ዘበኵሉ ጊዜ መንፈቃ ለነግህ ፤ ወመንፈቃ ለፍና ሠርክ፣

በየጊዜው የሚሠዋው ላዳን ግን ከሁለት ተከፍሎ እኩሌ ታው ለነግህ እኩሌታው ለሠ ርክ ይሁን ፤

፳፩፤ ምስለ ቅብዕ በቴጉን ይገብ ርዎ ወለዊሶሙ ያመጽእዎ ፤ እስመ መሥዋዕት ፍቱት ውእቱ፣

‹‹ለዊሶሙ ምስለ ቅብዕ ወይገ ብር በቴጉን ወያመጽእዎ›› ብሎ ይገጥሟል፤ ‹የተፈተተ እንደ ሾና ያለ ነውና› በዘይት ለውሰው በብረት ምጣድ ጋግረው ያቅርቡት፤

ወቍርባነ ዘመዓዛ ሠናይ ለእግዚ አብሔር፣

በጎ መዓዛ ያለው ቍርባን ነውና፤

፳፪፤ ካህን ዘቅቡዕ ህየንቴሁ እም ደቂቁ ይገብሮ፣

‹‹ህየንቴሁ ለአሮን›› ነው፣ በአ ሮን ፈንታ ከልጆቹ ተቀብቶ የከበረው ካህን ይሠዋው፤

ሕግ ውእቱ ዘለዓለም ወበኵሉ ጊዜ ይትገበር፣

የዘለዓለም ሕግ ነውና በየጊ ዜው ሁሉ ይሠዋ፤

፳፫፤ ወኵሉ መሥዋዕት ዘካህናት ይነድድ ኵሎ ጊዜ ወአልቦ ዘይትበላዕ እምኔሁ

‹ሰ› የቀረው ነው፣ ካህናት የሚያቀርቡት መሥዋዕት ግን በየጊዜው ይቃጠላል እንጂ ከእርሱ የሚበላ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም እምኔሁን ለሊቀ ካህናቱ ይሰጧል ፤ ከሊቀ ካህናቱ የተረፈው አይበላ፤ ይኸስ ስንኳን ከቀደመው ሊቀ ካህናት ከሐዲስም ሊቀ ካህናት የተረፈው ይበላል ብሎ፤ ከመሥዋዕተ ኃጢአቱ ጢሶለት የቀረው አይበላ ሲል ነው ፤

፳፱፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፴፤ ንግሮሙ ለአሮን ወለደቂቁ ወበሎሙ ከመዝ ውእቱ ሕጋ ለኃጢአት፤

የመሥዋዕተ ኃጢአት ሥርዓት እንዲህ ነው ብለህ ለአሮን ለልጆቹ ንገራቸው ብሎ ነገረው፤

ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት በህየ ይጠብሑ ዘበእንተ ኃጢአትኒ በቅድመ እግዚአብሔር፤

መሥዋዕተ መድኃኒቱን በሚሠዉበት ቦታ፤ ስለ ኃጢአትም በእግዚአብሔር ፊት የሚሠዉበትን መሥዋዕት በዚያ ይሠዉት ብሎ ነገረው፤

ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ፤

ከመሥዋዕቱ የተለየው መሥዋዕት ከሕዝቡ ለተለዩ ካህናት ነውና፤

፴፩፤ ካህን ዘይገብሮ ይበልዖ፤

የሚሠዋው ካህን ይብላው፤

ወበመካን ቅዱስ ይበልዕዎ በኀበ ዓፀደ ደብተራ ዘመርጡል፤

‹ይበልዖ ካህን› ካለ ብለው ወደ ቤታቸው እንዳይወስዱት ያስጠነቅቃል ፤ በከበረ ደብተራ ኦሪት ውስጥ ይብሉት አለ ፤

፴፪፤ ወኵሉ ዘገሠሦ ለውእቱ ሥጋ ይትቄደስ ፤

ይህን መሥዋዕቱን የሚነካው ማለት የሚመገበው ሁሉ ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ ይመገብ ፤

ወእመቦ ኀበ ተነዝኃ እምደሙ ውስተ ልብስ ኀበ ተነዝኀ ላዕሌሁ የሐፅብዎ በመካን ቅዱስ፤

መሥዋዕቱን ሲሠዋ ደም የተረጨበት ሰው ቢኖር፤ ልብስም ቢሆን የተረጨበትን በከበረ ቦታ ይጠቡት፤

፴፫፤ ወለልሕኵትሰ ዘቦቱ አብሰልዎ ይሰብርዎ፤

የቀቀሉበትን ሸክላም ይስበሩት አለ ፤ መሬትነት ስላለው ይሰርበዋልና ፤ ዛሬም ከሕግ ከሥርዓት የወጣውን መምህር መክረውት አስተምረውት



አልመለስም ቢል አውግዘው ይለዩት ሲል ነው፤

ወእመሰ በንዋየ ብርት አብሰልዎ የሐበርትዎ ወየሐፅብዎ በማይ፤

በብርት ዕቃ ‹በናስ› ቢቀቅሉት ግን አይሰርበውምና ወልውለው ሰንግለው ይሠዉበት፤ ዛሬም ከሕግ ከሥርዓት የወጣ መምህር መክረውት አስተምረውት ቢመለስ አውግዘው አይለዩት፤ ‹መልሰው ይሹሙት› ሲል ነው፤

፴፬፤ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ፤

የከበረው መሥዋዕት ለከበሩ ለካህናት ነውና ወንድ ወንዱ ሁሉ ይብላው፤

፴፭፤ ወኵሉ ዘበእንተ ኃጢአት ዘያበውኡ እምደሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ያስተሥርዩ ቦቱ ውስተ ቅድስት ኢይትበላዕ በእሳት ያነድድዎ ፤

‹‹ውስተ ደብተራና ውስተ ቅድስት አንድ ወገን››፤ ያስተሠርዩበት ዘንድ ከደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይዘው የሚገቡት መሥዋዕተ ኃጢአት ሁሉ ‹አላ ያለበት ነው› በእሳት ያቃጥሉት እንጂ አይበላ።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወከመዝ ውእቱ ሕጉ ለንስሓ፤

የመሥዋዕተ ኃጢአትን ጨርሶ የመሥዋዕተ ንስሓን አመጣ፤ የመሥዋዕተ ንስሓ ሥርዓቱ እንዲህ ነው፤

ቅዱስ ውእቱ ለቅዱሳን፤

ከመሥዋዕቱ የተለየው መሥዋዕት ከሕዝቡ ለተለዩ ካህናት ነውና፤

፪፤ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት በህየ ይጠብሕዎ ለበግዕ ዘንስሓ፤

‹ከመዝ ያለውን በህየ ብሎ አመጣው› መሥዋዕተ ኃጢአቱን በሚሠዉበት ቦታ በድለው ተመልሰው ያቀረቡትን በግ በዚያ ይሠዉት ፤

ወይክዕዉ ደሞ ውስተ ዓውደ ምሥዋዕ፤

ደሙንም በመሠዊያው ዙሪያ ይርጩት ፤

፫፤ ወኵሎ ስብሐ ያመጽእ ወሐቌ ሁኒ ወስብሐኒ ዘይከድን ንዋየ ውስጡ ወስብሐኒ ዘውስተ አማዑቱ፤

ከቀረበው መሥዋዕት የተገኘውን ስብ ሁሉ ጻሌውን ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሞራውን

www.ethiopianorthodox.org

ከአንጀቱ ውስጥ የሚገኘውን ስብ፤

፬፤ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወዘላዕለ ጸራዒቱ ፡፡

ሁለቱን ኵላሊቱን በላያቸው ያለውን ስብ በጭቅናው ላይ ያለውንም ስብ፤

ወከብደ እንተ ትንዕስ ምስለ ኵልያቲሁ ይመትሮ ካህን፡፡

ግልገል ጉበቱን ከሁለቱ ኵላሊቱ ጋር ካህኑ ለይቶ፤

፭፤ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ቍርባን ውእቱ ዘመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ዘበእንተ ንስሓ ውእቱ፡፡

በድለው ተመልሰው ያቀረቡት ስለሆነ፡፡ ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ነውና፡፡ ካህኑ በመሠዊያው ላይ ይጨምረው ‹ያጢሰው›፤

፮፤ ኵሉ ተባዕት እምካህናት ይበልዖ በመካን ቅዱስ ፡፡

ከካህናት ወገን ወንድ ወንዱ ሁሉ በከበረ ቦታ ይብላው፤

ወቅዱስ ውእቱ ለቅዱሳን፡፡

የከበረውም መሥዋዕት ከሕዝቡ ተለይተው ለከበሩ ለካህናት ነው፤

፯፤ በከመ ዘበእንተ ኃጢአት ከማሁ ዘበእንተ ንስሓኒ፡፡

የንስሓው መሥዋዕት እንደ ኃጢአቱ መሥዋዕት ነው፤

ወአሐዱ ሕጎሙ ለካህን ዘያስተሠሪ በእንቲአሆሙ ሎቱ ውእቱ ፡፡

የመሥዋዕተ ኃጢአትና የመሥዋዕተ ንስሓ ሥራታቸው አንድ ነውና፡፡ ከመሥዋዕተ ኃጢአት ጠሶስት የቀረው እንዲበላ ከመሥዋዕተ ንስሓም ጠሶስት የቀረውን ስለነሱ የሚያስተሠርየው ካህን ይብላው፤ አንድም መሥዋዕተ ኃጢአት መሥዋዕተ ንስሐ የሕዝቡን ኃጢአት ለሚያስተሠርይ ለካህኑ ይሁን ፤

፰፤ ወለካህን ዘያበውእ መሥዋዕተ ሰብእ ማዕሰ መሥዋዕቱ ዘውእቱ ሦዓ ሎቱ ውእቱ፡፡

‹‹ዘያበውእ መሥዋዕተና ዘውእቱ ሦዓ አንድ ወገን›› የመሥዋዕቱ ‹የበጉ› ቍርበትም ለሠዋው ካህን ይሁን ፤

፲፤ ወኵሉ መሥዋዕት ዘግቡር ለኵሉ ደቂቀ አሮን ዕሩይ ውእቱ ለለአሐዱ፡፡

የተሠዋው የመሥዋዕቱም ተረፍ ሁሉ ለአሮን ልጆች ላንዱም ላንዱም የተካከለ ነው፤



፲፩፤ ወዘመዝ ውእቱ ሕገ ሠሥዋዕተ መድኃኒት ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር፡፡

ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የሠሥዋዕተ ሠድኃኒት ሕጉ እንዲህ ነው፡፡ ‹ሐተታ› ሕጉንስ ተናግሮታል ብሂሉን አልተናገረውም ነበርና ስለዚህ ደገመው፡፡ ሠሥዋዕተ መድኃኒት የሚሰውም ከአባር ከቸነፈር አድኗቸው የሚሠዉት ነው ፤

፲፪፤ ወለእመ በእንተ አኰቴት አምጽአ ያመጽእ ውስተ መሥዋዕተ አኰቴት ኅብስተ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ወጸሪቀ ናዕት ዘሥንዳሌ ዘልውስ በቅብዕ ፡፡

ስለ ምስጋና የምስጋና መሥዋዕት ቢያቀርብ በዘይት የታበቀ በዘይት የተለወሰ የስንዴ ዳቦ ያምጣ፡፡ መሥዋዕተ አኰቴት የሚለውም ሥርዓት ተሠርቶላቸው ታምራት ተደርጎላቸው የሚሠዉት ነው ፤

፲፫፤ ምስለ ኅብስት ዘብሑዕ ቍርባኖ ለመሥዋዕተ አኰቴት ዘመድኃኒት፡፡

‹ጸሪቀ ናዕት ብሎ ነበርና› ድኅነት ሲሆንበት ‹ሲደረግበት› ለመሥዋዕተ አኰቴት የሚቀርበውን ቡሆ ጨምሮ ያቅርበው፤

፲፬፤ ወይወስድ እምኔሁ አሐደ እምኵሉ ቍርባኑ ሀብተ እግዚአብሔር ለካህን ዘይክዕዎ ለውእቱ ደመ አኰቴት ሎቱ ውእቱ፡፡

ከሚሠዋውም ከመሥዋዕቱ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈንታ አንዱን የሠዋው ካህን ይውሰድ ፤

፲፭፤ ወሥጋሁኒ ዘመሥዋዕተ አኰቴት ሎቱ ውእቱ፡፡

ከመሥዋዕተ አኰቴትም የተረፈው ሥጋ ለሱ ነው፤

፲፮፤ ወበዕለተ ያመጽእዎ ይበልዕዎ ወኢይኅድጉ ዘያተርፉ ለነግህ ፡፡

መሥዋዕተ መድኃኒት ‹መሥዋዕተ አኰቴት› አያድርጉምና በሠዉት ቀን ይብሉት፤

፲፯፤ ወለእመሰ ዘቦ ብፅዓት አው ዘበፈቃዱ ያበውእ ቍርባኖ በዕለተ አምጽአ መሥዋዕቶ ይበልዕዎ ወበሳኒታሂ ፡፡

መሥዋዕቱ የስለትም ‹የፈቃድም› ቢሆን ግን በመጣበት ቀን በማግስቱም ቢሆን ይብሉት፤

፲፰፤ ወለእመ ተርፈ እምሥጋ መሥዋዕቱ እስከ ሣልስት ዕለት በእሳት ያውዕይዎ ፡፡

ከመሥዋዕተ ብፅዓት ‹ከመሥዋዕተ ፈቃድ› በልተው

www.ethiopianorthodox.org

የተረፈውን በነጋው ይብሉት ብሎ ነበርና ከሁለተኛው ቀን ተርፎ እስከ ሦስተኛው ቀን ያደረ ቢኖር በእሳት ያቃጥሉት፤

፲፰፤ ወለእመሰ በልዐ እምውእቱ ሥጋ በሣልስት ዕለት ኢይትዌከፎ ለዘአብአ ወኢይትኌለቆ እስመ ርኩስ ውእቱ ፤

በሦስተኛው ቀን ቢበሉት ግን የረከሰ ነውና ላቀረበው ሰው እግዚአብሔር አይቀበልለትም፣ ከመሥዋዕትም አይቈጠርለትም፣ ‹ሐተታ› ምነው ሕግ ያፈረሱ ካህናቱ፣ መሥዋዕት ላቀረበው ሰው ስለምን አይቀበለውም አለ ቢሉ፣ ካህናቱ እንዲጠበቁ እንዲጠነቀቁ ሕዝቡም መሥዋዕት የሚያቀርቡ ኃጢአት ይሠረይልናል፣ በረከት ይሰጠናል ብለው ነውና፣ ሕዝቡ ይህን ሰምተው ኃጢአት ካልተሠረየልን፣ በረከት ካልተሠጠን ለምን እናቀርባለን ብለው ገንዘብ ከመስጠት፣ መሥዋዕት ከመሠዋት እንዳይከለከሉ ብሎ ‹ኢይትዌከፎ አለ እንጂ ዕዳውስ ለካህናቱ ነው ፤

ወነፍስ እንተ በልዓት እምኔሁ ይእቲ ትነሥእ ኃጢአቶ ፤

ሦስት ቀን ካደረው መሥዋዕት የበላች ሰውነትም ‹‹ኃጢአቶ ለዘአብአ ነው›› የዚያን ሰው ፍዳ ኃጢአቱን ትቀበላለች ፤

፲፱፤ ወሥጋኒ እምከመ ለከፎ እምኵሉ ርኩስ ኢይብልዕዎ አላ በእሳት ያውዕይዎ ፤

በእሳት ያቃጥሉት እንጂ ርኵስ ከሚያሰኘው ወገን የነካውን ሥጋ አይብሉት ፤

ወኵሉ ንጹሕ ይብላዕ እምኔሁ ፤

‹‹እምኔሁ ለኵሉ ንጹሕ ሲል ነው፣ ንጹሕ ከሆነው ከዕለቱ መሥዋዕት የተረፈውን ይብላ እንጂ ከሁለተኛው ቀን የተረፈውን አይብላ፤ አንድም ንጹሕ የሆነ ሰው ሁሉ ከሱ ይብላ ፤

፳፤ ወነፍስ እንተ በልዓት እምውእቱ ሥጋ ዘመሥዋዕተ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር እንዘ ርኵስ ላዕሌሁ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ፤

ላዕሌሁ ለመሥዋዕተ መድኃኒት ነው፣ ‹‹እንተ በልዓትና ይእቲ ነፍስ አንድ ወገን ነው››፣ እንደረከሰች እያወቀች ‹ረክሳለች› የእግዚአብሔር ድኅነት ከሚደረግበት መሥዋ



ዕት የበላች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ፤ አንድም በወገኖቿ ውስጥ ተፈርዶባት ትጥፋ ፤

፳፩፤ ወነፍስኒ እንተ ገሠሠት እምኵሉ ርኵስ ፤

ርኵሰት ካለው ወገን ሁሉ የነካች ሰውነት ፤

አው እምርኵሰ ሰብእ አው ዘእምእንስሳ ዘኢኮነ ንጹሐ ፤

ከሴት ያደረውን ዝንየት ያገኘውን ሰው የነካች ከእንስሳም ወገን ንጹሕ ያልሆነውን የነካች ፤

ወበልዓት እምውእቱ ሥጋ ዘመሥዋዕተ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ፣

ይህን ሁሉ ነክታ የእግዚአብሔር ድኅነት ከሚደረግበት መሥዋዕት የተረፈውን የበላች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ፤

ጉባኤ

፳፪፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፳፫፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ኵሎ ስብሐ ላሕም ወበግዕ ወዘጠሊ ኢትብልዑ ፤

ለእስራኤል ልጆች የላሙን፣ የበጉን፣ የፍየሉን ስብ ሁሉ አትብሉ ብለህ ንገራቸው ፤

፳፬፤ ወኵሉ ስብሐ ምውት ወዘብላዓ አርዌ ለግዩር ይኩንክሙ ፤

አውሬ የነከሰው የሞተው ‹የበክቱ› ስብ ለመጻተኛ ይሁናችሁ፣ ‹ለግብር ይኩንክሙ ቢል› ለመጫኛ ለዳውላ ይሁናችሁ ሲል ነው ፤

ወአንትሙሰ ባሕቱ ኢትብልዕዎ ፤

እናንተ ግን አትብሉት ብለህ ንገራቸው ፤

፳፭፤ ወኵሉ ዘበልዓ ስብሐ እምዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ እመራዕይ ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ ፤

‹እምዘያመጽኡና እመ ራዕይ አንድ ወገን›፣ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ካቀረቡት ስቡን የበላ ሰው ሁሉ ያች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ፤

፳፮፤ ወኵሎ ደመ ኢትብልዑ በኵለሄ በኀበ ሀለውክሙ ኢዘእንስሳ ወኢዘአዕዋፍ ፤

www.ethiopianorthodox.org

መሥዋዕት በሠዋችሁበት ቦታ ሁሉ የእንስሳትም ቢሆን የአዕዋፍም ቢሆን ብርንዶውን አትብሉ፤ አንድም በቁሙ ደሙን አትብሉ፤ ‹ሐተታ› እንዳለፈው፤

፳፮፤ ወኵላ ነፍስ እንተ በልዓት ደመ ለትደምሰስ እምሕዝባ ፤

ብርንዶውን፤ አንድም ደሙን፤ የበላች ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ፤

፳፯፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፳፱÷፴፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ዘያመጽእ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ያመጽእ ቊርባኖ በእደዊሁ ስብሐ ተላዕ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ቅድመ እግዚአብሔር፤

ድኅነት የሚደረግበትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ ሰው የፍሪንባውን ስብ ግልገል ጉበቱን ቍርባን አድርጎ በእጁ በእግዚአብሔር ፊት ያቅርብ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው፤ ‹‹በእደዊሁ አለ›› በሰውልኮ የሚቀር አለና፤

፴፩፤ ወይወድዮ ካህን ለስብሐ ተላዕ ላዕለ ምሥዋዕ ፤ ወተላዑስ ይኩን ለአሮን ወለደቂቁ፤

‹‹ይወድዮ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ምሥዋዕ ብሎ ይገጥሟል››፤ በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያ ሊሆን የፍሪንባውን ስብ በመሠዊያው ላይ ያጢሰው፤ ጢሶ ለት የቀረው ግን ለአሮን ለልጆቹ ይሁን፤

፴፪፤ ወአገዳሁ ዘየማን እመሥዋዕተ መድኃኒትክሙ ይሁብ ሀብተ ለካህን ዘያበውእ ደመ መድኃኒቱ ወስብሐኒ ዘደቂቀ እስራኤል፤

ድኅነታቸው ሲደረግበት ከቀረበው መሥዋዕት ቀኝ ወርቹ ደመ መድኃኒቱ የእስራኤል ልጆች ኃጢአት ሲሠረይበት ስቡን ለሚያቀርብ ለካህኑ ዕድል ፈንታ ይሁን፤

፴፫፤ አገዳ ዘየማን ለአሮን ወለደቂቁ ክፍል ውእቱ፤

ቀኝ ወርቹ ለአሮን ከርሱም በኋላ ለልጆቹ ዕድል ፈንታ ነው፤

፴፬፤ እስመ ተላዓ ወአገዳ ዘየማን ነሣእኩ እመሥዋዕተ መድኃኒቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወወሀብክዎ ለአሮን ወለደቂቁ ይኩኖሙ ሕገ ዘለዓለም እምደቂቀ እስራኤል፤



(ነሣእኩ እምደቂቀ እስራኤል፤ ነሣእኩ እመሥዋዕተ መድኃኒቶሙ ብሎ ይገጥሟል)፤ ድኅነታቸው ሊደረግበት ካቀረቡት መሥዋዕት ከእስራኤል ልጆች ፍሪንባውን ቀኝ ወርቹን ተቀብዬ ለሚያገለግሉኝ ለአሮን ለልጆቹ የዘለዓለም ሕግ ይሆናቸው ዘንድ ሰጥቻቸዋለሁና (ተላዑስ ይኩን ለአሮን ወለደቂቁ ብለህ እሠር፤)

፴፭፤ ዝንቱ ውእቱ ክፍሉ ለአሮን ወለደቂቁ እመሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር እምአመ ይትቀብዑ ይኩኑ ካህናተ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆኑ ዘንድ ከተቀቡበት ቀን ጀምሮ ለአሮንና ለልጆቹ ዕድል ፈንታቸው ይህ ፍሪንባው ቀኝ ወርቹ ነው፤ ግብራችሁ የማናዊ ነው ሲል፤ አንድም ሰውን መክራችሁ አስተምራችሁ ወደ የማናዊ ግብር ትመልሳላችሁ ሲል ነው፤

፴፮፤ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር የሀብዎሙ እምአመ ቀብዕዎሙ እምደቂቀ እስራኤል፤

ከእስራኤል ልጆች ተለይተው ከተቀቡ ጀምሮ ይህን ይሰጧቸው ዘንድ ይስጧቸው ብሎ እግዚአብሔር እንዳዘዘ መጠን፤

ወይኩኖሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊሆሙ፤

ዋዌውን ትቶ ይህ በዘመናቸው የዘለዓለም ሕግ ይሁናቸው፤

፴፯፤ ወዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለቍርባን ወለመሥዋዕት፤

ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የመሥዋዕትና የቍርባን ሥርዓት ይህ ነው፤

ለዘበእንተ ኃጢአትኒ ወለዘበእንተ ንስሓኒ ወለዘፍጻሜኒ ወለዘመሥዋዕተ መድኃኒትኒ፤

የመሥዋዕተ ንስሐና የመሥዋዕተ ኃጢአት፣ የበግዓ ፍጻሜና የመሥዋዕተ መድኃኒት ሥርዓቱ ይህ ነው፤

፴፰፤ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና በዕለተ አዘዞሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ያብኡ ቊርባኖሙ ቅድመ እግዚአብሔር በገዳም ዘሲና፤

ሲና በሚባል ምድረ በዳ (በረሃ) ቍርባናቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቡ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች ባዘዛቸው ቀን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ሙሴን እንዳዘዘው የመሥዋዕትና የቊርባን ሕግ ይህ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ ንሥኦሙ ለአሮን ወለደቂቁ፣

አሮንንና ልጆቹን አምጣቸው፤

ወአልባሲሆሙኒ ወቅብዓ ዘይትቀብዑ ወላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት ወክልኤተ አባግዐ ወመሶበ ናዕት፣

ልብሳቸውንና የሚቀቡትን ዘይት ስለ ኃጢአታቸው የሚሠዋውን ላም ሁለት በጎችን ዳቦ ያለበትን መሶብ ናዕተ መሶብ ቢል በመሶብ ያለውን ዳቦ አምጣ ብሎ ለሙሴ ነገረው፤

፫፤ ወአስተጋብእ ኵሎ ተዓይነ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

የእሥራኤልን ሠራዊት ሁሉ ልዩ ወደ ሆነችው ድንኳን ደጃፍ ሰብስብ ብሎ ነገረው፤

፬፤ ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ወአስተጋብአ ኵሎ ተዓይነ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው አደረገ ፣ የእስራኤልን ሠራዊት ሁሉ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሰበሰበ፣ (ሐተታ) የሕዝቡን ንጹሕነት የመሥዋ ዕቱን ደግነት ለማጠየቅ ብር ሃን የሚያበራላቸው ጌታ በረ ድኤት የሚገለጽላቸው ነውና፤

፭፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለተዓይን ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአ ብሔር ትግበሩ፣

ሙሴም ሠራዊቱን ትሠሩት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው ሕግ ይህ ነው አላቸው፤

፮፤ ወነሥኦሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ወሐፀቦሙ በማይ፣

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው አሮንንና ልጆቹን ወስዶ በውሃ አጠመቃቸው ማለት ከሕዝቡ ለይቶ አከበራቸው፤

፯፤ ወአልበሶ ለአሮን አልባሰ ቢሶስ ወአቅነቶ ቅናተ ወአልበሶ ጸደሬ ወወደየ ላዕሌሁ ልብሰ መትከፍት

አሮንን አረንጓዴ የሚመስል የሐር ቀሚስ አለበሰው፣ የወርቅ ዝናር አስታጠቀው፣ ምሉጣ ግምጃ አለበሰው፣ ይኸውም እጀ ሰፊ መጎናጸፊያ ነው፣ በእጀ ሰፊው ላይም የጫንቃ ልብስን አለበሰው፣ ደረበለት፤

፰፤ ወአቅነቶ መልዕልተ ግብረታ ለልብሰ መትከፍት ወአሠራ ቦቱ፣



በጫንቃው ልብስ ላይም መታ ጠቂያን አስታጠቀው፣ በሱም አንድ አደረገው፤

ወወደየ ላዕሌሁ ልብሰ ሎግዮ ዘተአምር ወዘጽድቅ፣

ጽድቅ የሚሠራበት፣ ምልክት የሚታይበት የደረት ልብስ ንም በላዩ ላይ አለበሰው፣ ተአምር አለ፣ ኃጢአታቸው ይታወቅበታልና ጽድቅ አለ፣ ቃሉን ሰምተው በጎ ሥራ ይሠሩበታልና፤

፱፤ ወወደየ አክሊለ ዲበ ርእሱ ወወደየ ላዕለ ውእቱ አክሊል መንገለ ገጹ ቈጽለ ወርቅ ዘቅዱስ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው በራሱ ላይ አክሊል፤ አንድም ኵፌት ደፋለት፣ በአ ክሊሉ ላይም በፊቱ በኩል አኽያ ሽራኽያ የተጻፈበትን የወርቅ ሻኵራ አደረገለት፤

፲፤ ወነሥአ ሙሴ እምቅብዐ ዘይትቀብዑ ወነዝኀ ላዕለ ምሥዋዕ ስብዓ ወቀብዖ ለምሥዋዕ፣

ወነዝኀ ላዕለ ምሥዋዕና ወቀብዖ ላዕለ ምሥዋዕ አንድ ወገን ነው፣ ሙሴም ካህናቱ ተቀብተው ከሚከብሩበት ዘይት ወስዶ መሠውያውን ሰባት ጊዜ ረጨው፣ ሰባት ፍጹም ነው፣ በፍጹም ትጋት ኃጢአት እንዲሠረይ ለማ፤በየቅ፣

፲፩፤ ወቀደሰ ኵሎ ንዋዮ ወማዕ ከከኒ ወመንበሮ ቀደሰ ወቀብዓ ለደብተራ ወለኵሉ ንዋያ፣

ንዋየ ቅድሳቱን ሁሉ ሰኑን፣ ኵስኵስቱን ፣ የኵስኵስቱን መቀመጫ ፤ አንድም የአሮንን መቀመጫ ወንበር ቀብቶ አከበረው፣ ደብተራ ኦሪትንም ቀብቶ አከበራት፣ ዕቃዋንም ሁሉ አከበረው፤

፲፪፤ወከዓወ ሙሴ እምቅብዕ ዘይት ቀብዑ ላዕለ ርእሰ አሮን ወቀብዖ ወቀደሶ፣

ሙሴም ተቀብተው ከሚከ ብሩበት ዘይት ወስዶ በአሮን ራስ ላይ አፈሰሰበት፣ ቀብቶም አከበረው፤

፲፫፤ ወአምጽኦሙ ሙሴ ለደቂቀ አሮን ወአልበሶሙ አልባሰ ወአቅነ ቶሙ ቅናታተ፣

ሙሴም የአሮንን ልጆች አም ጥቶ በአባታቸው በአሮን አም ሳል ልብሰ ተክህኖ አለበሳቸው፣ የወርቅ ዝናር አስታጠቃቸው፤

ወወደየ ላዕሌሆሙ አክሊለ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር እንዳዘዘው በራሳቸው ላይ አክሊል ደፋላቸው፣

፲፬፤ ወአምጽአ ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት፣

ስለ ኃጢአት የሚሠዋውን ላም አቀረበ፤

ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ላሕም ዘበ እንተ ኃጢአት ወጠብሕዎ፣

ኃጢአት ሊሠረይበት በቀረበው ላም ራስ ላይ አሮንም ልጆቹም እጃቸውን አኑረው ሠዉት፣ ባንተ ምክንያት ከሁሉ በላይ እንሆናለን ሲሉ፤ አንድም ባንተ ምክንያት ኃጢአታችን ይሠረያል ሲሉ፤

፲፭፤ ወነሥአ ሙሴ እምደሙ ወወደየ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ በዓውዱ በአፃብዒሁ ወአንጽሖ ለምሥዋዕ፣

ሙሴም ከደሙ አምጥቶ በመሠዊያው ቀንዶች ዙሪያ በጣቱ እየዘገነ ረጨው፣ መሠዊያውንም አነጻው፣ አከበረው፤

ወከዓወ ደሞ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ወቀደሶ ከመ ያስተሥሪ ቦቱ፣

የምሥዋዑንም እግር ኃጢአት ያስተሠርይበት ዘንድ ከደሙ ቀብቶ አከበረው፤

፲፮፤ ወነሥአ ሙሴ ስብሐ ዘውስተ ንዋየ ውስጡ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወወደየ ላዕለ ምሥዋዕ፣

ሙሴም በሆድ ዕቃው ውስጥ ያለውን ስብ ሁለቱን ኵላሊቶቹንና ግልገል ጉበቱን በላያቸው ያለውን ስቡን አምጥቶ በመሠዊያው ላይ (ጨመረው) አጤሰው፤

፲፯፤ ወማዕሶኒ ወሥጋሁኒ ወካዕሴሁኒ ለውእቱ ላሕም አውዓየ በእሳት አፍኣ እምትዕይንት በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው የዚያን በሬ ቊርበቱን ሥጋውንና ሰንበሩን ከከተማው ውጭ በእሳት አቃጠለው፤

፲፰፤ ወአምጽአ ሙሴ በግዓ ለመሥዋዕት ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ በግዕ፣

ሙሴም ለመሥዋዕት የሚሆን በግን አመጣ፣ አሮንና ልጆቹም እጃቸውን በዚያ በግ ራስ ላይ አኖሩ፤

፲፱፤ ወጠብሖ ሙሴ ለውእቱ በግዕ ወከዓወ ደሞ ውስተ ዓውደ ምሥዋዕ፣

ሙሴም ያን በግ አርዶ ደሙን በመሠዊያው ዙሪያ



አፈሰሰው፣ ከላይ ጠብሕዎ ብሎ ከዚህ ጠብሖ ሲል አያጣላምን ቢሉ አያጣላም፣ ላም ላንድ ሰው አይቻልምና ደቂቀ አሮንን ጨምሮ ከላይ ጠብሕዎ አለ፣ በግ ግን ላንድ ሰውም ቢሆን አያቅትምና ከዚህ ጠብሖ አለ፤

፳፤ ወመተሮ ለውእቱ በግዕ በበዓባላቲሁ ወወደየ ሙሴ ርእሶ ወአባላቲሁ ወስብሐ ወከርሦ ወእገሪሁኒ ሐፀበ በማይ፣

ሙሴም ለመሥዋዕት የቀረበውን በግ በየብልቱ ለየው፣ ራሱን ብልቱን ስቡንና ፈርሱን እግሩን በውሃ አጠበው፤

፳፩፤ ወወደየ ኵሎ ላዕለ ምሥዋዕ እስመ መሥዋዕት ውእቱ ዘመዓዛ ሠናይ ወቊርባን ውእቱ ለእግዚአብሔር በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ነውና ሁሉንም በመሠዊያው ላይ ጨመረው፤

፳፪፤ ወአምጽአ ሙሴ ካልአ በግዓ ዘፍጻሜ ወወደዩ አሮን ወደቂቁ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ በግዕ ወጠብሕዎ፣

አሁን አምጽአ ሙሴ በግዓ ብሎ ነበርና ካልአ አለ፣ ሙሴም ተቀብተው የሚከብሩበትን ሁለተኛውን በግ አመጣ፣ አሮንና ልጆቹም ለመሥዋዕት በመጣው በግ ራስ ላይ እጃቸውን ጭነው ሠዉት፣ ላሙንስ ይሁን በጉን አንድ ሰው አይሠዋውምን፣ ለምን ጠብሕዎ አለ ቢሉ ላም የሚያህል ሙክት አይጠፋምና ስቡን ሲፈልጉ የሚሠዉት ስለሆነ፤

፳፫፤ ወነሥአ ሙሴ እምደሙ ወወደየ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ ለአሮን እንተ የማን ወላዕለ ከተማ አፅ ባዕተ እዴሁ እንተ የማን ወላዕለ ከተማ አፅባዕተ እግሩ እንተ የማን፣

ሙሴም ከተሠዋው በግ ከደሙ አምጥቶ የአሮን የቀኝ ጆሮውን ጫፍ የቀኝ እጁን ጫፍና የቀኝ እግሩን ጫፍ ቀባ፤

፳፬፤ ወአምጽኦሙ ሙሴ ለደቂቀ አሮን ወወደየ ሙሴ እምውእቱ ደም ላዕለ ከተማ ዕዘኒሆሙ ዘየማን ወላዕለ ከተማ አፃብዓ እደዊሆሙ ወላዕለ ከተማ አፃብዓ እገሪሆሙ ዘየማን፣

ሙሴም የአሮንን ልጆች አምጥቶ ከዚያ ደም የቀኝ እጃቸውን ጫፍና የቀኝ ጆሮ

www.ethiopianorthodox.org

ዋቻውን ጫፍ፣ የቀኝ እግራ
ቸውን ጫፍ ቀባቸው፤

፳፫፤ ወከዓዎ ሙሴ ለውእቱ ደም ውስተ
ዓውደ ምሥዋዕ፣

ተቀብተውለት (ቀብቶለት) የቀ
ረውንም ደም ሙሴ በመሠ
ዊያው ዙሪያ አፈሰሰው፤

፳፮፤ ወነሥአ ሙሴ ስብሐ
ወሐቌሁ ወስብሐ ከርሡ ወከብደ
እንተ ትንዕስ ወክልኤሆን ኵልያ
ቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወአገዳ
ዘየማን፣

ሙሴም ዳሌውን ስቡን የሆ
ዱንም ስብ ሁለቱን ኩላ
ሊቶቹንና ግልገል ጉበቱን በላ
ያቸው ያለውንም ስብ ቀኝ
ወርቹንም አመጣ፤

፳፮፤ ወነሥአ እመሶብ ዘፍጻሜ
ዘሀሎ ቅድመ እግዚአብሔር
ኅብስተ ናዕት አሐተ ወኅብስተ
ዘቅብዕ አሐተ ወጸሪቀ አሐተ
ወወደዮን ዲበ ስብሕ ወዲበ አገዳ
ዘየማን፣

ሙሴም በእግዚአብሔር ፊት
ካለው ዳቦውን ከሚያስቀ
ምጡበት መሶብ አንዲት
የቂጣ ድፎ በዘይት የተለ
ወሰች፣ አንዲት እንጎቻ፣ አን
ዲት ስስ ቂጣ አምጥቶ በቀኝ
ወርቹና በስቡ ላይ አኖራ
ቸው፤

፳፯፤ ወአንበረ ኵሎ ዲበ እደወ
አሮን ወላዕለ እደወ ደቂቁ ወአ
ብአሙ መባአ ቅድመ እግዚአ
ብሔር፣

ሁሉንም በአሮን እጆች ላይና
በልጆቹ እጆች ላይ አኖረው፣
መባም አድርጎ ወደ እግዚአ
ብሔር አቀረባቸው፤

፳፰፤ ወነሥአ ሙሴ እምእደዊ
ሆሙ ወወደዮ ላዕለ ምሥዋዕ
ወዲበ መሥዋዕተ ፍጻሜ ቍርባን
ወመዓዛ ሠናይ ውእቱ ለእግዚ
አብሔር፣

ሙሴም ከእጃቸው ተቀብሎ
ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ
ሲሆን ደሙን ተቀብተው የከ
በሩበት መሥዋዕት ባለበት
በመሠዊያው ላይ አኖረው፤

፳፱፤ ወነሥአ ሙሴ ተላዐ ወመ
ተረ ከመ ይደዮ ቅድመ እግዚአብ
ሔር እምበግዕ ዘፍጻሜ፣

ሙሴም ደሙን ተቀብተው
ከከበሩበት በግ ፍርንባውን
አምጥቶ በእግዚአብሔር ፊት
ያኖረው ዘንድ ለየው፤

ወኮነ ክፍሉ ለአሮን በከመ አዘዞ
እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘ
ዘው የአሮን ዕድል ፈንታ
ሆነ፤



፴፤ ወነሥአ ሙሴ እምቅብዕ
ዘይትቀብዕ ወእምደም ዘምሥዋዕ
ወነዘኃ ላዕለ አሮን ወላዕለ
አልባሲሁ ወላዕለ ደቂቁ፣

ሙሴም ተቀብተው ከከበ
ሩበት ዘይትና በመሠዊያው
ከቀረበው ደም አምጥቶ አሮ
ንን ልብሶቹን ልጆቹን የልጆ
ቹን ልብስ ረጨው፣ እነሱንስ
ይሁን፣ ልብሳቸውንማ ደሙ
አያባላሸውምን ቢሉ በተአ
ምራት ይጠፋ ነበር፤ አንድም
ለማክበር የሚቀባ ጥቂት
ጥቂት ነውና አይበላሽም፤

ወቀደሶ ለአሮን ወለአልባሲሁ
ወለደቂቁ ወለአልባሰ ደቂቁ፣

ነዝኀ ያለውን ቀደሰ ብሎ ገለ
ጸው፣ አሮንን ልጆቹን ከሠራ
ዊቱ ወይም ከሕገዙ፣ [illegible]
ተክህናውን ከልብሰ [illegible]
ሥት ለይቶ ቀብቶ አከበረው፤

፴፩፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን
ወለደቂቁ አብስሉ ውእተ ሥጋ
በዓፀደ ደብተራ ዘመርጡል
ወበመካን ቅዱስ ወበህየ ብልዕዎ፣

ዓፀድና መካን አንድ ወገን፣
ይህንንም ለመሥዋዕት የቀረ
በውን በከበረ ቦታ በደብተራ
ኦሪት ዙሪያ ቀቅላችሁ ብሉት
ብሎ አዘዛቸው

ወኅብስተኒ ዘውስተ መሶብ ዘፍ
ጻሜ፣

ደሙን ሲቀቡት ፣ የሠዉት
የበጉ ሥጋ ካለበት መሶብ ያለ
ውንም ዳቦ ብሉት አላቸው፤

በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር ወይ
ቤለኒ አሮን ወደቂቁ ይብልዕዎ፣

እግዚአብሔር አሮንና ልጆቹ
ይብሉት ብሎ እንዳዘዘኝ ብል
ዕዎ ላለው፤ አንድም ውስተ
ዓፀደ ደብተራ ይበልዕዎ ብሎ
እንዳዘዘኝ በህየ ብልዕዎ ላለው፤

፴፪፤ ወዘተርፈ እምሥጋ ወኅብ
ስት በእሳት ያውዕይዎ፣

በልተውት የቀረውንም በእ
ሳት ያቃጥሉት፤

፴፫፤ ወኢትፃኡ እምኖኅተ ደብ
ተራ ዘመርጡል ሰቡዓ ዕለተ እስከ
አመ ትፌጽሙ ዕለተ ፍጻሜክሙ፣

የምትቀቡበት እስኪፈጸም
ድረስ ሰባት ቀን ከደብተራ
ኦሪት ደጅ እንዳትወጡ ብሎ
ሥርዓት ይሠራላቸዋል ፣
ያስተምራቸዋል፤

እስመ ሰቡዓ ዕለተ ይትፌጸማ
እደዊክሙ፣

እጆቻችሁ ሰባት ቀን ይቀባ
ሉና ኢትፃኡ ላለው፤

፴፬፤ በከመ ተገብረ በዛቲ ዕለት
እንተ አዘዘ እግዚአብሔር ከመ
ይግበሩ በዘያስተሠርዩ ለክሙ፣

www.ethiopianorthodox.org

ዛቲ ዕለት እግዚአብሔር ሙሴን ያዘዘባት ቀን ናት፣ ኃጢአታቸሁን በሚያስተሠርይላችሁ ገንዘብ የሚያስተሠርዩበትን ያደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን በአዘዘበት ቀን እንደ ተደረገ፤

፴፭፤ ወንበሩ ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ሰቡዓ ዕለተ ሌሊተ ወመዓልተ፣

ሰባት ቀን በመዓልትም በሌሊትም በደብተራ ኦሪት ደጅ ተቀመጡ አላቸው ፣ ሌሊተ ብሎ መዓልተ ባይል በሌሊት አትውጡ አለ እንጂ በቀን መቼ አትውጡ አለ ፣ መዓልተ ብሎ ሌሊተ ባይልም በቀን አትውጡ አለ፣ መቼ በሌሊት አትውጡ አለ ብለው ምክንያት እንዳይሰጡ ጠንቅቆ ይጽፏል፤

ወዕቀቡ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ከመ ኢትሙቱ እስመ ከማሁ አዘዘኒ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ንገራቸው ብሎ አዞኛልና እንዳትቀሠፉ በደብተራ ኦሪት ሁናችሁ የእግዚአብሔር ሕጉን ጠብቁ፤

፴፮፤ ወገብሩ አሮን ወደቂቁ ኵሎ ቃለ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ

አሮንና ልጆቹም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ሕግ ሁሉ ፈጸሙ።

## ምዕራፍ ፱

## ጉባኤ ፣

፩፤ ወኮነ በሳምንት ዕለት ጸውዖሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ወለአዕሩገ እስራኤል

ኮነ ያለውን ጸውዖሙ ብሎ አመጣው፣ ኢትባኡ እምኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ሰቡዓ ዕለተ ብሎ ነበርና ሙሴ በስምንተኛው ቀን አሮንና ልጆቹን ጠርቶ አዕሩገ እስራኤልን እንደ ምስክር አድርጎ አቁሞ፤

፪፤ ወይቤሎ ለአሮን ንሣእ ለከ ላሕመ እምአልሕምት ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዐ ለመሥዋዕት ወአምጽኦሙ ቅድመ እግዚአብሔር፣

አሮንን ለይቶ ስለ ኃጢአት የሚሠዋውን ላምና ለመሥዋዕት የሚሆነውን በግ ሳንተጥቅም ሲሆኑ በእግዚአብሔር ፊት አቅርባቸው አለው፤

፫፤ ወንግሮሙ ለአዕሩገ እስራኤል ወበሎሙ ንሥኡ አሐደ ሐርጌ እምአጣሊ ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዐ ወላሕመ ወማሕስዐ ዘዓመት ንጹሐነ ለመሥዋዕት፣



የእስራኤልንም ሽማግሌዎች የኃጢአት ማስተሥረያ የሚሆን ከፍየል ወገን አንድ ሙክት በግና ላም፣ ዓመት የሆነውን ጠቦት ሁሉም ነውር የሌለባቸውን ለመሥዋዕት አምጡ ብለህ ንገራቸው አለው፤

፬፤ ወላሕመኒ እምአልሕምት ወበግዐኒ ለመሥዋዕተ መድኃኒት ቅድመ እግዚአብሔር ወስንዳሌ ዘልውስ በቅብዕ እስመ ዮም ያስተርኢ ለክሙ እግዚአብሔር፣

ዮም ያላት ስምንተኛዪቱ ቀን ናት፣ ዛሬ እግዚአብሔር ይገለጽላችኋልና ከላሞች ወገን አንድ ላምና በእግዚአብሔር ፊት ድኅነት በሚደረግበት መሥዋዕት አንድ በግ በዘይት የታሸ የስንዴ ዳቦ አምጡ ብለህ ንገራቸው አለው፤

፭፤ ወነሥኡ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ቅድመ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወመጽኡ ኵሉ ተዓይን ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር፣

በደብተራ ኦሪት ደጅ ሙሴ አምጡ ብሎ እንዳዘዛቸው አመጡ፣ ሠራዊቱም ሁሉ መጥተው በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ፣ ቅድመ እግዚአብሔር ማለቱም እግዚአብሔር የማይለየው ስለ ሆነ ነው፤

፮፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘይቤለክሙ እግዚአብሔር ግበሩ፣

ትግበሩ ሲል ነው፣ ትሠሩት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ሕግ ይህ ነው፤ አንድም እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ሕግ ይህ ነውና ግበሩ አድርጉት አላቸው፤

ወያስተርኢ ለክሙ ስብሐተ እግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔርም ረድኤት ይገለጽላችኋል፤ አንድም ግበሩ ብሎ ነበርና ጨለማ ይሆንብናል እንዳትሉ የእግዚአብሔር ብርሃን ይታያችኋል አላቸው፤

፯፤ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ሑር ኀበ ምሥዋዕ ወግበር ዘበእንተ ኃጢአትከ ወዘመሥዋዕትከ ወአስተሥሪ ለርእስከ ወለቤትከ፣

ሙሴ አሮንን ወደ መሠዊያው ሂደህ ስለ ኃጢአትህ ያቀረብከውን መሥዋዕት ሠውተህ የራስህን፣ የወገኖችህንም ኃጢአት አስተሥርይ፤

ወእምዝ ግበር መሥዋዕተ ለሕዝብ፣ ወአስተሥሪ ሎሙ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር፣

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ያቀረቡትን መሥዋዕት ሠውተህ እግዚአብሔር እንዳዘዘ ኃጢ

www.ethiopianorthodox.org

አታቸውን አስተሥርይላቸው አለው፤ ‹ሐተታ› እስካሁን የሕዝቡንና የመሥዋዕቱን ደግ ነት ለማጠየቅ የመጀመሪያ ሥርዓት ነውና ሙሴ ሲያደ ርግ ነበር፣ አሁን ግን ሙሴ አሮንን ያዝዘዋል፤

፰፤ ወሖረ አሮን ኀበ ምሥዋዕ ወጠብሐ ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአቱ፣

አሮንም ወደ መሠዊያው ሂዶ ስለ ኃጢአቱ ያቀረበውን ላም ሠዋ፤

፱፤ ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ኀቤሁ ወጠምዓ አፃብዒሁ ውስተ ደሙ ወወደየ ላዕለ አቅርንተ ምሥዋዕ ፣

ኀቤሁ ለአሮን ነው፣ የአሮን ልጆች ካህናቱም ደሙን ተቀ ብለው ወደ አሮን አቀረቡ፣ አሮንም ካቀረቡለት ደም በጣቱ ጠልቆ በመሠዊያው ቀንዶች ጨመረው፤

ወከዓወ ደሞ ላዕለ መንበረ ምሥ ዋዕ ፣

የተረፈንውንም ደም ከመ ሠዊያው እግር አፈሰሰው፤

፲፤ ወስብሐ ወክልኤሆን ኵልያቶ ወከብዶ እንተ ትንዕስ ወደየ ላዕለ ምሥዋዕ በከመ አዘዞ እግዚ አብሔር ለሙሴ፣

ስቡን፣ ሁለቱን ኵላሊቱን ለምለም ጉበቱንም እግዚአብ ሔር ሙሴን እንዳዘዘው በም ሥዋዑ ጨመረው፤

፲፩፤ ወሥጋሁሰ ወማዕሶ አውዓዩ በእሳት አፍኣ እምትዕይንት፣

‹‹ወይወስዱ አፍኣ እምትዕ ይንት ወያውዕይዎ በእሳት ›› ብሎ ነበርና ሥጋውንና ቁር በቱን ግን ከከተማው በአፍኣ ወስደው በእሳት አቃጠሉት፤

፲፪፤ ወጠብሐ ዘመሥዋዕትኒ፣

ለመሥዋዕት የቀረበውንም ላም ሠዋው፤

ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ኀቤሁ ወከዓዎ ዓውደ ምሥዋዕ፣

የአሮን ልጆችም ደሙን ወደሱ አቀረቡ፣ በመሠዊያው ዙሪያም አፈሰሰው፤

፲፫፤ ወመሥዋዕቶኒ አምጽኡ ሎቱ በበመለያልይሁ ወርእሶኒ ወወደዮ ውስተ ምሥዋዕ፣

የተሠዋውንም ሥጋ በየብ ልቱ ከራሱ ጋር አቀረቡለት፣ እሱም ተቀብሎ በመሠዊያው ላይ ጨመረው፤

፲፬፤ ወሐፀበ ንዋየ ውስጡ ወእ ገሪሁ ወወደዮ ላዕለ ምሥዋዕ ዲበ መሥዋዕት፣



እግሮቹንና የሆድ ዕቃውን ግን በውሃ አጥቦ በመሠ ዊያው ላይ ካለ ከመሥዋዕቱ ጨመረው፤

፲፭፤ ወእምዝ አብአ ቍርባኖሙ ለሕዝብ፣

ወጠብሐ ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአቱ ብሎ በቊ. ፰ ተና ግሮ ነበርና የራሱን መሥ ዋዕት ካቀረበ በኋላ የሕዝቡን መሥዋዕት አቀረበ፤

ወነሥአ ለውእቱ ሐርጌ ዘበእንተ ኃጢአት ዘሕዝብ ወጠብሖ ወአንጽሖ ወመተሮ ዘከመ ቀዳሚ፣

‹‹ነሥአ ወአንጽሖ ጠብሖ ወ መተሮ ሲል ነው›› ተቀብሎ ንጹሕ ያደርጋዋል አለ፣ ነውር ነቀፋ ያለበትን አይ ሠዋምና ሠውቶም በየብልቱ ለያየው፤ (ሐተታ) ከመ ዘቀ ዳሚ አለ፣ ፊትና ኋላ ቢሆ ንም ሥርዓቱ አንድ ነውና ፤

፲፮፤ ወአብአ መሥዋዕተ ወገብሮ ዘበሕጉ፣

እንደ ሕጉ እንደ ሥርዓቱ አድርጎ አቀረበው፤

፲፯፤ ወአምጽአ እመሥዋዕተ ስን ዳሌ ምልዓ እዴሁ እምኔሁ ወወ ደዮ ላዕለ ምሥዋዕ ዘእንበለ መሥ ዋዕት ዘነግህ፣

ካቀረቡለትም ከስንዴው መሥ ዋዕት እጅ ያህል ቆርሶ በነግህ ከሚያቀርበው መሥዋዕት ሌላ በመሠዊያው ላይ አጤሰው፤

፲፰፤ ወእምዝ ጠብሐ ላሕመ ወበግዓ ለመሥዋዕተ መድኃኒት ዘሕዝብ፣

ወነሥአ ለውእቱ ሐርጌ ዘበ እንተ ኃጢአት ብሎ በቊ. ፲፭ ተናግሮ ነበርና መሥዋዕተ ኃጢአቱን ካቀረበ በኋላ መሥ ዋዕተ መድኃኒቱን አቀረበ፤

ወአምጽኡ ደቂቀ አሮን ደሞ ኀቤሁ ወከዓወ ዓውደ ምሥዋዕ፤

የአሮን ልጆች ደሙን አቀ ረቡለት፣ በምሥዋዑ ዙሪያ አፈሰሰው፤

፲፱፤ ስብሐ ላሕምኒ ወዘበግዕ ወሐ ቋሁኒ ወስብሐኒ ዘይገለብባ ለከርሥ ወክልኤሆን ኵልያቲሁ ወስብሐ ዘላዕሌሆን ወከብዶ እንተ ትንዕስ፣

የበጉንና የላሙን ስብ ዳሌውን ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስቡን ሁለቱን ኵላሊቱን በላያቸው ያለውን ስብ ግልገል ጉበቱን፤

፳፤ ወስብሐ ዘዲበ ተላዕ ወደየ ውስተ ምሥዋዕ፣

በፍሪንባው ያለውን ስብ አም ጥቶ በመሠዊያው ላይ ጨመ ረው፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወተላዓ ወአገዳ ዘየማን መተረ አሮን እስመ ሀብቱ ውእቱ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ አዘዞ ለሙሴ፤

አሮንም ቀኙ ወርቹንና ፍሪንባውን ለየ፣ ‹‹ወአገዳሁ ዘየማን ይሁብ ሀብተ ለካህን›› ብሎ ምዕ. ፯ ቍጥር ፴፪ ላይ ለሙሴ እንዳዘዘው በእግዚአብሔር ፊት ከቀረበው መሥዋዕት ዕድል ፈንታው ቀኙ ወርቹ ፍሪንባው ነውና፤ አንድም አጢሶለት የቀረው ፍሪንባው ቀኙ ወርቹ በእግዚ አብሔር ትእዛዝ ዕድል ፈን ታው ቀኙ ወርቹ ነውና ‹መተረ› ለየ፤

፳፪፤ ወአልዓለ እዴሁ ላዕለ ሕዝብ ወባረኮሙ፣

አሮንም በአንብሮተ እድ ባረካ ቸው፣ በኦሪትስ የቃል እንጂ የእጅ ቡራኬ የለም ብሎ ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጎ መረቃቸው፤

ወወረደ ገቢሮ ዘበእንተ ኃጢአት ወዘበእንተ መሥዋዕተ መድኃኒት፤

‹‹ሑር ኀበ ምሥዋዕ ወግበር ዘበእንተ ኃጢአት" ብሎ በቍጥር ፯ ነግሮት ነበርና አሮንም መሥዋዕተ ኃጢ አቱን፣ መሥዋዕተ መድኃኒ ቱን ሠውቶ ተመለሰ፣ ወረደ ማለቱም መሥዋዕት የሚሠ ዋበት ደብተራ ኦሪት የምትተ ከልበት እንደ ባማ ከፍ ያለ ቦታ ነውና ፣

፳፫፤ ወቦኡ ሙሴ ወአሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፤

አሮንም መሥዋዕት ለማቅረብ ከተመለሰ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ፤

ወወጺኦሙ ባረክዎሙ ለኵሉ ሕዝብ፤

ከደብተራ ኦሪትም ወጥተው ሕዝቡን መረቋቸው፤

ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር ለኵሉ ሕዝብ፤

ለሕዝቡም ሁሉ የእግዚአብ ሔር ብርሃነ ረድኤቱ ተገለጸ ላቸው፤ አንድም ወደፊት ‹‹ወወፅአት እሳት የሚል ነውና ›› የአምላክነቱ መገለጫ ብርሃን ለሕዝቡ ሁሉ ተገልጦ ታየ፤

፳፬፤ ወወጽአት እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ወበልዓት መሥዋ ዕቶ ዘላዕለ ምሥዋዕ ወስብሐኒ፤



‹‹ወአስተርአየ ስብሐተ እግ ዚአብሔር ብሎ ነበርና ›› እሳት ከሰማይ ወርዳ ስቡን በላችለት፣ ሙሴ አሮንን ለማ ክበር መሥዋዕቱን ለማሥመር፤

ወርእዩ ኵሉ ሕዝብ ወደንገፁ ወወድቁ በገጾሙ፤

ወመጽኡ ኵሉ ተዓይን ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ብሎ ነበርና፣ በእግዚአብ ሔር ፊት የቆሙ ሕዝቡም እሳቱን አይተው ደንግጠው በግንባራቸው ወደቁ፣ ድንጋ ጼው የአንክሮ ነውና ወድቁ ማለቱም የስግደት ይመስላል። 

## ምዕራፍ ፲

### ጉባኤ

፩፤ ወነሥኡ ደቂቀ አሮን ናዳብ ወአብዩድ አሐዱ አሐዱ ማዕጠ ንቶሙ፤

የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ አንዱም አንዱም ማዕጠንታ ቸውን ያዙ፣ አሁን በዚህ ምክን ያት ተቀሠፉ የሚል ነውና፣

ወወደዩ ውስቴቱ እሳተ ወወደዩ ላዕሌሁ ዕጣነ፤

በውስጡ እሳት አድርገው በላዩ ዕጣን ጨመሩበት፤

ወአምጽኡ ቅድመ እግዚአብሔር እሳተ ዘእምባዕድ ዘኢአዘዞሙ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ካላዘዛቸው ከሌላ ቦታ እሳት ጭረው አመጡ፤

፪፤ ወወጽአት እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ወበልዓቶሙ ወሞቱ በቅድመ እግዚአብሔር፣

በዚህ ምክንያት ከእግዚአ ብሔር የታዘዘች እሳት ወርዳ አቃጠለቻቸው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቀሠፉ፣ ከዚህ የሞቱበትን ምክንያት አል ገለጸም፣ ወደፊት ያመጣዋል፤

፫፤ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ዝው እቱ ዘይቤ እግዚአብሔር በእለ ይቀርቡኒ እትቄደስ፣

ሙሴ አሮንን ጠርቶ እንዲህ አለው፣ ሳይበቁ በቅተናል ብለው በሚቀርቡኝ ሰዎች እመሰገናለሁ ማለት እነሱን አጥፍቼ በነሱ ጥፋት እመሰ ገናለሁ፤

ወበኵሉ ተዓይን እሴባሕ ፣

‹በተዓይነ ፳ኤልም ሁሉ እመሰገናለሁ አለ ፣ መምህ ራን ናቸውና የነሱን ትምህ ርት አጽንተው ያመሰግኑኛል ሲል ነው፣ ይህም ምጸት ነው፣ የነሱ አብነት የክፉ ሆነ

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ የበጎ አልሆነምና፣ ቢበድሉኝ ተዓይነ እስራኤልን ሁሉ አጥፍቼ እመሰገናለሁ ሲል ነው፤

ወደንገፀ አሮን፣

ሙሴ ይህን ሁሉ ነገር በነገረው ጊዜ አሮን ደነገጠ፣ ‹የልጅ ሞት አንጀት ይቆርጣልና ፤ አንድም ሊቀ ካህናት ለሁሉ አዛኝ ነውና ‹‹ወበኵሉ ተዓይን እሴባሕ›› ብሎ ስለ ነገረው ደነገጠ፤

፬፤ ወጸውዖሙ ሙሴ ለሳሜሳዲ ወለኤልሳፍን ደቂቀ አዚሔል ፤ ‹አዛሔል› እኁሁ ለአበ አሮን፣

ሙሴም የአሮንን የአባቱን ወንድም የአዛሔልን ልጆች ኤልሳፍንና ሳሜሳዲን ጠርቶ ፤

ወይቤሎሙ ሑሩ ንሥኡ አኃዊክሙ እምቅድመ መቅደስ ወአውጽእዎሙ አፍአ እምትዕይንት፣

ወንድሞቻችሁ ሙተዋልና ሂዳችሁ ከቤተ መቅደስ አውጥታችሁ ከከተማው በአፍኣ ቅበሯቸው አላቸው፤ ‹ሐተታ› የወንድሞቻቸውን ኃፍረት ለሌላ አልገልጥም ብሎ፤ አንድም ባጠገቡ የነበሩ እነሱ ናቸውና፣ ማን ይንገር የነበር፣ ማን ያርዳ የቀበር

እንዲሉ፣ አስቀድሞ ለሙሴ እንደ ነገረው በዚህ ይታወቃል፣ ‹ምነው የእሱስ የወንድሙ ልጆች አይደሉምን› ስለምን አኃዊክሙ አለ ቢሉ ያዘዛቸውን አፍርሰው ነበርና ‹የቍጣ አነጋገር ነው›፣ ይህም ለተረት የተጻፈ አይደለም፣ ዛሬም መጠጥ አብዝቶ የሰከረ ካህን ከሹመቱ ይሻራል፣ ከመዓርጉ ይዋረዳል፣ ከሰከረ ከሕግ ወጥቶ የማይገባ ሥራ ይሠራልና፤

፭፤ ወቦኡ ወአውጽእዎሙ በአልባሲሆሙ አፍኣ እምትዕይንት በከመ ይቤሎሙ ሙሴ፣

አካላቸውን በልቶ በተአምራት ልብሳቸውን ትቶታልና ሙሴ እንዳዘዛቸው ገብተው በልብሳቸው እየጠቀለሉ ተሸክመው ከከተማው ውጭ ቀበሯቸው፤ አንድም ከነልብሳቸው በልቷቸዋል ብሎ እለ አሚሳድ በልብሳቸው እየጠቀለሉ አወጧቸው፣ ‹ቦኡ› አለ፣ የሞቱ ከቤተ መቅደስ ነውና አውጽእዎሙ ለማለት እንዲመች፤

፮፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን ወለአልአዛር ወለይታምር ደቂቀ ርእሰክሙ ኢትቅርጹ ወአልባሲክሙኒ ኢትስጥጡ ከመ ኢትሙቱ፣



ሙሴም አሮንንና የአሮንን ልጆች አልአዛርን ይታምርን እንዳትቀሠፉ በናዳብና በአብዩድ ሞት ራሳችሁን አትላጩ፣ ልብሳችሁንም አትቅደዱ አላቸው፤

ወኢይኩን መንሱት ላዕለ ኵሉ ተዓይን፣

በእስራኤል ሠራዊት ሁሉ ጥፋት እንዳይመጣ አላቸው፣ እግዚአብሔር በወዳጆቹ አድሮ ሳይመክር አያጠፋምና፣ ይህም ለከንቱ አይደለም ዛሬም በክህነት የሚያገለግል ሰው ዘመድ ሞተብኝ ብሎ ፊቱን ነጭቶ ራሱን ተላጭቶ ልብሱን ቀድዶ ማዘን አይገባውም ሲል ነው፤

አኃዊክሙሰ ኵሉ ቤተ እስራኤል እሙንቱ ይብክይዎሙ ለእለ አውዓዮሙ እግዚአብሔር፤

ወንድሞቻችሁ የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ግን እግዚአብሔር በእሳት መቅሠፍት ላጠፋቸው ለናዳብና ለአብዩድ ያልቅሱላቸው፤

፯፤ ወእምኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኢትፃኡ ከመ ኢትሙቱ፣

እናንተ ግን እንዳትቀሠፉ ከደብተራ ኦሪት አትውጡ አላቸው፤

እስመ ቅብዕ ዘይትቀብዑ ዘእግዚአብሔር ሀለወ ላዕሌክሙ፤

‹ቅብዕ ዘእግዚአብሔር ነው› እግዚአብሔር ያደረበት፣ ተቀብተው የሚከብሩበት ቅብዕ በላያችሁ አለና ፤

ወገብሩ በከመ አዘዞሙ ሙሴ፣

እነሱም ሙሴ ልብሳችሁን አትቅደዱ ፣ ራሳችሁን አትላጩ እንዳላቸው አደረጉ፤

፰፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለአሮን ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር አሮንን ተናገረው፣ እንዲህ አለው፣ እስካሁን አሮንን አይነጋገረውም ነበር፣ አሁን ግን ተነጋገረው፣ በልጆቹ ሞት ልቡ አዝኗልና እግዚአብሔር ያጽናህ እንደማለት፣ ይህስ አይደለም፣ ተከታዩ ‹ኢትስተዩ ወይነ ነው ብሎ› ነገር በመልእክት አይፈጸምምና ሕጉን ለማስጠናት ነገሩን በቃል ለማስረዳት፤

፱፤ ወይቤሎ ወይነ ወሜሰ ኢትስተይ አንተ ወደቂቅከ ምስሌከ እንዘ ትበውኡ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፣

አንተም ልጆችህም ወደ ደብተራ ኦሪት በምትገቡበት ጊዜ፤

www.ethiopianorthodox.org

አው እምዘ ትበውኡ ኀበ ምሥዋዕ ከመ ኢትሙቱ፤

ወደ መሠዊያውም በምትገ ቡበት ጊዜ እንዳትቀሠፉ የወ ይን ጠጅ፣ የማር ጠጅ አት ጠጡ ብሎ ተነጋገረው፤ ምሥ ዋዕማ ያለ በደብተራ ኦሪት ውስጥ አይደለምን ቢሉ ቢሆ ንም የምሥዋው ቦታ ልዩ ነውና ፤ አሁን ዛሬ ካንድ ዕድሞ ውስጥ ደጀ ሰላም ቤተ ልሔም እንዲኖር፤

ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ዝንቱ፤

ይኸውም የዘለዓለም ሕግ ነው፤

፲፤ ዘቦቱ ይትፈለጡ ቅዱሳን ወር ኵሳን ወንጹሓን ወእለ ኢኮኑ ንጹሓነ፤

ይኸውም ቅዱሳንና ርኩሳን፣ ንጹሐንና ንጹሐን ያልሆኑ የሚለዩበት የዘለዓለም ሕግ ነው፤ ‹ሐተታ› ቅዱሳን ንጹሐን በልተው ጠጥተው ወደ ቤተ እግዚአብሔር አይ ገቡም፤ ርኵሳንና ኢንጹሐን ግን በልተው ጠጥተው ይገባ ሉና ዘይትፈለጡ ቦቱ አለ፤

፲፩፤ ወትሜህሮሙ ለደቂቀ ፳ኤል ኵሎ ሕግየ ዘነገርክዎሙ በእደ ሙሴ፤

በሙሴ ቃል የነገርኋቸውንም ሕጌን ሁሉ ለያዕቆብ ልጆች አስተምራቸው አለው፤ በካህ ናት ነው እንጂ ሕጉ የታዘዘ እኛስ በልተን ጠጥተን እን ገባለን እንዳይሉ፤

፲፪፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለአሮን ወለአልዓዛር ወለይታምር ደቂቁ እለ ተርፉ፤

ሙሴ አሮንንና ከሞት የቀሩ ልጆቹን ይታምርንና አልአ ዛርን እንዲህ አላቸው፤

ንሥኡ መሥዋዕተ ዘተርፈ እምቍ ርባኑ ለእግዚአብሔር ወብልዑ ናዕተ ኀበ ምሥዋዕ ቅዱስ ለቅዱ ሳን ውእቱ፤

ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው መሥዋዕት የተረፈውን ተቀ ብላችሁ በመሠዊያው ዘንድ ቂጣ አድርጋችሁ ብሉት፤ ከመሥዋዕቱ የተለየው ተረፈ መሥዋዕቱ ከሕዝቡ ለተለዩ ለካህናት ነውና፤

፲፫፤ እስመ ሕግ ውእቱ ለከ ወሕጎሙ ውእቱ ለደቂቅከ እመሥ ዋዕቱ ለእግዚአብሔር፤

ይህ ላንተ ሕግ ነውና፣ ካንተም በኋላ ለልጆችህ ሕግ ነውና፣ ለእግዚአብሔር ከቀረበው



መሥዋዕት የተረፈውን መሥ ዋዕት ተቀብላችሁ ብሉት፤

እስመ ከማሁ አዘዘኒ እግዚአብሔር፤

‹ካህን ዘይገብሮ ይበልዖ ወበ መካን ቅዱስ ይበልዖ ብሎ› እግዚአብሔር አዞኛልና ምዕ. ፯፥ ቍ. ፳፯፤

፲፬፤ ወተናግሮ ዘመባእ ወአንጻሩ ዘመ ባእ ትብልዑ በመካን ቅዱስ አንተ ወደቂቅከ ወቤትከ ምስሌከ፤

የመባውን ፍሪንባውን ወር ቹን በከበረ ቦታ አንተም ልጆችህም ብሉት ፤ ወገኖ ችህም ካንተ ጋር ይብሉ ‹ምስሌከ ማለቱ› ለተረፋ ማለፊያና መናኛ የለውምና፤

ሕግ ውእቱ ለከ ወሕጎሙ ውእቱ ለደቂቅከ ዘተውህበ ለከሙ እመሥ ዋዕተ መድኃኒት ዘደቂቀ እስራኤል፤

የእስራኤል ልጆች ድኅነት ከሚደረግበት መሥዋዕት ተለ ይቶ የተሰጣችሁ ለልጆችህም ላንተም ሕግ ነውና፤

፲፭፤ አገዳ ዘመባእ ወተላዕ ዘይ ፈልጡ እምስብሕ ዘመሥዋዕት በቅድመ እግዚአብሔር ይኩንከ ለከ ወለደቂቅከ ምስሌከ፤

በእግዚአብሔር ፊት ከሚሠ ዉት ከመሥዋዕቱ ስብ የሚ ለዩት ፍሪንባውና የመባው ወርች ላንተ ይሁን፣ ካን ተም በኋላ ለልጆችህ ይሁን፤ ‹ዘይፈልጡ እምስብሕ አለ› ስቡን አይበሉትምና፤

ሕግ ዘለዓለም በከመ አዘዘኒ እግዚ. አብሔር፤

እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ይህ የዘለዓለም ሥርዓት ነውና፤

፲፮፤ ወነሠሦ ሙሴ ለሐርጌ ዘበ እንተ ኃጢአት ወሶበ ኃሠሦ ናሁ ውዑይ፤

ስለ ኃጢአት የተሠዋውን በልተው በዚህ ሙተው እንደ ሆነ ብሎ ሙሴ መክቱን መረመረ፤ በመረመረውም ጊዜ ወዲያው ተቃጥሎ ሲነድ አገኘው፤

ወተምዐ ዲበ አልአዛር ወይታምር ደቂቀ አሮን እለ ተርፉ፤

ከሞት በተረፉት በአሮን ልጆች በይታምርና በአልአዛር ሙሴ ተቈጣባቸው፣ በፍቅር ቢጠይ ቃቸው እውነቱን አይነግሩት ምና ተቆጥቶ ጠየቃቸው፤

፲፯፤ ወይቤሎሙ ለምንት ኢበላዕ ክሙ ዘበእንተ ኃጢአት በመካን ቅዱስ እስመ ቅዱስ ውእቱ ለቅዱ ሳን፤

www.ethiopianorthodox.org

ለምን በላችሁ ብላቸው አል በላነውም ይሉኛል ብሎ በከበረው ቦታ ለምን አልበላችሁትም አላቸው፤ የተለየው መሥዋዕት ከሕዝቡ ተለይተው ለከበሩ ለካህናት ነውና፤

፲፯፤ ወወሀበክሙ ዘንተ ትብልዑ ከመ ትጎድጉ ኃጢአተ ትዕይንት ወታስተሥርዩ ሎሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

‹ትጎድጉና ታስተሥርዩ አንድ ወገን› የእስራኤልን ሠራዊት ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ታስተሠርዩ ዘንድ ይህን ሰጥቷችኋልና ለምን አልበላችሁትም? አላቸው፤

፲፰፤ እስመ ለዘቦአ ደሙ ውስተ መቅደስ በቅድሜሁ በውስጥ ትበልዕዎ በመካን ቅዱስ በከመ ተአዘዝኩ፤

ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዝኩ ደሙን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚያገቡበት መሥዋዕተ ኃጢአቱን በደብተራ ኦሪት ውስጥ በከበረ ቦታ ትበሉት ነበርና በውስጥ አልበላችሁት ይሆናል አላቸው፤ ደብተራ ኦሪትን እግዚአብሔር የማይለያት ስለሆነ ቅድሜሁ ይላታል፤

፳፤ ወተናገሮ አሮን ለሙሴ ወይቤሎ ፤

‹ለምንት ኢበላዕክሙ ብሎ› ሙሴ አሮንን ተቆጥቶት ነበርና አሮን ለሙሴ እንዲህ ብሎ መለሰለት፤

፳፩፤ ዮም ሶበ ቀደሱ ዘበእንተ ኃጢአቶሙ ወመሥዋዕቶሙኒ ቅድመ እግዚአብሔር ዛቲ፡ ረከበተኒ ወዮጊ ኢኮነ ሠናየ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ እብላዕ ዘበእንተ ኃጢአት፤

እስራኤል ስለ ኃጢአታቸው ከገንዘባቸው የለዩትን መሥዋዕተ ኃጢአቱን ሳልበላ ይች መከራ ያገኘችኝ መሥዋዕተ ኃጢአቱንስ በልቼ ቢሆን በጎ ባልሆነም ነበር ማለት ባስፈረደችብኝ ነበር፤ ሳይበሉ ነው እንጂ አለው፤

ወሰምዐ ሙሴ ወአደሞ፤

ሙሴም የአሮንን ነገር ሰምቶ መሥዋዕተ ኃጢአቱን እንዳል በሉ ተረድቶ ደስ አለው ፤ ‹ሐተታ› ምክንያቱ ምንድነው ቢለው፤ ሲበሉ ሲጠጡ አምሽተው እሳቱ ጠፍቶ ለማዕጠንት ከሌላ ቦታ እሳት አምጥተው ነው አሉት ፤ ‹ወይነ ወሜሰ ኢትስተዩ ብሎ አዝዟቸዋል› ይህን ከላይ ያለ ስፍራው ተናግሮት ነበርና አሁን በቦታው ተናገረው።።



## ምዕራፍ ፲፩
## ጉባኤ

፩፤ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ፤

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፤ ሙሴንስ ይሁን አሮንንማ መች ተነጋግሮት ያውቃል ቢሉ በሙሴ አስጠግቶ፤ አንድም አሮንንም አልፎ አልፎ ይነጋገረው ነበርና፤

፪፤ ንግርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበልዎሙ ዝንቱ ውእቱ እንስሳ ዘትበልዑ እምኵሉ እንስሳ ዘሀሉ ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም ካለው እንስሳ ሁሉ የምትበሉት እንስሳ ይህ ነው ብላችሁ ንገሯቸው፤ አንድም ወደ ፊት ዘውስተ ማይ ብሎ የሚያመጣ ነውና በየብስ ከሚኖሩ እንስሳ የምትበሉት ይህ ነው፤

፫፤ኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወዘሥጡቅ ጽፈሪሁ እማዕከሉ፤

ዝንቱ ያለውን አመጣው፤ የምትበሉት እንስሳ ሁሉ እግሩ የተከፈለው ጥፍሩ የተሠነጠቀው ነው፤

ወእንተ ክልኤቱ ውእቱ ወዘያመሰኩዕ ኪያሁ ብልዑ፤

የሚያመሰኳውን ግልገል ሰኰና ያለውን ብሉ፤ ‹ሐተታ› እንተ ክልኤቱ ማለቱ ከላይ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ብሎ ነበርና እግሩ የተከፈለውን፤ ጥፍሩ የተሠነጠቀውን ፤ የሚያመሰኳውን ብሉት አለ፤ ከቂም ከበቀል የተለየውን የሚጸመውን የሚጸልየውን ሰው ቀድሞ በረድኤት ኋላ በልጅነት እቀበለዋለሁ ሲል፤ አንድም ጸሎቱን እቀበለዋለሁ፤ ልመናውን እሰማዋለሁ ሲል ነው፤

፬፤ ወዝንቱ ባሕቱ ዘኢትበልዑ እምዘ ያመሰኵዕ ወእምዘ ንፉቅ ሰኰናሁ፤

‹‹ዝንቱ ውእቱ ዘትበልዑ ብሎ ነበርና› ፤ ነገር ግን ከሚያመሰኳው እግሩ ከተከፈለው ወገን የማትበሉት ይህ ነው፤

ገመል እስመ ያመሰኵዕ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሁ ዝንቱ ርኩስ ውእቱ ለክሙ፤

ግመል ያመሰኳል፤ ነገር ግን እግሩ የተከፈለ አይደለምና ይህ ለናንተ የረከሰ ነው አትብሉት፤

፭፤ ወዳስጼዳሂ እስመ ያመሰኵዕ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሁ ዝንቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ጥንቸል ያመሰኳል እግሩ የተከፈለ አይደለምና ለናንተ ርኩስ ነው ፤

፮፤ ወኪሮግልዮስኒ እስመ ንፉቅ ሰኰናሁ ወስጡቅ ጽፈሪሁ እማዕከሉ፣ ወኢያመሰኩዕ ውእቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣

አሳማም ሰኰናው የተከፈለ ነው፣ ከመካከሉ ግልገል ሰኰናው የተሰነጠቀ ነው፣ ነገር ግን አያመሰኳምና እርሱም ለእናንተ የረከሰ ነው ፤

፯፤ ወሐራውያኒ እስመ ንፉቅ ሰኰናሁ ወስጡቅ ጽፈሪሁ እማዕከሉ ወኢያመሰኩዕ ውእቱኒ ርኩስ ውእቱ ለክሙ፣

እሪያም እግሩ የተከፈለ ነው፣ ከመካከሉ ጥፍሩ የተሰነጠቀ ነው ፣ ነገር ግን አያመሰኳምና እርሱም ለእናንተ የረከሰ ነው ፤

፰፤ እምነ ሥጋሆሙ ኢትብልዑ ወበድኖሙሂ ኢትግሥሡ እስመ ርኩሳን ውእቶሙ ለክሙ፤

እኒህ ሁሉ ለእናንተ የረከሱ ናቸውና ሥጋቸውን አትብሉ፣ በድናቸውን አትዳስሱ፣ አትንኩ፤ (ሐተታ) እግሩ የተከፈለውን ጥፍሩ የተሰነጠቀውን የሚያመሰኳውን ብሉ አለ፤ አንድም የማያመሰኳውን እግሩ ያልተከፈለውን ጥፍሩ ያልተሰነጠቀውን አትብሉት አለ ፤ ከቂም ከበቀል ሳይለይ የጾመውን የጸለየውን ጾሙን ጸሎቱን አልቀበለውም ሲል ነው ፤

፱፤ ወዝንቱ ዘትበልዑ እምኩሉ ዘውስተ ማይ ፣

የየብሱን ተናግሮ ነበርና ዘውስተ ማይ ለማለት ደገመው በውሃ ውስጥ ከሚኖሩ እንስሳትም የምትበሉት ይህ ነው፣ ዝንቱ ያለውን ያመጣዋል ፤

ዘቦ ክንፍ ወዘቦ ቅሳር ዘሀሎ ውስተ ማይ ወዘውስተ ባሕር ወዘውስተ አፍላግ ውእቱ ዘትበልዑ ፣

በውሃ፣ በባሕር፣ በፈሳሽ ውስጥ ካለው የምትበሉት ክንፍ ገለፈት ያለውን ነው አለ፣ ምግባር፣ ሃይማኖት ያለውን ሰው ቀድሞም በረድኤት፣ ኋላም በልጅነት እቀበለዋለሁ ሲል ነው ፤

፲፤ ወኵሉ ዘአልቦ ክንፍ ወቅሳር ዘውስተ ማይ ወዘውስተ ባሕር ወዘውስተ አፍላግ ወእምኵሉ ዘይጐሥዕ ማይ ወእምኵሉ ነፍሰ ሕይወት እንተ ውስተ ማይ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣



(ዘውስተ ማይና ውስተ ማይ ወእምኵሉና እምኵሉ አንድ ወገን) ፣ ከውሃ ውስጥ ከሚወጣው በደመ ነፍስ ሕያው ከሚሆነው ፍጥረት ወገን ክንፍ ገለፈት የሌለው ለናንተ የረከሰ ነው ፤

፲፩፤ ወርኩሰ ይኩንክሙ እምሥጋሆሙ ኢትብልዑ ወበድኖሙ አስቈርሩ፤

ለናንተም ርኩስ ይሁናችሁ፣ ሥጋቸውን አትብሉ፣ ውዳቂያቸውን (በድናቸውን) አትዳስሱ ማለት እናንተ ተጸይፋችሁ ሌላውም እንዲጸየፍ አድርጉ ፤

፲፪፤ ወኵሉ ዘአልቦ ክንፍ ወቅሳር ዘሀሎ ውስተ ማይ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣

በውሃ ውስጥ ያለ ገለፈት ክንፍ የሌለው ሁሉ ለእናንተ የረከሰ ነው ፤

፲፫፤ ወዝንቱ ውእቱ ዘታስቆርሩ እምአዕዋፍ ወዘኢትበልዑ እስመ ርኩስ ውእቱ ፣

ርኩስ ስለሆነ ከአዕዋፍ ወገን የምትጸየፉት የማትበሉት ይህ ነው ፤ ቢርቀው ደግሞታል፣ ሐተታ ክንፍ ገለፈት የሌለውን አትብሉት አለ፣ ምግባር ሃይማኖት የሌለውን ሰው ቀድሞ በረድኤት ዛሬም በልጅነት አልቀበለውም ሲል፤ አንድም ጸሎቱን አልቀበለውም ሲል ነው ፤

ንስር ወግሪጳ ወአልያጦን

ንስር የወል ስም፣ ንስር ያለውን ይተረትራል፣ ግሪጳ ዘማች አሞራ፣ በሀገራችን ሽመላ ነው፣

ወአልያጦን፣

አልያጦን እባብ ዋጭ አሞራ፤

፲፬፤ ወጊጳ ወገላውቃ ወሆባይ ወዘአምሳሊሁ ፤

ጊጳ፣

አገዳ ሰበር አሞራ፣

ገላውቃ፣

ጭላት- አራት ራስ አሞራ

ሆባይ፣

አንጭት አሞራ ፤ ነሳሳለትና ይህን የመሰለውን ሁሉ ፣

፲፭፤ ወቋዕ ወኵሉ ዘአምሳሊሁ ፤

ቁራውን ይህን የመሰለውን ሁሉ አትብሉ ፤ የጥቁሩን በቁራ፣ የነጩን በአንጭት ተናገረው ፤ ይኸውም ከእስራ

www.ethiopianorthodox.org

ኤል ምክንያት ለማጥፋት ነው ፤ የነጩን ተናግሮ የጥቁሩን ባይናገር ፣ የነጩን ነገረን እንጂ መቼ የጥቁሩን ነገረን፣ የጥቁሩን ተናግሮ የነጩን ባይናገርም የጥቁሩን ነገረን እንጂ የነጩን መቼ ነገረን ባሉ ነበርና አርቆ እንደማጠር ነው ፤

፲፮ ወሰገኖ ወኵሉ ዘአምሳሊሁ ሰገኖ፣

ሰጕን፣ እሱን የመሰለውን ሁሉ

ወሰሮን፣ ወዘአምሳሊሁ ፣

ሰሮን ይብራ፣ ጠላቋ እሱን የመሰለውን ሁሉ፣

ወጉዛ ወዘአምሳሊሁ ፣

ጉዛ ጭላት አሞራ እሱን የመሰለውን ሁሉ

፲፯፤ ወጉጋ ወቅጥራቅጥሬን ወኢብን ፣

ጉጋ፣

ጉጉት፣

ቅጥራቅጥሬን፣

ድንቢጥ፣

ኢብን፣

የመስቀል ወፍ ፤

፲፰፤ ወጽርፍያና ፣ ወአድገ መረብ፣ ወቀቀኖ፣

ጽርፍያና፣

ጋጋኖ፣ እርኩም፣ ፍላፁት፤ አንድም ሳቢሳ፣

አድገ መረብ፣

የሜዳ (የበረሀ) አህያ፣

ቀቀኖ፣

እርኩም፣

፲፱፤ ወአሮድዮን፣ ወከራድዮን ወሄጳጳ፣ ወጽግነት፣

አሮድዮን፣

ያፌ ያሬድ፣ አንድም ሲላ፣ ከራድዮን ነጭ፣ ወፍ፣

አንድም ታላቅ አሞራ፣ ይለዋል ፣

ሄጳጳ፣

ጥንብ አንሣ አሞራ

ጽግነት፣

የሌሊት ወፍ፣

፳፤ ወኵሉ ዘይትሐወስ እምአዕዋፍ ዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ርኵስ ውእቱ ለክሙ ፤



ከአዕዋፍ ወገን በክንፍ የሚበር፣ በአራት እግሩ የሚሽከረከር ሁሉ ለናንተ የረከሰ ነው አትብሉት ፤

፳፩፤ አላ ዝንቱ ውእቱ ዘትበልዑ እምዘይትሐወስ እምአዕዋፍ ዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ፣

በክንፍ ከሚበሩ ከአዕዋፍ ጀምሮ በአራት እግሩ እስከሚሽከረከረው ፍጥረት ድረስ የምትብሉት ይህ ነው እንጂ፣ የማይበሉትንና የሚበሉትን ቈጥሮ ይናገራል ፤

ዘቦ አገዳ መልዕልተ እገሪሁ በዘይሠርር ቦቱ መልዕልተ ምድር ፤

ከምድር በላይ በሚበር ገንዘብ የሚበርበት በእግሩ ላይ መጕረጥ (ማጉርጥ) ያለው ነው ፤

(በዘይሠርር ቦቱ) አለ፣ ሲበር መጕረጡ (ማጕርጡ) ምድር ነክቶ ሽብረክ ብሎ ነውና ፤

፳፪፤ ዝንቱ ዘትበልዑ ፣

የምትበሉት ይህ ነው፣

ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምኔሁ ፤

ከርሱ የማትበሉት ይህ ነው አለ፣ ያመጣዋል ፤

ደጎብያ ወዘአምሳሊሁ ፤

ኵብኩባ ፤ ይህን የመሰለውንም ሁሉ፤

ወአቃጣን ወዘአምሳሊሁ ፤

ፌንጣ እርሱን የመሰለውን ሁሉ ፤

ወአፍዮማክን ወዘአምሳሊሁ ፤

አሸን እርሱን የመሰለውን ሁሉ ፤

ወአንበጣ ወዘአምሳሊሁ ፤

አንበጣ እርሱን የመሰለውን ሁሉ ፤

፳፫፤ ወእምዘይሠርር በአርባዕቱ እገሪሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፣

ከወፍ ጀምሮ በአራት እግሩ እስከሚሽከረከር አውሬ ድረስ ለናንተ የረከሰ ነው አለ፣ እንደ ዝንጀሮ እንደ ጦጣ ያለው ነው ፤

ወቦሙ ትረኵሱ ፤

አሁን ሲናገረው በመጣው በአዕዋፍ በአራዊት ሁሉ ትረክሳላችሁ፣ (ሐተታ) አራት ጥፍር አምስተኛ መጕረጥ ያለውን ብሉ፣ የሌለውን አትብሉ አለ ፣ አራት ባሕርያተ

www.ethiopianorthodox.org

ሥጋ አምስተኛ የባሕርየ ነፍስ ግብር የሌለውን በልጅ ነት አልቀበልም ያለውን፤ እቀ በላለሁ ሲል ነው ፡፡

፳፬ ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፤

በድናቸውን የነካ የዳሰሰ ሁሉ እስከ ሠርክ የረከሰ ነው ፡፡

፳፭፡ ወኵሉ ዘአልዓለ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፤

በድናቸውን አንስቶ የተሸከመ ሰውም እስከ ሠርክ ድረስ የረ ከሰ ነውና ልብሱን ይጠብ ፡፡

፳፮ ወእምኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወሥጡቅ ጽፈሪሁ ወዘኢያመሰኵዕ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤

ከእንስሳም ሁሉ ሰኰናው የተከፈለው፤ ጥፍሩ የተሰነጠ ቀው የማያመሰኳው ለናንተ የረከሰ ነው፡፡

ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ ፤

ኵሉ ዘገሠሠ ለማለት ደገ መው፤ በድናቸውን የዳሰሰ ሰው ሁሉ የረከሰ ነው ፡፡

፳፯፡ ወኵሉ ዘየሐውር በእደዊሁ እምኵሉ አራዊት ዘየሐውር በአርባዕቱ እገሪሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤

ከአራዊት ሁሉ በእጁ፤ በአራት እግሩ የሚሄደው ሁሉ ለና ንተ የረከሰ ነው፤ (ሐተታ) ዘየሐውር በእደዊሁ አለ፤ የአራዊት የፊት እግራቸውን የአዕዋፍ ክንፋቸውን እጅ ይለዋልና ፡፡ ጠላት የሚያ ጠቁበት ፊታቸውን የሚያድ ፉበት (የሚጠርጉበት) ስለ ሆነ፡፡

ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፡፡

ሬሳቸውንም የዳሰሰ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው ፤

፳፰፡ ወዘፆረ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፡፡

ዘአልዓለ በድኖሙ ያለውን ዘፆረ በድኖሙ ብሎ ደገ መው፤ ሬሳቸውንም አንስቶ የተሸከመ ሰው ልብሱን ይጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው ፡፡

፳፱፡ ወዝንቱ ዘርኵስ ውእቱ ለክሙ እምዘይትሐወስ ውስተ ምድር ፡፡

በምድር ተሐውሶ ያለው ይህ ሁሉ ለናንተ የረከሰ ነው ፤



አንጺዋ፤

አይጥ

ወጽቁጽቋን፤

ጽቁጽቋን፤

ፍልፈል፤

ወሐርገጽ፤

ሐርገጽ፤

አዞ፤

ወላጽቂት፤

ላጽቂት፤

እንሽላሊት፤ ሽረሪት፤

ወሐንጻን፤

ሐንጻን፤

እንዝዝ፤ አርጃኖ፤

ወአንጕግ፤

አንጕግ፤

ጉማሬ፤

ወጋሌ፤

ጋሌ፤

እባብ፤ እንሽላሊት፤

ወከሜሌዎን፤

ከሜሌዎን፤

እንቃቅላ፤

ወሰጳላክስስ፤

ሰጳላክስስ፤

እስስት፤

፴፡ ዝንቱ ውእቱ ዘርኵስ ለክሙ እምኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር፤

በየብስ ከሚንቀሳቀሰው ሁሉ ይህ ለናንተ የረከሰ ነው ፡፡

ወኵሉ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፡፡

ውዳቂያቸውን የዳሰሰ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው ፡፡

፴፩፤ ወኵሉ ዘወድቀ በድኖሙ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ፡፡

ሬሳቸው በላዩ የወደቀበት ሁሉ የረከሰ ነው ፡፡

፴፪፤ እምኵሉ ንዋየ ዕፅ ወእመኒ ልብስ አው ማዕስ አው ሐስል ፡፡

ሥራ ከሚሠራበት እንጨት ሁሉ ቢወድቅበት የረከሰ ነው ፡፡ (ንዋየ ዕፅ) ገበታ ማንካ ነው ፡፡ አንድም በእጅ የሚይዙት በትር፤ የሚወረ ውሩት ጦር ነው፤ ልብስም፤ ቢሆን ጀንዲም ቢሆን (ሐስል) አቅማዳ ዳውላም ቢሆን ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ወእምኵሉ ንዋይ ዘይገብሩ ቦቱ ግብረ ውስተ ማይ ይጥምዕዎ ፤

ሥራ ከሚሠሩበት ዕቃ ሁሉ የወደቀበት ቢኖር ከውሃ ውስጥ ይንከሩት ማለት ይጠቡት ፤

ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ ወእምዝ ንጹሕ ውእቱ ፤

እስከ ሠርክ የረከሰ ነው፤ ከሠርክ በኋላ ግን ንጹሕ ነው፤

፴፫፤ ወኵሉ ንዋየ ልሕኵት ዘወድቀ ላዕሌሁ እምዝንቱ ኵሉ ውስተ ከርሡ እምከመ ውስተ ውስጡ ወድቀ ርኩስ ውእቱ ወይስብርዎ ፤

ላዕሌሁ ለልሕኵት ነው፣ አሁን ሲናገረው ከመጣው የማሰሮ ዕቃ ሁሉ የወደቀበት (የነካው) በውስጡ ከሆነ የረከሰ ነውና ይስበሩት ፤

፴፬፤ ወኵሉ በዘትበልዑ እክለ ወእመኒ ዘትወድዩ ውስቴቱ ማየ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤

እህል በምትበሉበትም ዕቃ ሁሉ ውሃ በምትቀዱበት ማድጋ (እንስራ) ቢሆን ቢነካው የረከሰ ነው፤

ወእመኒ ንዋየ ስቴ በዘቦቱ ትሰትዩ ርኩስ ውእቱኒ ፤

በምትጠጡበት ብርሌ ብር ጭቆ ዋንጫም ቢሆን ቢነካው እርሱም የረከሰ ነው ፤

፴፭፤ ወኵሉ ዘወድቀ ላዕሌሁ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ ፤

ነሳሳለትና ኵሉ ብሎ አመጣው፣ በድናቸው የወደቀበት ሁሉ ለናንተ የረከሰ ነው ፤

ወእመሰ እቶን አው መንበረ መቅጹት ትነሥትዎ እስመ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤

ጉልቻም ቢሆን ምድጃም ቢሆን ለናንተ የረከሰ ነውና አፍርሱት፤

፴፮፤ ዘእንበለ አንቅዕተ ማያት ወዓዘቃት ወአዕያጋተ ማያት ወዝንቱ ዘንጹሕ ለክሙ ፤

ምንጩ ኵሬው (አዕያጋት) እንደ ጣና (እንደ ምጥዋ) ያለው ነው፣ ይህ ለናንተ ንጹሕ ነውና ከዚህ በቀር ያለዚህ ፤

፴፯፤ ወእመሰ ወድቀ በድኖሙ ላዕለ ዘርእ ዘይዘራእ ንጹሕ ውእቱ፣

በሚዘራው ዘር ውስጥ ግን በድናቸው ቢወድቅ ንጹሕ ነው ማለት አያረክሰውም ፤

፴፰ ወእመሰ ተክዕወ ማይ ላዕለ ኵሉ ዘርእ ዘወድቀ በድኖሙ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ለክሙ ፤



እዝት (እዥ) ቢፈስበት ግን በድኑ በወደቀበት ላይ ዘሩን አይዝሩ፣ ለእናንተ የረከሰ ነውና ፤

፴፱፤ ወእመቦ ዘሞተ እምእንስሳ ዘይከውኑክሙ ለበሊዕ ዘገሠሠ በድኖሙ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

ለመብል (ለምግብ) ከሚሆኗችሁ ከእንስሳ ወገን ቢሞት በድናቸውን የዳሰሰ ሰው ቢኖር እስከ ሠርክ ድረስ የረከሰ ነው ፤

፵፤ ወዘበልዓ ማውታሁ ይሕፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

ሙቶ ያደረውን በክቱን የበላ ሰውም ልብሱን ይጠብ፣ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ሠርክም የረከሰ ነው ፤

ወዘአልዓለ በድኖሙ ይሕፅብ አልባሲሁ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

ሬሳቸውን (ወደቃውን) አንስቶ የተሸከመ ልብሱን ይጠብ፣ እስከ ሠርክም የረከሰ ነው ፤

፵፩፤ ወኵሉ አርዌ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ርኵስ ውእቱ ለክሙ ወኢትብልዕዎ ፤

በየብስ የሚመላለሰው አውሬ ሁሉ (ማለት) ለምግብ ያልታዘዘው አውሬ ሁሉ ለናንተ የረከሰ ነውና አትብሉት ፤

፵፪፤ ወለኵሉ ዘየሐውር በከብዱ ኢትብልዕዎ ወለዘየሐውር በአርባዕቱ እግሩ ፤

በልቡ የሚሳበውን በአራት እግሩ የሚሽከረከረውን ሁሉ አትብሉት፤

ወለዘብዙኅ እገሪሁ እምኵሉ አርዌ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ኢትብልዕዎ እስመ ርኵስ ውእቱ ለክሙ ፤

በዚህ ዓለም ከሚመላለሰው አውሬ ሁሉ እግሩ ብዙ የሆነውን (እንደ ሾህ እግር) ያለውንም አትብሉ፣ ለናንተ የረከሰ ነውና ፤

፵፫፤ ወኢታርኵሱ ነፍሰክሙ በኵሉ አራዊት ዘይትሐወስ ውስተ ምድር፣

በዚህ ዓለም ከሚመላለሰው አውሬ ሁሉ በልታችሁ ሰውነታችሁን አታርክሱ ፤

ወኢትርኰሱ በእሉ ወኢትኩኑ ርኵሳነ ቦሙ ፤

እነዚህን በልታችሁ አትርከሱባቸው፤ በእኒህም ርኩሳን አትሁኑ ፤

፵፬፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወተቀደሱ ወቅዱሳነ ኩኑ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ከኃጢአት ተለዩ፣ ንጹሐ ንም ሁኑ ፤

እስመ አነ እግዚአብሔር አምላ ክክሙ ቅዱስ አነ ፣ ወኢታገምኑ፣ ነፍሰክሙ በኵሉ አራዊት ዘይት ሐወስ ውስተ ምድር፤

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብ ሔር ንጹሐ ባሕርይ ነኝና በዚህ ዓለም ከሚኖረው አውሬ ሁሉ ማለት የማይገባውን በልታችሁ ሰውነታችሁን አታ ሳድፉ ፤

፵፭፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውፃእኩክሙ እም ድረ ግብጽ ከመ እኩንክሙ አምላ ከክሙ ወትኩኑ ቅዱሳነ እስመ ቅዱስ አነ ፣

ፈጣሪ እሆናችሁ ዘንድ ከግብጽ ያወጣኋችሁ ፈጣሪያ ችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና እኔ ንጹሕ እንደሆንሁ እና ንተም ንጹሕ ትሆኑ ዘንድ፤ አንድም ክቡር እንደ ሆንሁ ክቡራን ትሆኑ ዘንድ (ኢታ ገምኑ ነፍሰክሙ ላለው ፤)

፵፮፤ ዝንቱ ውእቱ ሕግ ዘበእንተ እንስሳ ወዘበእንተ አዕዋፍ ወዘበእንተ አራዊት ፣

ስለ እንስሳትና ስለ አዕዋፍ ስለ አራዊትም የተነገረው ሕግ ይህ ነው፣ ሲናገረው መጥቷልና ፤

ወዘበእንተ ኵሉ ነፍስ እንተ ትትሐወስ ውስተ ማይ ወውስተ ምድር ፤

በየብስና በባሕር ስለሚመላ ለሰው (የደመ ነፍስ ወገን ሁሉ) የተነገረው ሕግ ይህ ነው፣ እየተረተረ ሲናገረው መጥቶ ነበርና (ኵሉ ብሎ ጠቅሎ ተናገረው ፤

፵፯፤ ዘይፈልጥ ማዕከለ ርኵሳን ወማዕከለ ንጹሐን ፤

በርኵሳንና በንጹሐን መካከል ድንበር ሁኖ የሚለይ የአ ራዊት ሕግ ይህ ነው፤ (ሐተታ) ርኵሱ ንጹሑን ይበላዋል፣ ንጹሑ ግን ርኵ ሱን አይበላውምና እንዲህ አለ፤

ወታሌብዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምኵሉ ሕያው ዘይበልዑ ወዘኢይ በልዑ ፤

ለያዕቆብ ልጆች በደመ ነፍስ ሕያው ከሚሆነው የሚበሉ ትንና የማይበሉትን ልብ አስደርጋቸው (ንገራቸው)፣ ከላይ ንግርዎሙ ብሎ ሙሴ ንና አሮንን አዝዟቸው ነበርና ቢርቀው ደግሞታል ፤ አን ድም ለማጽናት ደግሞታል ።



## ምዕራፍ ፲፪
## ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፥

እግዚአብሔር ለሙሴ እን ዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወንግሮሙ እንዘ ትብል ብእሲት እመ ፀንሰት ወወለደት ተባዕተ ርኵስት ይእቲ እስከ ሰቡዕ ዕለት በከመ መዋዕለ ትክቶሃ፣

ሴት ወንድ ልጅ ፀንሳ ብትወልድ እንደ ግዳጇ ወራት እስከ ሰባት ቀን ድረስ የረከሰች ናትና ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራ ቸው አለው፣ ሔዋንን አብ ነት አድርጎ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሱ ሴቶች ሥርዓት ይሠራል፤

፫፤ ወበሳምንት ዕለት ታገዝሮ ከተማ ነፍስቱ ፤

ወለሕፃን ትገዝርዎ በሳም ንት ዕለት ብዬ ለአብርሃም እንደ ነገርሁት ፤

ኦሪት ዘፍ. ፲፯ ቍጥር ፲፪ በስምንተኛው ቀን የብልቱን ሰንኮፍ ታስገዝረው ፤

፬፤ ወ፴ ወ፫ተ ዕለተ ትነብር በእንተ ደማ ለነጺሖታ እምነኩሉ ርኵስ ፤

ስለ ደሟ ከርኵሰቷ መንጻት የሚገባት ስለሆነ ሠላሳ ሦስት ቀን ከሰው ተለይታ ትቀመጥ ፤

ወእምነኩሉ ቅዱስ ኢትግሥሥ ወውስተ መቅደስ ኢትባእ እስከ ትፌጽም መዋዕለ ንጹሕ ፤

የንጽሕናዋ ወራት ማለት አርባው ቀን እስኪፈጸም ድረስ ወደቤተ መቅደስ አትግባ፣ የነጻውንም ሁሉ አትንካ፣ (ሐተታ) ሰባት ቀን ርኵስት ናት አለ ፣ ሠላሳ ሦስት ቀን ቅዱስ ሳትነካ፣ ከቤተ እግዚአብሔር ሳትገባ ትቀመጥ አለ ፣ ሰባትና ሠላሳ ሦስት አርባ ይሆናል፣ አዳምን በፈጠረው በ፵ ቀን በልጅነት አክብሮ ብርሃን አልብሶ ገነት አግብቶት ነበ ርና፣ ይህን ሥርዓት አድር ገው በሕገ ኦሪት የነበሩ ሰዎች ወንድ ልጅ በተወለደ በ፵ ቀን ዕጕለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ አስይዘው ወደ ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ይገቡ ነበር ፤ ዛሬ እኛም ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀን ከቤተ ክርስቲያን አስገብተን አጥም ቀን ሥጋውን ደሙን አቀብለን እንድንወጣ ፤

፭፤ ወእመሰ ወለደት አንስተ ርኵስት ይእቲ ፲ተ ወ፬ተ መዋዕለ በከመ ትክቶሃ ፤

ሴት ልጅ ብትወልድ ግን እንደ ግዳጇ ጊዜ አሥራ አራት ቀን የረከሰች ናት፣ ይህ ዓለም በተፈጠረ በሁለተኛው ሰባት ሔዋን ተፈጥራ ነበርና ፤

ወስሳ ወስድስተ ዕለተ ትነብር በእንተ ደማ ለነጺሐታ ፤

ስለ ደሟ ከርኩሰቷ መንጻት የሚያሻት ስለ ሆነ ስሳ ስድስት ቀን ከሰው ተለይታ ትቀመጥ አለ፣ (ሐተታ) አሥራ አራትና ስሳ ስድስት ቢገጥሙት ሰማንያ ይሆናል ሔዋንን በፈጠራት በ፹ ቀን በልጅነት አክብሮ ገነት አስገብቷት ነበርና በሕገ ኦሪት የነበሩ ሰዎች ይህንኑ ሥርዓት አድርገው ፤ ሴት ልጅ በተወለደች በሰማንያ ቀን እኀለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ አስይዘው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይገቡ ነበር፣ ዛሬም እኛ ሴት ልጅ በተወለደች በሰማንያ ቀን ከቤተክርስቲያን አስገብተን አጥምቀን ሥጋውን ደሙን አቀብለን እንድንወጣ ለማጠየቅ፣

ኵፋሌ ፬ ቁጥ. ፲፥ ፲፯፤

፮፤ ወአመ ተፈጸመ መዋዕለ ንጽሐ እመኒ በእንተ ወልድ ወእመኒ በእንተ ወለት ታመጽእ በግዓ ዘዓመት ለመሥዋዕት ፤

የንጽሕናዋ ወራት በተፈጸመ ጊዜ ማለት በወንድ አርባ ቀን፣ በሴት ሰማንያ ቀን በተፈጸመ ጊዜ ዓመት የሆነው በግ ለመሥዋዕት ታምጣ፤

ወእመኒ እኍለ ርግብ አው ዘማዕነቅ በእንተ ኃጢአት ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኀበ ካህን ፤

ታመጽእ በእንተ ኃጢአት ነው፣ በግ ቢታጣ የርግብ ግልገል፣ ይህም ቢታጣ ዋኖስ (ቡላል) ስለ ኃጢአቷ ካህኑ ወዳለበት ወደ ደብተራ ኦሪት ታምጣ ፤

፯፤ ወያበውእ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ላቲ ካህን ወያነጽሓ እምነቅዓ ደማ ፤



እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ካህን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቦ ከደሟ ርኩሰት ያንጻት፣ ኃጢአቷንም ያስተሥርይላት፤

ዝንቱ ውእቱ ሕግ ለእንተ ትወልድ እመኒ ተባዕተ ወእመኒ አንስተ ፤

ሴትም ብትሆን ወንድም ቢሆን ለምትወልድ ሴት የታዘዘው ሥርዓት ይህ ነው አለ ፣ ሲናገረው መጥቷልና ፤

፰፤ ወእመሰ አልባቲ ውስተ እዴሃ ወኢተአክል ለበግዕ ታመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ አው ክልኤተ እኍለ ርግብ አሐደ ለመሥዋዕት ወአሐደ ዘበእንተ ኃጢአት ፤

በእጇ ገንዘብ ባይኖራት በግ ለመግዛት ባትበቃ ግን ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት የርግብ ግልገል አንዱን ለመሥዋዕት አንዱን ስለ ኃጢአት ታምጣ ፤

፱፤ ወያስተሠሪ ላቲ ካህን ወትነጽሕ ፣

ሊቀ ካህናቱ ኃጢአቷን ያስተሠርይላታል ከኃጢአቷም፣ ትነጻለች፡፡

## ምዕራፍ ፲፫

፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ፤

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ተናገራቸው ፤

፪፤ ወይቤሎሙ እመቦ ብእሲ ዘወፅአ ውስተ ኀበረ ማዕሱ ትእምርት ከመ ርምየት ፤

በሰውነቱ እንደ እትራት ምልክት የወጣበት ሰው ቢኖር ፤

ወዓዕደወት ወኮነት ውስተ ማዕሱ ኀብረ ለምጽ ለይሑር ኀበ አሮን ካህን አው ኀበ አሐዱ እምደቂቀ ካህናት ፣

ዓዕደወትና ኮነት አንድ ወገን፣ በሰውነቱ ላይ ብትነጣ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ አሮን ይሂድ፣ አሮን ቢታጣ (ባይኖር) እግዚአብሔርን ከሚያገለግሉ ከልጆቹ ወደ አንዱ ይሂድ ፤

፫፤ ወይርአያ ካህን ለይእቲ ኀብር እንተ ውስተ ኀብረ ማዕሱ ፣

ካህኑ አሮን ወይም ከልጆቹ አንዱ በሰውነቱ መልክ ውስጥ የወጣችውን ለምጽ መርምሮ ይያት ፤

እመ ተወለጠ ሥእርታ ለይእቲ ኀብር ወዓዕደወት ፣

በለምጹ የበቀለችውም ጠጉር ነጭ ሁና ከጥቁረቷ ብትለወጥ ፤

ወእመኒ እኩይ ርእየታ ለይእቲ ኀብር ዘውስተ ኀብረ ማዕሱ ወኀብረ

www.ethiopianorthodox.org

ለምጽ ይእቲ ይርአያ ካህን ወያርኵሳ ፤

በሰውነቱ ውስጥ ያለች የዚ ያች መልክ አስተያየቷ ቢከፋ ማለት (ቢሰፋ) የለምጽ መልክ ናትና ካህኑ መርምሮ አይቶ ርኩስ ይበላት አለ፣ ለምጽ የወጣበትን ሰው በውጭ ቆይ ይበለው፣

፬፤ ወእመሰ ፀዓዳ ጎብር ይእቲ ውስተ ጎብረ ማዕሱ ወኢኮነ እኩየ ርእየታ ወኢተወለጠ ሥዕርታ ወኢፃዕደወ፣

በሰውነቱ ነጭ መልክ ብትኖር ያችም ባትሰፋ ባትጠፋ የጠጉ ሯም መልክ ባይለወጥ ነጭ ባይሆን፤

ወይእቲ ኢታስተርኢ በሕቁ ያጸንሖ ካህን ሰቡዓ ዕለተ በእንተ ይእቲ ጎብር፣

ይችውም ፈጽማ ጎልታ ባት ታይ ስለ ወጣችበት ለምጽ ሊቀ ካህናቱ ሰባት ቀን ያቆያት ማለት የወጣችበትን ሰው ሰባት ቀን ያቆየው፣

፭፤ ወበሳብዕት ዕለት ይርአያ ካህን ለይእቲ ጎብር፤

በሰባተኛው ቀን አስመጥቶ ሊቀ ካህናቱ የቀደመችውን ለምጽ መርምሮ ይያት፤

ወናሁ ሀለወት ዓዲሃ ይእቲ ጎብር ቅድሜሁ ወኢኀደገት ይእቲ ጎብር እማዕሱ ያጸንሖ ካህን ካልአ ሰቡዓ ዕለተ፣

ያች ለምጽ ገና ሁና ከፊቱ ባትጠፋ፣ ከሰውነቱም ባትጠፋ ብትሰፋ ካህኑ ዳግመኛ ሰባት ቀን ያቆየው፤

፮፤ ወይርአዮ ካህን ዳግመ በሳብ ዕት ዕለት፣

ካህኑ ዳግመኛ አስመጥቶ በሰ ባተኛው ቀን ይያት፤

ወናሁ ኢታስተርኢ በሕቁ ይእቲ ጎብር ወኢኀደገት እማዕሱ ይእቲ ጎብር ያነጽሓ ካህን እስመ ትእም ርት ይእቲ፣

ለምጺቱ ፈጽማ ጎልታ ባት ታይ ከሰውነቱ ባትጠፋ ምል ክት ናትና ካህኑ ያንጻት ማለት ሰውየውን ንጹሕ ነው ይበለው፤

ወየሐፅብ አልባሲሁ ወንጹሐ ይከ ውን፣

ልብሱን አጥቦ ንጹሕ ይሁን፣

፯፤ ወእመሰ ተወለጠት ይእቲ ጎብር ወኮነት እኪተ ውስተ ማዕሱ እምድኅረ ርእዮ ካህን ወአንጽሖ የሐውር ዳግመ ኀበ ካህን፣

የወጣችበት ለምጽ ከመልኳ ብትለወጥ ግን ፣ ካህኑ አይቶ



ካነጻውም በኋላ ከሰውነቱ ባትጠፋ ዳግመኛ ወደ ሊቀ ካህናቱ ይሂድ፣ ለለምጹ ነው እንጂ ለሊቀ ካህናቱስ ሦስተኛ ነው፤

፰፤ ወይሬእዮ ካህን ወናሁ አከየት ይእቲ ጎብር ውስተ ማዕሱ ያረኵሳ ካህን እስመ ለምጽ ይእቲ፣

ሊቀ ካህናቱ መርምሮ አይቶ በገላው ውስጥ ሰፍታ ቢያገ ኛት ለምጽ ናትና ሊቀ ካህናቱ ርኩስ ይበላት ማለት ሰውዬ ውን ይለየው፤

፱፤ ወነብረ ለምጽ እመ ወፅአት ላዕለ ብእሲ የሐውር ኀበ ካህን፣

የለምጽ መልክ በማናቸውም ሰው ብትወጣ ወደሊቀ ካህናቱ ይሂድ፤

፲፤ ወይሬእዮ ካህን፣

ሊቀ ካህናቱም መርምሮ ይየው፤

ወናሁ ከመ ርእየተ ፀዓዳ ይእቲ ውስተ ማዕሱ ወአውፅአት ሥእ ርተ ፀዓዳ ውስተ ማዕሱ ወጕንደ የት ውስተ ሥጋሁ ውስተ ዘዳኅን ጎብረ ማዕሱ፣

በሰውነቱ ብትነጣ እንደ እት ራት ብትሆን በሰውነቱም ነጭ ጠጕር ብታወጣ ደኅና በሆነው በሰውነቱ ወጥታ ብትዘገይ፤

፲፩፤ ይእቲ ትእምርት ፀዓዳ፣

ይችውም እትራት በደኅነኛው ገላው ውስጥ ነጭ ጠጕር አውጥታ ብትገኝ፤

ያረኵሶ ካህን ወኢያነጽሖ እስመ ርኩስ ውእቱ፣

ርኩስ ነውና ሊቀ ካህናቱ ይለየው እንጂ አያንጻው፤

፲፪፤ ወእመሰ ወፅአ ለምጽ ውስተ ማዕሱ፣

በሰውነቱ ውስጥ ለምጽ ቢወ ጣበት፤

ወከደነ ጎብረ ለምጽ ኵሎ ማዕሶ እምርእሱ እስከ እገሪሁ ኵለንታሁ ይሬእዮ ካህን፣

«ኵሎ ማዕሶና ኵለንታሁ አን ድ ወገን»፣ ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩ መላ ገላውን የለምጽ መልክ ቢሸፍነው ሊቀ ካህናቱ ይመርምረው፤

፲፫፤ ወርእዮ ካህን ከመ ከደነ ጎብረ ለምጽ ኵሎ ማዕሶ እምርእሱ እስከ እገሪሁ ያነጽሖ ካህን፣

ሊቀ ካህናቱ ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩ የለምጽ መልክ እንዳለበሰው መርምሮ አይቶ ንጹሕ ይበለው ማለት ፍጹም ለምጻም ይበለው፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ኵለንታሁ ተወለጠ ወፃዕደወ ወበእንተ ዝንቱ ንጹሕ ውእቱ፤

መላ ሰውነቱ ተለውጦ ነጭ ሁኗልና ስለዚህ ንጹሕ ነው ማለት ፍጹም ለምጻም ነው፤

፲፬፤ ወበዕለተ አስተርአየ ላዕሌሁ ኅብር ዘዳኅን ይረኵስ፤

‹‹ላዕሌሁ ለለምጽ ነው›› በነጩ፥ ለምጽ ላይ ደኅና በሆነ ሰውነቱም ላይ ምልክት በታየ በት ቀን ይረክሳል፤

፲፭፤ ወይሬእዮ ካህን ለውእቱ ኅብር ዘዳኅን ወያረኵሶ ውእቱ ኅብር ዘዳኅን፤

ደኅና በሆነ ሰውነቱ ያለ ያነን መልክ ካህኑ መርምሮ ይየው፤ በደኅናው ሰውነቱ ያለ የለምጽ መልክ ያረክሰዋል ርኩስ ያሰኘዋል፤

ወበእንተ ዝንቱ ርኩስ ውእቱ እስመ ለምጸ ኮነ፤

ለምጻም ሁኗልና ስለዚህ ነገር የረከሰ ነው፤

፲፮፤ ወእመሰ ኀደገ ውእቱ ኅብር ዘዳኅን ወተወለጠ ወፃዕደወ የሐውር ኀበ ካህን፤

ደህና በሆነ ሰውነቱ ያለ ያ የለምጽ መልክ ቢተወው ወደ ደኅንነት ቢለወጥ ነጭ ባይሆን ወደ ካህኑ ይሂድ፤

፲፯፤ ወይሬእዮ ካህን ወናሁ ኢተወለጠት ይእቲ ኅብር ወኢፃዕደወት ያነጽሖ ካህን ለይእቲ ኅብር እስመ ንጹሐ ኮነ፤

ካህኑ አይቶ ያች መልክ ባትለወጥ ነጭ ባትሆን ንጹሕ ሆኗልና ያችን መልክ ያንጻት ማለት ንጹሕ ነህ ይበለው፤

፲፰፤ ወለእመ ፈርገገ ሥጋሁ ውስተ ርምየተ ቍስሉ ሐይዎ፤

ከዳነ በኋላ ቁስሉ በነበረበት በእትራቱ ውስጥ እንደገና ቢያ ትርበት፤

፲፱፤ ወወፅአ ውስተ ውእቱ መካነ ቍስሉ ፀዓዳ ከመ ርምየት እንተ ታስተርኢ ፀዓድዒደ አው ቀያሕይ ሕተ ያሬእዮ ለካህን፤

ቁስል በነበረበት ሰውነት ውስጥ ነጭ ሁና ወይም ቀይ ሁና እንደምትታይ እትራት የለምጽ ምልክት ቢወጣ ለካ ህኑ ያሳየው፤ (ፀዓድዒድ ፍጹ ም ነጭ) ቀያሕይሕት ዝንጉ ርጉር ነው፤

፳፤ ወርእዮ ካህን ወናሁ እኪት ይእቲ እማዕሱ ወስእርታኒ ተወለጠ ወፃዕደወ ያረኵሶ ካህን፤

ካህኑም አይቶ እነሆ ከሰው ነቱ የተለየች ብትሆን፤ ጠጉ ሯም ከቀደመው ተለውጦ



ነጭ ቢሆን ካህኑ ርኩስ ብሎ ይለየው፤

እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ ወውስተ ርምየት ወፅአት፤

የለምጽ መልክ ናትና በእትራ ትም ላይ ወጥታለችና፤

፳፩፤ ወእመሰ ርእዮ ካህን ከመ አልቦ ውስቴታ ሥዕርት ፀዓዳ ወኢ ኮነት እኪተ ውስተ ኅብረ ማዕሱ ፤

«ውስቴታ ለለምጽ ነው» ነገር ግን ካህኑ አይቶ በለምጹ ውስጥ ነጭ ጠጉር ባይኖር በሰውነቱም ውስጥ የተለየች ባትሆን፤

ወለሲሣኒ ኢታስተርኢ ያጽንሖ ካህን ሰቡዓ ዕለተ፤

በአፍኣም ጕልታ ባትታይ ካህኑ ሰባት ቀን ያቆየው፤

፳፪፤ ወለእመ ተከዕወት ውስተ ማዕሱ ያረኵሶ ካህን እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ ወውስተ ርምየት ወፅአት፤

በሰውነቱ ብትሰፋ ግን የለምጽ መልክ ናትና በእትራቱም ላይ ወጥታለችና ካህኑ ርኩስ ነህ ብሎ ይለየው፤

፳፫፤ ወእመሰ በመካና ነበረት ይእቲ ኅብር ወኢተከዕወት ርምየተ ቍስል ይእቲ ያነጽሓ ካህን፤

ያች መልክ በወጣችበት ቦታ ብትኖር ባትሰፋ የቍስል እት ራት ናትና ካህኑ ያንጻት ማለት ነጹሕ ነህ ይበለው፤

፳፬፤ ወለእመ ፈርገገ ሥጋሁ እማዕሱ እመኒ ውስተ ውእየተ እሳት ወወፅአት ውስተ ማዕሱ ዘዳኅን እምውእየተ እሳት፤

ቍስሉ ከሰውነቱ ቢሰፋ፤ እሳት በልቶትም ቢሆን፤ በእሳት ከመ ቃጠሉ የተነሣ በደኅና ሰውነቱ ውስጥ ብትወጣ፤

ወአስተርአየት ኅብር እንተ ታቅየሐ ይሕ አው ፀዓድዒድ ይሬእያ ካህን፤

ቀይ ወይም ነጭ የሆነች መልክ ብትታይ ካህኑ መር ምሮ ይያት፤

፳፭፤ ወናሁ ወለጠት ኅብረ ፀዓዳ ወስእርተ ወአስተርአየት ወርእየ ታኒ እኩይ እማዕሱ ለምጽ ይእቲ ወውስተ ውእየት ወፅአት፤

ባሕርይዋን ለውጣ ነጭ ገላ ሁና ነጭ ጠጉር አብቅላ ብት ታይ እሳት በበላውም ብትወጣ በሰውነቱ ብትሰፋ ለምጽ ናት፤

ወያረኵሳ ካህን እስመ ኅብረ ለምጽ ይእቲ፤

የለምጽ መልክ ናትና ካህኑ ሰውየውን ርኩስ ብሎ ይለየው፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፤ ወእመሰ ርእዮ ካህን ወናሁ አልቦ ውስቴታ ስእርት ፀዓዳ ዘያስተርኢ ወኢኮነት እኪተ እማዕሱ ወለሲሃኒ ኢታስተርኢ ያጸንሓ ካህን ሰቡዓ ዕለተ።

ካህኑ አይቶ የሚታይ ነጭ ፀጉር በውስጧ ባይኖር በሰውነቱ ባትሰፋ እርሷም ጉልታ ባትታይ ካህኑ ሰውየውን ሰባት ቀን ያቆየው፤

፳፯፤ ወይሬእዮ ካህን በሳብዕት ዕለት ወለእመ ተከዕወት ውስተ ማዕሱ ያረኵሳ ካህን እስመ ኀብረ ለምጽ ይእቲ ወውስተ ውእየት ወጽአት።

በሰባተኛው ቀን ካህኑ አስመ ጥቶ ይየው፣ በሰውነቱ ውስጥ ብትሰፋ የለምጽ መልክ ናትና እሳት በበላው ገላውም ወጥታ ለችና ሊቀ ካህናቱ ርኵስ ብሎ ይለየው፤

፳፰፤ ወእመሰ በመካና ነበረት ይእቲ ኀብር ወኢተከዕወት ውስተ ማዕሱ ወለሲሃኒ ኢታስተርኢ ርምየተ ውእየት ይእቲ ወያነጽሓ ካህን እስመ መካነ ውዕየት ይእቲ።

በሰውነቱ ባትሰፋ በወጣችበት ቦታ ብትኖር ግን እርሷም ባት ታይ የእሳት መቃጠል እት ራት ናትና ካህኑ አይቶ ሰው የውን ንጹሕ ነህ ይበለው፤

፳፱፤ ወእመቦ ብእሲ አው ብእሲት ዘወፅአ ኀብረ ለምጽ ውስተ ርእሱ አው ውስተ ጽሕሙ።

በራሱ ውስጥ ወይም በጽሕሙ የለምጽ መልክ የወጣበት ሰው ቢኖር፤

፴፤ ወርእያ ካህን ለይእቲ ኀብር ወናሁ ርእየታ እኩይ እማዕሱ ወቦ ውስቴታ ስእርት ፀዓዳ ቀጣን እንተ ወፅአት ወያረኵሶ ካህን እስመ ትእምርተ ለምጽ ይእቲ ዘርእስ አው ዘጽሕም ።

ሊቀ ካህናቱ መርምሮ ይያትና በሰውነቱ ብትሰፋ የወጣችባት ፀጉርም ብትነጣ ብትቀጥን በራሱም ቢሆን በጽሕሙም ቢሆን የለምጽ ምልክት ናትና ካህኑ ርኵስ ብሎ ይለየው ፤

፴፩፤ ወእመሰ ርእዮ ካህን ኀብራ ለይእቲ ትእምርት ወኢኮነ እኩየ ርእየታ እማዕሱ ወስእርትኒ ፀዓዳ አልቦ ውስቴታ ያጸንሖ ካህን ሰቡዓ ዕለተ ።

የዚያችን ምልክት መልክ ካህኑ አይቶ ከሰውነቱ ባትሰፋ ግን በውስጧም ነጭ ፀጉር ባይኖር ካህኑ ሰባት ቀን ያቆየው ፤

፴፪፤ ወይሬእያ ካህን በሳብዕት ዕለት ወናሁ ኢተከዕወት ይእቲ ኀብር ወስእርትኒ ፀዓዳ አልቦ ውስቴታ ወርእየታኒ ለይእቲ ኀብር ኢኮነ እኩየ እማዕሱ።



ካህኑ በሰባተኛው ቀን አይቶት ባትሰፋ በውስጧም ነጭ ፀጉር ባይኖር የዚያችም ለምጽ መልኳ በሰውነቱ ባይሰፋ «ይትላፀይ ያለበት ነው» ፀጉሩን ይላጭ፤

፴፫፤ ወሶበ ይትላፀይ ውስተ ይእቲ መካነ ማዕሱ ኢትወፅእ ይእቲ ኀብር ያጸንሓ ካህን ለይእቲ ኀብር ካልአ ሰቡዓ ዕለተ።

በተላጨም ጊዜ ለምጽ ከነበረ በት ገላው ውስጥ ያች የለምጽ መልክ ባትወጣ ያችን መልክ ካህኑ ሁለተኛ ሰባት ቀን ያቆያት፤

፴፬፤ ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር በሳብዕት ዕለት ወናሁ ኢተከዕወት ይእቲ ኀብር ውስተ ማዕሱ እምድ ኅረ ተላፀየ።

በሰባተኛዪቱ ቀን ያችን የለምጽ መልክ ካህኑ ይያትና ከተላጨ በኋላም በሰውነቱ ካልሰፋች፤

ወርዕየታኒ ኢኮነ እኩየ እማዕሱ ያነጽሓ ካህን።

መልኳም ከሰውነቱ ካልሰፋ ካህኑ ያንጻት ማለት ሰውየ ውን ንጹሕ ነህ ይበለው፤

ወየሐፅብ አልባሲሁ ወንጹሐ ይከውን።

ልብሱንም ይጠብ ንጹሕም ይሆናል፤

፴፭፤ ወእመሰ ተከዕወት ኀብር ውስተ ማዕሱ እምድኅረ አንጽሕዎ።

ንጹሕ ነህ ካሉት በኋ የለምጽ መልክ በሰውነቱ ብትሰፋ ግን፤

፴፮፤ ይሬእዮ ካህን ወናሁ ተከዕ ወት ይእቲ ኀብር ውስተ ማዕሱ ኢይፈትን ካህን ስእርተ ፀዓዳ እስመ ርኵስ ውእቱ።

ካህኑ አይቶ ያች መልክ ከተ ላጨች በኋላ ስፍታ ብትገኝ የረከሰ ነውና ነጭ ፀጉር አይ ፈልግ፤

፴፯፤ ወእመሰ ውስተ መካና ነበረት ይእቲ ኀብር ወስእርትኒ ጸሊም ወፅአ ውስቴታ ሕያውት ይእቲ ትነብር ወንጹሕ ውእቱ ወያነጽሖ ካህን፤

ያች መልክ በቦታዋ ብትኖር በውስጧም ጥቁር ፀጉር ቢወጣ የወጣችው ለምጽ መዳኗ ነውና የወጣበት ሰው ንጹሕ ነው፣ ሊቀ ካህናቱም ነጹሕ ነህ ይበለው፤

፴፰፤ ለብእሲኒ አው ለብእሲትኒ እመቦ ዘወፅአ ውስተ ማዕሰ ሥጋሁ በራህርህት አው ፀዓድዒድ ይሬእያ ካህን።

ከወንድም ቢሆን ከሴት በሰው ነቱ ውስጥ ቋቁቻ የወጣበት ወይም ኀንብርብሬ ለምጽ የወ ጣበት ሰው ቢኖር ካህኑ መር ምሮ ይየው፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፱፤ ወናሁ ውስተ ማዕሰ ሥጋሁ በራህርህት አው ፀዓድዒድ ኀንብርብሬ ይእቲ፡ ወወፅአት ውስተ ማዕሰ ሥጋሁ ንጹሕ ውእቱ፣

«ማዕሰ ሥጋሁና ማዕሰ ሥጋሁ አንድ ወገን» በሰውነቱ ውስጥ የወጣችው ለምጽ ቋቁቻም ቢሆን ወይም ነጭ ቢሆን ዝንጉርጉር ናትና ከሰው የተለየ ነው፣ የሁለቱን መልክ አስተባብሮ ይዟልና፤ አንድም ከፍጹም ለምጻም የተለየ ነው፤

፵፤ ወእመቦ ዘተመልጠ ርእሱ በራህ ውእቱ ወንጹሕ ውእቱ፣

ራሱ የተመለጠ ሰው ቢኖር ግን በራ ነው፣ ንጹሕም ነው፤

፵፩፤ ወእመሰ መንገለ ፍጽሙ ተመልጠ ርእሱ ዘስንሒት ውእቱ ወንጹሕ ውእቱ፣

በግንባሩ በኩል ራሱ ቢመለጥም ሰደዳ ነውና ንጹሕ ነው፣ ዋዌውን ትቶ ነው፣

፵፪፤ ወእመሰ ወፅአት ውስተ ብርሀቱ ወውስተ ስንሒቱ ኀብር ፀዓዳ አው ቀያሕይሕት ለምጽ ይእቲ፣

በበራውም በሰደዳውም ቢሆን ነጭ መልክ ወይም ቀይ መልክ ብትወጣ ግን ለምጽ ናት፤

፵፫፤ ወይሬእያ ካህን ወናሁ ርእየተ ኀብራ ፀዓዳ አው ቀያሕይሕት ውስተ ብርሀቱ አው ውስተ ስንሒቱ ከመ ርእየተ ለምጽ ውስተ ማዕሰ ሥጋሁ ዘለምጽ ውእቱ ብእሲሁ፣

ሊቀ ካህናቱ መርምሮ አይቶ የወጣበት ለምጽ የነጭ ኀብር መልክ ቢሆን ወይም የቀይ ኀብር መልክ ቢሆን በበራውና በሰደዳው ውስጥ የታየው ከሰውነቱ ተለይቶ እንደ ለምጽ መልክ ነውና ያ ሰው ለምጻም ይባላል፤

፵፬፤ ወምዕረ ይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር እንተ ውስተ ርእሱ አው እንተ ውስተ ስንሒቱ፤

በበራው ወይም በሰደዳው ውስጥ የወጣች ያችን ለምጽ ካህኑ ያን ጊዜ መርምሮ ይያት፣ «ምዕረ» አለ፣ ለበራው ለሰደዳው ጠጉር የለውምና ሰባት ቀን ላቆየው አይበል፣ ያን ጊዜ ይለየው ሲል ነው፤

፵፭፤ ወለዘለምጽኒ ዘሀለወት ላዕሌሁ ይእቲ ኀብር ዘለምጽ ውእቱ፡ ፍቱሐ ይኩን አልባሲሁ፣

በለምጻሙ ሰው ላይ ያለች ያች መልክ የለምጽ መልክ ናትና ሰናፊሉን ያውልቅ፤

ወርእሱኒ ክሡተ ይኩን ወይገልብብ አፉሁ ወርኩሰ ይሰመይ፣



ራሱ የተገለጠ ይሁን አለ፣ አይከናነብ አፉን ይሸፍን አለ፣ አይናገር ሲል ነው፣ ርኩስም ይባላል፤

፵፮፤ ወኵሎ መዋዕለ መጠነ ሀሎ ላዕሌሁ ለምጽ ርኩስ ውእቱ፣

ለምጽ በላዩ ባለበት ዘመን ሁሉ ርኩስ ነው፤

ወዕሉለ ይንበር ወአፍኣ እምትዕይንት ይኩን ምንባሩ፣

ከሰው ተለይቶ ይኑር፣ መኖሪያውም ከከተማው በአፍኣ ይሁን፤ (ሐተታ) በምን ምክንያት ይወጣባቸዋል ቢሉ፣ ከሕግ ከሥርዓት ሲወጡ፣ ኃጢአት ሲሠሩ ይወጣባቸዋል፣ በያዝያን በግያዝ እንደወጣ ይወጣባቸዋል፣ ለምጽ የወጣበትን ሰው ካህኑ አይቶ እስከ ሰባት ቀን ያሰነብተዋል፣ በሰባተኛው ቀን ባይሰፋ ከሰው አይለየውም፣ ዳግመኛ ሰባት ቀን ያሰነብተዋል፣ በሁለት ሰባት ባይነጻ ኀንብርብሬውን ለምጻም ከሰው ይለየዋል፣ ፍጹም ለምጻሙን ግን አይለየውም፣ ይህ ለጊዜው ሥርዓት ሁኖ ተሠርቷል፣ ለኋላው ግን ምሳሌ ነው፣ ኀንብርብሬው ይለይ አለ፣ እርሱ ደኀና ነኝ ብሎ ወደ ሰው ይቀርባል፣ ሌላውም ደኀና መስሎት ይቀርበዋል፣ ሰውንም ያረክሳልና ፍጹም ለምጻሙን አይለይ አለ፣ እርሱ ደኀና ነኝ ብሎ ወደሰው አይቀርብም፣ ሌላውም ደኀና ነው ብሎ አይጠጋውምና ሰው አያረክስም፤ አንድም ኀንብርብሬ የተርታ ኃጥእ፣ ለዚያ ከለምጽ ለመዳን ተስፋ ድኂን አለው፣ ከሰው ቢለዩት ይድናል፣ ከቦታውም ይመለሳል፣ ተርታ ኃጥእም ንስሐ ተቀብሎ ለጊዜው ይለያል፣ ቀኖናውም ያንሳል፣ ኃጢአቱም ይቀላል፣ ፍጹም ለምጻም የፍጹም ኃጥእ ምሳሌ፣ ያ ቢለዩት ተስፋ ድኂን የለውም፣ ፍጹም ኃጥእም ቀኖናው ጽኑዕ ስለ ሆነ ይህን ሁሉ ቀኖና ጨርሼ ከሰው ልገናኝ ነው? ብሎ እንደወጣ ይቀራልና፤ አንድም ኀንብርብሬ፣ የተርታ መናፍቅ ምሳሌ፣ ይለይ ማለቱ መንፈሳዊ መስሎ ወደ ሕዝቡ ይቀርባል፣ ሕዝቡም መንፈሳዊ መስሏቸው ይቀርቡታል፣ ያስታቸዋልና ፍጹም

www.ethiopianorthodox.org

ለምጻም የፍጹም መናፍቅ ምሳሌ፣ ከፍጹም መናፍቅ ሕዝቡ ክርስቲያን ነው ብለው አይሰበሰቡለትም፣ እርሱም አይ ቀርብም፣ ሰውን አያስትምና ፍጹም ለምጻም ሰናፊሉን ያውልቅ አለ፣ መናፍቅም ሃይ ማኖት አለኝ አይበል፣ ‹አይከና ነብ አለ፣ ክብር አለኝ አይበል›፣ አፉን ይሸፍን አለ፣ አያስተ ምር ሲል ነው፤

፵፯፤ ወውስተ ልብስኒ እመ ወፅአ ትእምርተ ለምጽ እመኒ ውስተ ልብሰ ፀምር ወእመኒ ውስተ ልብሰ አጌ፣

በልብስ ላይም የለምጽ ምል ክት ቢወጣ በብዝትም ቢሆን፣ በሻድሬውም ቢሆን፣ ‹በቀይ ሐርም በነጭ ሐርም› ቢሆን፤

፵፰፤ እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋዕሙ፣ እመኒ ውስተ ፀምር ወእመኒ ውስተ አጌ ወእመኒ ውስተ ማዕስ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ምግባረ ማዕስ፣

‹በዝኃው በማገ ቢወጣ ፋዕሙ አለ› ድሩ ይጎርሰዋ ልና፣ በቀይ ሐሩም በነጭ ሐሩም ቢወጣ በጀንዲውም ሥራው ባላለቀለት ማለት በቁርበቱ ሁሉ ቢወጣ፤

፵፱፤ ወወፅአት ኀብር እንተ ታሕመለምል አው እንተ ታቅየሐ ይሕ ውስተ ልብሰ ፀምር ወአጌ እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋዕሙ አው ውስተ ማዕስ አው ውስተ ኵሉ ንዋየ ማዕስ ወነብረ ለምጽ ይእቲ ያሬእያ ለካህን፣

ነጭ ወይም ቀይ መልክ በቀዩ ሐርና በነጩ ሐር በድሩም በማጉም ቢሆን ወይም በጀንዲው ይህንንም በመ ሰለው ሁሉ ብትወጣ የለ ምጽ መልክ ናትና ለካህኑ ያሳያት፤

፶፤ ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር ወያጸንሓ ሰቡዓ ዕለተ፣

ካህኑም መርምሮ አይቶ ሰባት ቀን ያቆያት፣

፶፩፤ ወይሬእያ ካህን በሳብዕት ዕለት ወለእመ ተከዕወት ይእቲ ኀብር ውስተ ውእቱ ልብስ እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋዕሙ አው ውስተ ማዕስ አው ውስተ ኵሉ ንዋየ ማዕስ ለምጽ እንተ ኢትትኃደግ ይእቲ፣

በሰባተኛው ቀን ካህኑ ዳግ መኛ አይቶ ያች መልክ በዚያ ልብስ ብትሰፋ፣ በድሩም ቢሆን በማጉም ቢሆን በጀን ዲውም ብትሰፋ የማትለቅ ለምጽ ናትና፤

፶፪፤ ወያውዕይዎ ለውእቱ ልብስ ዘፀምር ወእመኒ ዘአጌ ወእመኒ ማዕስ ወለኵሉ ንዋየ ማዕስ ውስተ



ዘወፅአት ይእቲ ኀብር እስመ ለምጽ ይእቲ እንተ ኢትትኃደግ በእሳት ያውዕይዎ፣

ለምጽ የወጣበትን ልብስ ሁሉ ለምጺቱ የማትጠፋ ናትና በእሳት ያቃጥሉት፤

፶፫፤ ወእመሰ ርእዮ ካህን ወኢተከዕወት ይእቲ ኀብር ውስተ ውእቱ ልብስ እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋዕሙ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋየ ማዕስ፣

ሊቀ ካህናቱ አይቶ በዚህ ሁሉ ላይ ባትሰፋ ግን፤

፶፬፤ የአዝዝ ካህን ይሕፅቡ ኀበ ወፅአት ይእቲ ኀብር፣

ያች ለምጽ የወጣችበትን ልብስ ያጥቡት ዘንድ ሊቀ ካህናቱ ይዘዝ፤

ወይጸንሓ ካህን ለይእቲ ኀብር ዳግመ ሰቡዓ ዕለተ፣

ያችን የለምጽ መልክ ዳግመኛ ሰባት ቀን ይጠብቃት፤

፶፭፤ ወይሬእያ ካህን ለይእቲ ኀብር እምድኅረ ሐፀብዋ ወለእመ ኢኀደጋ ኀብረ ርእየታ ወለእመኒ ተዘርወት ይእቲ ኀብር ርኵስ ውእቱ ወበእሳት ያውዕይዎ፣

ካጠቧት በኋላም በአሥራ አራተኛው ቀን አስመጥቶ ካህኑ መርምሮ ይያት፣ የነጭ ነቷ መልክ ባይተዋት ያች ለምጽ ብትሰፋ ግን ርኩስ ነውና በእሳት ያቃጥሉት፤

እስመ ወፅአት ውስተ ውእቱ ልብስ አው ውስተ ስፍሑ አው ውስተ ፋዕሙ፣

በዚህ ሁሉ ስለወጣችበት ያቃ ጥሉት፣

፶፮፤ ወለእመሰ ርእዮ ካህን ኢታስተርኢ ይእቲ ኀብር እምድኅረ ሐፀብዋ ያሴስሉ መካና እምውስተ ውእቱ ልብስ፤

ካጠቧት በኋላ ካህኑ አይቶ ያች መልክ ባትሰፋ ካልጠፋች ከወ ጣችበት ልብስ ቦታዋን ያርቁ፤

እመኒ እምውስተ ስፍሑ ወእመኒ እምውስተ ፋዕሙ ወእመኒ እም ውስተ ማዕስ፣

ከድሩም ቢሆን ከማጉም ቢሆን ከጀንዲውም ቢሆን ለምጽ የወጣችበትን ቆርጠው ይጣሉት፤

፶፯፣ ወእመሰ ዳግመ አስተርአየት ውስተ ውእቱ ልብስ፣

በዚያ ልብስ ላይ ዳግመኛ ብትታይ ግን፤

እመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋዕሙ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋየ ማዕስ ለምጽ ይእቲ ወበእሳት ያውዕይዎ ለዘውስቴቱ ወፅአት ይእቲ ኀብር፣

www.ethiopianorthodox.org

በድሩም በማጉም በጀንዲውም ቢሆን ብትታይ ለምጽ ናትና ያች የለምጽ መልክ የወጣች በትን በእሳት ያቃጥሉት ፤

፶፰፣ ወለእመሰ ተሐፂቦ ውእቱ ኀብር እመኒ ዘውስተ ስፍሑ ወእመኒ ዘውስተ ፋዕሙ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋየ ማዕስ ኀደገ ይእቲ ኀብር የሐዕብዎ ዳግመ ወንጹሐ ይከውን ፤

ያ ልብስ ከታጠበ በኋላ ድሩ ንም ማጉንም የቁርበቱን ዕቃ ሁሉ ያች መልክ ብትተው ማለት ለምጺቱ ብትጠፋ ዳግመኛ ይጠቡት፣ ንጹሕም ይሆናል ፤

፶፱፣ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘኀብረ ለምጽ ዘይወፅእ ውስተ ልብስ፣

በልብስ ላይ የሚወጣ የለምጽ ሥርዓቱ ፍርዱ ይህ ነው ፤

እመኒ ዘፀምር ወእመኒ ዘአጌ ወእመኒ ውስተ ስፍሑ ወእመኒ ውስተ ፋእሙ ወእመኒ ውስተ ኵሉ ንዋይ ዘማዕስ በዘያነጽሕዎ ወበዘያረኵስዎ፣

በቀይ ሐር፣ በነጭ ሐር ልብስ በድሩም በማጉም በቁርበቱም ዕቃ ሁሉ ቢሆን ንጹህ ነው፣ ርኩስ ነው በሚሉት ገንዘብ በልብስ ላይ የሚወጣ የለምጽ ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው፣ (ሐተታ) በልብሱ ላይ ለምጽ በምን ምክንያት ይወጣበታል ቢሉ ከሕግ ከሥርዓት ቢወጡ ኃጢአት ቢሠሩ ነው ፤ አንድም ለቤተ እግዚአብሔር የሚሆን ካባ ላንቃ መጎናጸፊያ እንሰጣለን ብለው ተስለው ቢያስቀሩ በለበሱት ልብስ ላይ ይወጣበታል ፤ በየ ዝያን ልብስ እንደወጣ ይህስ ይሁን በጀንዲው በቁርበቱ በምን ምክንያት ይወጣበታል? ቢሉ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሆን ምንጣፍ ስጋጃ ሰርፍ ወላንሳ እንሰጣለን ብለው ተስለው ቢያስቀሩ በምንጣፋቸው ያወጣል፤ አንድም በምንጣፋቸው ሁነው የማይገባ ሥራ ቢሠሩ ይወጣበታል።

## ምዕራፍ ፲፬

### ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘለምጽ በዕለተ ነጽሐ የሐውር ኀበ ካህን፣



ለምጽ ለወጣበት ሰው ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው፣ ከለምጹ በዳነበት ቀን ወደ ሊቀ ካህናቱ ይሂድ ፤

፫፤ ወይወፅእ ካህን አፍአ እምትዕይንት ወይሬእዮ ካህን ወናሁ ኀደኀ ኀብረ ለምጹ ለዘለምጽ፣

ካህኑም ከከተማ ወደውጭ ወጥቶ ለምጽ የወጣበትን ሰው የለምጹ መልክ ለቅቆ ታልና ከለምጹ ስለዳነ መር ምሮ ይየው ፤

፬፤ ወሐዊሮ ኀቤሁ ካህን ያመጽእ ውእቱ ዘነጽሐ ክልኤተ ደዋርሀ ሕያዋተ ወንጹሐተ ወዕፀ ጽሕድ ወለየ ክዑበ ወቈጽለ ሁስጹ ፣

(ወሐዊሮ እምኀበ ካህን ያመ ጽእ ሲል ነው) ፣ ከለምጹ የዳነው ሰው ከሊቀ ካህናቱ ተሰናብቶ ሂዶ ሽልምልም የሆኑ ሁለት ዶሮዎች የጥድ እንጨት ከነቅርንጫፉ የቀይ ሐር ጉንጉን አውባን ቅጠል (አሽክት) ይህን ሁሉ ያምጣ ፤

፭፤ ወይኤዝዝ ካህን ይጥብሕዋ ለአሐቲ ዶርሆ ውስተ ማይ ጥዑም ውስተ ንዋየ ልሕኵት ፣

ካህኑም ከሁለቱ ዶሮዎች አን ዲቱን አርደው ደሟን ተቀብ ለው ጥሩ ውሃ ካለበት ሸክላ ይጨምሩት ዘንድ ይዘዝ፤

፮፤ ወይነሥኦ ካህን ለካልዕት ዶርሆ እንተ ሕያውት ወለዕፀ ጽሕድ ወለለይ ክዑብ ወለቈጽለ ሁስጹ ወይጠምዖሙ በደማ ለእንታክቲ ዶርሆ እንተ ጠብሕዋ ውስተ ማይ ጥዑም ፣

ካህኑም ያልታረደችውን ሁለ ተኛዪቱን ዶሮ ይዞ የጥዱን እንጨት የሐሩን ጉንጉን የአሽክቱን ቅጠል አምጥቶ የታረደችው ዶሮ ደም ካለበት ጥሩ ውሃ ነክሮ፤

፯፤ ወይነዝኆ ስብዓ ለውእቱ ዘነጽሐ እምለምጽ ወንጹሐ ይከውን፣

ከለምጹ የነጻውን ሰው ሰባት ጊዜ ይርጨው ንጹሕም ይሆናል፣ (ሐተታ) ሰባት ፍጹም ነውና ፈጽሞ እንደነጻ ለማጠየቅ፤ አንድም በፍጹም ትጋት ኃጢአት እንዲሠረይ ለማጠየቅ፤

ወይፌንዋ እንተ ሕያውት ውስተ ገዳም ፣

ያልታረደችውንም ዶሮ ወደ ምድረ በዳ ይስደዳት ፤

፰፤ ወየሐፅብ አልባሲሁ ውእቱ ዘነፅሐ ወይትላፀይ ኵሉ ስእርቶ

www.ethiopianorthodox.org

ወይትሐፀብ በማይ ወንጹሐ ይከውን፤

ከለምጹ የነጻውም ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ፀጉሩንም ይላጭ፤ በውሀ ይታጠብ ፤ ንጹሕም ይሆናል ፤

ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት ወይነብር አፍአ እምቤቱ ሰቡዓ መዋዕለ ፤

ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ ገብቶ ሰባት ቀን ከቤቱ በውጭ ይቀመጥ፤

፱፤ ወበሳብዕት ዕለት ይትላፀይ ኵሎ ስዕርተ ርዕሱ ወጽሕሞ ወሐንገዞ፤

በሰባተኛው ቀን የራስ ጠጉሩን ጽሕሙን ቅንድቡን ፤ አንድም ብብቱን፤

ወኵሎ ስዕርቶ ይትላፀይ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወሥጋሁኒ የሐፅብ በማይ ወንጹሐ ይከውን ፤

ነሣሣለትና ጠቅሎ አመጣው፤ መላ ጠጕሩን ይላጭ፤ ልብሱንም ገላውንም በውሃ ይጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል፤ (ሐተታ) ሰባት ቀን ከቤቱ በውጭ ይቆይ ብሎ ነበርና ንጹሕ ሆኖ ወደ ቤቱ ይግባ ለማለት ደግሞታል፤ ይህም ለጊዜው ሥርዓት ሆኖ ተሠርቷል፤ ለኋላው ምሳሌ ነው፤ ለምጻሙ ሰው የአዳም፤ ለምጽ የፍዳ የመርገም፤ ለምጻም ከሰው መለየቱ አዳም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ከማኅበረ መላእክት ተለይቶ ለመኖሩ ምሳሌ፤ የታረደችው ዶሮ የትስብእት፤ ያልታረደችው የመለኮት፤ አንዲቱ ተሠውታ አንዲቱ መዳኗ ጌታም በሰውነቱ ሐማሚ መዋቲ ሲሆን በመለኮቱ ሕማም ሞት የለበትምና ፤

፲፤ ወበሳምንት ዕለት ያመጽእ ክልኤተ አባግዐ ንጹሐነ እለ ዓመት ሎሙ ወዓዲ አሐደ በግዐ ንጹሐ ዘዓመት፤

በስምንተኛዪቱ ቀን ነውር የሌለባቸውን ዓመት የሆናቸውን ሁለት በጎች ያምጣ፤ ዳግመኛ ነውር የሌለበትን ዓመት የሆነውን አንድ በግ ያምጣ፤

ወሠለስተ መስፈርተ ስንዳሌ ለመሥዋዕት ዘልውስ በቅብዕ ወአሐደ ግምዔ ቅብዕ ፤

በዘይት የተለወሰ ሦስት ላዳን ስንዴ ዳቦና አንድ ማሰሮ ዘይት ለመሥዋዕት ያምጣ ፤



፲፩፤ ወያቀውሞ ካህን ለውእቱ ብእሲ ዘነጽሐ ወዘንቱኒ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፤

ሲናገረው መጥቶ ነበርና ዝንቱ ብሎ አጸፈ፤ ካህኑም ከለምጹ የዳነውን ሰው በደብተራ ኦሪት ደጅ ያቁመው፤ ቅድመ እግዚአብሔር አለ፤ እግዚአብሔር አይለየውምና ፤

፲፪፤ ወይነሥእ ካህን አሐደ በግዐ ወያበውዖ በእንተ ኀስሐ ወለውእቱኒ ግምዔ ቅብዕ ወይፌልጦ ፍልጣነ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ካህኑ ከሦስቱ በጎች አንዱን የንስሐ መሥዋዕት ሊሆን ያቅርበው፤ ዘይት ያለበትንም ማሰሮ በጉን ጨምሮ በእግዚአብሔር ፊት ለይቶ ያቅርባቸው ፤

፲፫፤ ወይጠብሕዎ ለውእቱ በግዕ ውስተ መካን ኀበ ይጠብሑ ዘመሥዋዕት ወዘበእንተ ኃጢአትኒ በመካን ቅዱስ፤

ውስተ መካንና በመካን ቅዱስ አንድ ወገን፤ የቀረበውንም በግ የንስሐ መሥዋዕት ሊሆን መሥዋዕተ ኃጢአቱን፤ መሥዋዕተ መድኃኒቱን በሚሠዉበት በከበረው ቦታ ይሠዉት፤ (ሐተታ) የሚሠዉዋው ሊቀ ካህናቱ አይደለም፤ ስለ ምን ይጠብሕዎ አለ ቢሉ በማስተንተን በሥራ የሚረዱት አሉና፤

እስመ ዘበእንተ ኃጢአት ከመ ዘንስሐ ውእቱ ለካህን ቅዱስ ለቅዱሳን ውእቱ ፤

(እስመ ዘንስሐ ከመ ዘበእንተ ኃጢአት ውእቱ ሲል ነው)፤ የንስሐው መሥዋዕት እንደ ኃጢአቱ መሥዋዕት ነውና ጢሶለት የቀረው ለካህኑ ይሁን፤ የከበረው መሥዋዕት ለከበሩ ለካህናት ነውና ፤

፲፬፤ ወይነሥእ ካህን እምደም ዘንስሐ ወይወዲ ውስተ ከተማ ዕዝኑ እንተ የማን ለዘነጽሐ ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን፤

ካህኑም ለንስሐ ከተሠዋው በግ ደም ዘግኖ ከለምጹ የነጻውን ሰው ቀኝ ጆሮውን፤ ቀኝ እጁን፤ ቀኝ እግሩን ጫፍ ጫፉን ይቅባው ፤

፲፭፤ ወይነሥእ ካህን እምቅብዕ ዘውስተ ግምዔ ወይሠውጥ ውስተ እዴሁ እንተ ፀጋም ፤

በማሰሮውም ካለው ዘይት ታፍኖ በግራ እጁ ይያዝ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፤ ወይጠምዕ ካህን አፅባዕቶ እንተ የማን ውስተ ውእቱ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ እንተ ፀጋም ወይነዝኅ እምውእቱ ቅብዕ ስብዐ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ካህኑም በግራ እጁ ካለው ዘይት ቀኝ ጣቱን ነክሮ በእግ ዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው ፤

፲፯፤ ወለዘተርፈሰ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ እንተ የማን ለውእቱ ዘነጽሐ ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን በመካነ ደም ዘነዝኃ፤

የቀረውን በእጁ ያለውን ዘይት ግን የነጻውን የዚያን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ በቀባበት በደሙ ቦታ የቀኝ እጁንና የቀኝ እግሩን ጫፍ ይቅባው ኦለ ፤ ግብርህ የማናዊ ነው ሲል፤ አንድም ከፀጋማዊ ግብር ወደ የማናዊ ግብር ተመለስህ ሲል ነው፤

፲፰፤ ወለዘተርፈ ቅብዕ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ካህን ላዕለ ርእሱ ለዘነጽሐ ወያስተሠሪ ሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ቀኝ ቀኝ አካሉን ተቀብቶለት የተረፈውንም ዘይት ካህኑ ከለምጹ በነጻው ሰው ራስ ላይ ያፍስሰው፤ ኃጢአቱንም በእግዚ አብሔር ፊት ያስተሥርይለት፤

፲፱፤ ወይገብር ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሠሪ ሎቱ ለውእቱ ዘነጽሐ በእንተ ኃጢአቱ፤

‹‹ዘበእንተ ኃጢአትና በዘነጽሐ በእንተ ኃጢአቱ›› አንድ ወገን፤ የኃጢአቱንም መሥዋዕት ሠውቶ ከለምጹ የነጻውን ሰው ኃጢአቱን ካህኑ ያስተሥር ይለት፤

ወእምዝ ይጠብሕ ካህን ዘመ ሥዋዕት ፤

መሥዋዕተ ኃጢአቱን ከሠዋ በኋላም የድኅነቱን መሥ ዋዕት ይሠዋ ፤

፳፤ ወያበውእ ዘመሥዋዕትኒ ወዘቍርባንኒ ላዕለ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሐር ወያስተሠሪ ሎቱ ወይነጽሕ ፤

የንስሐውንና የኃጢአቱን መሥ ዋዕት (ያበውእ ብሎ ነበርና) መሥዋዕተ መድኃኒቱንም በእግዚአብሔር ፊት በመሠዊ ያው አቅርቦ ኃጢአቱን ያስተ ሥርይለት፤ እርሱም ይነጻል፤

፳፩፤ ወእመሰ ነዳይ ውእቱ ወአልቦ ውስተ እዴሁ ያመጽእ ማሕስዓ በግዕ አሐደ ዘይፈልጡ በእንተ ንስሐ በዘያስተሠርዩ ሎቱ ወአሐተ መስፈርተ ሥንዳሌ ዘልውስ በቅብዕ ለመሥዋዕት ወአሐደ ግምዔ ቅብዕ፤

ድሀ ቢሆን በእጁ ገንዘብ ባይኖር ግን ኃጢአቱን በሚያ ተሠርዩለት ገንዘብ ስለንስሐ አንድ የበግ ጠቦት በዘይት የተለወሰ አንድ ላዳን ስንዴ ዳቦ አንድ ማሰሮ ዘይት ያምጣ፤



፳፪፤ ወክልኤተ ማዕነቀ አው ክልኤተ እጕለ ርግብ ዘቦቱ ውስተ እዴሁ ወትከውን አሐቲ ዘበእንተ ኃጢአት ወአሐቲ ለመሥዋዕት ፤

ሁለት ዋኖስ (ወይም) በእጁ ካለው ሁለት የርግብ ግልገል ያምጣ ፤ አንዲቱ ለመሥዋ ዕተ ኃጢአት፤ አንዲቱ ለመ ሥዋዕተ መድኃኒት ትሁን ፤

፳፫፤ ወያበውኦን በሳምንት ዕለት በዘያነጽሕዎ ወይወስድ ኀበ ካህን ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ከኃጢአት በሚያነጹት ገንዘብ በስምንተኛው ቀን ያቅርባ ቸው፤ ካህኑ ወደ አለበት ወደ ደብተራ ኦሪት ደጅ ይውሰድ፤ ቅድመ እግዚአብሔር ማለቱ ሊቀ ካህናቱንም ደብተራ ኦሪ ትንም እግዚአብሔር አይለያ ቸውምና ለሁሉም የተመቸ፤

፳፬፤ ወይነሥእ ካህን ለውእቱ በግዕ ዘንስሐ ወለውእቱ ግምዔ ዘቅብዕ ወያነብሮ ለቍርባን ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ካህኑም ለንስሐ የገባውን በግና የማሰሮውን ዘይት ተቀ ብሎ በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያ ሊሆን ቍርባን አድርጎ ያቅርበው ፤

፳፭፤ ወይጠብሖ ለውእቱ በግዕ ዘንስሐ ፤

የንስሐ መሥዋዕት ሊሆን የቀረበውንም በግ ተቀብሎ ይሠዋው ፤

ወይነሥእ እምደሙ ለዘንስሐ ወይወዲ ላዕለ ከተማ ዕዝኑ ዘየማን ወላዕለ ከተማ እዴሁ እንተ የማን ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን ለዘነጽሐ ፤

ካህኑም ለንስሐ መሥዋዕት ሊሆን ከቀረበው በግ ደም ተቀብሎ የነጻውን ሰው ቀኝ ቀኝ አካሉን ይቅባው ፤

፳፮፤ ወይሠውጥ ካህን እምውእቱ ቅብዕ ውስተ እዴሁ እንተ ፀጋም፤

ከማሰሮውም ዘይት በግራ እጁ ያስይዘው ፤

፳፯፤ ወይነዝኅ በአፅባዕቱ እንተ የማን እምውእቱ ቅብዕ ዘውስተ እዴሁ እንተ ፀጋም ስብዐ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

www.ethiopianorthodox.org

በግራ እጁ ካለው ከዚያ ዘይት ካህኑ በቀኝ እጁ ነክሮ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው ፤

፳፰፤ ወእምውእቱኒ ቅብዕ ዘሀሎ ውስተ እዴሁ ይወዲ ካህን ላዕለ ከተማ ዕገሁ ዘየማን ለውእቱ ዘነጽሐ ወላዕለ ከተማ እዴሁ ዘየማን ወላዕለ ከተማ እግሩ እንተ የማን በመካነ ደመ ለዘነጽሐ ፤

በእጁ ካለው ከዚያ ዘይትም ካህኑ አምጥቶ ለውእቱ ዘነጽሐና ለዘነጽሐ አንድ ወገን፤ የነጻውን ሰው ደሙን በቀባበት ቦታ የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፤ የቀኝ እጁን ጫፍ፤ የቀኝ እግሩን ጫፍ ይቅባው፤

፳፱፤ ወለዘተርፈሰ ቅብዕ እምዘሀ ለወ ውስተ እዴሁ ይወድዮ ካህን ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ዘነጽሐ ወያስተሥሪ ሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር፤

ቀብቶለት የቀረውን በእጁ ያለውን ዘይት ግን ካህኑ የነጻውን ሰው ራሱን ይቅባው፤ በእግዚአብሔርም ፊት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ፤

፴፤ ወይገብር አሐተ እምውእቶን ማዕነቅ ወእመኒ እምእጕለ ርግብ እምዘቦቱ ውስተ እዴሁ ፤

ከነዚያ ዋኖሶች በእጁ ካለ ከርግቦችም ወገን ቢሆን አንዲቱን ይሠዋ ፤

፴፩፤አሐተ በእንተ ኃጢአት ወአሐተ ለቍርባን ምስለ መሥዋዕት፤

አንዲቱን ስለ ኃጢአት አንዲቱን ለቍርባን ከመሥዋዕት ጋራ ይሠዋ፤

ወያስተሥሪ ሎቱ ለውእቱ ዘነጽሐ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ለዚያ ለነጻው ሰው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ፤

፴፪፤ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘወፅአ ኅብረ ለምጽ ላዕሌሁ፤

የለምጽ መልክ በላዩ ለወጣበት ሰው ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው፤

ወለዘአልቦኒ ውስተ እዴሁ በዘያ ነጽሕዎ ፤

ንጹሕ በሚያደርጉት ገንዘብ በእጁ ገንዘብ የሌለውም ሰው ሕጉ ይህ ነው ፤



ጉባዔ ፤

፴፫፤ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን እንዲህ ብሎ ነገራቸው፤

፴፬፤ እምከመ ቦእክሙ ውስተ ምድረ ከነዓን እንተ እሁበክሙ አነ ትረስዋ እፌኑ ትእምርተ ለምጽ ውስተ አብያቲሃ ለይእቲ ምድር እንተ ታጠርይዋ ፤

ትወርሷት ዘንድ እኔ ወደምሰጣችሁ ወደ ከነዓን ምድር በገባችሁም ጊዜ በምትገዟት ገንዘብ በምታደርጓት በዚያች ምድር ባሉ ቤቶች (ወገኖች) የለምጽ ምልክት አመጣለሁ፤

፴፭፤ ወእመቦ ዘወፅአ ውስተ ቤቱ ይንግር ለካህን ወይብል ከመ ትእምርተ ለምፅ ርኢኩ ውስተ ቤትየ ፤

በቤቱም ለምጽ የወጣበት ሰው ቢኖር በቤቴ የለምጽ ምልክት አየሁ ብሎ ለካህኑ ይንገር ፤

፴፮፤ ወየአዝዝ ካህን ያወፅኡ ንዋዮ ለውእቱ ቤት እንበለ ይባእ ካህን ለርእዮቱ ለውእቱ ቤት ወለይእቲ ትእምርተ ለምጽ፤

ሊቀ ካህናቱ ያችን የለምጽ ምልክትና ለምጽ የታየበትን ቤት ከማየቱ አስቀድሞ ለማየት ሳይገባ ከቤት ያለውን ዕቃ ያወጡ ዘንድ አውጡ ብሎ ይዘዝ፤

ወኢያረኩስ ኵሎ ዘሀሎ ውስተ ውእቱ ቤት ፤

ሊቀ ካህናቱ (ሳይገባ) ገብቶ ሳያየው በውስጡ ያለውን ሁሉ አያረክሰውምና (ኢይረኵስ ኵሉ ይላል) ፤ በቤት ያለው ሁሉ ርኩስ አይባልምና ፤

፴፯፤ ወእምዝ ይበውእ ካህን ወይሬእዮ ለውእቱ ቤት ወለይእቲ ትእምርተ ለምጽ፤

ዕቃው ከወጣ በኋላ ካህኑ ገብቶ ያን ቤት ይየው፤ ያችንም ለምጽ ምልክት (ይርአያ) ይያት፤

ወናሁ ሀለወት ይእቲ ትእምርተ ለምጽ ውስተ ዓረፍቱ ለውእቱ ቤት ወእመኒ ታሕመለምል ወእመኒ ታቅየሐይሕ ወርእየታኒ የአኪ እምዓረፍት ፤

በቤቱ ግድግዳ የለምጽ ምልክት ብትኖር ብትነጣም ብትቀላም መልኳም በግድግዳው ላይ ቢሰፋ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፰፤ ወወፂአ ካህን እምውእቱ ቤት ኀበ ኆኅት ያጽንሖ ለውእቱ ቤት ሰቡዓ ዕለተ ፤

ካህኑም ከገባበት ቤት በገባበት ደጃፍ ወጥቶ ሰባት ቀን ያቆየው ፤

፴፱፤ ወይመጽእ በሳብዕት ዕለት ወይሬእዮ ለውእቱ ቤት ወናሁ ተዘርወት ይእቲ ኀብር ውስተ ዓረፍቱ ለውእቱ ቤት፤

ካህኑም በሰባተኛው ቀን መጥቶ ለምጽ የወጣበትን ቤት መርምሮ ዳግመኛ ይየውና በቤቱ ግድግዳ የወጣችውም ለምጽ ብትሰፋ ፤

፵፤ ወይኤዝዝ ካህን ያውፅኡ ዕበኒሁ ዘሀለወት ቦቱ ይእቲ ትእምርተ ለምጽ ወያውፅእዎ አፍኣ እምይእቲ ሀገር ውስተ መካን ርኩስ፤

ካህኑም ያች የለምጽ ምልክት ያለችበትን እንጨት ቢሆን መዝዘው፤ ደንጊያ ቢሆን ፈንቅለው ከከተማው ውጭ አውጥተው ይጥሉት ዘንድ ይዘዝ፤

፵፩፤ ወያመጽኡ ካልዓ ዕብነ ውቁረ ወይወድዩ ውስተ መካኖን ለውእቶን ዕበን ፤

ሌላ የለዘበ ደንጊያ አምጥተው፤ አውጥተው በጣሉት ደንጊያ ቦታ ይተኩበት ፤

፵፪፤ ወያመጽኡ ካልዓ መሬተ ወይመርግዎ ለውእቱ ቤት ፤

ደንጊያው ሲፈነቀል ጭቃው አይቀርምና ሌላ ጭቃ አቡክተው ይምረጉት ፤

፵፫፤ ወእመሰ ገብአት ይእቲ ኀብር ወወፅአት ውስተ ውእቱ ቤት እምድኅረ አውፅኡ ዕበኒሁ፤

ደንጊያውን አውጥተው ከጣሉት በኋላ ያች የለምጽ መልክ ዳግመኛ በቤቱ ብትወጣ፤

ወእምድኅረ ገሠሥዎ ለውእቱ ቤት ወእምድኅረ መረግዎ ይበውእ ካህን ወይሬእያ ፤

(ገሠሥዎና መረግዎ አንድ ወገን)፤ ሠርተው ከመረጉት በኋላ ካህኑ ገብቶ ይያት ፤

፵፬፤ ወለእመ ተዘርወት ይእቲ ኀብር ዘውስተ ውእቱ ቤት ለምጽ እንተ ኢትትኃደግ ይእቲ ውስተ ውእቱ ቤት ወርኩስ ውእቱ፤

በዚያ ቤት የወጣችው የለምጽ ምልክት በቤቱ ውስጥ ብትሰፋ የማትለቅ ብትሆን የረከሰ ነውና ፤

፵፭፤ ወይነሥትዎ ለውእቱ ቤት ዕፀዊሁኒ ወዕበኒሁኒ ወኵሎ መርዔቶ ለውእቱ ቤት ይክዕዉ አፍአ እምሀገር ውስተ መካን ርኩስ ፤



የዚያን ቤት ጣራውንም ግድግዳውንም ምርጉንም አፍርሰው ከከተማው ወደ ውጭ አውጥተው በረከሰ ቦታ ይጣሉት፤

፵፮፤ ወዘቦአ ውስተ ውእቱ ቤት በኵሉ መዋዕል እምዘአዕለልዎ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ፤

ርኩስ ብለው ከለዩት በኋላ በዘመኑ ሁሉ ከዚያ ቤት የገባ ሰው እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው፤

፵፯፤ ወዘቤተ ውስተ ውእቱ ቤት የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ወዘበልዓ በውእቱ ቤት የሐፅብ አልባሲሁ ፤

በዚያ ቤት ያደረ ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም ይታጠብ፤ እስከ ማታም የረከሰ ነው፤ ከዚያ ቤት ገብቶ የበላም ሰው ልብሱን ይጠብ ፤

፵፰፤ ወእመሰ መጽአ ካህን ወቦአ ወርእዮ ወናሁ ኢተዘርወት ይእቲ ኀብር ውስተ ውእቱ ቤት ፤

ካህኑ ገብቶ አይቶ በቤቱ የወጣችው ያች የለምጽ መልክ ባትሰፋ፤

እምድኅረ መረግዎ ያነጽሖ ካህን ለውእቱ ቤት እስመ ኀደገቶ ይእቲ ኀብር ፤

የወጣችው ለምጽ ትታዋለችና ስለተወችው ያን ቤት ካህኑ ያንጻው ማለት ንጹሕ ነህ ይበለው ፤

፵፱፤ ወይነሥእ ካህን በዘያነጽሖ ለውእቱ ቤት ክልኤተ ደዋርሃ ወዕፀ ጽሕድ ወለየ ክዑበ ወቈጽለ ሁስጱ ፤

ካህኑ ያን ቤት በሚያነጻው ገንዘብ ሁለት ዶሮዎች፤ የጥድ እንጨት፤ እጥፍ ሆኖ የተሠራ ቀይ ሐር፤ የአሽክት ቅጠል ያምጣ፤

፶፤ ወይጠብሕዋ ለአሐቲ ዶርሆ ውስተ ንዋየ ልሕኵት ውስተ ማይ ጥዑም ፤

አንዲቱን ዶሮ አርደው ደሟን በሸክላ ካለው ጥሩ ውሃ ይጨምሩት ፤

፶፩፤ ወይነሥእ ዝክተ ዕፀ ጽሕድ ወለየ ክዑበ ወቈጽለ ሁስጱ ወዶርሆ እንተ ሕያውት ወይጠምዖሙ ውስተ ውእቱ ደመ ዶርሆ እንተ ጠብሕዋ ውስተ ማይ ጥዑም ወይነዝኆ ለውእቱ ቤት ስብዓ ፤

ካህኑ የጥዱን እንጨት የቀዩን ሐር አሽክቱን ያልተሠዋችውን ዶሮ አምጥቶ በጥሩ ውሃ አጠገብ በተሠዋችው ዶሮ ደም ነክሮ ያንን ቤት ሰባት ጊዜ ይርጨው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፶፬፤ ወያነጽሖ ካህን ለውእቱ ቤት በደማ ለይእቲ ዖርሆ ወበማይ ጥዑም ወበዖርሆ እንተ ሕያውት ወበዕፀ ጽሕድ ወበቆጽለ ሁስጱ ወበለይ ክዑብ ፤

ካህኑ ያን ቤት በዚህ ሁሉ ያንጻው ፤

፶፭፤ ወይፌንዋ ለይእቲ ዖርሆ እንተ ሕያውት አፍኣ እምሀገር ወያግእዛ ውስተ ገዳም ወያስተሠሪ በእንተ ውእቱ ቤት ወይነጽሕ ውእቱ ቤት፤

ያልተሠዋችውን ዖሮ ከከተማ ወደውጭ ሰዶ በምድረ በዳ ነፃ ያውጣት ፤ ያንንም ቤት ከለምጹ ያንጻው ንጹሕም ይሆናል፤

፶፮፤ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለኵሉ ትእምርተ ለምጽ ወኀብሩ ለዘለምጽ፤

የለምጽ ምልክት የለምጽ መልክ የወጣበትም ሰው ሥርዓቱ ይህ ሲናገረው የመጣው ነው፤

ለልብስኒ ወለቤትኒ ወለትእምርተርምየትኒ ወዘኅንብርብሬኒ በዘተአምሩ ፤

ለምጽ የወጣበት የልብስም የቤትም የእትራትና የቋቍቻ ምልክት በምታውቁ ገንዘብ ይህ ነው ፤

፶፯፤ እመ ርኩስ ውእቱ ወእመ ንጹሕ ውእቱ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘለምጽ ፤

ንጹሕም ቢሆን፤ ርኩስም ቢሆን የለምጽ ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው ፤ ቢርቀው ደግሞታል ፤ የልብስን ሐተታ ተናግረናል፤ በቤቱ ላይ ለምጽ በምን ምክንያት ይወጣበታል ቢሉ ቤቱን እንሰጣለን ብለው ተስለው ቢያስቀሩ፤ አንድም የማይገባ ሥራ ቢሠሩበት ይወጣበታል ፤ በማናቸውም ሰው ቤት ለምጽ ቢወጣ ሊቀ ካህናቱ ገብቶ አይቶ ሰባት ቀን ይቆይ ይላል፤ ሁለተኛ በስምንተኛው ቀን አይቶ ደኅና ቢሆን ግቡበት ይላቸዋል፤ ለምጹ ባይጠፋ ዳግመኛ ሰባት ቀን ያቆየዋል፤ በሁለት ሰባት ባይጠፋ ደንጊያዩቱን አውጥታችሁ ሌላ ደንጊያ ተክታችሁ ምረጉት ይላቸዋል፤ ዳግመኛ ቢወጣ ቤቱን ያፈርሱታል፤ ለጊዜው ሥርዓት ሁኖ ተሠርቷል፤ ለዛሬው ግን አምሳል ሊሆን ተጽፏል፤ ቤት የቤተ ማኅበር አምሳል፤ ለምጽ ቢወጣበት ሰባት ቀን ያቆየው ማለቱ አበ ማኅበሩ ከሕግ ከሥርዓት ወጥቶ ቢበድል ይምከሩት ያስተምሩት ሲል ነው፤ ደኅና ቢሆን ይግቡበት አለ፤ ቢመለስ አይለዩት ሲል፤ ባይጠፋ ሰባት ቀን ያቆዩት ማለቱ ባይመለስ ዳግመኛ ይምከሩት ያስተምሩት ሲል፤ ባይጠፋ እሱን አስወጥተው ሌላ ደንጊያ ያግቡበት አለ፤ አልመለስም ቢል እሱን ሽረው ሌላ ይሹሙ ሲል፤ ዳግመኛ ቢወጣበት ቤቱን ያፍርሱት ማለቱ ዳግመኛ የተሾመው ሰው ከሥርዓት ወጥቶ ቢበድል እሱንም ይሻሩት ከአንድነት ይለዩት ሲል ነው።

## ምዕራፍ ፲፭

፩፤ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን እንዘ ይብል፤

እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን እንዲህ ብሎ ነገራቸው፤

፪፤ ንግርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበልዎሙ ብእሲ ብእሲ እመቦ ዘይትከዓዎ ዘርኡ እምነፍስቱ በእንተ ውእቱ ዘይትከዓዎ ርኩስ ውእቱ፤

አንዱም አንዱም ሰው ከአካሉ ዘር የሚፈሰው ቢኖር ስለሚፈስሰው ዘር ርኩስ ነው ብላችሁ ለእስራኤል ልጆች ንገሯቸው፤

፫፤ ወዝንቱ ውእቱ ሕገ ርኩሱ ለዘይትከዓዎ ዘርኡ እምነፍስቱ፤

ከአካሉ ዘር የሚፈሰውም ሰው የርኵሰቱ (የኃጢአቱ) ሥርዓት ይህ ነው፤

ወነበረ ከማሁ ውስተ ነፍስቱ ዘይትከዓዎ ውእቱ ርኩስ ዘላዕሌሁ ኵሉ መዋዕለ ዘነበረ እንዘ ይትከዓዎ እምነፍስቱ ውእቱ ዘይትከዓዎ ይረኵስ፤

በኖረበት ዘመን ሁሉ ዘሩ ከአካሉ ሲፈስ የኖረ ሰው ከአካሉ የሚፈሰው ዘር ራሱንም ሌላውንም ያሳድፈዋል፤

፬፤ ወኵሉ ዓራት ዘሰከበ ላዕሌሁ ርኩስ ውእቱ ወኵሉ ንዋይ ዘነበረ ላዕሌሁ ይረኵስ፤

የተኛበት አልጋ የረከሰ ነው፤ የተቀመጠበትም ዕቃ ሁሉ ይረክሳል ማለት ወንበሩ፤ ምንጣፉ ሁሉ ርኩስ ይባላል፤

፭፤ ወብእሲኒ ዘገሠሠ ዓራቶ ይሕፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ፤

አልጋውን የዳሰሰ ሰውም ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስም የረከሰ ነው፤



www.ethiopianorthodox.org

፮፤ ወዘነበረኒ ላዕለ ንዋይ ዘው
እቱ ነበረ ላዕሌሁ ይሕፅብ
አልባሲሁ ወይትሐፀብ በማይ
ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፡

እሱ በተቀመጠበት ወንበር
ምንጣፍ የተቀመጠ ሰውም
ልብሱን ይጠብ፣ በውሀም
ይታጠብ፣ እስከ ማታ ድረ
ስም የረከሰ ነው፤

፯፤ ወዘገሠሦኒ ለውእቱ ዘይትከ
አዎ ዘርኡ ይሕፅብ አልባሲሁ
ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወር
ኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፡

ዘሩ የሚፈሰውን ሰው የዳሰ
ሰውም ሰው ልብሱን ይጠብ፣
ሰውነቱንም በውሀ ይታጠብ፣
እስከ ማታ ድረስም የረከሰ
ነው፤

፰፤ ወእመ ወረቀ ዲበ ዘንጹሕ
ይሕፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ
በማይ ወርኵስ ውእቱ እስከ
ሠርክ፡

በንጹሕ ሰው ላይ ምራቁን
እንትፍ ቢል፤ አንድም ምራ
ቁን በተፋበት ቦታ ሰው
ቢቀመጥ ከዚያ ቦታ የተቀ
መጠ ሰው፤ አንድም የተተ
ፋበት ሰው፤ ልብሱን ይጠብ፣
በውሀም ይታጠብ፣ እስከ
ማታም ድረስ የረከሰ ነው፤

፱፤ ወኵሉ ሕንባላት ዘላዕሌሁ
ነበረ ርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፡

የተቀመጠበትም ኰርቻ፤ አን
ድም መጫኛ መደላድል
ሁሉ እስከ ማታ ድረስ የረ
ከሰ ነው፤

፲፤ ወኵሉ ዘገሠሠ እምኵሉ
ዘነበረ ላዕሌሁ ርኵስ ውእቱ እስከ
ሠርክ፡

የተቀመጠበትንም ሁሉ የነካ
ሰው እስከ ማታ ድረስ የረ
ከሰ ነው፤

ወዘርእዮኒ የሐፀብ አልባሲሁ ወይ
ትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኵስ
ውእቱ እስከ ሠርክ፡

ዳስሶ ያየውም ሰው ልብሱን
ይጠብ፣ ገላውንም በውሀ ይታ
ጠብ ፣ እስከ ማታ ድረስም
የረከሰ ነው፤

፲፩፤ ወዘገሠሦኒ ለዘገሠሦ ለው
እቱ ዘይትከዓዎ ዘርኡ እንበለ
ይትሐፀብ እደዊሁ ይሕፅብ አል
ባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ
ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፤

እጁን ሳይታጠብ ዘሩ የሚ
ፈሰውን ሰው የነካውን የነካ
ሰው እጁን ይታጠብ፣ ልብሱ
ንም ይጠብ፣ ሰውነቱንም



በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ማታ
ድረስም የረከሰ ነው፤

፲፪፤ ወለኵሉ ነዋየ ልሕኵት
ዘውእቱ ገሠሦ ይሰብርዎ፤

እሱ የነካውን የሸክላ ዕቃ
ሁሉ ይሰበሩት ፤

ወለንዋየ ዕፀሰ ይሕፅብዎ በማይ
ወንጹሐ ይከውን፡

ሰደቃ ገበታ ቢሆን ግን በውሀ
ይጠቡት፣ ንጹሕም ይሆናል፤

፲፫፤ ወእመሰ ኀደጎ ውእቱ ዘይት
ከዓዎ ይኌልቁ ሎቱ ሰቡዐ መዋ
ዕለ ለአንጽሖቱ፤

የሚፈሰው ዘሩ ቢተወው ግን
እሱን ለማንጻት ሰባት ቀን
ይቁጠሩለት ፤

ወየሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ
ሥጋሁ በማይ ንጹሕ ወንጹሐ
ይከውን፡

ልብሱን ይጠብ፣ ሰውነቱንም
በንጹሕ ውሃ ይታጠብ፣ ንጹ
ሕም ይሆናል፤

፲፬ ወበሳምንት ዕለት ይነሥእ
ሎቱ ክልኤተ ማዕነቀ አው
ክልኤተ እጕለ ርግብ ወያ
መጽእን ቅድመ እግዚአብሔር
ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል
ወይሁቦ ለካህን፡

በስምንተኛው ቀን ሁለት
ዋኖስ ወይም ሁለት ርግብ
አምጥቶ ልዩ በሆነች በደ
ብተራ ኦሪት ደጃፍ በእግዚ
አብሔር ፊት ለካህኑ ይስ
ጠው፤

፲፭፤ ወይገብር ካህን አሐተ በእ
ንተ ኃጢአት ወአሐተ ለመሥ
ዋዕት ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን
ቅድመ እግዚአሔር በእንተ ኵሉ
ዘይትከዓዎ፤

ካህኑም አንዲቱን ስለኃጢ
አት ፈንታ፣ አንዲቱን ስለ
ድኅነት መሥዋዕት ይሠዋና
ዘሩ ስለሚፈሰው ሰው በእግዚ
አብሔር ፊት ያስተሥርይ
ለት፤

፲፮፤ ወእመቦ ብእሲ ዘሰከበ ምስለ
ብእሲት ይትሐፀብ በማይ ኵሎ
ሥጋሁ ወስዑብ ውእቱ እስከ ሠርክ፡

ከሴት ጋር ያደረ ሰውም
ቢኖር ሰውነቱን ሁሉ በውሃ
ይታጠብ፣ እስከ ማታ ድረ
ስም ኃጢአተኛ ነው፤

፲፯፤ ወኵሉ ልብስ ወኵሉ ማዕስ
ዘበጽሐ ላዕሌሁ ዝኤት የሐፅብዎ

www.ethiopianorthodox.org

በማይ ወርኊስ ውእቱ እስከ ሠርክ፤

(ላዕሌሁ ለልብስ ለማዕስ ነው)፣ ዝኔት የፈሰሰበትን ልብስ ቁርበት ሁሉ በውሀ ይጠቡት፣ እስከ ማታ ድረስም የረከሰ ነው፣ ሐተታ ደራርበው ይለ ብሳሉ፣ ደራርበው ያነጥፋሉና ኵሉ በማለት ተናገረው፤

፲፰፤ ወብእሲትኒ ለእመ ሰከበት ምስለ ብእሲ ትትሐፀብ በማይ ወር ኵስት ይእቲ እስከ ሠርክ፣

ሴትም ከወንድ ጋር ብታድር በውሀ ትታጠብ እስከ ማታ ድረስም የረከሰች ናት፤

፲፱፤ ወእመቦ ብእሲት እንተ ይትከዓዋ ደም ወነበረ እንዘ ይትከ ዓዋ እምነፍስታ ሰቡዕ መዋዕል ውእቱ ዘትክቶሃ፣

ደም የሚፈስሳት ሴት ብትኖር ከሰውነቷ ሲፈስ ቢቆይ የግ ዳጇ ወራት ሰባት ቀን ነው ፤

ወኵሉ ዘገሠሣ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

የነካትም ሰው ሁሉ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው፤

፳፤ ወኵሉ ዘላዕሌሁ ሰከበት እንዘ ትክት ይእቲ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ወኵሉ ዘነበረት ላዕሌሁ ይረኵስ፣

በግዳጇ ሳለች የተኛችበት ሁሉ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው፣ የተቀመጠችበትም ሁሉ ይረክሳል፤

፳፩፤ ወኵሉ ዘገሠሠ ዓራታ ይሕፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

የተኛችበትንም አልጋ የነካ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፣ ገላውንም ይታጠብ፣ እስከ ማታ ድረስም የረከሰ ነው፤

፳፪፤ ወኵሉ ዘገሠሠ እምኵሉ ንዋይ ዘነበረት ላዕሌሁ የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

ከተቀመጠችበትም ዕቃ ላይ የተ ቀመጠ ሰው ሁሉ እስከ ሠርክ ድረስ ርኵስ ነውና ልብሱን ይጠብ፣ ገላውንም ይታጠብ፤

፳፫፤ ወእመኒ እንዘ ሀለወት ላዕለ ዓራታ አው ላዕለ ንዋይ ዘዲቤሁ ትነብር ይእቲ ዘገሠሠ ርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

በአልጋዋ ላይ ሳለችም ቢሆን በምትቀምጥበትም ዕቃ ላይ ሳለች ማለት በወንበር በም ንጣፍ ሳለች፣ የተቀመጠችበ ትን የነካ ሰው እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው፤



፳፬፤ ወዘሰከበ ምስሌሃ ብእሲ ላዕሌሁ ይገብእ ርኵሳ ወርኵሰ ይከውን ሰቡዓ ዕለተ፣

ከግዳጇ ሳትነፃ የደረሰባት ሰውም ኃጢአቷ ወደሱ ይመ ለሳል፣ ሰባት ቀንም የረከሰ ይሆናል፣ (ሐተታ) እርሷን ‹‹ሰቡዕ መዋዕል ውእቱ ዘት ክቶሃ›› ብሏት ነበርና የርሱ ንም እንዲህ አለ፤

ወኵሉ ዓራት እንተ ላዕሌሁ ሰከበ ርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

እርሷ የተኛችበትን አልጋ ርኵስ ነው ብሎ ነበርና እር ሱም የተኛበት አልጋ እስከ ማታ የረከሰ ነው፣ ኃጢአ ታቸው እኩል ሁኗልና፤

፳፭፤ ወእመቦ ብእሲት እንተ ይትከዓዋ ደም ብዙኃ መዋዕለ፣

ብዙ ቀን ደም የሚፈስሳት ሴት ብትኖር ፤

ወፈድፋደ እመዋዕለ ትክቶሃ ወእ መኒ እምድኅረ መዋዕለ ትክቶሃ ተከዕዋ በኵሉ መዋዕል ዘይትከዓዋ ርኵስት ይእቲ በከመ መዋዕለ ትክቶሃ ከማሁ፣

ከመና ከማሁ አንድ ወገን ነው፣ የግዳጇን ወራት ሰባት ቀን ብሎ ነበርና የደሟ መፍሰስ ከሰባት ቀን ቢበዛ

ከግዳጇም ወራት በኋላ በደዌ ምክንያት በየጊዜው ደም የሚ ፈስሳት ሴት ብትኖር እን ደግዳጇ ወራት የረከሰች ናት፤

፳፮፤ ወኵሉ ዓራት ዘላዕሌሁ ሰከበት በኵሉ መዋዕል ዘይትከዓዋ ከመ ዓራተ ትክቶሃ ውእቱ፣

ደም በሚፈስሳት ቀን ሁሉ የተ ኛችበት አልጋ በግዳጇ ወራት እንደምትተኛበት አልጋ ነው፤

ወኵሉ ንዋይ ዘላዕሌሁ ነበረት ርኵስ ውእቱ በከመ ርኵሰ ትክ ቶሃ፣

የተቀመጠችበትም ዕቃ ሁሉ እንደ ግዳጇ ርኵሰት የረከሰ ነው፤

፳፯፤ ወኵሉ ዘገሠሣ ርኵስ ውእቱ ወየሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

የነካትም ሰው ሁሉ የረከሰ ነው፣ ልብሱን ይጠብ፣ ሰውነ ቱንም በውሃ ይታጠብ፣ እስከ ማታም የረከሰ ነው፤

፳፰፤ ወእመሰ ኃደጋ ውእቱ ዘይትከዓዋ ይኌልቁ ላቲ ሰቡዓ መዋዕለ ወእምድኅሬሁ ንጽሕተ ትከውን፣

የሚፈስሳት ደም ቢተዋት ግን ማለት ቢደርቅላት ሰባት ቀን ይቁጠሩላት ማለት ሰባት ቀን

www.ethiopianorthodox.org

ያቆዩዋት፣ ከዚያ በኋላ የነፃች ትሆናለች።

፳፱፤ ወበሳምንት ዕለት ትነሥእ ላቲ ክልኤተ ማዕነቀ አው ክልኤተ እጕለ ርግብ ወታመጽእ ኀበ ካህን ውስተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

በስምንተኛው ቀን ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት ርግብ ይዛ ልዩ ወደሆነች ድንኳን ደጃፍ ወደካህኑ ታምጣ።

፴፤ ወይገብር ካህን አሐተ በእንተ ኃጢአት ወአሐተ ለመሥዋዕት ወያስተሥሪ ላቲ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር በእንተ ውእቱ ርኵስ ዘተከዕዋ፣

ካህኑ አንዲቱን ስለ ኃጢአት ፈንታ አንዲቱን ስለ መሥዋዕተ ድኅነት ይሠዋና ስለፈሰሳት ደም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቷን ያስተሥርይላት።

፴፩፤ ወንጹሐነ ረስይዎሙ ለደቂቀ እስራኤል እምርኵሶሙ ከመ ኢይሙቱ በእንተ ርኵሶሙ ወከመ ኢያርኵሱ ደብተራዮ እንተ ኀቤሆሙ፣

ሲናገረው የመጣውን ጠቅሎ አመጣው፣ ስለሠሩት ኃጢአት እንዳይቀሠፉ በርሳቸው ዘንድ የምትኖር ማደሪያዬ ደብተራ ኦሪትንም እንዳያረክሱ የያዕቆብን ልጆች ከርኵሰታቸው ንጹሐን አድርጓቸው ፤ የታዘዘውን ትእዛዝና የተሠራውን ሕግ ፈጽማችሁ ንጹሐን በሏቸው።

፴፪፤ ዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለዘይት ከዓዎ ዘርኡ፣

ዘር ለሚፈሰው ሰው የተሠራውም ሕግ ይህ ነው፣ ምነው የያዘው ደም ስለሚፈሰው ሰው አልነበረምን ቢሉ ቅጣቱ አንድ ከሆነ ብሎ ፤

ወለዘሰከበ ምስለ ብእሲት ወስዑበ ኮነ ባቲ፣

ከግዳጇ ሳትነፃ ከሴት ጋር ያደረ በርሷም ያደፈ ሰው ሥርዓቱ ይህ ነው ፤ ይህንማ ተናግሮት አልነበረምን ቢሉ ለማጽናት ደገመው።

፴፫፤ ወለዘይትከዓዋኒ ደም በትክቶሃ ወለዘይትከዓምኒ ዘርኡ በመዋዕለ ይትከዓዎሙ ለተባዕትኒ ወለአንስትኒ፣

በመዋዕል ዘይትከዓዎሙ ሲል ነው።

በግዳጇ ደም የሚፈስሳትና ዘሩ የሚፈስሰው ሰው ወንድም ሴትም በሚፈስሳቸው ወራት ‹‹አሐዱ ውእቱ ያለ



በት ነው›› ፣ ፍርዱ አንድ ነው።

ወለብእሲኒ ዘሰከበ ምስለ ብእሲት ትክት፣

ከግዳጇ ካልነጻች ሴት ጋር ያደረ ሰውም ፍርዱ አንድ ነው ማለት ርኩስ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፲፮
## ጉባኤ

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ እምድኅረ ሞቱ ክልኤሆሙ ደቂቀ አሮን በእንተ ዘአምጽኡ እሳተ እምባዕድ ቅድመ እግዚአብሔር፣

እሳት ‹ፍሕም› ከሌላ ቦታ ጭረው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ስላመጡ ሁለቱ የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ ከተቀሠፉ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ተነጋገረው፣ ‹ሐተታ› ማምጣቱ ዕዳ ሁኖ ባቸው አይደለም፣ ከሌላ ቦታ ጭረው ባመጡት ፍህም ስለ አጠኑ ነው እንጂ፣ ከዚህ አስቀድሞ የሞቱበትን ምክን ያት አልተናገረም ነበርና ለመ ናገር ደገመው።

፪፤ ወይቤሎ በሎ ለአሮን እኁከ ኢይባእ በኵሉ ሰዓት ውስተ መቅደስ ውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ቅድመ ምስሐል ዘመልዕልተ ታቦት ወኢይሙት ባሕቱ እምከመ አስተርአይኩ በደመና፣

እኔ በደመና ከታየሁ በኋላ ነው እንጂ ካልታየሁ እንዳ ይቀሠፍ በታቦቱ ላይ ባለ በመግጠሚያው አንጻር ባለ በመጋረጃው ውስጥ ወዳለች ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ያለ ጊዜው እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው አለው።

፫፤ ወእምዝ ይባእ አሮን ውስተ ቅድስት ምስለ ላሕም ዘእምአልሕምት ዘበእንተ ኃጢአት ወበግዓ ለመሥዋዕት፣

እኔ ከታየሁ በኋላ ግን ከላሞች ወገን መርጦ ስለ ኃጢአት የሚሠዋ ላምና የድኅነት መሥዋዕት የሚሆን በግ ይዞ ይግባ።

፬፤ ወልብሰ አኄ ቅዱሰ ይልበስ ወድርማንቀ ዘአኄ ይደይ ላዕለ ሥጋሁ ወቅናተ ዘአኄ ይቅንት ወአክሊለ ዘአኄ ያንብር ላዕለ ርእሱ፣

የከበረ የነጭ ሐር ልብስ ይልበስ፣ በሰውነቱም የነጭ ሐር ‹ልብ አልባ› ያጥልቅ፣ የነጭ ሐር ቀሸመሪን ይታጠቅ፣ የነጭ ሐር ኵፌትንም በራሱ ያድርግ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ አልባስ ቅዱሳን እሙንቱ ወተሐጺቦ በማይ ኵሎ ሥጋሁ ይልበሶሙ፤

የከበሩ ልብሶች ናቸውና ገላ ውን በውሀ ታጥቦ ይልበሳ ቸው፤

፭፤ ወእምተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ይንሣእ ክልኤተ ሐራጊተ እምአጣሊ ዘበእንተ ኃጢአት ወአሐደ በግዓ ለመሥዋዕት፤

ከእስራኤል ወገኖች ሁለት የፍየል ሙክት፤ ስለኃጢአት መሥዋዕት አንድ በግ ስለ ድኅነት መሥዋዕት ይቀበል፤

፮፤ ወያበውእ አሮን ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለ ቤቱ ፤

አሮንም ተቀብሎ ለኃጢአት ማስተሥረያ ሲሆን በተሠ ዋው ላም የራሱንም የወገኖ ቹንም ኃጢአት ያስተሥርይ፤

፯፤ ወእምዝ ያመጽኦሙ ለእልክቱ ክልኤቱ ሐራጊት ወያቀውሞሙ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

መሥዋዕተ ኃጢአትን ካቀ ረበ በኋላ ሁለቱን ሙክቶች አምጥቶ ልዩ በምትሆን ድን ኳን ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ያቁማቸው፤ ቅድመ እግ ዚአብሔር አለው ደብተራ ኦሪትን እግዚአብሔር የማይ ለየው ስለሆነ፤

፰፤ ወይወዲ አሮን ሳዕለ ክልኤሆሙ ሐራጊት ዕፀወ ዘቦቱ ያስተዓፁ አሐዱ ዕፅ ዘእግዚአ ብሔር ወአሐዱ ዕፅ ለዘአብአ፤

አሮንም ዕጣ የሚጥልበትን እን ጨት በሁለቱ ሙክቶች፤ በሁ ለቱ ጊደሮች ላይ ያኑር፤ አንዱ ዕጣ የእግዚአብሔር አንዱ ዕጣ ያቀረበው ሰው ነውና፤

፱፤ ወያመጽእ አሮን ለሐርጌ ዘወ ድቀ ላዕሌሁ ዕፀ እግዚአብሔር ወያ በውኦ በእንተ ኃጢአት ለአስ ተሥርዮ፤

አሮንም የእግዚአብሔር ዕጣ የወደቀበትን ሙክት አቅርቦ ኃጢአት ስለማስተሥረይ ይሠ ዋው፤

፲፤ ወለሐርጌሰ ዘወድቀ ላዕሌሁ ዕፅ ዘአምጽኦ ያቀውሞ ሕያዎ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ያስተሥሪ ቦቱ ወከመ ይፈንዎ ኀበ ያግዕዝዎ ወኀበ የኀድግዎ ውስተ ገዳም፤

መሥዋዕት ያቀረበው ሰው ዕጣ የወደቀበትን ሙክት ግን ያመ ጣው ሰው ኃጢአቱን ያስተ ሠርይበት ዘንድ ነፃ አው ጥተው ወደሚተዉት ወደ ምድረ በዳ ይሰድደው ዘንድ



ሳይሠዋ በእግዚአብሔር ፊት ያቁመው፤

፲፩፤ ወያበውእ አሮን ላሕመ ዘበእንተ ኃጢአት ወያስተሠሪ ሎቱ ወለቤቱ ወይጠብሖ ለውእቱ ላሕም ዘበእንተ ኃጢአት፤

አሮንም የርሱንና የወገኖቹን ኃጢአት የሚያስተሠርይበትን ላም ስለሠሩት ኃጢአት ይሠ ዋው፤

፲፪፤ ወይነሥእ ማዕጠንተ ወይመ ልዕ እሳተ እምፍሕም ዘውስተ ምሥዋዕ ዘቅድመ እግዚአብሔር፤

በእግዚአብሔር ፊት ካለው ከምሥዋዑ እሳት ፍሕም ጭሮ ጽናውን ይምላው፤ ‹‹እሳት ነበልባሉ፤ ፍሕም አካሉ ነው ፤

ወይመልእ እዴሁ እምዕጣን ዘእ ፍን ወድቁቅ ወይበውእ ውስተ መን ጦላዕት፤

የተለቀመ የደቀቀ ዕጣን በእጁ ታፍኖ ከመንጦላዕቱ ውስጥ ይግባ፤

፲፫፤ ወይወዲ ውእተ ዕጣነ ውስተ ማዕጠንት ቅድመ እግዚአብሔር ወይከድን ጢሱ ለውእቱ ዕጣን ምስሐለ ለዘዲበ ታቦት ወኢይሙት፤

ከመንጦላዕቱም ገብቶ ከታ ቦቱ ፊት ሲደርስ እንዳይ ቀሠፍ የያዘውን ዕጣን ያጢስ፤ የዕጣኑም ጢስ በታ ቦቱ ላይ ያለ ምስህልን ማስተሥረያውን ያልብስ፤

፲፬፤ ወይነሥእ እምደሙ ለውእቱ ላሕም ወይነዝኅ በአፃብዒሁ ቅድመ ምስሐል ለመንገለ ሠርቁ ውስተ ገጹ ለምስሓል ወይነዝኅ ስብዐ ቅድመ እግዚአብሔር እምውእቱ ደም በአፃብዒሁ፤

‹‹ቅድመ ምስሐልና ውስተ ገጹ ለምስሐል አንድ ወገን›› ስለ ኃጢአት ፈንታ ከተሠ ዋው ከላሙ ደም በጣቱ ዘግኖ ‹‹ታፍኖ›› በምሥራቅ በኵል ምስሐልን ሰባት ጊዜ ይር ጨው፤ ሰባት ፍጹም ነው፤ ፍጹም አካሉን ይርጨው ‹ይቅባው›፤ አንድም በፍጹም ትጋት ኃጢአት እንዲሠረይ ለማጠየቅ፤

፲፭፤ ወይጠብሕ ሐርጌኒ ዘበእንተ ኃጢአት ዘእምነበ ሕዝብ ወያ በውእ እምደሙ ውስጠ እመንጦ ላዕት፤

ስለ ሕዝቡም ኃጢአት ሙክት ይሠዋ፤ ከደሙም ዘግኖ ከመ ንጦላዕቱ ውስጥ ያግባ ፤

ወይገብሮ ለደሙ በከመ ገብረ ደመ ላሕም ወይነዝኅ እምደሙ ላዕለ ምስሐል መንገለ ገጹ ለምስሐል፤

www.ethiopianorthodox.org

ደሙንም እንደ ላሙ ደም ያድርገው ማለት የምስሐልን ላዩንም ውስጡንም ይር ጨው፤

፲፮፤ ወያስተሠሪ በመቅደስ እምር ኩሰሙ ለእስራኤል ወበእንተ ኵሉ ዓመፃሆሙ ወበእንተ ኵሉ ኃጣው ኢሆሙ፤

በመቅደሱ ውስጥ ያሉን ሁሉ እድፍን እስራኤልን ከርኩሰታቸው፣ ከበደላቸው፣ ከኃጢአታቸው ያንጻቸው፤ አንድም በእንተን ለማውጣት ስለ ሠሩት ኃጢአት፣ ስለ በደሉት በደል እስራኤልን ከርኩሰታቸው ይቅር ይበላቸው፤ ‹ሐተታ› የቤተ መቅደስ ሥራ ስለሚሠራበት ደብተራ ኦሪትን መቅደስ አላት፣ በከበረ ቦታ ሲል ነው፣ በኦሪት ፍጹም ሥርየት እንዳልተሠጠ ለማጠየቅ በከፊል ተናገረው ፤

ወከመዝ ይገብር በደብተራ ዘመርጡል እንተ ተነድር ውስቴቶሙ በማዕከለ ርኩሰሙ፣

በርኩሰታቸው መካከል በምትኖር በደብተራ ኦሪት እንዲህ ያድርግ ማለት ሲናገረው የመጣውን ነው፣ በዙሪያዋ ሰፍረው ኀጢአት ይሠሩባታልና በማዕከለ ርኩሰሙ አላት፤

፲፯፤ ወአልቦ ዘይሄሉ ሰብእ ወኢመኑሂ ሶበ ይበውእ ውስተ መቅደስ ከመ ያስተሥሪ እስከ ይወፅእ ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለቤቱ ወለኵሉ ተዓይኒሆሙ ለእስራኤል፣

ሊቀ ካህናቱ ኃጢአት ያስተሠርይ ዘንድ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በገባ ጊዜ የራሱንና የወገኖቹን ሁሉ ኃጢአት አስተሥርዮ እስኪወጣ ድረስ የሚገባ ማንም ሰው አይኑር፤

፲፰ ወይወፅእ ኀበ ምሥዋዕ ዘሀሎ ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ቦቱ፣

ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ወዳለ ወደመሠዊያው ወጥቶ ኃጢአቱን ያስተሥርይበት፤

ወይነሥእ እምደመ ላሕም ወእም ደመ ሐርጌ ወይወዲ ላዕለ አቅ ርንቲሁ ለምሥዋዕ በዓውዱሙ፣

ስለ ኃጢአት ከተሠዋው ከላሙና ከሙክቱ ደም ዘግኖ ከመሠዊያው ቀንዶች በዙሪያው ይርጨው፤

፲፱፤ ወይነዝኀ ላዕሌሁ እምውእቱ ደም በአፅባዕቱ ስብዓ ወያነጽሖሙ ወይቄድሶሙ እምኵሉ ርኵሶሙ ለደቂቀ እስራኤል፤



ከዚያም ደም በጣቶቹ ዘግኖ ምሥዋዑን ሰባት ጊዜ ይር ጨው፣ የእስራኤልን ልጆችም ከኃጢአታቸው ፈጽሞ ያንጻቸው፤

፳፤ ወይፌጽም አስተሥርዮ በመቅደስ ወበደብተራ ዘመርጡል ወበምሥዋዕ ወያመጽእ ሀርጌ ዘሕያው፣

ይህ፣ በግብር ብቻ ያለ ነው፣ [illegible] ክንዱ፣ [illegible] ክንዱ፣ ምሥዋዑንም እንዲህ አድርጎ ቀብቶ ያክብር፣ ያልተሠዋውንም ሙክት ያቅርበው፤

፳፩፤ ወይወዲ አሮን ፪ኤሆን እደዊሁ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ዘሕያው ወይትነኀይ በላዕሌሁ ኵሎ ኃጣውኢሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወኵሎ ዓመፃሆሙ ወኵሎ አበሳሆሙ፣

አሮን ባልተሠዋው ሙክት ራስ ላይ እጆቹን ያኑር፣ የያዕቆብን ልጆች ፍጹም ኃጢአታቸውን፣ በደላቸውንም ሁሉ በርሱ ያስተሥርይ፤

ወያነብሮ ላዕለ ርእሱ ለውእቱ ሐርጌ ዘሕያው ወይፌንዎ ሐቅለ ምስለ ብእሲ ዘተረሰየ፣

የሕዝቡን በደላቸውን ባልተሠዋው ሙክት ራስ ላይ ያኑረው ማለት በርሱ ምክንያት ያርቅላቸው፣ ከዚያም በኋላ ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ ሰው ጋር ሙክቱን በረሀ ይስደደው፣ ዘተሠረየ ቢል ኃጢአቱ ከተሠረየለት ሰው ጋር ዘተርእየ ቢል በረድኤት ከተገለጸ ሰው ጋር ሲል ነው፤

፳፪፤ ወይነሥእ ዝንቱ ሐርጌ ላዕለ ርእሱ ኃጣውኢሆሙ ወየሐውር ለሐውሩ ሐርጌ ውስተ ምድረ በድው ኀበ አልቦ ሰብ፣

ያም ሙክት የሕዝቡን ኃጢአታቸውን በራሱ ላይ ይሸክማል፣ እንጨት ወደሌለበት በረሀም ይሰደዋል፤

፳፫፤ ወይበውእ አሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወያነብር አልባሰ ዘአኀ ዘይለብሶ ሰበዊእ ውስተ መቅደስ ወያነብሮ ህየ፣

ወያነብር አልባሰ ዘአኀ ወያነብሮ ህየ አንድ ወገን ነው፣ አሮንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚለብሰውን የነጭ ሐር ቀሚስ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ያኑር፣

፳፬፤ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ በመካን ቅዱስ ወይለብስ አልባሲሁ፤

በከበረው ቦታ ገላውን ታጥቦ ልብሱን ይልበስ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወወጺኦ ይገብር መሥዋዕቶ ወመሥዋዕተ ሕዝብኒ፣

ከዚያም ወጥቶ የራሱንና የሕዝቡን መሥዋዕት ይሠዋ፤

፳፭፤ ወያስተሠሪ ለርእሱ ወለቤቱ ወለሕዝብኒ፣

የራሱንና የወገኖቹን የሕዝቡንም ኃጢአት ያስተሥርይ፤

ወለስብሕኒ ዘበእንተ ኃጢአት ይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ፣

ስለ ኃጢአት የተሠዋውን ስቡንም ከሥጋው ለይቶ በመሠዊያው ውስጥ ያኑረው፤

፳፮፤ ወዘክቱኒ ዘአውፅኦ ለሐርጌ ዘፈለጡ ከመ ያግዕዞ ኀበ ገዳም የሐፅብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት፣

ሕዝቡ የለዩትን ሙክት ወደ ምድረ በዳ ያወጣውም ሰው ልብሱን ይጠብ፣ ገላውንም ይታጠብ፣ ከዚህም በኋላ ወደ ከተማ ይግባ፣

፳፯፤ ወላሕምኒ ዘበእንተ ኃጢአት ወሐርጌኒ ዘበእንተ ኃጢአት ዘአብኡ ደሞሙ ከመ ያስተሥርዩ ቦቱ በውስተ መቅደስ ያወጽእዎሙ አፍአ እምትዕይንት ወያውዕይዎሙ በእሳት፣

ኃጢአት ያስተሠርዩበት ዘንድ ደማቸውን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ያገቡት የኃጢአቱን መሥዋዕት ላሙንና ሙክቱንም ከከተማ በአፍኣ (በውጭ) አውጥተው በእሳት ያቃጥሏቸው፤

ወአምዕስቲሆሙኒ ወሥጋሆሙኒ ወካእሴሆሙኒ ፣

ቁርበታቸውንም ፣ ሥጋቸውንም ፣ ሰንበራቸውንም ሁሉ ያቃጥሉት፤

፳፰፤ ወዘክቱ ዘአውዓዮሙ የሐፀብ አልባሲሁ ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወእምዝ ይበውእ ውስተ ትዕይንት፣

በእሳት ያቃጠላቸውም ሰው ልብሱን ይጠብ፣ ገላውንም ይታጠብ፣ ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ ይግባ፣

ወዝንቱ ሕገ ይኩንክሙ ለዓለም ፣

ይህም የዘለዓለም ሥርዓት ይሁናችሁ፤

፳፱፤ ወበሳብዕ ወርኅ አመ ዓሡሩ ለሠርቅ አሕምምዋ ለነፍስክሙ፣



በሰባተኛው ወር በጥቅምት ያውም ወሩ በባተ በዐሥረኛው ቀን ዕለተ ዮሴፍ ናት፣ ማለት ዮሴፍ የተሸጠባት ቀን ናትና በዚች ቀን ሰውነታችሁን በጾም አሳዝኗት፣ ጥቅምት ሰባተኛነቱ ለሚያዝያ ነው፣ «ወዝንቱ ወርኅ ይኩንክሙ ቀዳማየ አውራኅ» ብሏቸው እስራኤል የዘመን መስወጫ አድርገውታልና፤

ወኵሎ ግብረ ኢትግበሩ ባቲ ዘእምፍጥረቱኒ ወዘግዩርኒ ዘሀለወ ኀቤክሙ፣

ትውልዱ ከእሥራኤል የሆነ አምኖ ከናንተ ዘንድ ከሚኖር ከመጻተኛም የሆነ የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት፤

፴፤ እስመ በይእቲ ዕለት ያስተሠሪ በእንቲአክሙ ከመ ያንጽሕክሙ እምኵሉ ኃጣውኢክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወትነጽሑ፣

በዚች ቀን ከኃጢአታችሁ ሁሉ ያነጻችሁ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ያስተሠርይላችኋልና ከኃጢአታችሁም ትነጻላችሁና፤

፴፩፤ እስመ ሰንበተ ሰንበታት ይእቲ ለክሙ፣

ለናንተ በሱባዔ የምትጠራ በዓል ናትና፤ አንድም ከበዓል የምትበልጥ በዓል ናትና፤

ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ወሕግ ውእቱ ለክሙ ዘለዓለም፣

ሰውነታችሁን አሳዝኗት፣ ይህም ለናንተ የዘለዓለም ሕግ ነው፤

፴፪፤ ወያስተሠሪ ካህን ዘቀብዕዎ ወዘፈጸሙ እደዊሁ ከመ ይኩን ካህነ እምድኅረ አቡሁ፤

ከአባቱ ከአሮን ቀጥሎ ያገለግል ዘንድ እጁን የቀቡት ካህን በዚች ቀን የሕዝቡን ኃጢአት ያስተሠርያል፤

ወይለብስ አልባሰ አጌ አልባሰ ቅድሳት፣

የከበሩ በነጭ ሐር ያጌጡ ልብሶችንም ለብሶ፤

፴፫፤ ወያስተሠሪ በቅድስተ ቅዱሳን ወበደብተራ ዘመርጡል ወበምሥዋዕ ያስተሠሪ ሎቱ፤

ባሥራቱ ክንድ በሃያውም ክንድ፣ በምሥዋዓ ብርቱ፣ በዚህ ሁሉ ባቀረበው ጸሎት የሕዝቡን ኃጢአት ያስተሠርያል፣ በሁሉም ሥራ ይሠራበታልና ተርትሮ ተናገረው፣

ወበእንተ ካህናትኒ ወበእንተ ኵሉ ተዓይን ያስተሠሪ፤

የካህናቱንም የሕዝቡንም ሁሉ ኃጢአት ያስተሠርያል፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፬፤ ወዝንቱ ሕገ ይኩንክሙ ዘለዓለም ከመ ያስተሥሪ በእንተ ደቂቀ እስራኤል እምኵሉ ኃጢአቶሙ፤

የእስራኤልን ልጆች ከኃጢአታቸው ያነጻቸው ዘንድ ይህም የዘለዓለም ሥርዓት ይሁናችሁ፤

ወምዕረ ለለዓመት ይገብሮ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ይህንም በየዓመቱ ያድርገው፡፡

## ምዕራፍ ፲፯

### ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ በሎሙ ለአሮን ወለደቂቁ ወለኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወንግሮሙ ዘንተ ቃለ ዘአዘዘ እግዚአብሔር፤

«ዘንተ ቃለ ወደ ፊት የሚያመጣውን ነው» እግዚአብሔር ያዘዘውን ሕግ ለአሮን ንገረው ፤ ከሱም ለተወለዱ ለካህናት ከያዕቆብ ለተወለዱ ለሕዝቡም ንገራቸው ብሎ ነገረው፤

፫፤ ወይቤ ብእሲ ብእሲ እምቤተ እስራኤል እመቦ ዘጠብሐ ላሕመ አው በግዐ አው ጠሌ በውስተ ትዕይንት ወእመኒ በአፍኣ እምትዕይንት፤

ከያዕቆብ ልጆች አንዱም አንዱም በከተማ ውስጥ ከከተማ ወጭም ቢሆን ላም የሠዋ ወይም በግ ወይም ፍየል የሠዋ ሰው ቢኖር፤

፬፤ ኢያምጽአ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይግበሮ መሥዋዕተ አው ዘመድኃኒት ዘኅሩይ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ ሊቀበለው የተመረጠ ድኅነት የሚያሰጥ መሥዋዕት አድርጎ ያቀርበው ዘንድ ከቤቱ አርዶ አወራርዶ ወደ ደብተራ ኦሪት አያምጣ፤

ወእምከመ ጠብሖ በባዕድ ኢያምጽኦ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ያብእ ቍርባነ ለእግዚአብሔር፤ ቅድመ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር፤

«ኀበ ኆኅተ ደብተራና ቅድመ ደብተራሁ አንድ ወገን» በሌላም ቦታ ሠውቶ ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርጎ ያቀርበው ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪቱ አያምጣው፤



እስመ ቀቲለ ነፍስ ይከውኖ ለውእቱ ብእሲ ወከዓዌ ደም ውእቱ ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ፤

ለሠዋው ሰው ነፍስ መግደል ይሆንበታልና ፤ ደም አፍሳሽ ሆኗልና ይህን አፍርሳ ያቀረበችውም ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ፤

፭፤ ከመ ኢያምጽኡ ደቂቀ እስራኤል መሥዋዕቲሆሙ ኵሉ ዘይሠውዑ በገዳም፤

የያዕቆብ ልጆች በምድረ በዳ የሠዉትን ሁሉ እንዳያቀርቡ፤

ወያበውእዎ ለእግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ኀበ ካህን ወይሠውዕዎ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር፤

ነገር ግን የሚያቀርቡትን መሥዋዕት ከሊቀ ካህናቱ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት አቅርበው፤ ድኅነት የሚያሰጥ መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር ይሠዉት፤

፮፤ ወይክዑ ካህን ደሞ ላዕለ ምሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወይገብር ስብሐ ለመዓዛ ሠናይ ቅድመ እግዚአብሔር፤

ሊቀ ካህናቱም ደሙን ተቀብሎ በደብተራ ኦሪት ደጅ ይርጨው፤

ስቡንም በጎ መዓዛ አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቅርበው፤ ‹ያጢሰው› ፤

፯፤ ወኢይሡዑ መሥዋዕቶሙ ለከንቱ በዘቦቱ ይዜምዉ ድኅሬሆሙ፤

ጣዖት በማምለክ በሚሰስኑ ገንዘብ ይሰስኑ ዘንድ ላይረባቸው ላይጠቅማቸው መሥዋዕቱን አይሠዉ፤ አንድም በማሰስነት ገንዘብ ለከንቱ ጣዖት መሥዋዕት አይሠዉ፤ እንጨቱን፤ ደንጊያውን አምልከው ሀሐይን፤ ጨረቃን፤ ከዋክብትን ወደ ማምለክ ይሄዳሉና በዘቦቱ ይዜምዉ አለ፤

ወከመዝ ይኩንክሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ፤

በዘመናችሁ ሁሉ እንዲህ እንደ ተናገርኩት የዘለዓለም ሥርዓት ይሁናችሁ፤

፰፤ ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ እም ደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ ዘገብረ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር አው ቍርባነ፤

ከእስራኤል ልጆችም ሁኖ አምነው ከናንተ ዘንድ ከሚኖሩ ከአሕዛብም ወገን ሁኖ የድኅነት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ያቀረበ ሰው

www.ethiopianorthodox.org

ቢኖር መሥዋዕት የላሙ የበጉ የፍየሉ ቊርባን የስንዴው የወይኑ፤ አንድም መሥዋዕት የላሙ የበጉ የፍየሉ የስንዴው የወይኑ ቊርባን የሚጤሰው ነው፤

፱፤ ኢያምጽኦ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይግበሮ መሥዕተ ለእግዚአብሔር ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ፣

ለእግዚአብሔር ይሠዋው ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት ያምጣው፣ ይህን ሕግ ተላልፋ ያቀረበች ሰውነትም ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ፤

፲፤ ብእሲ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ ዘበልዓ እምኵሉ ደም፣

ከእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም አምነው በናንተ ዘንድ ከሚኖሩ ከአሕዛብም ወገን ቢሆን ከብርንዶው የበላ፤ አንድም ከደም ወገን የበላ፣ ደሙን አርግተው ቆልተው ይበሉታልና፤

አቀውም ገጽየ ላዕለ ይእቲ ነፍስ እንተ በልዓት ደመ ወእደመስሳ እምሕዝባ፣

ደሙን ብርንዶውንም በምትበላ ሰውነት ገጸ መዓቴን አጸናለሁ፣ ከወገኖቿም ለይቼ አጠፋታለሁ፤

፲፩፤ እስመ ደም ነፍሱ ውእቱ ለኵሉ ዘሥጋ፣

ለሥጋዊ ለደማዊ እንስሳ ሁሉ ደሙ ነፍሱ ነውና፤

ወአነ ረሰይክዎ ለክሙ ለመሥዋዕት በዘቦቱ ያስተሠርዩ በእንተ ነፍስክሙ እስመ በደሙ ትትቤዞ ነፍስክሙ፣

በደሙ ምክንያት ነፍሳችሁ ትድናለችና እኔም ስለሠራችሁት ኃጢአት በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ለነፍሳችሁ መዳኛ ሊሆን ለመሥዋዕት አደረግሁት፤

፲፪፤ ወበእንተ ዝንቱ እቤለክሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵላ ነፍስ እንተ እምኔክሙ ኢትብላዕ ደመ ወግዩር ዘሀሎ ኀቤክሙ ኢይብላዕ ደመ፣

ስለዚህ ነገር የእስራኤልን ልጆች እንዲህ እላችኋለሁ ፣ ከናንተ ወገን የተወለደች ሰውነት ሁሉ ብርንዶውን ደሙን አትብላ፣ አምኖ በናንተ ዘንድ የሚኖር መጻተኛም ይህን አይብላ፤

፲፫፤ ወብእሲ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ሀለዉ ኀቤክሙ እመቦ ዘነዓወ ንዒወ ወቀተለ እምእንስሳ፣



ከእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም አምነው ከናንተ ዘንድ ከሚኖሩ ከመጻተኞች አሕዛብም ቢሆን ከእንስሳ ወገን አድኖ የገደለ ሰው ቢኖር፤

አው ዖፌ እምዘይከውነክሙ ለበሊዕ ይክዑ ደሞ ወይደፍኖ በመሬት፣

ወይም ልትበሉት ከሚገባችሁ ወፍም ቢሆን አንገቱን ባርኮ ደሙን አቁቶ ከመሬት ይቅበረው፤

፲፬፤ እስመ ደሙ ለኵሉ ዘሥጋ ነፍሱ ውእቱ፣

የሥጋዊ የደማዊ ሁሉ ደሙ ነፍሱ ነውና፣እንስሳ የሚለው እንደ ቡኸር፣ እንደ ድኩላ፣ ያለው፣ ዖፍ የሚለው እንደ ቆቅ እንደ ዥግራ ያለው ነው፤

ወይቤሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ደሞ ለኵሉ ዘሥጋ ኢትብልዑ እስመ ደሙ ለኵሉ ዘሥጋ ነፍሱ ውእቱ፣

ለሥጋዊ ለደማዊ ሁሉ ደሙ ነፍሱ ስለ ሆነ፣ የእስራኤልን ልጆች የሥጋዊ የደማዊ ፍጥረትን ሁሉ ደሙን አትብሉት አላቸው፤

ወኵሉ ዘበልዖ ለይሠሮ፣

ይህን ሕግ አፍርሶ የበላ ሰው ሁሉ ይጥፋ፤

፲፭፤ ኵሉ ነፍስ ዘበልዓ ምውተ አው ብላዓ አርዌ እመኒ ዘእም ፍጥረቱ እስራኤል ወእመኒ ግዩር የሐፅብ አልባሲሁ፣

ሙቶ ያደረውን (በክቱን) የበላ፣ አውሬ የበላውንም ቢሆን የበላ ሰው፣ ትውልዱ ከእስራኤልም ቢሆን ከአሕዛብም ወገን ቢሆን ልብሱን ይጠብ፤

ወይትሐፀብ በማይ ሥጋሁ ወርኵስ ውእቱ እስከ ሠርክ፣

እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነውና ገላውን በውሀ ይታጠብ፤

፲፮፤ ወእመሰ ኢሐፀበ አልባሲሁ ወኢተሐፅበ ሥጋሁ በማይ ይከውኖ ኃጢአተ ላዕለ ርእሱ፣

ልብሱን ባያጥብ፣ ሰውነቱንም በውሀ ባይታጠብ ግን በልጁ በልጅ ልጁ ያይደለ በራሱ ላይ ዕዳ በደል ይሆንበታል።

## ምዕራፍ ፲፰

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ በከመ ምግባሮሙ ለምድረ

www.ethiopianorthodox.org

ግብጽ ዘነበርክሙ ባቲ ኢትግበሩ፤

**ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና የነበራችሁባት የግብጽ ሰዎችን ሥራ አትሥሩ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው፤**

፫፤ ወበከመ ምግባሮሙ ለምድረ ከነዓን ዘአነ አበውአክሙ ህየ ኢትግበሩ ወኢትሑሩ በሕጎሙ፤

**እኔ በማስገባችሁ በከነዓንም ምድር ብትኖሩ የሰብአ ከነዓ ንን ግብር አትያዙ፤ በሕጋቸ ውም አትኑሩ፤**

፬፤ ኵነኔ ዚአየ ግበሩ ወትእዛዝየ ዕቀቡ ወባቲ ሑሩ አነ እግዚአ ብሔር አምላክክሙ፤

**የኔን ሕግ አድርጉ፤ ትእዛዜ ንም ጠብቁ፤ በርሷም ጸንታ ችሁ ኑሩ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና «ኵነኔ ኢታ ምልክ» ትእዛዝ ዘጠኝ ነው፤**

፭፤ ዕቀቡ ትእዛዝየ ወኵሎ ኵነኔየ ወግበርዎ እስመ ዘገብሮ ሰብእ የሐዩ ቦቱ አነ እግዚአብሔር አም ላክክሙ፤

**ሕጌንና ትእዛዜን ሁሉ ጠብቁ፤ የሚሠራው ሰው ሕጌን በመ ጠበቅ በሕይወት ይኖራልና ፈጣ ሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ስለሆንኩ፤**

፮፤ ብእሲ ብእሲ ኀበ ኵሉ ሰብኡ ወሥጋሁኒ ዘይከውን ኢይባእ ይክ ሥት ኃፍረቶ እስመ አነ እግዚአ ብሔር አምላክክሙ፤

**አንዱም አንዱም ከወገኑ አይ ድረስ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚ አብሔር ነኝና ኃፍረቱን ይገ ልጥ ዘንድ ከዘመዱ አይድረስ፤ አንድም የዘመዱን ሚስት አይንካ፤**

፯፤ ኃፍረተ አቡከ ወኃፍረተ እምከ ኢትክሥት እስመ እምከ ይእቲ፤

**እናትህ ናትና ከእናትህ አትድ ረስ፤ አንድም ኃፍረተ አቡከ ከእንጀራ እናትህ ወኃፍረተ እምከ ፤ ከወላጅ እናትህ አት ድረስ፤**

፰፤ ኃፍረተ ብእሲተ አቡከ ኢትክ ሥት እስመ ኃፍረተ አቡከ ውእቱ፤

**ያባትህ ኃፍረት ነውና ከእን ጀራ እናትህ አትድረስ፤ የላይ ኛውን ገለጠው፤**

፱፤ ኃፍረተ እኅትከ እንተ እምአቡከ አው እንተ እምእምከ ኢትክሥት፤

**በናት እየቅል (የብቻ) ናት ብለህ ከአባትህ ልጅ፤ በአባት እየቅል ናት ብለህ ከእናትህ ልጅ አትድረስ፤**

ወእመኒ እንተ በአፍአ ተወልደት ወእመኒ እንተ እምአዝማዲከ ይእቲ ኢትክሥት ኃፍረታ፤



**ምንም በውጭም የተወለደች ብትሆን ፤ ማለት ከአሕዛብ ወገን የተወለደችም ብትሆን፤ ከዘመዶችህም ወገን ብትሆን ኃፍረቷን አትግለጥ ማለት አትድረስባት፤**

፲፤ ኃፍረተ ወለተ ወልድከ አው ወለተ ወለትከ ኢትክሥት ኃፍረቶን፤

የወንድ ልጅህን ልጅ፤ የሴት ልጅህንም ልጅ ፤ ኃፍረታቸ ውን አትግለጥ፤ ማለት አት ድረስባቸው፤

እስመ ኃፍረትከ ውእቱ፤

**ኃፍረትህ ነውና፤**

፲፩፤ ኃፍረተ ወለተ ብእሲተ አቡከ ኢትክሥት እስመ እኅትከ ወወለተ እምከ ይእቲ፤

**እኅትህ ናትና፤ የናትህም ልጅ ናትና ከእንጀራ እናትህም ልጅ አትድረስ፤**

፲፪፤ ኃፍረተ እኅተ አቡከ ኢት ክሥት እስመ ቤተ አቡከ ይእቲ፤

**ከአባትህ እኅት ከአክስትህ አት ድረስ፤ የአባትህ ወገን ናትና፤**

፲፫፤ ኃፍረተ እኅተ እምከ ኢትክ ሥት እስመ እምቤተ እምከ ይእቲ፤

**ከእናትህ እኅትም አትድረስ፤ የእናትህ ወገን ናትና፤**

፲፬፤ ኃፍረተ ብእሲተ እኁሁ ለአ ቡከ ኢትክሥት እስመ ዘመድከ ይእቲ፤

**ከአባትህ ወንድም ሚስት አት ድረስ፤ ያጎትህ ሚስት ናትና፤**

፲፭፤ ኃፍረተ ብእሲተ ወልድከ ኢትክሥት እስመ ብእሲተ ወልድከ ይእቲ ፤

የልጅህ ሚስት ናትና ከልጅህ ሚስት አትድረስ፤

፲፮፤ ኃፍረተ ብእሲተ እኁከ ኢትክ ሥት እስመ ኃፍረተ እኁከ ውእቱ፤

**የወንድምህ ሚስት ናትና ከወ ንድምህ ሚስት አትድረስ፤**

፲፯፤ ወኃፍረተ ብእሲት ምስለ ወለታ ኢትክሥት፤

**ከእናቷ ደርሰህ ከልጇ አትድ ረስ፤**

ወኢዘወለተ ወልዳ ወኢዘወለተ ወለታ ኢትግበር ከመ ትክሥት ኃፍረቶን እስመ ቤትከ ውእቶን ወኃጢአት ውእቱ፤

**ከሚስትህ ከወንድ ልጇ ልጅ አትድረስ፤ ከሴት ልጇም ልጅ አትድረስ ወገኖችህ ናቸውና፤ ኃጢአትም ነውና፤**

፲፰፤ ወብእሲተ ምስለ እኅታ ኢታ ውስብ ከመ ኢታስተቃንዖን፤

www.ethiopianorthodox.org

ይቀናናሉና እንዳይቀናኑ እኅት ማማቾችን አታግባ፤

ወኢትክስት ኃፍረቶን ዘዛቲኒ ወዘእ ኅታቲኒ፤

የታላቂቱንም የታናሺቱንም ኃፍ ረት አትግለጥ፤ ማለት ከሁለቱ አትድረስ፤

እንዘ ዓዲሃ ሕያውት ይእቲ፤

ታላቂቱ በሕይወት ሳለች ከታናሽቱ አትድረስ፤ ከሞተች በኋላ (ለያቅም ዘርአ) ባለው በኦሪቱ ሕግ የምታገባው ናትና እንዘ ሕያውት አለ፤

፲፱፤ ወኀበ ብእሲት ትክት ኢትባእ ዘእንበለ ትንጻሕ ከመ ትክሥት ኃፍረታ እንዘ ዓዲሃ ርኩስት ይእቲ፤

ገና በርኩሰት ሳለች ከርኩሰቷ ሳትነጻ በግድጅ (በደሟ) ወዳለች ሴት አትድረስ፤

፳፤ ወኢትባእ ኀበ ብእሲተ ካልዕከ ከመ ትስክብ ምስሌሃ ወኢትዝራእ ዘርአከ ላዕሌሃ፤

ከባልንጀራህ ሚስት አትድረስ፤ ልጅም ትወልድ ዘንድ ዘር ከዘር አትቀላቅል፤

፳፩፤ ወኢታስተጻምድ ለመልአከ ወልደከ ወኢታርኵስ ስሞ ለቅዱስ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ፤

እስራኤላዊ ልጅህን ከአሕዛብ አታጋባ፤ ፈጣሪህ እኔ እግዚ አብሔር ነኝና ልጅህን ከአ ሕዛብ አጋብተህ የከበረ የእግ ዚአብሔርን ስም አታስነቅፍ፤

፳፪፤ ወምስለ ተባዕት ኢትስክብ ከመ አንስት እስመ ርኩስ ውእቱ፤

የረከሰ ሥራ ነውና እንደ ሴት በወንድ አትሰስን፤ (ከወንድ አትድረስ)፤

፳፫፤ ወኢትሑር ኀበ እንስሳ ከመ ኢታውፅእ ዘርአከ ላዕሌሃ ከመ ኢትርኰስ ባቲ፤

ዘርህን በእንስሳ ላይ እንዳ ትቀላቅል፤ ከርሷም በመድረ ስህ እንዳትረክስ ከእንስሳ አት ድረስ፤

ወብእሲትኒ ኢትሑር ኀበ እንስሳ ከመ ይስክባ እስመ ርኩስ ውእቱ፤

ሴትም ይደርስባት ዘንድ ወደ ደማዊ ወደ እንስሳዊ ፍጥረት አትሂድ፤ የረከሰ ሥራ ነውና፤

፳፬፤ ወኢታርኵሱ ርእሰክሙ በዝንቱ ኵሉ ፤

ነሳሳለትና ጠቅሎ አመጣው፤ በማይገባ በዚህ ሁሉ ሥራ ራሳችሁን አታርክሱ፤

እስመ በዝንቱ ኵሉ ረኵሱ አሕዛብ እለ አነ አወፅኦሙ እምቅድሜክሙ



ወአገመንዋ ለምድር፤

እኔ ከፊታችሁ አስወጥቼ የም ሰዳቸው ሰብአ ከነዓን በዚህ ሁሉ ረክሰዋልና ምድርንም አር ክሰዋልና፤

፳፭፤ ወበእንተ ዝንቱ ፈደይክዎሙ ወተቈጥዓቶሙ ምድር ለእለ ይነብሩ ላዕሌሃ፤

ስለዚህም ነገር ፍዳ አመጣ ሁባቸው፤ ምድርም እንዲህ ሁነው በርሷ የሚኖሩትን ሕገ ወጥ የሆኑትን ተቈጥታቸዋ ለችና ማለት አጥፍታቸዋለ ችና እናንተም እንዳትጠፉ «ኢታርኵሱ ርእሰክሙ ላለው»

፳፮፤ ወዕቀቡ ኵሎ ሕግየ ወኵነኔየ ኢትግበሩ ምንተኒ እምዝንቱ ኵሉ ዘርኵስ ወኢዘእምፍጥረቱ እስራኤል ወኢግዩር ዘሀለወ ኀቤክሙ፤

ትውልዱ እስራኤላዊም ቢሆን አምኖ በናንተ ዘንድ የሚኖር መጻተኛም ቢሆን፤ ሕጌን ጠብቁ፤ ፍርዴንም ጠንቅቁ፤ ርኩስ ከሚ ያሰኝ ነገርን ሁሉ አትሥሩ ብሎ ያዳኝባቸዋል፤

፳፯፤ እስመ ዘንተ ኵሎ ርኩሰ ገብሩ ሰብእ እለ እምቅድሜክሙ ተፈጥሩ ውስተ ምድር ወአገመ ንዋ ለምድር፤

ከእናንተ አስቀድመው በዚህ ዓለም የነበሩ ሰዎች ይህን የረከሰ ሥራ ሠርተው ምድርን አርክሰው ነበርና፤

፳፰፤ አንትሙኒ ዑቁ ከመ ኢትትቈጣዕክሙ ምድር ለእመ አርኰስክምዋ በከመ ተቈጥዓቶሙ ለአሕዛብ እለ እምቅድሜክሙ፤

ከናንተ አስቀድመው በነበሩ አሕዛብ እንደተበሳጨችባቸው ምድር ብታጕሰቍሏት እንዳት በሳጭባችሁ ማለት እንዳታጠ ፋችሁ እናንተም ዕወቁ ‹ተጠ ንቀቁ›፤

፳፱፤ እስመ ኵሉ ዘገብረ እምዝ ንቱ ኵሉ ርኩስ ትሠሮ ይእቲ ነፍስ እምሕዝባ እንተ ገብረቶ፤

‹‹ነፍስ እንተ ገብረቶ ነው›› ርኩስ ሥራ የሠራ ሰው ሁሉ ጠፍቷልና ይህን የሠራች ሰው ነትም ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ፤

፴፤ ወዕቀቡ ትእዛዝየ ከመ ኢትግ በሩ እምኵሉ ሕጎሙ ለርኩሳን ዘኮኑ እምቅድሜክሙ፤

ከናንተ አስቀድሞ የነበሩ የአ ሕዛብን ኃጢአት እንዳትሠሩ ሕጌን ጠብቁ፤

ወኢትርኰሱ ቦሙ እስመ አነ እግዚ አብሔር አምላክክሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና በአሕዛብ ግብር እንዳትረክሱ ‹ማለት› እንዳት ጠፉ ሕጌን ጠብቁ ።

## ምዕራፍ ፲፱
## ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ በሎሙ ለኵሉ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል ቅዱሳነ ኩኑ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር አምላክ ክሙ ፤

የእስራኤልን ልጆች ወገኖች ሁሉ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚ አብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነኝና ንጹሐን ሁኑ፤ ልዩ ነኝና ከአ ሕዛብ ልዩ ሁኑ ብለህ ንገ ራቸው ብሎ ነገረው፤

፫፤ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ ይፍ ራህ አባሁ ወእሞ ወሰንበታትየ ዕቀቡ፤

ከናንተ አንዱም አንዱም እናት አባቱን ያክብር አለ፤ ይርዳ፤ ቅዳሜ ቅዳሜንም አክ ብሩ፤ የዓመቱን ቆጥሮ ሰን በታትየ ብሎ አበዛ፤ አንድም ዕለተ እሑድን በትንቢት ቆጥሮ ነው፤

፬፤ ወኢትትልዉ አማልክተ ወኢት ግበሩ ለክሙ አማልክተ ዘስብኮ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብ ሔር ነኝና ጣዖታቱን አትከ ተሉ አለ፤ አታምልኩ ተመ ትቶ የተሠራውንም ጣዖት አታ ምልኩ፤

፭፤ ወእመ ሦዕክሙ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር አንኢሐ ክሙ ሡዑ፤

ድኅነትን የሚያስጥ መሥዋ ዕት ለእግዚአብሔር ብትሠዉ ንጹሐን ሁናችሁ ሠዉ፤ አን ድም መሥዋዕተ ፈቃድ፤ መሥ ዋዕተ መደ ነኒት፤ መሥዋዕተ ብፅዓት ብታቀርቡ ሰውነታች ሁን ከኃጢአት ንጹሕ አድር ጋችሁ ሠዉ፤ አንድም መሥ ዋዕቱን ንጹሕ አድርጋችሁ አቅርቡ፤

፮፤ ወበዕለተ ትሠውዑ ይበልዕዎ አው በሣኒታ፤

‹ብልዕዎ ሲል ነው›፤ ይህን ንም በሠዋችሁበት ቀን ብሉት፤ ከሠዋችሁበትም ቀን ቢተርፍ በማግስቱ ብሉት፤



ወለእመቦ ዘተርፈ በሣልስት ዕለት ያውዕይዎ በእሳት፤

በሦስተኛው ቀን የተረፈ ቢኖር ግን በእሳት ያቃጥሉት፤

፯፤ ወለእመሰ በልዕዎ ውስተ ብትክ ይትኌለቍ ወኢይሠጠዎ፤

ከዚያ በኋላ ቢበሉት ግን አባላ የተመታውን፤ሙቶ ያደረ ውን የበላ ሰው ዕዳ እንዲሆ ንበት ዕዳ ይሆንባቸዋል፤ እግ ዚአብሔርም አይቀበለውም፤

፰፤ ወለዘበልዖ ኃጢአተ ይከውኖ እስመ አርኰሰ ቅድሳቶ ለእግዚአ ብሔር ለትሠሮ ይእቲ ነፍስ እንተ በልዓቶ እምሕዝባ፤

ይህንንም የበላ ሰው ዕዳ ይሆንበታል የእግዚአብሔርን መሥዋዕት አራክሷልና፤ አን ድም የእግዚአብሔር ማደሪያ ሰውነቱን አጐስቁሏልና ያች የበላች ሰውነትም ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ፤

፱፤ ወአመ ማዕረር ሶበ ተዓፅዱ እክለ ምድርክሙ ኢታንጽሑ ዓጺደ ገራህትክሙ ወኢትዕርዩ ዘወድቀ እክለ እንዘ ተዓፅዱ፤

በመከር ወራት በምድራችሁ የበቀለውን አዝመራ ባጨዳ ችሁ ጊዜም አጥርታችሁ አት ጨዱ ፤ ስታጭዱም የወደቀ ውን እህል አትልቀሙት፤

፲፤ ወዓፀደ ወይንከኒ ኢታስተና ጽሕ ቀሚመ ወኢትትቀረም ሕን ባባተ ወይንከ ዘወድቀ ለነዳይ ወለግዩር ተኃድጎ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤

የወይንህንም ቦታ አጥርተህ አትልቀመው፤ የወደቀውንም ፍሬ አጥርተህ አትልቀም፤ ገን ዘብ ለሌለው ምንደኛ፤ መሬት ለሌለው መጻተኛ ተውለት እንጂ፤ የማከብር የማደኸይ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፲፩፤ ወኢትስርቁ ወኢተሐስዉ ወአልቦ ዘይትዔገል ካልኦ፤

አትስረቁ በሐሰት አትመስ ክሩ፤ አንድም ሐሰት አትና ገሩ፤ ብርቱው ደከማውን፤ ባለ ጸጋው ደኃውን የሚቀማው አይኑር፤

፲፪፤ ወኢትምሐሉ በስምየ በሐሰት ወኢታርኵሱ ስሞ ቅዱሰ ለአምላክ ክሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤

ስሜን ጠርታችሁ በሐሰት አትማሉ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና የፈጣሪ ያችሁን ክቡር ስሙን አታስ ነቅፉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወኢተዓምፅ ካልዓከ ወኢትሂድ ወኢይቢት ንቤከ ዓስቡ ለዓሳብከ እስከ ይጸብሕ፤

ባልንጀራህን አትበድል፤ ገንዘቡንም አትቀማ፤ የሠራተኛህንም ደመወዝ ነገ እሠጥሃለሁ ብለህ ባንተ ዘንድ አይደር፤

፲፬፤ ወኢትንብብ ሕሡመ ላዕለ ጽሙም ወኢትደይ ዕቅፍተ ቅድመ ዕውር፤

አይሰማኝም ብለህ በደንቆሮው ክፉ ነገር አትናገር፤ አያየኝም ብለህ በዕውሩ ፊት መሰናክል አታኑር፤ አንድም ጽሙመ ልቡና ዕውረ ልቡና እስራኤልን ጣዖት አምልክ አትበለው፤

ወፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከሙ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራው፤ አምልከው፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፲፭፤ ወኢትግበሩ ዓመፃ በውስተ ፍትሕ፤

በፍርድ ጊዜም ነገሩ ሲታወቃችሁ እንበድል ብላችሁ በሐሰት አትፍረዱ፤

ወኢታድልዉ ለገጸ ዐቢይ ወኢለገጸ ነዳይ በጽድቅ ኩንኖ ለካልዕከ፤

ባለጸጋውን አፍራችሁ፤ ደሀውን ንቃችሁ፤ አቃላችሁ በሐሰት አትፍረዱ፤ ለድሀው ወንድምህ ለባለጸጋው ጓደኛህ በውነት ፍረድ እንጂ፤

፲፮፤ ወኢተሑር በጕሕሉት ውስተ ሕዝብከ፤

መማለጃ ተቀብለህ በልብህ ክፉ ነገር ይዘህ ወደ ወገኖችህ በሸንገላ አትሂድ፤

ወኢትቁም ላዕለ ነፍሰ ካልዕከ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ፤

ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና በባልንጀራህም ላይ በጠላትነት አትነሣ፤

፲፯፤ ወኢተዓምፆ ለካልዕከ ወኢትጽልኦ በልብከ ዝልፎ ወአይድዮ እንተ ተነይሶ ለካልዕከ ወኢትግበር በእንቲአሁ ኀጢአተ፤

ባልንጀራህን አትበድለው፤ የምትነቅፈውን ገልጠህ ንገረው እንጂ በልብህ አትጥላው፤ በርሱ ዕዳ በደል የሚሆንበትንም አታድርግ፤

፲፰፤ ወኢትትበቀል ለሊከ ወኢትቀየም ላዕለ ደቂቀ ሕዝብከ ወአፍቅር ካልዓከ ከመ ነፍስከ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ፤

በወገኖችህ ልጆችም ፈጽመህ ቂም በቀል አትያዝ፤ የሁላችሁ

ፈጣሪ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ አድርገህ ውደድ፤

፲፱፤ ወዕቀብ ሕግየ ወኢትሕርስ ብዕራየከ በዘባዕድ አርዑት፤

ሕጌን ጠብቅ፤ በሬህንም በሌላ ቀንበር አትጥመድ፤ አንድም በታላቅ ቀንበር አትጥመደው፤ ‹‹ርኅራኄ ነው›› ፤ አንድም የሕገ እግዚአብሔር ማደሪያ ሰውነትህን ለሕገ ጣዖት አታስገዛ፤

ወኢትትክል ውስተ ዓፀደ ወይንከ ዘዘዚአሁ፤

በወይንህም ቦታ ዘሩ ብዙ ዓይነቱ ልዩ የሆነ ተክል አትትክል፤ ‹ሐተታ› አንዱ አንዱን እንዳያፈራ ያደርገዋልና፤ ለመሰብሰብም ያስቸግራልና ፤ አንድም የሕግ ማደሪያ በሆነ ልቡናህ ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ጣዖትን አንድ አድርገህ አትያዝ፤

ወልብስኒ ዘእምክልኤቱ እንመቱ ኃፍረት ውእቱ ወኢትልበስ፤

ሥራው ከሁለት ወገን የሆነ ልብስንም አትልበስ ‹‹ሻድሬ›› የተልባ እግር አንድ አድርገህ አትልበስ ኃፍረት ነውና፤ ምነው ንድየትን መንቀፍ ነውን



ቢሉ፤ አይደለም፤ ሐኬትን ሲነቅፍ ነው እንጂ ሰው ሥራ ከያዘ የዓመት ልብስ፤ የዕለት ጉርስ አያጣምና፤ አንድም ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ጣዖትን አንድ አድርጎ መያዝ ኃፍረት ነው ሲል ነው፤

፳፤ ወዘሰከበ ምስለ ብእሲት እንተ ዕቅብት ይእቲ ለብእሲ ገብር እንተ ቤዛሃ ኢተውህበ ላቲ ወግዕዛነ ኢተግዕዘት ይዔይኖ ሎቱ ዘይሁቦ ወኢይመውት እስመ ኢግዕዘት፤

ለወንድ ባሪያ የታጨችውን አርነት ያልወጣችውን ሴት ከክብር ያሳነሰ፤ የሚከፍለውን ዋጋ ይገምግሙለት፤ ነፃ አልወጣችምና ይሙት በቃ አይፈረድበት፤

፳፩፤ ወያመጽእ ዘበእንተ ንስሐሁ በግዓ ለእግዚአብሔር ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፤

ስለ በደለበት ኃጢአቱ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የበግ መሥዋዕት ወደ ደብተራ ኦሪት ያምጣ፤

፳፪፤ ወያስተሠሪ ሎቱ ካህን በውእቱ በግዕ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ነስሐ በዘአበሰ ወትትኃደግ ሎቱ ኃጢአቱ እንተ አበሰ፤

ካህኑም ባቀረበው በግ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን ያስ

www.ethiopianorthodox.org

ተሥርይለት ፣ በበደለው ኃጢአት ንስሐ ገብቷልና፣ የበደለውም በደል ይሠረይለታልና፤

፳፫፤ ወእመ ቦእክሙ ውስተ ምድር እንተ ይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወተከልክሙ እምኵሉ ዕፀ ዘይበልዐ ታነጽሕዎ እምኵሉ ርኵስ፣

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደ ሰጣችሁ ምድር ወደ ከነዓን በገባችሁ ጊዜ ‹ዘትበልዐ› ሲል ነው፣ ከምትበሉት፣ ዕፀ ሁሉ ተክላችሁ ከርኵሰቱ አንጹት አለ፤

ወፍሬሁኒ ዘሠለስቱ ዓም ርኩስ ውእቱ ለክሙ ኢትብልዕዎ፣

የሦስተኛው ዓመት ፍሬም ለናንተ የረከሰ ነውና አትብሉት፣ ‹ሐተታ› ወይን በተተከለ በሦስተኛው ዓመት ያፈራል፣ ያፈራውም ፍሬ ለአዕዋፍ ይሆናል፤

፳፬፤ ወበራብዕ ዓም ይኩን ኵሉ ፍሬሁ ቅዱስ ወስቡሐ ለእግዚአብሔር፣

ባራተኛው ዓመት ያፈራው ፍሬም ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን፤

፳፭፤ ወበሐምስ ዓም ብልዑ ውእቱ ለክሙ ፍሬሁ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ባምስተኛው ዓመት ያፈራው ፍሬ ግን ለናንተ ነውና ብሉት፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፳፮፤ ወኢትበልዑ በውስተ አድባር ወኢትርከሱ ወኢትጠየሩ በዖፍ ፤

በተራራ የተሠዋውን በልታችሁ አትርከሱ፣ እንደ ቆለኛም በወፍ አታማርቱ፤

፳፯፤ ወኢትግበሩ ለክሙ ቈናዘዕተ እምፀጉረ ርእስክሙ ወኢትላጽዩ ጽሕመ ገጽክሙ፣

ከራስ ጠጉራችሁ ቁንጮ ጉተና አታውጡ፣ የፊታችሁንም ጽሕም አትላጩ፤ አንድም ግንባራችሁን አትበጡ፣ ቅንድባችሁን አትከተቡ፤

፳፰፤ ወእመቦ ዘሞተ መላጼ ኢታቅርቡ ውስተ ሥጋክሙ፣

የሞተ ሰው ከወገናችሁ ቢኖር ወደሰውነታችሁ ምላጭ አታቅርቡ አለ አትላጩ፤

ወኢትፍጥሩ ለክሙ ፈጠራ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ከመጽሐፍ ሳታገኙ ፣ ከመምህራን ሳትማሩ፣ ልብ ወለድ አታስተምሩ፤



፳፱፤ ወኢታርኵስ ወለተከ ወኢታዘምዋ፣

ክብሯን አሳንሰህ ልጅህን ሴሰኛ አታሰኛት፤

ወኢትዘሙ ምድር ወኢትምላዕ ምድር ዓመፃ ፤

በምድር ሰውን መናገር ነው፣ አንተን አይታ ልጅህ እንዳ ትሰስን ፣ ከናንተም የተነሣ ምድር ዓመፅን እንዳትመላ እንደ ማየ አይኅ ያለ ጥፋትም እንዳያገኛት፣

፴፤ ዕቀቡ ሰንበታትየ ወፍርሁ እምቅዱሳንየ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ከስድስቱ ዕለታት ለይታችሁ ቀዳሚትን አክብሩ ፣ ካከበርኋቸው ከነቢያት ከካህናትም የተነሣ ፍሩ፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፴፩፤ ወኢትትልዉ ሰብአ ሐረስ ወሰብአ ሥራይ ከመ ኢትርኰሱ ቦሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና በእሊህ እንዳትረክሱ ፣ ሥር የሚምሱትንና ሟርተኞችን አትከተሉ ፤

፴፪፤ ቅድመ ዘሲበት ተንሥእ ወአክብር ገጸ አረጋዊ፣

ሽማግሌው ሲመጣ ተነሣለት፣ የሽማግሌውንም ፊት አይተህ አክብር ፣ ሕፃኑን አታክብር ማለት አይደለም፣ በጸናው መናገር ነው፤

ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላከከ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔርንም ፍራው፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፴፫፤ ወለእመቦ ዘመጽአ ኀቤክሙ ግዩር ኢትሳቅይዎ በውስተ ምድርክሙ፣

አምኖ ወደናንተ የመጣ መጻተኛም ቢኖር መከራ አታጽኑበት፤

ከመ ዘእምፍጥረቱ ይኩን ለክሙ ግዩር ዘመጽአ ኀቤክሙ፣

አምኖ ወደናንተ የመጣ መጻተኛ ከናንተ እንደ ተወለደ ይሁን፤

፴፬፤ ወአፍቅርዎ ከመ ርእስክሙ እስመ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ ወአነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

በግብጽ ምድር ሁለት መቶ አሥራ አምስት ዓመት መጻተኞች ነበራችሁና እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ ውደ

www.ethiopianorthodox.org

ዱት፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፴፭፤ ወኢትግበሩ ዓመፃ በውስተ ፍትሕ ወኢበውስተ ኁልቈ ሐሳብ፣

በፍርድ ጊዜም ዓመፅን አታድርጉ፣ በሐሰት አትፍረዱ፣ በመቆጣጠር ጊዜም አንድ ሰጥታችሁ ሁለት ፣ ሁለት ሰጥታችሁ ሦስት ነው አትበሉ፤

ወኢበመስፈርት ወኢበመዳልው ፣

በታናሽ መስፈሪያ ፣ በታናሽ ሚዛን ሰጥታችሁ፣ በታላቅ መስፈሪያ፣ በታላቅ ሚዛን አትቀበሉ፤ አንድም በታላቅ መስፈሪያ፣ በታላቅ ሚዛን ተቀብላችሁ፣ በታናሽ መስፈሪያ በታናሽ ሚዛን አትስጡ፤

፴፮፤ መዳልውክኒ ዘበጽድቅ ይኩን፡ ወመስፈርትክኒ ዘበጽድቅ ይኩን፡ ወአዕባኒክኒ ዘበጽድቅ ይኩናክ፡

ሚዛንህም፣ መስፈሪያህም፣ አዋቂህም ‹ወይም› የሚዛንህ ደንጊያ እውነተኛ ይሁን፤

እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውጻእኩክሙ እምድረ ግብጽ፣

ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፴፯፤ ወእቀቡ ኵሎ ሕግየ ወኵሎ ትእዛዝየ ወግበርዎ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ኢታምልክን ፣ ዘጠኙን ቃላት ጠብቃችሁ ሥሩት።

## ምዕራፍ ፳

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እመቦ እምደቂቀ እስራኤል አው እምግዩራን እለ ገብኡ ውስተ እስራኤል ዘአስተፃመረ ወልዶ ለመልአክ ሞተ ለይሙት ወሕዝብ እለ ውስተ ምድር ለይውግርዎ በዕብን፣

ከእስራኤል ልጆች ወይም አምነው ወደ እስራኤል ከተመለሱ መጻተኞች አሕዛብ እስራኤላዊ ልጁን ከአሕዛብ አለቃ ወገን ያጋባ፤ አንድም መምለኬ እግዚአብሔር ሰውነቱን ለጣዖት ያስገዛ ሰው በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት፣ ባለፈው ሥርዓቱን ሲናገር መጥቶ ነበርና ከዚህ ቅጣቱን አመጣ፤



፫፤ ወአነኒ አቀውም ገጽየ ላዕለ ውእቱ ብእሲ ወእደመስሶ እምሕዝቡ እስመ ወሀበ ወልዶ ይጸመድ ለመልአክ፣

እኔም ይህን ባደረገ ሰው ገጸ መዓቴን አጸናበታለሁ፣ ዕብራዊ ‹እስራኤላዊ› ልጁን ለአሕዛብ አለቃ፣ መምለኬ እግዚአብሔር ሰውነቱን ለጣዖት አስገዝቷልና፣ ከወገኖቹ ለይቼ አጠፋዋለሁ፤

ከመ ያርኵስ ቅድሳትየ ወከመ ያርኵስ ስመ ቅዱሳንየ፣

መሥዋዕቴን ያረክስ ዘንድ፣ የወዳጆቼን የነቢያትን የካህናትን ስም ያዋርድ ዘንድ እንዲህ አድርጓልና፤

፬፤ ወእመቦ ተዓወርዎ ሰብአ ይእቲ ምድር ለውእቱ ብእሲ፤

በሀገር ያሉ ሰዎች ያን ሰው በደንጊያ ወግረው፣ በእሳት አቃጥለው መግደልን ቸል ቢሉት ግን፤

ወሠወሩ አዕይንቲሆሙ እምኔሁ እንዘ ያስተፃምድ ወልዶ ለመልአክ ወኢቀተልዎ፤

እስራኤላዊ ልጁን ለአሕዛብ አለቃ ሲያጋባ አይተው ዓይናቸውን ከሱ ቢመልሱ ማለት ፈርተው ባይገድሉት፤

፭፤ አቀውም ገጽየ ላዕለ ውእቱ ብእሲ ወላዕለ አዝማዲሁ፣

በዚያ ሰውና በዘመዶቹ ላይ ገጸ መዓቴን አጸናለሁ፤

ወእደመስሶ ሎቱ ወለኵሎሙ እለ ኀብሩ ምስሌሁ ከመ ይዘምዉ በመላእክት እምሕዝቦሙ፤

እሱን አጠፋዋለሁ፣ ከወገኖቻቸው ተለይተው ከሱ ጋራ በጣዖቱ ይሰስኑ ዘንድ ማለት ጣዖት ያመልኩ ዘንድ የተባበሩትንም ሁሉ አጠፋቸዋለሁ፤

፮፤ ወእመቦ ብእሲ ዘተለወ ሰብአ ሐረስ ወሰብአ ሥራይ ከመ ይዘሙ ድኅሬሆሙ፤

እነዚህን ተከትሎ ጣዖት በማምለክ ኃጢአት በመሥራት ይሰስን ዘንድ ሟርተኞችን፣ ሥር የሚምሱትን፣ ቅጠል የሚበጥሱትን የተከተለ ሰው ቢኖር፤

አቀውም ገጽየ ላዕለ ውእቱ ብእሲ ወላዕለ አዝማዲሁ ወእደመስሶ እምሕዝቡ፤

ይህን ባደረገ ሰው እሱን መስለው ይህን በሠሩ ወገኖቹም ላይ ገጸ መዓቴን አጸናለሁ፣ ከወገኖቹም ለይቼ አጠፋዋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፣ ወኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ቅዱስ አነ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ንጹሕ ነኝና ንጹሐን ሁኑ፤ አንድም እኔ ከአማልክተ ሐሰት ልዩ ነኝና እናንተም ከአሕዛብ ግብር ልዩ ሁኑ፤

፰፣ ወዕቀቡ ሕግየ ወትእዛዝየ ወግበርዎ እስመ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሰክሙ፤

ኢታምልክን ዘጠኙን ቃላት ጠብቁ፣ ይህንንም ሁሉ አድርጉት፣ የማከብራችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፱፣ ወለእመቦ ብእሲ ዘነበበ ሕሱመ ላዕለ አቡሁ ወእሙ ሞተ ለይሙት እስመ ጊጉይ ውእቱ፣

በአባቱና በናቱ ላይ ክፉ ነገርን የተናገረ ሰው ቢኖር በደለኛ ነውና የሞት ሞት ይሙት፤

፲፣ ወእመቦ ብእሲ ዘዘመወ በብእሲተ ብእሲ አው በብእሲተ ካልኡ ሞተ ለይሙት ዘዘመወኒ ወእንተ ዘመወትኒ፤

ከወንድ ሚስት የደረሰ ወይም በባልንጀራው ሚስት የሰሰነ ሰው ቢኖር የሞት ሞት ይሙት፣

ወንዱም ሴቲቱም በደለኞች ናቸውና ይሙቱ፤

፲፩፣ ወእመቦ ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ አቡሁ ከሠተ ኀፍረተ አቡሁ ሞተ ለይሙት ወክልኤሆሙ ጊጉያን እሙንቱ፤

ከአባቱ ሚስት የደረሰ ሰው ቢኖር የአባቱን ኀፍረት ገልጧልና ሁለቱም በደለኞች ናቸውና የሞት ሞት ይሙቱ፤

፲፪፣ ወለእመቦ ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ ወልዱ ሞተ ለይሙቱ ክልኤሆሙ እስመ ኃጢአተ ገብሩ ወጊጉያን እሙንቱ፣

ከልጁ ሚስት የደረሰ ሰው ቢኖር ሁለቱም ከሕግ ወጥተው ኃጢአት ሠርተዋልና የሞት ሞት ይሙቱ፤

፲፫፣ ወለእመቦ ዘሰከበ ምስለ ተባዕት ከመ አንስት ርኩሰ ገብሩ ሞተ ለይሙቱ ክልኤሆሙ ጊጉያን እሙንቱ፣

ባል ከሚስቱ እንዲደርስ ከወንድ የደረሰ ሰው ቢኖር፣ ርኩስ የሚያሰኝ ሥራ ሠርተዋልና በደለኞች ተብለው ሁለቱም ይሙቱ፤

፲፬፣ ዘነሥአ ወለተ ምስለ እማ ኃጢአት ውእቱ ወበእሳት ለያውዕ



ይዎሙ ኪያሁ ወኪያሃኒ ወኢት ምጻእ ላዕሌክሙ ኃጢአት፣

ከናትና ከልጅ የደረሰ ሰው ታላቅ ኃጢአት ነውና እርሱንም እርሷንም በእሳት ያቃጥሏቸው፣ በነሱ አንፈርድም ብላችሁ ግብር አበር ሁናችሁ ባትፈርዱ ያች በደል እናንተን ወደ ማጥፋት እንዳትመጣ፤

፲፭፣ ወዘሰከበ ምስለ እንስሳ ሞተ ለይሙት ወእንስሳሁኒ ቅትሉ፣

ከእንስሳም የደረሰ ሰው ቢኖር የሞት ሞት ይሙት፣ እንስሳውንም ግደሉት፤

፲፮፣ ወብእሲትኒ ለእመ ሖረት ኀበ እንስሳ ከመ ይስክባ ብእሲተኒ ቅትሉ ወእንስሳሁኒ ውግሩ ክልኤሆሙ ጊጉያን እሙንቱ፣

ፍርድ አንድ ወገን አይደለምና ሴትም ይደርስባት ዘንድ ወደ እንስሳዊ ፍጥረት ብትሄድ ፣ ሁለቱም ርኵሳን ናቸውና እርሷን በእሳት አቃጥላችሁ እንስሳውን በደንጊያ ወግራችሁ ግደሉ፤

፲፯፣ ወዘሰከበ ምስለ እኅቱ እመኒ እንተ እምአቡሁ ወእመኒ እንተ እምእሙ ወርእየ ኀፍረታ ወይእቲኒ ርእየት ኀፍረቶ ጽእለት ውእቱ፣

በናት የብቻ ናት ብሎ ከአባቱ ልጅ፣ በአባት የብቻ ናት ብሎም ከናቱ ልጅ የደረሰ ሰው ቢኖር፣ ኀፍረቷን ቢገልጽ ማለት ቢደርስባት፣ እርሷም የርሱን ኀፍረት ብትገልጽ ማለት የሚያሰክር አጠጥታ ብትወድቅበት ሎጥን ልጆቹ እንዳሳቱት ነው፤

ለይሡረዉ በቅድመ ደቂቀ ዘመደሙ እስመ ከሠተ ኀፍረተ እኅቱ፡ ጌጋየ ይከውኖ

የዘመዶቻቸው ልጆች እያዩ በዘመዶቻቸው ፊት ይጥፉ አለ ይህን ያየህ ተቀጣ እንደ ማለት ነው፣ የእኅቱን ኀፍረት ገልጧልና ይህም ዕዳ በደል ይሆንበታል፤

፲፰፣ ወዘሰከበ ምስለ ብእሲት ትክት ወርእየ ኀፍረታ ወከሠተ ነቅዓ ደማ ወይእቲኒ ከሠተት ነቅዓ ደማ ለይሠረዉ ክልኤሆሙ እሙላዶሙ፣

በግዳጇ ካለች ሴት የደረሰ ደሟ እየፈሰሰ ኀፍረቷን ቢገልጥ ማለት ቢደርስባት፣ እርሷም ሠውራ ነቅዓ ደሟን ብትገልጥ፣ ሁለቱም ከወገኖቻቸው ተለይተው ይጥፉ፤

፲፱፣ ወኢትክሥት ኀፍረተ እኅተ አቡከ ወእኅተ እምከ እስመ

www.ethiopianorthodox.org

ዘመዶሙ ለእመ ከሠቱ ኃጢአተ ይከውኖሙ።

ያባትህንና የእናትህን እኅት ኃፍረት አትግለጥ አለ፤ ከአክስትህ አትድረስ ፤ ወንዶች ከወገኖቻቸው ቢደርሱ፤ ዕዳ በደል ይሆንባቸዋልና፤

፳፤ ወዘሰከበ ምስለ እንተ ዘመዱ፤ ከሠተ ኃፍረተ ዘመዱ ዘእንበለ ውሉድ ለይሙቱ።

ከሠተና ሰከበ አንድ ወገን፤ ከዘመዱ የደረሰ ሰው ቢኖር ለሌላው አብነት ሳይሆኑ ሁለቱም ይሙቱ፤ አንድም የግብር ልጅ ሳይተኩ ይሙቱ፤ አንድም በቁሙ ልጅ ሳይወልዱ ይሙቱ፤

፳፩፤ ወብእሲ ዘሰከበ ምስለ ብእሲተ እኁሁ ከሠተ ኃፍረተ እኁሁ ዘእንበለ ውሉድ ለይሙቱ።

ከወንድሙ ሚስት የደረሰ ሰው የወንድሙን ኃፍረት ገልጧልና ለሌላው አብነት ሳይሆኑ ይሙቱ፤ አንድም ያለ ልጅ ይሙቱ፤

፳፪፤ ወዕቀቡ ኵሎ ትእዛዝየ ወግበርዎ ወኢትትበአሰክሙ ምድር እንተ ውስቴታ አነ አበውአክሙ ከመ ትንበሩ ባቲ።

ሕጌን አጽንታችሁ ጠብቃችሁ ሥሩት፤ አሥሩን ቃላት ኵሎ በማለት ተናገረ፤ ይህን ያላደረጋችሁ እንደሆነ በውስጧ ትኖሩ ዘንድ እኔ ወደ ርሷ የማገባችሁ ምድር አትቀበላችሁም፤ የሰዎቹን ለምድር ሰጥቶ ተናገረ፤

፳፫፤ ወኢትሑሩ በሕገ አሕዛብ እለ አወፅእሙ እምኔክሙ።

ከናንተ ለይቼ አስወጥቼ በምሰዳቸው በአሕዛብ ሕግ ጸንታችሁ አትኑሩ፤

እስመ ዘንተ ኵሎ ገብሩ ወአስቈረርክዎሙ።

አሕዛብ ይህን ሁሉ ስለአደረጉ እኔ ተጸይፌያቸዋለሁና፤

፳፬፤ ወእቤለክሙ አንትሙ ዘትወርስዋ ለምድሮሙ ወአነ እሁበክሙ ከመ ታጥርይዋ ለምድር እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ።

የሰብአ ከነዓንን ምድር እናንተ ትወርሷታላችሁ ብያለሁና ማርና ወተት የምታስገኝ ማለት ተድላ ደስታ የሚገኝባት ከነዓንን ገንዘብ ታደርጓት ዘንድ እኔ እሰጣችኋለሁ፤

አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘፈለጥኩክሙ እምኵሉ አሕዛብ።



ከአሕዛብ ሁሉ የለየኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፳፭፤ ወፈለጥኩ ለክሙ ማዕከለ እንስሳ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ ወማዕከለ ኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር።

ከእንስሳም ሆነ ከአዕዋፍ ወገን የሚበላውንና የማይበላውን ለየሁላችሁ፤

ወኢታርኵሱ ነፍሰክሙ በእንስሳ ወበአዕዋፍ ወበኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ዘፈለጥኩ ለክሙ ዘርኵሶ።

በእንስሳና በአዕዋፍ በዚህ ዓለም በሚመላለስ በለየሁላችሁ ፍጥረት ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ፤ አንድም በዚህ ሁሉ ሰውነታችሁን እንዳታረክሱ የሚበላውንና የማይበላውን ለየሁላችሁ፤

፳፮፤ ወትከውኑኒ ቅዱሳነ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘፈለጥኩክሙ እምኵሉ አሕዛብ ከመ ትኩኑኒ ሊተ።

ለኔ ቤተሰብ ወገን ትሆኑኝ ዘንድ ከአሕዛብ የለየኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ንጹሕ ነኝና ንጹሐን ሁኑልኝ፤

፳፯፤ ብእሲኒ ወብእሲትኒ ለእመቦ ዘኮኑ ሐራስያነ አው ዘሥራይ ሞተ ለይሙቱ ወበዕብን ለይውግርዎሙ እስመ ጊጉያን እሙንቱ።

ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ሟርተኞች የሆኑ ሥር የሚምሱ፤ ቅጠል የሚበጥሱ ሰዎች ቢኖሩ የሞት ሞት ይሙቱ፤ በደለኞች ናቸውና በድንጊያ ወግረው ይግደሏቸው።

## ምዕራፍ ፳፩
## ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ።

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

በሎሙ ለካህናት ለደቂቀ አሮን ወንግሮሙ ከመ ኢይርኩሱ በነፍስ እንተ እምሕዝቦሙ።

ለ እና ለ አንድ ወገን ነው፤ ሕዝቡ ከወገናቸው በሆነች ሰውነት ደርሰው እንዳይረክሱ ይነግሯቸው ዘንድ ከአሮን ለተወለዱ ካህናት ንገራቸው ብሎ ነገረው፤

፪፤ ወእምቤት ዘቅሩቦሙ እመኒ ዘአቡሆሙ አው ዘእምእሞሙ አው ዘእምደቂቆሙ አው ዘእምአዋልዲሆሙ አው ዘእምእኁሁ አው ዘእምእኅቱ።

www.ethiopianorthodox.org

በአባታቸውም በእናታቸውም ቢሆን አቅራቢያ ከሆነ ወገና ቸው ከወንዶች ልጆቻቸው ከሴቶች ልጆቻቸውም ወገን፣ ከወንድማቸውም ፣ ከእኅታቸ ውም ወገን ቢሆን ደርሰው እንዳይረክሱ፤ አንድም ወን ድም ከእኅቱ፣ እኅትም ከወ ንድሟ ደርሰው እንዳይረክሱ፤

፫፤ አው በድንግል እንተ ቅርብት ይእቲ ሎቱ እንተ ኢኮነት ለብእሲ በእሉ ኢይርኩሱ በዘእምሕዝቦሙ ከመ ኢይኩኖሙ ጽዕለተ፣

ለወንድ ባልደረሰች ፣ ለሱ አቅራቢያ በሆነች በድንግሊ ቱም ቢሆን፣ ከወገናቸው በተ ወለዱ በሊህ ሁሉ እንዳይረ ክሱ፣ ይህም ነውር ነቀፋ እንዳይሆንባቸው ንገራቸው ብሎ ነገረው፤

፭፤ ወኢትትላጸዩ ርእሰክሙ ላዕለ ዘሞተ ወኢትትላጸዩ ጽሕመ ገጽ ክሙ ወኢትጥብሑ ሥጋክሙ፤

ካህናቱም ከወገኖቻችሁ ሰው ቢሞት የራስ ጠጕራችሁን፣ የፊት ጽሕማችሁን አትላጩ፣ ፊታችሁንም አትንጩ፤

፮፤ ወይኩኑ ቅዱሳነ ለአምላኮሙ ወኢያርኲሱ ስመ አምላኮሙ፣

ለፈጣሪያቸው የተለዩ የነጹ ይሁኑ፣ የፈጣሪያቸውንም ስም አያርክሱ፤

እስመ እሙንቱ ያቄርቡ መሥዋ ዕተ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ወይኩኑ ቅዱሳነ፣

ለፈጣሪያቸው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርባሉና ከሕ ዝቡ የተለዩ ከኃጢአት የነጹ የከበሩ ይሁኑ፤

፯፤ ብእሲተ ዘማ ወጽእልተ ኢያ ውስቡ፣

ይህች ሴት ለግቢ የተስ ማማች ከራቀ ነገድ የተወለ ደች ናት፣ ነገር ግን በዝሙቷ ምክንያት ክብሯን አስወስዳ «ጽዕልት እምንዕሳ»' ወይም ሕግ አፍራሽ ተብላለችና ዘማዩቱን አያግቡ፤

ወብእሲተኒ እንተ አውዕአ ምታ እስመ ቅዱስ ውእቱ ለእግዚአ ብሔር አምላኩ፣

ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር የተ ለየ ነውና ከአሮን የተወ ለደው ካህን ባሏ የፈታትን ሴት አያግባ፤

፰፤ ወትቄድሶ እስመ ቍርባኖ ለእ ግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ያቀርብ፣



እርሱ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚ አብሔር መሥዋዕት ያቀርባ ልና አክብረው፤

፰፤ ወይኩን ቅዱስ እስመ ቅዱስ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶ፣

ከሕዝቡ ለይቼ የማከብረው እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ክቡር ነኝና የከበረ ይሁን፤

፱፤ ወለተ ብእሲ ካህን ለእመ አጸ አለት በዝሙት ስመ አቡሃ፣ ያነ ሥርዋ ላቲ ወበእሳት ያውዕይዋ፣

ከካህናቱም ያንዱንም ያንዱን ካህን ሴት ልጅ ከሕግ ወጥታ አመንዝራ ሁና ያባቷን ስም ብታስነቅፍ ለጊዜው ይግረ ፏት፣ ከግብሯ ባትመለስ ግን በእሳት ያቃጥሏት፤

፲፤ ወካህን ዘየዐቢ እምአኃዊሁ ዘሦጡ ቅብዓ ዲበ ርእሱ ዘቡሩክ ወዘፍጹም ውእቱ እዴሁ ዘይለብስ ዘቅድሳት ርእሶ ኢይላጺ ወአል ባሲሁኒ ኢይሥጥጥ፣

ከወንድሞቹ ተለይቶ ተቀብቶ የከበረው ልብሰ ተክህኖ የለበ ሰው ካህንም ከወገኑ ሰው ቢሞትበት ራሱን አይላጭ፣ ልብሱንም አይቀደድ፤

፲፩፤ ወኀበ ኵላ ነፍስ እንተ ሞተት ኢይባዕ ወኢኀበ አቡሁ ወኢኀበ እሙ ከመ ኢይርኩስ፣

እንዳይረክስ እናቱም ብትሞት አባቱም ቢሞት ወደ ሞተ ሰው አይግባ፤

፲፪፤ ወእምውስተ መቅደስ ኢይፃእ ወኢያርኵስ ስሞ ቅዱስ ለአምላኩ እስመ ቅብዕ ቅዱስ ዘይትቀብዐ ዘአምላኩ ሀለወ ላዕሌሁ፣

ተቀብተው የሚከብሩበት የከ በረ የፈጣሪው ቅብዐ ክህነት በራሱ ላይ አለና የፈጣሪውን የከበረ ስሙን እንዳያረክስ ቅድስተ ቅዱሳን አይውጣ፤

እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር፣

ፈጣሪው እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፲፫፤ ወይንሣእ ብእሲተ ድንግለ እምነገዱ፣

ከወገኑ የተወለደች ድንግል ሴትንም ያግባ፤

፲፬፤ ባሕቱ መበለተ ወእንተ አውጽአ ምታ ወጽዕልተ ወዘማ እላንተ ኢያውስብ፣

ነገር ግን ጋለሞታዩቱን ባሏ የፈታትን፣ ክብረ ድንግ ልናዋን አስወስዳ የተነቀፈ ችውን ፣ አመንዝራ የሆነች ውን፣ እነዚህን አያግባ፤

አላ ድንግለ እምዘመዱ ወእምነገዱ ይንሣእ ሎቱ ብእሲተ፣

www.ethiopianorthodox.org

ከወገኑ የተወለደች ክብረ ድን ግልናዋን የጠበቀችውን ማስት አድርጎ ያግባ እንጂ፤

፲፭፤ ወኢያርኵስ ውሉዶ በውስተ ሕዝቡ፣

በወገኖቹም ዘንድ ልጆቹን አያጕስቍል፣ እሊህ የአመን ዝሬ ልጆች ተብለው ይሰ ደባሉና፤ አንድም አብነት ሁኗቸው የሱን ግብር ይዘው ይረክሳሉና፤

ወአነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶ፣

የማነጻው እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፲፮፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፲፯፤ ንግሮ ለአሮን ወበሎ ብእሲ ዘእምነገድከ በመዋዕሊክሙ እመቦ ዘቦቱ እምኔሁ ዘኮነ ወዘኢኮነ ንጹሐ ኢይባእ ያቅርብ ቍርባኖ ለአምላኩ፣

በዘመናችሁ ከወገንህ ከርኵ ሰት ነገር ሁሉ ያለበት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ቢኖር የፈጣ ሪውን ቍርባን ያቀርብ ዘንድ አይግባ፣ ወይም ከካህናት አይቈጠር ብለህ ለአሮን ንገ ረው አለው፤

፲፰፤ ኵሉ ብእሲ ዕውር ወሐንካስ ወኢዘበሕቁ ሐፂር ወኢምቱረ ዕገን፣

አንካሳ፣ ዕውር፣ ጆሮው የተቈ ረጠ፣ አንድም ጆሮው የማይ ሰማ ዓቅም የሌለው ድንክ፤

፲፱፤ ወኢዘስብረት ቦ ውስተ እዴሁ አው ዘስቡር እግሩ፣

እጁ እግሩ የተሰበረ ሰው ቢኖር፤

፳፤ ወኢዘስናም ወኢዘነውር ቦ ወኢዘጸምላጥ አዕይንቲሁ፣

ጥርሰ ገጣጣ፣ ነውር ነቀፋ ያለበት ዓይነ መጭማጫ ዓይነ ሸውራራ፤

ወኢብእሲ ዕቡቅ ወኢዘጽርንዕት ቦቱ ወኢዘአሐቲ እስኪቱ፣

እከክ፣ ደረመን፤ አንድም ክን ታሮት፣ ቋቍቻ ያለበት፣ ያባለዘሩም ፍሬው አንድ የሆ ነች አይግባ፤

፳፩፤ ኵሉ ዘቦቱ ነውር ወዘኢኮነ ንጹሐ እምዘርአ አሮን ካህን ኢይ ቅረብ ከመ ያብእ መሥዋዕተ ለእግ ዚአብሔር እስመ ኢኮነ ንጹሐ፣

ከአሮን የተወለደ ንጹሕ ያይ ደለ ነውር ነቀፋ ያለበት ሁሉ የእግዚአብሔርን መሥዋዕት ይሠዋ ዘንድ አይቅረብ፤



፳፪፤ ወኢይባእ ያቅርብ ቍርባነ ለአምላኩ እምቅድስተ ቅዱሳን፣

የፈጣሪውንም ቍርባን ያቀ ርብ ዘንድ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አይግባ፤

ወዘቀደሰ ባሕቱ ይብላዕ፣

ነገር ግን የለዩትን ይብላ ማለት ዓሥራቱን፣ ቀዳምያቱን ይብላ፤

፳፫፤ ወነበ መንጦላዕት ኢይባእ ወነበ ምሥዋዕ ኢይቅረብ እስመ ኢኮነ ንጹሐ ከመ ኢያርኵስ ቅድሳተ ፣

ነገር ግን ንጹሕ ስለ አይደለ መሥዋዕቱን እንዳያረክስ ወደ መሠዊያው አይቅረብ፣ ወደ መጋረጃውም አይግባ፤

እስመ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድ ሰክሙ፣

የማነጻችሁ እኔ እግዚአብ ሔር ነኝና፣ (ሐተታ) አሁን ዛሬ ነውረ ነፍስ የተገኘበት ቄስ ከሹመቱ እንዲሻር፣ መሥ ዋዕት ከማቅረብ እንዲከለከል፣ ቀድሞም ነውረ ሥጋ የተገ ኘበት ሰው መሥዋዕት ከማቅ ረብ ይከለከል ነበርና፣ ዓሥራ ቱን ቀዳምያቱን ይብላ ማለቱ ግን፣ አሁን ዛሬ ቄሱ ከሹ መቱ ቢሻር መሥዋዕት ከማ ቅረብ ቢከለከል፣ ከተረፈ መሥ ዋዕቱ እንዳይከለከል፣ ቢረክሱ የማነጻቸው፣ ቢዋረዱ የማከ ብራቸው እኔ ነኝና «ወዘቀ ደሰ ባሕቱ ይብላዕ» ዓሥ ራቱን ቀዳምያቱን ይብላ አለው፤

፳፬፤ ወነገሮሙ ሙሴ ለአሮን ወለደቂቁ ወለኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ፣

ይህንንም ትእዛዝ ሙሴ ለአሮ ንና ለልጆቹ ለእስራኤልም ልጆች ሁሉ ነገራቸው።

## ምዕራፍ ፳፪

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ በሎሙ ለአሮን ወለደቂቁ ከመ ይትዓቀቡ እምቅድሳቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣

የያዕቆብ ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው ያመጡትን ተንከባ ክበው ይጠብቁ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ንገራቸው አለው፤

ወኢያርኵሱ ስምየ ቅዱሰ በኵሉ ዘይቄድሱ ሊተ፣

www.ethiopianorthodox.org

ለኔ ለይተው በሚያቀርቡት ገንዘብ ሁሉ የከበረ ስሜን እንዳያረክሱ ንገራቸው አለው።

፫፤ አነ እግዚአብሔር ዘእቤሎሙ በመዋዕሊክሙ፤

በዘመናችሁ ይህን የምነግራቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ።

ኵሉ ብእሲ ዘይበውእ ውስተ መቅደስ ዘእምቅድስት ዘርእክሙ ውስተ ኵሉ ዘይቄድሱ ደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር እንዘ ርኵሱ ላዕሌሁ ለይሠሮ እምሕዝቡ እስመ አነ እግዚአብሔር፤

የእስራኤል ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው ለእግዚአብሔር የሚ ያቀርቡትን ይዞ በኃጢአት ሳለ ወደ ቤተ መቅደስ የሚገባ ከከ በረች ወገናችሁ የሚሆን ካህን ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ፤ ፈጣ ሪው እኔ ነኝና።

፬፤ ወለእመ እምዘርአ አሮን ዘለ ምጽ አው ዘይትከዓዎ ዘርኡ ኢይብላዕ እምቅድሳት እስከ አመ ይነጽሕ፤

ከአሮን ወገን ለምጽ ያለበት ዘሩ የሚፈሰውም ቢኖር ከኃ ጢአቱ እስኪነጻ ድረስ ከመ ሥዋዕቱ አይብላ።

፭፤ ወዘገሠሠ እምኵሉ ርኵሰ ነፍስ ወእመኒ ብእሲ ዘወጽአ እምኔሁ ዘርኡ፤

ሰውነቱ ከረከሰ ጋር የተነካካ ከሱም ዘሩ የሚፈሰውም ሰው ቢሆን።

አው ዘገሠሠ እምኵሉ ዘይት ሐወስ ዘያረኵስ እምኵሉ ርኵስ ውእቱ እስከ ሠርከ፤

በዚህ ዓለም ከሚመላለሰው ከሚያረክሰው ሁሉ የተነካካ ሰው እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ነው።

፮፤ ወኢይብላዕ እምቅድሳት ለእመ ኢተሐፅበ ሥጋሁ በማይ፤

ሰውነቱን በውሀ ካልታጠበ ከመሥዋዕቱም አይብላ።

፯፤ ወእምከመ ዓረበት ፀሐይ ንጹሕ ውእቱ፤ ወይእተ ጊዜ ይብላዕ እምቅድሳት እስመ ሲሳዩ ውእቱ፤

ፀሐይ ከገባች በኋላ ግን ንጹሕ ነው፤ ያን ጊዜ ከመሥ ዋዕቱም ይብላ የዕለት ምግቡ ነውና።

፰፤ ወማውታ ወብላዓ አርዌ ኢት ብልዑ ከመ ኢትርኰሱ ቦሙ እስመ አነ እግዚአብሔር፤

በነሱ እንዳትረክሱ ሙቶ ያደ ረውን አውሬ የበላውን (የነከ ሰውን) አትብሉ፤ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።



፱፤ ዕቀቡ ትእዛዝየ ከመ ኢይኩን ክሙ ኃጢአተ ወከመ ኢትሙቱ በእንቲአሁ፤

የሠራሁትን ሕግ አፍርሳ ችሁ እንዳትቀሠፉ በደለኛም እንዳትባሉ ሕጌን ጠብቁ።

ወለእመ ኢረኰሱ ቦቱ አነ እግዚአ ብሔር ዘእቄድሶሙ፤

ሕጉን አፍርሰው የረከሰውን በልተው ካልጐሰቈሉ፤ የማከብ ራቸው፤ ከኃጢአት የማነጻቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝና።

፲፤ ወኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምቅድሳት፤

ከነገደ ሌዊ ያልተወለደ ከሌላ ነገድ የተወለደ ሰው ሁሉ ከመሥዋዕቱ አይብላ።

ኀደርቱኒ ለካህን ወገባእቱኒ ኢይብ ልዑ እምቅድሳት፤

የካህን እንግዳ፤ የካህን ምን ደኛም ቢሆን ከመሥዋዕቱ አይብሉ።

፲፩፤ ወለእመሰ ቦ ዘአጥረየ ካህን ገብረ ዘተሣየጠ በወርቁ ውእቱ ለይብላዕ እስመ ሲሳዩ ውእቱ፤

ዘአጥረየና ዘተሣየጠ አንድ ወገን፤ ካህኑ በወርቁ የገዛው ባሪያ ቢኖር የዕለት ምግቡ ነውና እሱ ይብላ።

ወልድኒ ዘቤቱ እሙንቱ ይብልዑ ሲሳዮሙ ውእቱ፤

ከቤት የተወለዱ ውላጆችም ቢሆኑ ምግባቸው ነውና እነሱ ይብሉ።

፲፪፤ ወወለተ ብእሲ ካህን ለእመ አውሰበት ብእሴ ዘእምካልእ ዘመድ ኢትብላዕ እምአሥራት ዘቅድሳት።

የሲቀ ካህናቱ ሴት ልጅም ከነገደ ሌዊ ልዩ ከሚሆን ከሌላ ነገድ ብታገባ ከተለየው ዓሥራት አትብላ።

፲፫፤ ወባሕቱ ለእመ ኮነት መበለተ ወኃደጋ ምታ ለትግባእ ውስተ ቤተ አቡሃ ከመ አመ እምንዕሳ ለትብላዕ እምሲሳየ አቡሃ፤

ነገር ግን ባሏ ፈትቷት ጋለ ሞታ ብትሆን ወደ አባቷ ቤት ተመልሳ እንደ ልጅነቷ እንደ ትንሽነቷ ወራት ከአባቷ ምግብ ትብላ ማለት ከአሥ ራቱ ትብላ።

ወኵሉ ዘእምባዕድ ዘመድ ኢይብላዕ እምኔሁ፤

ከነገደ ሌዊ ያልተወለደ ሰው ሁሉ አይብላ።

፲፬፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘበልዐ እምቅድሳት በኢያእምሮ ይወስክ ሐምስተ እዴሁ ላዕሌሁ ወይሁቦ ለካህን ዘቅድሳት ፤

www.ethiopianorthodox.org

የተሠራውን ሕግ ባለማወቅ ከመሥዋዕቱ የበላ ሰው ቢኖር አምስት ትርፍ ስድስተኛ ዓይነቱን ጨምሮ በደብተራ ኦሪት ለተሾመው ካህን ይስጠው፤

፲፭፤ ወኢያርኩሱ ቅድሳቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር፤

የእሥራኤል ልጆችም ለእግዚአብሔር የሚያመጡትን መሥዋዕታቸውን አያርክሱ ፤ አንድም ደቂቀ እስራኤል ከገንዘባቸው ለይተው ያቀረቡትን ካህናቱ አያርክሱ፤

፲፮፤ ወይከውኖሙ ኃጢአተ እምከመ በልዑ ቅድሳቶሙ ንስሐ ላዕሌሆሙ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእቄድሶሙ፤

የማነጻቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝና በኃጢአት ሳሉ መሥዋዕታቸውን ቢበሉ ዕዳ በደል ይሆንባቸዋልና ንስሐ አለባቸው ፤ አንድም ካህናቱ በኃጢአት ሳሉ መሥዋዕቱን ቢበሉ ዕዳ በደል ይሆንባቸዋል፤

፲፯፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፲፰፤ ንግሮሙ ለአሮን ወለደቂቁ ወለኲሎሙ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል ወለግዩራን እለ ሀለዉ እለ ውስተ እስራኤል ዘአምጽኡ ቍርባኖሙ በእንተ ኲሉ ዘበፅዐ፤

ለአሮን ለልጆቹ አምነው ከእሥራኤል ዘንድ ለሚኖሩ አሕዛብና ከእስራኤል ልጆች ለተወለዱ ወገኖች ንገራቸው፤ ስለተሳሉት ስለት የሚያመጡት ቍርባን፤

አው በእንተ ኲሉ ዘሐለዩ ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር፤

ወይም ስላሰቡት ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ብለው የሚያመጡት መሥዋዕት፤

፲፱፤ እምዘይኄይስ ይኩን ተባዕተ ንጹሐ እመራዕይ ወእምአባግዕ ወእምአጣሊ፤

ከሚሻለው ከፍየሉ፣ ከበጉ፣ ከላሙ መንጋ ነውር የሌለበት ወንድ ይሁን ብለህ ንገራቸው፤

፳፤ ኲሉ ዘቦቱ ነውር ኢያምጽኡ ለእግዚአብሔር እስመ ኢይሠጠወክሙ፤

(ኢይሠጠዎሙ ሲል ነው) ፤ አይቀበላቸውምና ነውር ነቀፋ ያለበትን ሁሉ ለእግዚአብሔር አያቅርቡ፤



፳፩፤ ወብእሲኒ ለእመቦ ዘአምጽአ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር በእንተ ዘበፅዐ አው በፈቃዱ፤ እመራዕይ አው እምአባግዕ፤

ስለተሳለ ወይም በፈቃዱ ከበግ፣ ከላም መንጋ ድኅነት የሚደረግበትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያመጣ ሰው ቢኖር፤

ንጹሐ ይኩን ዘይሠጠዎ ኲሉ ዘአልቦቱ ነውር፤

የሚቀበለው ሁሉ ነውር ነቀፋ የሌለበት ንጹሕ ይሁን፤

፳፪፤ ዕውረሰ ወስቡረ ወምቱረ ልሳን ወሕሱፈ ወዕቡቀ ወዘጽርንዕት ቦቱ ኢያምጽኡ ለእግዚአብሔር፤

ዓይኑ የታወረውን፣ እግሩ የተሰበረውን፣ ምላሱ የተቈረጠውን፣ እንደ አንገት (ጭርት) ባለ በሽታ የቈሰለ፤ አንድም ፎናና (ወዕቡቀ) እከካም፣ ደረመናም፣ ዋጣ የያዘውን፣ (ወዘጽርንዕት ቦቱ) ክንታሮት፤ አንድም እንደ ቋቍቻ ያለ ነጭ ደረመን ያለውን ይህን ሁሉ ለእግዚአብሔር አያምጡ፤

ወለቍርባንኒ ኢተሀቡ እምኔሆሙ ውስተ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር፤

በእግዚአብሔር መሠዊያ ከነሱ ለመሥዋዕት አታቅርቡ፤

፳፫፤ ለላሕምኒ ወለበግዕ ዘምቱረ ዕዝን አው ዘምቱረ ዘነብ ተሐትሞ፤

ላምም ቢሆን፣ በግም ቢሆን፣ ጆሮ ቆራጣ፣ ጅራተ ጕማዳ ከሆነ ለራስህ ቈጥረህ ታኖረዋለህ፤

ወጥሪተ ርእስከ ትሬስዮ ለብዕ ዓትከስ ኢይሠጠወከ፤

ለራስህም ጥሪት ታደርገዋለህ፣ ስለ ስለትህ ግን አይቀበልህም፤

፳፬፤ ዘጽንጽው ወዘጽቱም ወዘምቱር ወዘአጥራቂ ኢያምጽእዎ ለእግዚአብሔር፤

(ዘጽንጽው) ጕባጣ፤ አንድም ቈልማማ፣(ወዘጽቱም) ሰባራ፣ (ወዘምቱር) ቆራጣ፣ (ወዘአጥራቂ) የተቀጠቀጠ፤ አንድም የቀዘነውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው አያምጡ፤

ወበምድርክሙኒ ኢትግበርዎ፤

በሀገራችሁም አታኑሩት አለ፣ ደዌው ይናኛልና፤

፳፭፤ እምነበ ባዕድኒ ዘመድ ኢታብኡ፣ ዘከመዝ ቍርባነ ለአምላክክሙ እምገዘንቱ ኲሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ያለ መሥዋዕት ከሌላ ትውልድ፣ ከሌላ ነገድ አም ጥታችሁ ለፈጣሪያችሁ ቍር ባን አድርጋችሁ አታቅርቡ፤

እስመ ሙሱን ውእቱ ወነውር ቦቱ ወኢይሠጠወክሙ፣

ክፉ ጥፉ ነውና፣ ነውር ነቀፋ አለበትና እግዚአብሔር አይቀ በላችሁም፤

## ገባኤ

፳፮፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

ለእመ ወለደት እጐልት አው በግዕት አው ጠሊት ሰቡዓ ዕለተ የሃሉ ዕጓላ ኀበ እሙ፣

የላም ጊደር፣ በግም ብት ሆን፣ ፍየልም ብትሆን፣ ብት ወልድ ልጇ ሰባት ቀን ከእ ናቱ ጋር ይኑር፤

፳፯፤ ወአመ ሳምንት ዕለት ወእምድኅሬሁ ይሠጠወክሙ ለቍ ርባን መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር፣

በስምንተኛውና በዘጠነኛው ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋ ዕት አድርጋችሁ ብታቀርቡት ግን ይቀበላችኋል ፤

፳፰፤ ወኢትጥብሑ ዕጐልተ አው በግዕተ አው ጠሊተ ምስለ ዕጓላ በአሐቲ ዕለት፣

ላምም፣ በግም፣ ፍየልም ብት ሆን ከልጇ ጋራ በአንዲት ቀን አትሠዉ፣ ‹የርኅራኄ አነጋገር ነው›፤

፳፱፤ ወለእመ ሦዕከ መሥዋዕተ ብዕዓት ትፍሥሕትከ ለእግዚአብ ሔር ዘይሠጠወክሙ ሡዑ ሎቱ ፣

‹ለእመ ሦዕከ ካለ ዘይሠጠ ወከ ቢል በቀና ነበር፣ ልማደ መጽሐፍ ነው›፣ ደስ የሚያሰኝ የብፅዓት መሥዋዕት ብትሠዋ ወዶ የሚቀበላችሁን ለእግዚ አብሔር ሠዉለት፤

፴፤ ወበይእቲ ዕለት ይብልዕዎ ወኢያትርፉ እምሥጋሁ ለነግህ ፣

ካህናትም በተሠዋው ቀን ይብ ሉት እንጂ ለነገ ይሁን ብለው ከመሥዋዕቱ አያስቀሩ፤

፴፩፤ ወዕቀቡ ትእዛዝየ ወግበርዎ እስመ አነ እግዚአብሔር ፣

ሕጌን ጠብቃችሁ ሥሩት፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብ ሔር ነኝና፤

፴፪፤ ወኢታርኵሱ ስምየ ቅዱሰ ወእትቄደስ በማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እስመ አነ እግዚአብሔር ዘእቄድሶሙ፣



ክቡር ስሜን አታርክሱ፣ የማከ ብራችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና በእስራኤል ልጆች መካ ከል እከብራለሁ፣ እመሰገናለሁ፤

፴፫፤ ዘአውጻእክዎሙ እምድረ ግብጽ ከመ እኩንክሙ አምላ ክክሙ አነ እግዚአብሔር ፤

‹ዘአውፃእኩክሙ ሲል ነው› ፈጣሪያችሁ እሆናችሁ ዘንድ ማለት የፍቅር አባት እሆና ችሁ ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ።

## ምዕራፍ ፳፫

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እን ዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ በዓላቲሁ ለእግ ዚአብሔር ዘሰመይክሙ በቅዱስ አስማት እሉ እሙንቱ ፤

የያዕቆብን ልጆች በክቡር ስም የጠራችኋቸው የእግዚ አብሔር በዓላት እሊህ ናቸው ብለህ ንገራቸው አለው፣ የሚ ያመጣውን እሉ እሙንቱ ብሎ አጸፌ ፤

፫፤ ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ግብረከ ወበሳብዕት ዕለት ሰንበት ይእቲ፣

ግበር ሲል ነው፣ ስድስት ቀን ሥራህን ሠርተህ ሰባተኛ ዪቱ ቀን ግን በዓል ናት ፤

ወዕረፍተ ቅድስተ ተሰምየት ለእግዚአብሔር ኵሎ ግብረ ኢትግበሩ ባቲ በኵሉ በሐው ርቲክሙ እስመ ሰንበት ለእግዚ አብሔር ይእቲ ፤

‹በኵሉ ነገድክሙ ሲል ነው›፣ ለእግዚአብሔር የተለየች ዕረፍት ትባላለችና የእግ ዚአብሔር በዓሉ ስለሆነች በየነገዳችሁ ሁሉ ሥራ አት ሥሩባት፤ ‹ሐተታ› ይህንም ይዘው እስራኤል ቀዳሚትን ሲያከብሩ የተዘረጋ አያ ጥፉም የታጠፈ አይዘረጉም ነበር ፤

፬፤ እሉ እሙንቱ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር ዘሰመይክሙ በቅ ዱስ ስም በውስተ መክፈል ትክሙ ፤

በየክፍላችሁ ‹በየአገራችሁ› በከበረ ስም የጠራችኋቸው የእግዚአብሔር በዓላት እሊህ ናቸው ፤

፭፤ በቀዳሚ ወርኅ አመ ዕለተ ዐሡሩ ወረቡዑ ለሠርቅ በጊዜ ዕርበት ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር፣

www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያው ወር ሚያዝያ በባተ ባሥራ ዓራት ቀን ፀሐይ በገባ ጊዜ የእግዚአብሔር በዓል ነውና፤

፮፤ ወአመ ዕለተ ዓሡሩ ወሐሙሱ ለሠርቀ ዝንቱ ወርኅ በዓለ ናዕት ዘእግዚአብሔር ሰቡዓ ዕለተ ናዕተ ብልዑ ፤

ሚያዝያ በባተ ባሥራ አምስተኛውም ቀን የእግዚአብሔር የቂጣ በዓል ነውና ሰባት ቀን ቂጣ ብሉ ፤

፯፤ ወቀዳሚት ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ፤

መጀመሪያዪቱ ቀን ለናንተ የከበረች ናትና የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት ፤

፰፤ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ሰቡዐ ዕለተ ፤

ሰባት ቀንም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ ፤

ወሳብዕትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ፤

ሰባተኛዪቱም ቀን ለናንተ የተለየች ናትና በስድስቱ ዕለታት የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት፤ በዓለ ናዕትን የሚያከብሩ ሰባት ቀን ነው ፤ መጀመሪያውንና መጨረሻውን ቀን ተናግሮ በመካከል ያሉትን አምስቱን ዕለታት ተወ ፤ መጀመሪያውንና መጨረሻውን ታከበሩ መካከሉን አይሽሩትም ብሎ፤ አንድም ዛሬ እኛ ትንሣኤንና አግብኦተ ግብርን አብልጠን እንድናከብር እነሱም መጀመሪያውንና መጨረሻውን አብልጠው ያከብሩ ነበርና፤

፱፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፲፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ፤

ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ፤

እመ ቦእክሙ ውስተ ምድር እንተ እሁበክሙ አነ ወዓፀድክሙ ማዕረራ ታበውኡ ከላስስተ እምቀዳሜ ማዕረርክሙ ኀበ ካህን ፤

እኔ ወደማወርሳችሁ ወደ ከነዓን ምድር በገባችሁ ጊዜ ‹መከሯን› አዝማራዋን አጭዳችሁ መጀመሪያ ከደረሰው እህል እሸት ነዶውን ወደ ሊቀ ካህናቱ አግቡ፤



፲፩፤ ወያበውኦ ካህን ለውእቱ ክልስስት ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ይሠጠውክሙ ፤

ሊቀ ካህናቱም እሸት ነዶውን ወስዶ ይቀበላችሁ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ያቅርበው፤

ወበሳኒታሃ ለቀዳሚት ሰንበት ያበውኦ ካህን ፤

ሊቀ ካህናቱም እሸት ነዶውን በመጀመሪያዪቱ ሱባዔ ማግስት ያቅርበው፤ ‹ሐተታ› በመጀመሪያው ሱባዔ ሚያዝያ በባተ በአሥራ ዓራት ቀን በጉን ሠውተዋል፤ በአሥራ አምስተኛው ቀን በቂጣ የሚያደርጉትን ሱባዔ ጀምረዋል፤ ከዓሥራ ስድስተኛው ቀን ጀምረው እሸት ነዶ ያቀርባሉ፤ እስከ አምሳ ቀን በዓለ ሰዊት ነውና ፤

፲፪፤ ወትገብሩ በዕለት እንተ አምጻእክሙ ውእተ ክልስተ በግዓ ንጹሐ ዘአሐቲ ዓመቱ ለመሥዋዕት ለእግዚአብሔር ፤

እሸት ነዶውንም ባመጣችሁበት ቀን መሥዋዕት የሚሆን ዓመት የሆነው ነውር የሌለውን በግ ለእግዚአብሔር ሠዉ ፤

፲፫፤ ወቍርባኑ ክልኤቱ ዓሥራት ዘስንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ወሞዓሕቱ ራብዕተ እዴሃ ለኢን ወይን ፤

በጎ መዓዛ ሁኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ቍርባንንም በዘይት የታበቀ የሁለት ላዳን ስንዴ ዳቦና ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱት የገንቦ አራተኛ ወይን ነው፤

፲፬፤ ወይእተ ዕለተ እንተ ባቲ ታበውኡ ቍርባኖ ለአምላክክሙ ኢትብልዑ ኅብስተ ሐዲሰ ወኢቅልወ እስከ ታበውኡ ቍርባኖ ለአምላክክሙ በይእቲ ዕለት ፤

ለፈጣሪያችሁ ቍርባን በምታቀርቡባት ቀን እስክታቀርቡ ድረስ እሸት ነው ብላችሁ አዲስ እህል አትብሉ፤ የተቆላ ጥሬም ቢሆን አትብሉ ፤

ወሕገ ይኩንክሙ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ በኵሉ በሐውርቲክሙ፤

ይህም በየሀገራችሁ ሁሉ በሕይወት በምትኖሩበት ዘመን የዘለዓለም ሕግ ይሁናችሁ፤

፲፭፤ ወትኄልቁ እምሳኒታ ሰንበት እምይእቲ ዕለት እንተ ባቲ አባእክሙ ውእተ ክልስስተ ዘይሠርዐ፤

www.ethiopianorthodox.org

እሸት ነዶውን ካገባችሁባት ከመጀመሪያዪቱ ሱባዔ ማግ ስት ጀምራችሁ ሥራ የሚሠራበትን ቀን ቁጠሩ፣ ሰባቱን ሱባዔ ነው ፤

፲፮፤ ሰቡዓ ሰናብተ ትኄልቁ ፍጹመ እስከ ሳኒታሃ ለደኃሪት ሰንበት ሐምሳ ዕለተ ፤

እስከ ኋለኛዪቱ ሱባዔ ማግ ስት ድረስ አምሳውን ቀን ሰባት ሱባዔ አድርጋችሁ ቁጠሩ፣ ‹ሐተታ› ከሚያዝያ ዓሥራ ስድስት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ አራት ሰባት ሱባዔ ነው፣ ሰኔ አምስት ቀን በዓለ ሠዊት ነውና ፤

፲፯፤ ወታበውኡ መሥዋዕተ ሐዲሰ ለእግዚአብሔር ዘእምውስተ ምድር ክሙ ፤

ሰኔ አምስት ቀን ከምድራ ችሁ የተገኘውን ከመጀመ ሪያው መከር ለእግዚአብ ሔር መሥዋዕት አድርጋ ችሁ አቅርቡ ፤

ታበውኡ ኅብስተ ዘይሠርዑ ክልኤተ ኅብስተ ዘዘክልኤቱ ዓሥራት ዘስንዳሌ ይኩን አሐቲ ኅብስቱ ፤

ካህናቱ ሠርተውት የሚያ ቀርቡት አንዱ ኅብስት የሁ ለት የሁለት ላዳን ስንዴ ይሁን ፤

ወአብሒአክሙ ታበስልዎ እምቀ ዳሚ እክልክሙ ለእግዚአብሔር፤

መጀመሪያ ከደረሰው እህ ላችሁ አምጥታችሁ አኮምጥ ጣችሁ አብስላችሁ ለእግዚ አብሔር አቅርቡ፣ እህሉ አዲስ ነውና ሆድ እንዳይጎረብጥ ነው ፤

፲፰፤ ወታበውኡ ምስለ ውእቱ ኅብስት ሰብዓተ አባግዓ ዘዘዓመት ወአሐደ ላሕመ እመራዕይ ወሐ ራጊተ ክልኤተ ንጹሓነ ፤

ከኅብስቱ ጋር ለእግዚአብሔር ቊርባን አድርጋችሁ የምታቀ ርቡት ዓመት የሆናቸውን ሰባት በጎች ከላም መንጋም ‹አንድ በሬ› ሁለት ነውር የሌለባቸው ጊደሮች ይሁኑ ፤

ወይኩን ቊርባኖሙ ወመሥዋዕ ቶሙ ወሞፃሕቶሙ መሥዋዕተ መዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ፤

ቊርባናቸው፣ መሥዋዕታቸው፣ ወይናቸውም ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት ይሁን ፤

፲፱፤ ወግበሩ አሐደ ሐርጔ እም አጣሊ በእንተ ኃጢአት ወክልኤተ



አባግዓ ዘዘዓመት ለመሥዋዕተ መድኃኒት ፤

ከፍየሎች መንጋ አንድ ሙክት ስለ መሥዋዕተ ኃጢአት ዓመት የሆናቸው ሁለት በጎች ለድኅነት መሥዋዕት አቅርቡ፤

፳፤ ወያበውኦ ካህን ምስለ ውእቱ ኅብስት ዘቀዳሚ እክል ክልኤተ አባግዓ ወይሠርዖ ቅድመ እግዚአ ብሔር ቅዱስ ውእቱ ለእግዚአ ብሔር ፤

ካህኑ መጀመሪያ ከደረሰው እህል መሥዋዕት ጋራ ሁለ ቱን በጎች ተቀብሎ ለእግዚአ ብሔር የተለየ ነውና ይህን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ያቅ ርበው፣

ወለካህን ለዘአብኦ ሎቱ ይኩን፣

ከመሥዋዕቱም ጢሶለት የቀ ረው ላቀረበው ካህን ይሁን፤

፳፩፤ ወይሰምይዋ ለዛቲ ዕለት ቅድስተ ፤

ይህችን ቀን የተለየች የከበ ረች በኋት አለ፤ አክብሯት ሲል ነው፤ በዓለ ሠዊት ናት፤

ወኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግ በሩ ባቲ ፤

የምትሠሩትንም ሥራ ሁሉ አትሥሩባት ፤

ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕ ሊክሙ በኵሉ ኀበ ሀሎክሙ፣

በኖራችሁበት ዘመን ሁሉ የዘለዓለም ሥርዓት ይሁ ናችሁ ፤

፳፪፤ ወአመ ተዓፅዱ እክለ ምድርክሙ ኢትጠናቀቁ ዓፂደ ዘተርፈ ውስተ ገራህትክሙ ፤

በምድራችሁም የበቀለውን አዝመራ በአጨዳችሁ ጊዜ ከእርሻችሁ ውስጥ የቀረውን ማጨድን አትጠናቀቁ አለ፣ አጥርታችሁ አትጨዱ ፤

ወዘወድቀ ኢትዕርዩ ለነዳይ ወለግዩር ኅድግዎ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

ከመሬት የወደቀውንም ገንዘብ ለሌለው ምንደኛ፣ መሬት ለሌ ለው መጻተኛ ተዉለት እንጂ አጥርታችሁ አትልቀሙት፣ የም ሰጥ የምነሳ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ፤

፳፫፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፳፬፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ በሳብዕ ወርኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ዕረፍተ ትኩንክሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ የሰባተኛው ወር የጥቅምት መባቻ ዕረፍት ትሁናችሁ ብለህ ንገራቸው፤

ተዝካረ ዘመጥቅዕ ቅድስተ ትሰመይ ለእግዚአብሔር ፤

የነጋሪት መታሰቢያ ማለት ነጋሪት የሚመታባት ቀን ትሆናችሁ ዘንድ ለእግዚአብሔር የተለየች በዓል ትባል፤ ‹ሐተታ› ዛሬ እኛ መስከረም ሲብት ሕዝቡን ሰብስበን በዓላትን ፤ አጽዋማትን እንድናውጅ፤ እነሱም ጥቅምት ሲብት ነጋሪት መትተው ሕዝቡን ሰብስበው በዘመነ ብሉይ የተሠሩ በዓላትን አጽዋማትን አውጀው ይለያዩ ነበርና፤

፳፭፤ኵሉ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፤

የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቅርቡባት እንጂ፤

፳፮፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

አመ አሡሩ ለሳብእ ወርኅ ዕለተ አስተሥርዮ ይእቲ ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ፤

ጥቅምት በባተ በአሥር ቀን ኃጢአታችሁ የሚሠረይባት ቀን ናትና ለናንተ የተለየች ‹የከበረች› ትሁን፤ ‹‹ጾመ ዮሴፍ ናት››፤ ዕለተ አስተርእዮ ቢል ጌታ በረድኤት የሚገለጽባት፤ እናንተ በባለሟልነት የምትገለጹባት ቀን ናት ሲል ነው ፤

፳፯፤ ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፤

በዚችም ቀን ሰውነታችሁን በጾም አድክሟት፤ ለእግዚአብሔርም መሥዋዕት አቅርቡ፤

፳፰፤ ወኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ በይእቲ ዕለት ፤

በዚችም ቀን የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት ፤

እስመ ዕለተ አስተሥርዮትክሙ ይእቲ እንተ ባቲ ያስተሠርዩ በእንቲአክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

ካህናት ስለናንተ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስተሠርዩባት ቀን ናትና ፤ አስተርእዮትክሙ ቢል ጌታ በረድኤት የሚገለጥባት ቀን ናትና፤



፳፱፤ ወኵላ ነፍስ እንተ ኢታሐምም ርእሳ በይእቲ ዕለት ለትሠሮ ወትደምሰስ እምሕዝባ ፤

በዚችም ቀን ራሷን የማታሳዝን ሰውነት ሁሉ ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ፤

፴፤ ወነኵላ ነፍስ እንተ ትገብር ግብረ በይእቲ ዕለት ለትደምሰስ እምሕዝባ ፤

በዚችም ቀን ሥራ የምትሠራ ሰውነት ሁሉ ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ፤

፴፩፤ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ በኵሉ በኀበ ሀለውክሙ ፤

ባላችሁበት ዘመን ሁሉ የዘለዓለም ሕግ ይሁናችሁ ፤

፴፪፤ ሰንበተ ሰንበታት ይእቲ ለክሙ አሕምምዋ ለነፍስክሙ እምተሱዑ ለወርኅ እምሠርክ እስከ ሠርክ አሡሩ ለወርኅ አሜሃ አሰንብቱ ሰንበተክሙ ፤

ከበዓላት የምትበልጥ በዓል ናትና፤ አንድም በሱባዔ የምትቈጠር በዓል ናትና ጥቅምት በባተ በዘጠነኛው ቀን ከሠርክ ጀምሮ እስከ አሥረኛው ቀን ሠርክ ድረስ ሰውነታችሁን አሳዝኗት፤ በዓላችሁንም አክብሩ ፤

፴፫፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፴፬፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ አመ አሡሩ ወሐሙሱ ለውእቱ ወርኅ በዓለ መጸለት ሰቡዓ ዕለተ ለእግዚአብሔር ፤

ጥቅምት በባተ በአሥራ አምስተኛው ቀን በዓለ መጸለትን ሰባት ቀን አክብሩ፤ በዓለ መጸለት ማለት በዓለ ጽላሎት ማለት ነው ፤

፴፭፤ ወዕለት ቀዳሚት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ወኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ፤

መጀመሪያዪቱ ቀን ለናንተ የከበረች ናትና የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት ፤

፴፮፤ ሰቡዓ ዕለተ ታበውኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፤

ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ ፤

ወሳምኒትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፤

ስምንተኛዪቱም ቀን ለናንተ የከበረች ናትና ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ዘፀዓት ውእቱ ኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትግበሩ ባቲ ፤

ሰውና ሰው ‹ሰውና በዓል› የሚለያዩበት ነውና፤ አን ድም መሰናበቻ ቀን ነውና የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ አትሥሩባት ፤

፴፯፤ እሉ እሙንቱ በዓላቲሁ ለእግዚአብሔር ዘሰመይክምሙ በስም ቅዱስ በዘቦሙ ያበውኡ መባአ ለእግዚአብሔር ወቍርባነ ወመሥዋዕቶሙኒ ወሞፃሕቶሙኒ ዘኵሉ አሚር ፤

ቅዳሜ ቅዳሜ ከሚያቀርቡት መሥዋዕት በቀር መባውን ቍርባን መሥዋዕት አድር ገው በሚያቀርቡባቸው ገንዘብ በክቡር ስም የጠራኋቸው የእ ግዚአብሔር በዓላት እሊህ ናቸው፤

፴፰፤ ዘእንበለ ሰናብቲሁ ለእግ ዚአብሔር ወዘእንበለ ዘመባእክሙ ወዘእንበለ ዘኵሉ ብፅዓቲክሙ ወዘእንበለ በፈቃድክሙ ዘታበውኡ ለእግዚአብሔር ፤

በፈቃዳችሁ መባችሁን ስለታ ችሁን ለእግዚአብሔር ከምታ ቀርቡባቸው በዓላት በቀር የእግዚአብሔር በዓላት እሊህ ናቸው ፤

፴፱፤ ወአመ ዕለተ አሡሩ ወሐሙሱ ለውእቱ ሳብዕ ወርኅ አመ ፈጸምክሙ አስተጋብኦተ እክለ ምድርክሙ ትገብሩ በዓለ ለእግዚአ ብሔር ሰቡዓ ዕለተ ፤

ሰባተኛው ወር ጥቅምት በባተ በአሥራ አምስተኛው ቀን የምድራችሁን እህል መሰብ ሰብ በጨረሳችሁ ጊዜ ለእግዚ አብሔር ሰባት ቀን በዓል አድርጉ ፤

ወዕለት ቀዳሚት ዕረፍት ይእቲ ወዕለትኒ ሳምኒት ዕረፍት ይእቲ፤

መጀመሪያዪቱና ስምንተ ኛዪቱ ቀን ዕረፍት ናት አለ፤ በዓል ናት፤ ‹ሐተታ› እን ዳለፈው ፤

፵፤ ወትነሥኡ ለክሙ አመ ዕለተ ቀዳሚት እምፍሬ ዕፅ ዘሠናይ ፤

ሱባዔውን በምትጀምሩባት በመጀመሪያዪቱ ቀን ከመል ካሙ እንጨት ፍሬ ቆርጣ ችሁ ያዙ ፤

ወፀበርተኒ ወበቀልተ ተመርት ወእምዕፅ ቈጽለ አዕፁቅ ወዘኰሓኒ ወዘእምነ ፈለግኒ አዕፁቀ ዘንጹሕ ወትትፌሥሑ ቅድመ እግዚአ ብሔር አምላክክሙ ሰቡዓ ዕለተ በበዓመት ፤

ፀበርት ግንዱ ከነቅጠሉ፤ ተመ ርትና በቀልት ፍሬው ነው፤ የዘንባባውን ቅጠል ከነፍሬው



ከእንጨቱም ቅጠሉን ከነጫፉ የአኻያውንም ቅጠል ከነጫፉ ከወንዝ የሚገኘውን ለጋ ለጋ ውን ቅጠል ዳስ አድርጋችሁ፤ ጥላ ጥላችሁ በዓለ መጸለትን አክብሩ፤ በየዓመቱ በፈጣሪ ያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ቀን ደስ ይበላችሁ ፤

፵፩፤ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ ከመ ትግበሩ በዓለ በሳብዕ ወርኅ ፤

በሰባተኛው ወር በጥቅምት በዓል ታደርጉ ዘንድ በዘመናችሁ ሁሉ የዘለዓለም ሕግ ይሁናችሁ፤

፵፪፤ ወትነብሩ ውስተ መጸለት ሰቡዓ ዕለተ ኵሉ ዘእምፍጥረቱ እስራኤል ይንበር ውስተ መጸለት፤

ትውልዱ እስራኤል የሆነ ሰው ሁሉ ሰባት ቀን በመ ጸለት ውስጥ ማለት በጥላው ውስጥ ተቀመጡ፤ ደመና ጋርዶ ከግብጽ አወጣነ ለማ ለት ነው ፤

፵፫፤ ከመ ይርአዩ ትውልድክሙ ከመ በምጽላል አንበርክዎሙ ለእስራኤል አመ አውጻእክዎሙ እምድረ ግብጽ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚ አብሔር እስራኤልን ከግብጽ ሀገር በአወጣኋቸው ጊዜ በጥላ እንዳስቀመጥኋቸው ማለት ደመና ጋርዷ እንዳወጣኋቸው የልጅ ልጆቻችሁ ያዩ ዘንድ ‹ያውቁ ዘንድ› ፤

፵፬፤ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስ ራኤል ኵሎ በዓላቲሁ ለእግዚአ ብሔር እግዚእ ፤

ሙሴም የባሕርይ ገገር ፈጣሪ የሆነ የእግዚአብሔርን በዓል ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው።

## ምዕራፍ ፳፬

ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ያምጽኡ ለከ ቅብዓ ዘይት ንጹሐ ወውጉዓ ለማኅቶት በዘተኀትዉ ማኅቶተ ኵሎ ጊዜ አፍኣ እመንጦላዕት ዘደብተራ መርጡል፤

ልዩ በሆነች ድንኳን ከመጋ ረጃው በአፍኣ በአሥራ ሁለቱ ሰዓተ ሌሊት ሁሉ መብራት በምታበሩ ገንዘብ የተከለሰውን የጠራውን ዘይት ለመብራት ያመጡልህ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ብሎ ነገረው፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ ወያኀትዉ አሮን ወደቂቁ እም ሠርክ እስከ ነግህ ቅድመ እግዚ.አብሔር ለዘልፍ ሕገ ዘለዓለም ይኩንክሙ በመዋዕሊክሙ ፤

ባለ ዘመናችሁ ሁሉ ሕግ ይሆናችሁ ዘንድ ሊቀ ካህናቱ አሮንና ልጆቹ ሌዋውያን ከደ ብተራ ኦሪት መጋረጃ በአፍኣ በእግዚ.አብሔር ፊት ያብሩት ፤

፬፤ ወዲበ መራናት እንተ ንጽሕት አኀትዉ ውእተ ማኅቶተ ቅድመ እግዚ.አብሔር እስከ ይጸብሕ ፤

ያንንም መብራት ከሠርክ ጀምራችሁ እስኪ.ነጋ ድረስ ንጽሕት በሆነች መቅረዝ ላይ በእግዚ.አብሔር ፊት አብሩት፤

፭፤ ወንሥኡ ሥንዳሴ ወግበሩ ዓሠርተ ወክልኤተ ኅብስተ ዘክልኤቱ ዓሥራት ይኩን አሐዱ ኅብስቱ ፤

ልጦ ጕርዶ የወጣውን ስንዴ አምጥታችሁ አሥራ ሁለት ዳቦ ጋግሩ፤ ሁለቱ ቁና ስንዴ አንድ ዳቦ ይሁን ፤

፮፤ ወትሠርዕዎ ምክብዒተ ስድስተ ኅብስተ ወትሠርዕዎ አሐተኔ ዲበ ማዕድ ንጽሕት ቅድመ እግዚአብሔር፤

ስድስቱን ዳቦ እጥፍ አድርጋችሁ በእግዚ.አብሔር ፊት በነጻች ማዕድ ላይ ባንድነት ሥሩት ፤

፯፤ ወትሠርዐ ምስሌሁ ስኂነ ንጹሐ ወጼወ ወይኩን ውእቱ ኅብስት ለተዝካር ሥሩዐ ቅድመ እግዚ.አብሔር ፤

ጨው በርበሬ ጨምሩበት፤ ይህም ኅብስት ለመታሰቢያ በእግዚ.አብሔር ፊት ለዘወትር የተሠራ ይሁን፤ ስድስቱን በነግህ ይሠዉ.ታል፤ ‹ይመገቡታል›፤ የቀረውን ስድስቱን በሠርክ ይመገቡታልና ፤

፰፤ ወበዕለተ ሰንበት ትሠርዕዎ ለዘልፍ በኀበ ደቂቀ እስራኤል ወሕግ ዘለዓለም ውእቱ ፤

ቅዳሜ ቀን በየሳምንቱ በእስ ራኤል ልጆች ዘንድ ሥሩት፤ እሱም የዘለዓለም ሥርዓት ነው ፤

፱፤ ወይኩን ለአሮን ወለደቂቁ ፤

ለሊ.ቀ ካህናቱ ለአሮንና ለል ጆቹ ለሌዋውያን የዘለዓለም ሕግ ይሁን፤

ወይብልዕዎ በመካን ቅዱስ እስመ ቅዱስ ዘቅዱሳን ውእቱ ሎሙ እምዘ ይሠውዑ ለእግዚ.አብሔር፤

ለእግዚ.አብሔር ከሚሠዉት የእ ስራኤል መሥዋዕት ለነሱ የከ በረ ነውና በከበረ ቦታ ይብሉት፤



ሕግ ዘለዓለም ውእቱ፤

ይኸውም የዘለዓለም ሥርዓት ነው፤

፲፤ ወወፅአ ወልደ ብእሲ.ት እስራኤላዊት፤

በዚ.ያም ወራት የአንዲ.ት ዕብ ራዊት ልጅ ወጣ አለ፤ በነገር ተነሣ፤

ወአቡሁሰ ግብጻዊ በማዕከለ ደቂቀ እስራኤል፤

አባቱ ግን በእስራኤል ልጆች መካከል የሚኖር የግብጽ ሰው ነው፤

ወተበዓሱ በውስተ ትዕይንት ወልደ ብእሲ.ት እስራኤላዊት ወብእሲ. እስ ራኤላዊ፤

ያ የዕብራዊት ልጅና አንድ ዕብራዊ በሰፈር ውስጥ ተጣሉ፤ የተጣሉበት ምክንያት አልታ ወቀም፤

፲፩፤ ወሰመየ ወልዳ ለእንታክቲ ብእሲ.ት እስራኤላዊት ወረገመ ስመ እግዚአብሔር፤

የዚ.ያች ዕብራዊት ልጅም የእ ግዚ.አብሔርን ስም ጠርቶ ተሳደበ፤ በግብጽ ሳለሁ ጌታህ አልነበርሁምን ብሎ ስመ እግ ዚ.አብሔርን ነቀፈ፤ ይህም ስመ

እግዚ.አብሔርን በመንቀፉ የሐ ሳዊ መሢ.ሕ ፊታውራሪ ነው፤

ወአምጽእዎ ኀበ ሙሴ፤

ከሰሰው ወደ ሙሴ አመ ጡት፤

ወስማ ለእሙ ሰሎሚ.ት ወለተ ዳቤር ዘእምነገደ ዳን፤

የናቱም ስሟ ከነገደ ዳን የተወለደ የዳቤር ልጅ ሰሎ ሚ.ት ነው፤

፲፪፤ ወወደዮ ውስተ ሞቅሕ እስከ ይኳንኖ በትእዛዘ እግዚ.አብሔር፤

ሙሴም ቢ.መረምረው አዎን ስላለ በእግዚ.አብሔር ትእዛዝ እስኪ.ቀጣው ድረስ በግዞት ቤት አሥሮ አኖረው፤

፲፫፤ ወነበበ እግዚ.አብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚ.አብሔር ለሙሴ እንዲ.ህ ብሎ ነገረው፤

፲፬፤ አውፅኦ አፍኣ ለዘረገመ እምትዕይንት ወይደዩ እደዊሆሙ ዲበ ርእሱ ኵሎሙ እለ ሰምዕዎ ወይውግርዎ በዕብን ኵሎሙ ትዕይንት፤

እግዚ.አብሔርን የተሳደበውን ሰው ከከተማ ወደ ውጭ አውጣውና ሲ.ሳደብ የሰሙት

www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ሁሉ እጃቸውን በራሱ ላይ አኑረው በደንጊያ ወግ ረው ይግደሉት፣ ፍዳህ በራስህ ነው ሲሉ፤

፲፭፤ ወንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ ለእመ ረገመ አምላከ ጌጋየ ይከውኖ፤

አንዱም አንዱም ሰው ፈጣ ሪውን ቢሰድብ ዕዳ በደል ይሆንበታል፤

፲፮፤ እስመ ሰመየ ስመ እግዚአብሔር ሞተ ለይሙት ወበዕብን ለይውግርዎ ኵሉ ትዕይንት፣

የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ተሳድቧልና የሞት ሞት ይሙት፣ ሕዘቡም ሁሉ በደንጊያ ወግ ረው ይግደሉት፤

፲፯፤ እመኒ ግዩር ወእመኒ ዘእምፍ ጥረቱ እስራኤል እምከመ ሰመየ ስመ እግዚአብሔር ለይሙት፣

መጻተኛም ቢሆን ትውልዱ ከእስራኤልም ቢሆን የእግዚአ ብሔርን ስም ጠርቶ ከተሳደበ በደንጊያ ተወግሮ ይሙት፤

፲፰፤ ወኵሉ ብእሲ ዘቀተለ እምኵሉ ነፍሰ ሰብእ ለይቅትልዎ፣

ከሰው ወገን ነፍስ የገደለ ሰው ቢኖርም ይግደሉት፤

ወእመሰ ቀተለ እንስሳ ይፍዲ ነፍሰ ህየንተ ነፍስ፣

ከእንስሳ ወገን የገደለ ቢኖር ግን ተባት ቢሆን ተባት፣ እን ስት ብትሆን እንስት ከብት ይክፈል፤

፲፱፤ ወእመሰ ዘአቍሰለ ካልኦ በከመ ገብረ ላዕለ ካልኡ ከማሁ ይግበሩ ላዕሌሁ፣

ወንድም ወንድሙን መትቶ ያቈሰለ ቢኖር ግን በወንድሙ እንዳደረገ በሱም ያድርጉበት፤ አለ እንዳቈሰለ ያቍስሉት፤

፳፤ ስብረት ህየንተ ስብረት፣ ወዓይን ህየንተ ዓይን ወስን ህየንተ ስን በከመ አቍሰለ ሰብአ ከማሁ ይግበሩ ላዕሌሁ፣

እጁን እግሩን ቢሰብረው እጁን እግሩን ይስበሩት፣ ዓይኑን ቢያጠፋው ዓይኑን ያጥፉት፣ ጥርሱን ቢሰብረው ጥርሱን ይስበሩት፣ እሱ ሰውን እንዳቈ ሰለ በሱም እንደዚያው ያድር ጉበት ማለት እንዳቈሰለ ያቍ ስሉት፤ ነሣሣለትና ጠቅልሎ አመጣው፤

፳፩፤ ወዘዘበጠ ሰብአ ወቀተለ ሞተ ለይሙት፣

ሰውንም መትቶ የገደለ ሰው የሞት ሞት ይሙት፤



፳፪፤ አሐዱ ውእቱ ኵነኔሆሙ ለግዩርኒ ወለዘእምፍጥረቱኒ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

የመጻተኛውም ትውልዱ እስ ራኤላዊ የሆነውም ቅጣታ ቸው አንድ ነው፣ ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፤

፳፫፤ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወአውጽእዎ ለዘጸረፈ አፍአ እምትዕይንት ወወገርዎ በዕብን ኵሉ ተዓይን፣

ሙሴም እግዚአብሔር የነገረ ውን ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው፣ የእግዚአብሔርን ስም የነቀፈውን ሰውም ከከ ተማ ውጭ አውጥተው ሕዝቡ ሁሉ በደንጊያ ደብድበው ገደሉት፤

ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

የእስራኤልም ልጆች እግዚአ ብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ።

## ምዕራፍ ፳፭

### ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ በደብ ረሲና እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበ ሎሙ እመ ቦእክሙ ውስተ ምድር እንተ አነ እሁበክሙ ተዓርፍ ምድር ወታሰንብት ለእግዚአብሔር፣

እኔ ወደምሰጣችሁ ወደ ከነ ዓን በገባችሁ ጊዜ ምድሪቱ ለእግዚአብሔር ዕረፍትን ታድ ርግ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው፤

፫፤ ስድስተ ዓመተ ትዘርእ ገራኅ ተከ ወስድስተ ዓመተ ትገምድ ወይነከ ወታስተጋብእ ፍሬሁ፣

ስድስት ዓመት እርሻህን ዝራ፤ ስድስት ዓመትም ወይንህን ቈርጠህ ፍሬውን ሰብስብ፤ አሁን በስድስተኛው ዓመት የሚዘሩ ሁኖ አይደለም መሰብሰቢያውን ሲያይ እንዲህ አለ እንጂ፤

፬፤ ወበሳብዕ ዓም ሰንበት ዕረፍታ ውእቱ ለምድር ወታሰነብት ለእግ ዚአብሔር፣

በሰባተኛው ዓመት ግን የም ድር ዕረፍት ነውና ምድር ከመታረስ ከመቆፈር ለእግዚ አብሔር ዕረፍት ታድርግ፤

ገራህተከኒ ኢትዝራእ ወዓፀደ ወይን ከኒ ኢትግምድ፣

እርሻህን አትዝራ፣ የወይንህንም ዘለላ አትቁረጥ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ ወዘለሊሁ ይበቊል ውስተ ገራህትከ ኢትዐፅድ ወአስካለ ወይንከኒ ዘቅዱስ ኢትቅስም በይእቲ ዓመት እስመ ዕረፍታ ለምድር ውእቱ፡፡

የምድር ዕረፍት ነውና በሰባተኛው ዓመት በርሻህ የበቀለውን ገቦውን አትጨድ፡፡ የተለየ የወይንህንም ዘለላ አትልቀም፤

፮፤ ወይኩን ውእቱ ዘሰንበታ ለምድር መብልዓ ለከ ወለገብርከ ወለአመትከ ወለገባኢከ ወለፈላሲከኒ ዘየኀድር ኀቤከ፡፡

ምድር ዕረፍት ባደገረችበት ዓመት የተገኘው ፍሬ ላንተ፡፡ ለወንድ ባሪያህ፡፡ ለሴት ባሪያህ፡፡ ለምንደኛህም፡፡ ባንተ ዘንድ ለሚኖር ስደተኛም ይሁን አለ፡፡ ሂዳችሁ ብሉት ከቤት ግን አታግቡት ሲል ነው፤

፯፤ ወለእንስሳከ ወለአራዊተ ምድርኒ ይኩንክሙ መብልዐ ኵሉ እክሉ፡፡

ካንተም የተረፈው እህል ሁሉ በምድር ላሉ አራዊትና እንስሳት ምግብ ይሁን፤

፰፤ ወትኌልቈ ለከ ሰብዓተ ሰናብተ ዕረፍተ ዘስድስቱ ዓመት ዘምስብዒት፡፡

የስድስቱን ዓመት እጥፍ ዕረፍት የምታደርግበትን ሰባቱን አንድ ሰባቱን አንድ እያልህ ቍጠር፤

ወእምዝ ትሬሲ ለከ ሰቡዓ ሰናብተ በዘትዜንዉ በመጥቅዕ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ በ፵፱ ወ፱ቱ ዓመት፡፡

ሰባቱን አንድ ሰባቱን አንድ እያልህ ከቈጠርህ በኋላ ባርባ ዘጠነኛው ዓመት በሀገራችሁ ሁሉ ነጋሪት መትታችሁ አዋጅ የምትነግሩበት የኢዮቤልዩ በዓል ይሁን፤

፱፤ ወበሳብዕ ወርኅ በዕለተ አስተርእዮ ትዜንዉ በመጥቅዕ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ፡፡

በባለሟልነት በምትገለጡባት፤ አንድም ጌታ በረድኤት በሚገለጥበት ዕለተ አስተርእዮ ቢል፡፡ ኃጢአታችሁ በሚሠረይበት በሰባተኛው ወር በጥቅምት በሀገራችሁ ሁሉ ነጋሪት እየመታችሁ አንዱ ኢዮቤልዩ ተፈጸመ፡፡ አንዱ ኢዮቤልዩ ተጀመረ በሉ፤

ወቀድስዋ ለይእቲ ዓመት ዘሃምሳ ኵላ ዓመታ፡፡

አምሳኛዪቱንም ዘመን ዓመቷን ሁሉ አክብሯት፤

፲፤ ወስብኩ ተኃድጎ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ፡፡



በሀገራችሁ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ባርባ ዘጠኝ ዓመት ኢዮቤልዩን አክብሩ ብላችሁ አስተምሩ፤

እስመ ዓመተ ተኀድጎ ውእቱ፡፡

ዓመተ ኅድገት ነውና ማለት ሰው ከሥራ የሚያርፍበት ነውና፤ አንድም ሰው ከመገዛት የሚለይበት ነውና፤

ወተአምረ ይኩንክሙ፡፡

አርባ ዘጠነኛው ዘመን፤ አንድም ሃምሳኛው ዘመን ምልክት ይሁናችሁ፤

ወይእቲ ኵሉ ውስተ ርስቱ ወይሑር ኵሉ ውስተ ሀገሩ፡፡

ሰው ሁሉ በዓመተ ኅድገት ወደ ርስቱ ይግባ፡፡ ወደ ሀገሩም ይመለስ፤

፲፩፤ ወትእምርተ ተኃድጎ ይኩንክሙ ውእቱ ዓመት ዘሃምሳ፡፡

አምሳኛውም ዓመት የዕረፍት ምልክት ይሁናችሁ፤

ወኵላ ዓመታ ኢትዝርኡ ወኢትዕፅዱ እንበለ ዘበቈለ ለሊሁ፡፡

በአምሳኛው ዓመት ሳትዘሩት ከበቀለው ከገቦው በቀር ዘርታችሁ አትጨዱ፤

ወኢትቅስሙ ዘተቀደሰ ባቲ እስመ ትእምርተ ተኃድጎ ውእቱ፤

የዕረፍት ምልክት ነውና (ዓመተ ኅድገት ነውና) ለምግብ የተለየባትን ያምስተኛውንም ዓመት ወይን አትልቀሙ፤ ወይን በተተከለ በሦስተኛው ዓመት ያፈራል፡፡ ያን አዕዋፍ ይበሉታል፡፡ ያራተኛው ዓመት ለቤተ እግዚአብሔር ይሆናል ፤ ያምስተኛው ዓመት ለባለቤቱ ይሆናልና እንዲህ አለ፤

፲፪፤ ወቅዱሰ ይኩንክሙ፤

ዓመተ ኅድገት የተለየ በዓል ይሁናችሁ፤

ወብልዑ ዘእምውስተ ገዳም እክለ፡፡

በስምንተኛው ዓመት ከተዘራው ብሉ፤ አንድም በምድረ በዳ ከተገኘው ብሉ፡፡ እህል ከቤት ይበቅላልና እንዲህ አለ ቢሉ ገቦውን ሲያይ እንዲህ አለ፤

፲፫፤ ወበይእቲ ዓመት ዘትእምርተ ተኃድጎ የአቱ ኵሉ ውስተ ርስቱ፡፡

በዓመተ ኅድገት ሰው ሁሉ ወደርስቱ ይግባ ፡፡ (ይእቲ ዓመት የሚላት) አርባ ዘጠነኛዪቱን ዓመት ነው፤

፲፬፤ ወእመኒቦ ዘተሠይጠ ኀበ ካልኡ ኢያጽሕቦ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ድኃው ከባለጸጋው ዘንድ የተ
ገዛው መገዛት ቢኖር በዓመተ
ኅድገት ባለጸጋው ድኃውን
ገንዘቤን አምጣ ብሎ አያስ
ጨንቀው፤

እስመ እምድኅረ ዓመተ ተኃድጎ
ይሠየጥ ለካልኡ፣

ከዓመተ ኅድገት በኋላ ለሌላ
ተገዝቶ ይሰጠዋልና፤

፲፭፤ ወበመዋዕለ ይዘርኡ እክለ
በውእቱ ዓመት ይፈድዮ በአምጣነ
ብዝኆን ለእላንቱ ዓመታት ወያ
በዝኅ ጥሪቶ፤

በመዋዕል ዘይዘራእ ሲል
ነው፣ እህል በሚዘራበት በስ
ምንተኛው ዓመት ተገዝቶ
ይክፈለው፣ እንደ ዘመኑ ብዛት
መጠን በዘመኑ ብዛት ልክ
ደመወዙን ያብዛለት፤ አንድም
ከዓመተ ኅድገት በኋላ ያስቀ
ረበትን ገንዘብ እንደ ገንዘቡ
ብዛት መጠን አብዝቶ ይስጥ፤

፲፮፤ ወአመ ይትኃደጋ ውእቶን
ዓመታት ይትኃደግ ተሠይጦ፣

ስድስት ዓመትም በተፈጸመ
ጊዜ ዓመተ ኅድገት ነውና
ለድኃው መገዛት ይቅርለት፤

ወበመዋዕለ ይዘራእ እክል ይፈድዮከ፤

እህል በሚዘራበት በስምን
ተኛው ዓመት ተገዝቶ ይከፍ
ልኻልና፤

፲፯፤ ወኢታጽሕቦ ለካልእከ ወፍ
ራህ እግዚአብሔርሃ አምላክከ
እስመ አነ እግዚአብሔር አምላ
ክክሙ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር
ነኝና ፈጣሪህ እግዚአብሔርን
ፍራው፣ በዓመተ ኅድገት ድኃ
ውን ግድ አምጣ ብለህ አታስ
ጨንቀው፤

፲፰፤ ወግበሩ ኵሎ ኵነኔየ ወፍት
ሕየ ወዕቀብዎ፣

ኵነኔየ ዘጠኙን ሕግጋት
ነው፤ (ፍትሕየ) ኢታምልክን
ጠብ ቃችሁ ሥሩት፤

ወትነብሩ ውስተ ምድርክሙ ተአ
ሚነክሙ፣

ሕጌን የጠበቃችሁ እንደሆነ
ጠላት ጠፍቶላችሁ ተዘል
ላችሁ በሀገራችሁ ትኖራ
ላችሁ፤

፲፱፤ ወትሁበክሙ ምድር ፍሬሃ
ወትበልዑ ወትጸግቡ፣

በልታችሁ ትጠግቡ ዘንድ
ምድርም ፍሬዋን ትሰጣች
ኋለች፤



፳፤ ወእመሰ ትብሉ ምንተ ንበልዕ
በውእቱ ሳብዕ ዓመት ለእመ ኢዘ
ራእነ ወለእመ ኢያስተጋባእነ እክለ፣

ካልዘራን ካልሰበሰብን በሰባተ
ኛው ዓመት ምን እንበላለን
ብትሉ ግን ፤

፳፩፤ አነ እፌኑ ለክሙ በረከትየ
ወአመ ሳድስ ዓመት ትገብር ፍሬሃ
ምድር ዘሠለስቱ ዓመት እክለ፣

እኔ በረከቴን እልክላችኋለሁ፤
ምድርም በስድስተኛው ዘመን
የሦስቱን ዓመት እህል ታፈ
ራለች፤

፳፪፤ ወትዘርኡ እምኔሁ በሳምን
ዓም፣

ከስድስተኛው ዓመት የተረ
ፈውን በስምንተኛው ዓመት
ትዘራላችሁ፤

ወትበልዑ እምውእቱ እክል፣ ከራሚ
እስከ ታስዕ ዓም እስከ አመ
ይበጽሕ እክል ትበልዑ ብሉየ
ከራሚ፣

ትበልዑና ትበልዑ ከራሚና
ከራሚ አንድ ወገን፣ ከከረመ
ውም ከስድስተኛው ዓመት
እህል አዲሱ እህል እስከ
ሚደርስበት እስከ ዘጠነኛው
ዓመት ብሉ፤

፳፫፤ ወምድርኒ ኢትሠየጥ ሥሉጠ
እስመ እንቲአየ ይእቲ ምድር

ይች ምድር የኔ ገንዘብ ናትና
በውጭ አትሸጥ ማለት ለአ
ሕዛብ አትሸጧት ሲል ነው፤

አንትሙኒ ግዩራነ ወፈላስያነ ኮን
ክሙ በቅድሜየ፣

እናንተም ስደተኛና መጻተኛ
ሁናችሁ ነበርና፤

፳፬፤ ወበኵሉ ደወለ ምድርክሙ
ነበ ምኵናን ዘዚአክሙ ታቤዝዉ
ምድረ፣

የናንተ ጉልት በሆነ በሀገ
ራችሁ አውራጃ ሁሉ ምድ
ርን ትቤዣላችሁ ማለት ለድ
ኃው አስጠምኑት ሲል ነው፤

፳፭፤ ወለእመ ነድየ ካልእከ ዘምስ
ሌከ ወሤጠ ለከ ምድሮ፣

ካንተ ጋር የሚኖረው ወንድ
ምህ ቸግሮት ምድሩን ላንተ
ቢሸጥልህ፤

ወእምዝ መጽአ ዘቅሩቡ ዘይሰክዮ
(ዘይኰስዮ) ታቤዝዎ ዘሤጠ ለከ
እኁሁ ፣

ዘይትካፈሎ ሲል ነው፣ ከዚህ
በኋላ በሥጋ የሚቀርበው
ርስት የሚካፈለው ሰው
ቢመጣ ወንድሙ የሸጠልህን
ውርስ ለሚገባው ወንድሙ
አስጠምነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፤ ወእመኒ አልቦ ዘይከውኖ ወእምዝ ረከበ ውእቱ ውስተ እዴሁ ወአዕከለ ለቤዝዎቱ ይኄልቍ ሎቱ ዓመተ ዘእምአመ ሤጠ፤

የሚካፈለው ወንድም ባይኖረው ከሸጠለትም በኋላ የሚቤዥበት የበቃ ገንዘብ በእጁ ቢያገኝ ከሸጠለት ቀን ጀምሮ ዓመቱን ይቍጠሩለት፤

፳፯፤ ወይፌድዮ በመጠነ በጽሑ ለውእቱ ብእሲ ዘነቤሁ ሤጠ ወያገብእ ሎቱ ገራህቶ፤

ለሸጠለትም ሰው የደረሰውን ያህል በደረሰው ልክ ገንዘቡን ይክፈለው ፤ የገዛውም ሰው ገንዘቡን ተቀብሎ እርሻውን ይመልስለት፤

፳፰፤ ወእመሰ ኢረከበ ውስተ እዴሁ በአምጣነ ይፌድዮ ይከውን ገራህቱ ለዘተሣየጠ እስከ ዓመተ ተኀድጎ፤

የሚከፍለው ገንዘብ በእጁ ባያገኝ ግን እስከ ዓመተ ኀድገት ድረስ በሚከፍለው ገንዘብ ልክ እርሻው ለገዛው ሰው ይሁነው፤

ወበዓመተ ተኀድጎ ያገብእ ሎቱ ገራህቶ ለዘሤጠ፤

ዓመተ ኀድገት በሆነ ጊዜ ግን እርሻውን ለሸጠለት ድኃ ይመልስለት፤

፳፱፤ ወለእመቦ ዘሤጠ ቤቶ በውስተ ሀገር እንተ ባቲ ቅጽር እስከ ይፈጽም መዋዕለ ይእቲ ዓመት ይከውኖ ለቤዝዎ፤ ወያቤዝውዎ፤

እንደ ዘጌ እንደ ቈራጣ ቅጽር ባለበት ሀገር ያለች ቤቱን የሸጠ ሰው ቢኖር የገዛው ሰው የገዛበትን ዘመን እስኪፈጽም ድረስ መቤገር ይገባዋል፤ እነሱም ይቤገሯት ማለት ገንዘቡን መልሰው ቦታቸውን መውሰድ ይገባቸዋል፤ የገዛው ሰው ከዓመት አስቀድሞ ቅጽር አይቀጽርበትም ተክል አይተክልበትም ነበርና፤

፴፤ ወእመሰ ተፈጸመት ኵላ ይእቲ ዓመት ወኢቤዘዎ ሥሉጠ ይከውኖ ውእቱ ቤት ለዘተሣየጠ፤

የገዛባት ዘመን ብትፈጸም ግን ለሻጩ ሰውጥ ሁና ትቅርለት፤ የገዛትም ሰው ከዚህ በኋላ ተክል ይትክልባት፤ ቅጽር ይቅጸርባት ይህ የሀገሩ ሥርዓት ነውና፤

ወኢያእትውዎ ሎቱ ውእተ ቤተ ዘሀለወ ውስተ ሀገር እንተ ባቲ ቅጽር ወይከውኖ ለውሉደ ውሉዱ ወኢይነሥእዎ እምኔሁ በዓመተ ተኀድጎ፤



ቅጽር ባለባት ሀገር ያለ ያን ቤት ለሻጩ አይመልሱለት፤ ለገዛው ሰው ለልጅ ልጁ ይሁነው እንጂ በዓመተ ኀድገትም ጊዜ ከርሱ አይውሰዱበት፤

፴፩፤ ወአብያተሰ ዘውስተ ሀገር እንተ አልባቲ ቅጽር ዓውዳ ከመ ገራህተ ምድር ይትቤዘውዎ፤

ዓውዳ ለሀገር ነው፤ በዙሪያዋ ቅጽር በሌላት ሀገር ውስጥ ያሉ ቤቶችን ግን በዓመተ ኀድገት ጊዜ እንደ እርሻ መሬት ለባለ መሬቱ ይመልሱለት፤

ወበኵሉ ጊዜ ያቤዝውዎ ወበዓመተ ተኀድጎኒ ያገብእዎ፤

በየጊዜው ሁሉ ይቤገሉለት፤ በዓመተ ኀድገትም ጊዜ ይመልሱለት፤

፴፪፤ ወአህጉረ ሌዋውያንኒ ይትቤዘዉ በኵሉ ጊዜ አብያቲሆሙ ዘውስተ አህጉሪሆሙ ያቤዝውዎሙ ለሌዋውያን፤

የሌዋውያንንም ቦታ በየጊዜው ይቤገሩት ማለት ይግዙት፤ በሀገራቸው ውስጥ ያለ ቤታቸውንም ቢሆን ለሌዋውያን ይቤገሩአቸው፤ ያስጠምኗቸው፤

፴፫፤ ወኵሉ ዘተቤዘወ እምነበ ሌዋውያን እመኒ አብያት ዘውስተ አሕጉሪሆሙ ዘገብአ ለአብዕልቲሁ ተሠይጠ ዘአግብአ ሎቱ በዓመተ ተኀድጎ በደወለ ዚአሆሙ፤

ለሌዋውያን አስጠምኖ በዓመተ ኀድገት የመለሱለት ሰው ቤቱንም ቢሆን መሬቱንም ቢሆን ዓመተ ኀድገት ሲያልፍ ለሌላ ሰው ቢያስጠም ነው፤

እስመ አብያተ አበዊሆሙ ወአህጉሪሆሙ ለሌዋውያን ውእቱ ወምክፍናኒ ዘዚአሆሙ ይኩን በማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ቤቱ የአባቶቻቸው ነውና፤ አገሩም የሌዋውያን ነውና በእስራኤል ልጆች መካከል ያለ ርስቱ ጉልቱ ለካህናት ይሁን፤

፴፬፤ ወገራውህኒ ዘደወለ አህጉሪሆሙ ኢይሠየጣ እስመ ደወሎሙ ውእቱ ዘለዓለም፤

የዘለዓለም ርስታቸው ነውና በሀገራቸው ያለ እርሻቸውም አይሸጥ፤

፴፭፤ እመኒ ነድየ ካልዕከ ዘምስሌከ ወስእነ ተገብሮ በነቤከ ተዓቅቦ ከመ ግዩር ወፈላሲ ወይሕዮ ካልእከ ዘምስሌከ፤

www.ethiopianorthodox.org

ባጠገብህ ከአንተ ጋር የሚኖር ወንድምህ አጥቶ ቢቸገር፣ ማረስ መቆፈርም ባይሆንለት፣ ባንተ ዘንድ እንደ ስደተኛ እንደ መጻተኛ ተንከባከበው፣ ድኃው ወንድምህም ከአንተ ጋር ይኑር፤

፴፮፤ ወኢትንሣእ እምኔሁ ርዴ ወኢ እመ ብዙኃ አጕንደየ፣

ገንዘብ አበድረኸው ብዙ ዘመን ቢያቆየው ከርሱ አራጣ አት ቀበል፤

ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላከከ እስመ አነ እግዚአብሔር፣

የምሰጥ የምነሳ እኔ እግዚ አብሔር ነኝና ፈጣሪህ እግዚ አብሔርን ፍራ፤

፴፯፤ ወኢተሀቦ ወርቀከ በርዴ ወእክለከኒ ኢትትረደዮ፣

ገንዘብህን እህልህን በአራጣ አታበድረው፤

፴፰፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአውጻእኩክሙ እም ድረ ግብጽ ከመ አሀብክሙ ምድረ ከነዓን ወእኩንክሙ አምላክክሙ፣

አባክሙ ሲል ነው፣ የፍቅር አባት እሆናችሁ ዘንድ የከነ ዓንንም ምድር አወርሳችሁ ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣ ኋችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እግ ዚአብሔር ነኝና፤

፴፱፤ ወእመ ተፀነሰ ካልእከ ወተሠ ይጠ ኀቤከ ኢይትቀነይ ለከ ከመ ገብር፣

ወንድምህ ተቸግሮ ባንተ ዘንድ ቢቀጠር እንደ ባሪያ አይባል (አይሁን)፤

፵፤ አላ ከመ ገባኢ ወከመ ፈላሲ ይኩንከ እስከ ዓመተ ተኃድጎ ይት ቀነይ ለከ፣

እንደ ዕለት ምንደኛ እንደ መጻተኛ ሁኖ እስከ ዓመተ ኅድገት ድረስ ያገልግልህ እንጂ፣

፵፩፤ ወበዓመተ ተኃድጎ ይወጽእ ውእቱ ወደቂቁ ምስሌሁ ወይገብእ ኀበ አዝማዲሁ ወውስተ ደወሉ ወየሐውር ብሔሮ፤

በዓመተ ኅድገት ጊዜ ግን እሱም ልጆቹም ወጥተው ከዘ መዶቻቸው ዘንድ ወደ ሀገ ራቸው ይሂዱ፤

፵፪፤ እስመ አግብርተ ዚአየ እሙ ንቱ እለ አውፃእኩ እምድረ ግብጽ ኢይሠየጡ ከመ ዘይሠየጥ ገብር፤

ከግብጽ ምድር ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ ናቸውና እንደሚ ሸጥ ባሪያ አይሸጡ አይለ ወጡ፤



፵፫፤ ወኢታጥቆ በፃማ ወፍራህ እግዚአብሔርሃ አምላከከ፣

ድሀውንም በግፍ በሐሰት አታ ስጨንቀው፣ ፈጣሪህ እግዚአ ብሔርን ፍራ እንጂ፤

፵፬፤ ወገብረሰ ወአመተኒ መጠነ ረከብከ እምአሕዛብ እለ ዓውድ ክሙ እምኔሆሙ ታጠርዩ ገብረኒ ወአመተኒ

እምአሕዛብና እምኔሆሙ አንድ ወገን፣ ወንድ ባሪያን ሴት ባሪያን ግን ያገኘኸውን ያህል በዙሪያችሁ ካሉ ከአሕዛብ ግዙ፤

፵፭፤ ወእምደቂቆሙኒ ለእለ የኃድሩ ምስሌክሙ እምኔሆሙ ታጠርዩ፣

ይህም ባይሆን ተማርከው ከናንተ ዘንድ ከሚኖሩ ልጆቻ ቸው ግዙ፤

ወእምአዝማዲሆሙኒ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ምድርክሙ ለጥሪትክሙ ይኩንክሙ፤

በሀገራችሁ ከሚኖሩ ከዘመ ዶቻቸውም ወገን ገንዘብ ይሆ ናችሁ ዘንድ ግዙ፤

፵፮፣ ወለውሉድክሙኒ ትከፍል ዎሙ ወይኩኑክሙ ለጥሪትክሙ ለዓለም፣

ለዘለዓለም ገንዘብ ይሆኗችሁ ዘንድ ለልጆቻችሁም አድሏ ቸው ማለት ከልጆቻችሁ ጋር በወንድምነት ይኑሩ፤

ወዘእምአኃዊከ ደቂቀ እስራኤል አሐዱ አሐዱ ኢያጥቆ ለካልኡ በፃማ፣

ከእስራኤል ልጆች ከወንድ ሞቻችሁ አንዱም አንዱም ወንድሙ በሐሰት በግፍ አያ ስጨንቀው፤

፵፯፤ ወእመሰ ኢረከበ ውስተ እዴሁ ውእቱ ግዩር ወእመኒ ገዘንቱ ፈላሲ ዘኀቤከ፣

ባንተ ዘንድ የሚኖር መጻተ ኛም፣ ስደተኛም ቢሆን በእጁ ገንዘብ ባያገኝ፤

፵፰፤ ወይቤሉከ ሰብአቲሁ አቤዝ ወነዮ ለዝንቱ ግዩር አው ለዝንቱ ፈላሲ ዘኀቤከ፣

ባንተ ዘንድ የሚኖረው መጻ ተኛ ስደተኛ ከገዛኻቸው በኋላ ወገኖቹ መጥተው ተቤዠን ቢሉህ ማለት መልስልን ቢሉህ፤

እመኒ ዘሰብአቲሁ ለውእቱ ግዩር ተቤዝዎ ይትቤዘዎ አሐዱ እም ሰብአቲሁ፣

www.ethiopianorthodox.org

ነው፤ ዓይናችሁን የሚያፈስ በሽታ አመጣባችኋለሁ፤ ሰውነታችሁም እንደ ሰም ትቀልጣለች፤

ወትዘርኡ ለከንቱ ዘርአክሙ ወይበልዑክሙ ፀርክሙ፤

እህላችሁን በከንቱ ትዘራላችሁ፤ ጠላቶቻችሁ ያጠፉትኋል፤

፲፯፤ ወእቀውም ገጽየ ላዕሌክሙ ወትወድቁ ቅድመ ፀርክሙ፤

እኔ ገጸ መዓቴን አጸናባችኋለሁ፤ በጠላቶቻችሁ ፊት ድል ተነስታችሁ ትወድቃላችሁ፤

ወያነትዑክሙ እለ ይጸልኡክሙ ወትነትዑ እንዘ አልቦ ዘይዴግነክሙ፤

የሚጠሏችሁ ሰዎች ድል ይነሷችኋል፤ የሚከተላችሁ ሰው ሳይኖር ትሸሻላችሁ፤

፲፰፤ ወእመ እስከ ዝንቱ ኢሰማዕክሙኒ እዌስክ መቅሠፍተክሙ ሰብዓተ መቅሠፍተ በእንተ ኃጣውኢክሙ፤

ይህን ሁሉ አድርጌባችሁ ነገሬን ባትቀበሉኝ እኔም ስለሠራችሁት ኃጢአት በመቅሠፍት ላይ መቅሠፍትን አመጣባችኋለሁ፤

፲፱፤ ወእሰብር ፅዕለተ ትዕቢትክሙ ወእሬስያ ለክሙ ለሰማይ ከመ ሐፂን ወለምድርኒ ከመ ብርት፤

ትዕቢትን ከልቡናችሁ፤ ስድብን ከአንደበታችሁ አጠፋለሁ፤ ሰማይን እንደ ብረት፤ ምድርንም እንደ ብርት አደርጋለሁ ማለት ሰማይ ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር እንዳይሰጥ፤ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል፤ የተከሉባትን እንዳታጸድቅ አደርጋለሁ፤

፳፤ ወይከውን ለከንቱ ኃይልክሙ ወኢትሁበክሙ ምድር ዘርአ ወዕፀወ ገዳምኒ ኢይሁቡክሙ ፍሬሆሙ፤

ኃይላችሁ ለከንቱ ይሆናል ማለት ላትረቡ ላትጠቀሙ ትደክማላችሁ፤ ምድርም የዘራችሁባትን አታበቅልም፤ የተከላችሁባትንም አታጸድቅም ፤ በምድረ በዳ ያሉ እንጨቶችም ፍሬያቸውን አይሰጧችሁም (አያፈሩላችሁም)፤

፳፩፤ ወእመኒ እምድኅረ ዝንቱ ሖርክሙ ግድመ ወኢፈቀድክሙ ትስምዑኒ እዌስከክሙ ሰብዓተ መቅሠፍተ በከመ ኃጣውኢክሙ፤

እንዲህም ካደረግሁባችሁ በኋላ ባጠገብ ብትኖሩ ማለት እስራኤል ነን እያላችሁ ግብረ አሕዛብ ብትሠሩ እኔን ልትሰ



ሙኝ ባትወዱ እንደ ኃጢአታችሁ ብዛት በመቅሠፍት ላይ መቅሠፍትን አመጣባችኋለሁ፤

፳፪፤ ወእፌኑ ላዕሌክሙ አራዊተ ምድር እኩያነ ወይበልዑክሙ ወያጠፍዑ እንስሳክሙ፤

የሚነክሷችሁ አራዊትን እሰ ነማባችኋለሁ፤ እነሱም ይበሏችኋል፤ ከብቶቻችሁንም ያጠፋሉ፤ እየገደሉ ይበሉባችኋልና፤

ወውኅዳነ ያተርፉክሙ ወበድወ ይሬስዩ ፍናዊክሙ፤

ሰውን ገድለው ከብቱን በልተው ጥቂት ጥቂት ያስቀሩላችኋል፤ እነሱ አገነውላቸው ማለት አይደለም፤ ሸሽተው አምልጠው የቀሩትን መናገር ነው፤ መንገዳችሁንም፤ ምድረ በዳ ያደርጉታል፤ መንገዱ ሰው፤ ከብት ካልሄደበት ምድረ በዳ ይሆናልና፤

፳፫፤ ወእመኒ እስከ ዝንቱ ኢፈራህክሙኒ አላ ሖርክሙ ግድመ ምስሌየ አነኒ አሐውር በመዓት ግድመ ምስሌክሙ፤

እስራኤል ነን እያላችሁ ግብረ አሕዛብ የምትሠሩ እናንተ ይህን ሁሉ አድርጌባችሁ ካል ፈራችሁኝ እኔም ከናንተ አጠገብ በቁጣ እኖራለሁ ማለት «መሐሪ ወመስተሣህል» እየተባልኩ የማልምልዳችሁ፤ ይቅር የማልላችሁ እሆናለሁ፤

ወእትቤቀለክሙ አነኒ ምስብዒተ በእንተ ኃጣውኢክሙ፤

እኔም ስለ ኃጢአታችሁ እጥፍ አድርጌ እበቀላችኋለሁ፤

፳፬፤ ወእመጽእ ላዕሌክሙ መጥባሕተ እንተ ትዴግነክሙ፤

እየተከተለች የምታጠፋ ጦርን አመጣባችኋለሁ፤ አንድም ሥልጣኔን እገልጻለሁ፤

ወትትቤቀለክሙ በቀለ ኪዳንየ ወትጕይዩ እምውስተ አህጉሪክሙ፤

መሐላዬ ተበቅላ ታጠፋችኋለች፤ የሚከተላችሁም ሳይኖር ከሀገራችሁ ትሸሻላችሁ፤

፳፭፤ ወእፌኑ ሞተ ላዕሌክሙ ወትገብኡ ውስተ እደ ፀርክሙ፤

ሞትን አመጣባችኋለሁ በጠላቶቻችሁም እጅ ትወድቃላችሁ፤

፳፮፤ ወሶበ አሕመምክሙ ኃጢአ እክል ዘትሴሰዩ ወያበስላ ዐሥሩ አንስት ኅብስተ በአሐዱ እቶን ወይሁባክሙ ኅብስተክሙ በመድሎት ትበልዑ ወኢትጸግቡ፤

www.ethiopianorthodox.org

የምትበሉት እህል አጥታችሁ በተቸገራችሁ ጊዜ ዐሥር ሴቶች ባንድ ምድጃ እንጀራ ይጋግራሉ፤ ለዚህ ብለን እየራሳችን እንጋግራለን? ብለው፤ እንጀራችሁንም ‹በሚዛን ማለት› መጥነው ያቀርቡላችኋል፣ በልታችሁ አትጠግቡም፣ ረድኤት መንሣቱን መናገር ነው ፤

፳፯፤ ወእመኒ እስከ ዝንቱ ኢሰማዕክሙኒ አላ ሖርክሙ ምስሌየ ግድመ ፤

ይህን ሁሉ አድርጌባችሁ ባትሰሙኝ ከኔ ጋር ባጠገብ ኖራችሁ እንጂ ማለት ግብረ አሕዛብ ሠራችሁ እንጂ እኔን ባትሰሙኝ ፤

፳፰፤ ወአነኒ አሐውር ምስሌክሙ በመዓት ግድመ ፤

እኔም ባጠገባችሁ በቁጣ እኖራለሁ ማለት አላድናችሁም ፤

ወእቀሥፈክሙ አነኒ ምስብዒተ በከመ ኃጣውኢክሙ ፤

እኔም እንደ ኃጢአታችሁ ብዛት መቅሠፍቱን ሰባት እጥፍ አድርጌ አመጣባችኋለሁ አለ፣ በሥጋ በነፍስ አጠፋችኋለሁ ሲል ነው ፤

፳፱፤ ወትበልዑ ሥጋ ደቂቅክሙ ወሥጋ አዋልዲክሙ ፤

የወንዶች ልጆቻችሁንና የሴቶች ልጆቻችሁን ሥጋ ትበላላችሁ፣ በኢዮራም ጊዜ እንደ ተደረገ ፤

፴፤ ወእደመስስ ምስሌክሙ ወእሜሩ ግብረ እደዊክሙ ዘዕፀው፣

ጣዖታችሁን እሰብራለሁ፣ ቢጋራችሁን አጠፋለሁ፣ የእጃችሁ ሥራ የሚሆን የእንጨቱን ጣዖት አጠፋለሁ፤

ወእዘሩ አብድንቲክሙ ላዕለ ምስለ አማልክቲክሙ ወትትቄጥዓክሙ ነፍስየ ፤

በጣዖታችሁም ምስል ላይ ሬሳችሁን እንሥቼ እጥላለሁ፣ ልቡናዬም ትበሣጭባችኋለች፤

፴፩፤ ወእገብሮን ለአህጉሪክሙ መዝበረ ወእደመስስ ቅድሳቲክሙ ወኢያዌኑ መዓዛ መሥዋዕቲክሙ፣

ሀገሮቻችሁን ፍራሽ አደርጋቸዋለሁ፣ ንዋየ ቅድሳታችሁንም አጠፋለሁ፣ የመሥዋዕታችሁን መዓዛም አልቀበልም ፤

፴፪፤ ወእሬስያ አነ ለምድርክሙ በድወ ወይዴመሙ በእንቲአሃ ፀርክሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ ፤

ምድራችሁን ምድረ በዳ አደርጋለሁ፣ በውስጧ የሚኖሩ ጠላቶቻችሁም በሀገራችሁ ጥፋት ይደነቃሉ፣ ሰው ሲጠፋ አገር ምድረ በዳ ይሆናልና ፤



፴፫፤ ወእዘርወክሙ ውስተ አሕዛብ ወታጠፍአክሙ መጥባሕት በኀበ ሖርክሙ ፤

በአሕዛብ አገር እበትናችኋለሁ፣ ሸሽታችሁ በሄዳችሁበትም አገር በሰይፍ አጠፋችኋለሁ፤

ወትከውን ምድርክሙ በድወ ወአህጉሪክሙኒ ይከውና ምዝቡረ፣

ምድራችሁ ባድማ ትሆናለች፣ ሀገሮቻችሁም ፍራሽ ይሆናሉ፤

፴፬፤ ወይእተ አሚረ ይኤድማ ለምድር ሰናብቲሃ በኵሉ መዋዕለ ሙስናሃ ፤

ያን ጊዜ በጥፋቷ ወራት ምድርን ዕረፍቷ ደስ ያሰኛታል ፤

፴፭፤ ወአንትሙኒ ትሄልዉ ውስተ ምድረ ጸላእትክሙ ፤

እናንተም ተማርካችሁ በጠላቶቻችሁ አገር ትኖራላችሁ ፤

ወይእተ አሚረ ታሰነብት ምድር ወይኤድማ ለምድር መዋዕለ ሙስናሃ ፤

ያን ጊዜም ምድር ዕረፍት ታደርጋለች፣ የጥፋቷ ወራትም ደስ ያሰኛታል ፤

ወታሰነብት ከመ ኢያሰንበተት በሰንበታቲክሙ አመ ሀለውክሙ ትነብሩ ውስቴታ፣

በውስጧ ሳላችሁ በበዓላችሁ ያላረፈችውን ያህል እናንት በጠፋችሁበት ወራት ዕረፍት ታደርጋለች ፤

፴፮፤ ወለእለ ተርፉኒ እምኔክሙ አመጽእ ድንጋፄ ውስተ ልቦሙ በምድረ ርስቶሙ ፤

ከናንተ ሸሽተው የተረፉትንም በርስታቸው ሳሉ በልቡናቸው ሽብር አመጣለሁ፤

ወይሜምዑ እምድምፀ ቈጽል ዘይትሐወስ ወይነትዑ ከመ ዘይነትዕ እምፀር ወይወድቁ እንዘ አልቦ ዘይዴግኖሙ ፤

በነፋስ ምክንያት ከሚንቀሳቀስ ቅጠል ድምፅ የተነሣም ይሸሻሉ፣ ከጠላቱ ፊት የሚሸሽ ሰው እየወደቀ እየተነሣ እንዲሸሽ እነሱም የሚከተላቸው ሳይኖር ይሸሻሉ ፤

፴፯፤ ወይትዔወሮ ብእሲ ለእኁሁ ከመ ዘውስተ ቀትል እንዘ አልቦ ዘይዴግኖሙ ወኢትክሉ ተቃውሞቶሙ ለፀርክሙ ፤

በሰልፍ ያለ ሰው ወንድሙን ቸል እንዲል፣ እሊህም የሚከተላቸው ሳይኖር ወንድም ወንድሙን ቸል ይለዋል ፤ ጠላቶቻችሁንም መከራከር አትችሉም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፰፤ ወትጠፍዑ በውስተ አሕዛብ ወትውኅጠክሙ ምድረ ፀርክሙ ፤

ተማርካችሁ ሂዳችሁ በአሕዛብ አገር ትሞታላችሁ፤ የጠላቶቻችሁም ምድር መቃብር ትሆናችኋለች ፤

፴፱፤ ወእለ ተርፉ እምኔክሙ ይደመሰሱ በእንተ ኃጣውኢሆሙ ወበእንተ ኃጣውአ አበዊሆሙ ወይትመሰዉ በምድረ ፀሮሙ ፤

ከናንተም ሸሽተው ሂደው የተረፉ ሰዎች በራሳቸውም ባባቶቻቸውም ኃጢአት ይጠፋሉ፤ በጠላቶቻቸውም ምድር እንደ ሰም ይቀልጣሉ፤ ‹ሐተታ› በአባቶቻቸው ኃጢአት የሚጠፉ ሁኖ አይደለም፤ መስለው ኃጢአት ይሠራሉ፤ ሕጉን ያፈርሳሉ፤ በዚያው ይጠፋሉና እንዲህ አለ፤

፵፤ ወያየድዑ ኃጣውኢሆሙ ወኃጣይአ አበዊሆሙ ከመ ክሕዱኒ ወተዓወሩኒ ወከመ ሖሩ ግድመ በቅድሜየ ፤

መከራውም ባማታቸው ጊዜ የራሳቸውንም ያባቶቻቸውንም ኃጢአት ይናገራሉና ቸል ብለው እንደካዱኝ በገቢረ ኃጢአት በአምልኮ ጣዖት እንደኖሩም ይናገራሉ፤

፵፩፤ ወአነሂ ሖርኩ ምስሌሆሙ ግድመ በመዓት ወአጠፍኦሙ በምድረ ፀሮሙ ፤

እኔም ከነሱ ጋር ባጠገብ ሳለሁ ማለት ይቅር ባይ አምላክ ስሆን ይቅር እንዳላልኋቸው ከመከራውም እንዳላዳንኋቸው ይናገራሉ፤ በጠላቶቻቸው አገር አጠፋቸዋለሁ ፤

ወይትኃፈር ልቦሙ ዘኢኮነ ግዙረ ወይእተ አሚረ ይገንዩ ለኃጣውኢሆሙ ፤

እንዲህም አድርጌ ባጠፋኋቸው ጊዜ ከኃጢአት ያልተለየ፤ ‹አላዋቂ ያይደለ› ልቡናቸው በመከራው ያፍራል፤ ያን ጊዜም ስለኃጢአታቸው ይለማመጣሉ ይገዛሉ ማለት ንስሐ ይገባሉ ፤

፵፪፤ ወውእተ አሚረ እዜከር ኪዳንየ ዘምስለ ያዕቆብ ወኪዳንየ ዘምስለ ይስሐቅ ወኪዳንየ ዘምስለ አብርሃም እዜከር ፤

‹‹እዜከርና እዜከር አንድ ወገን››፤ ያን ጊዜ ንስሐቸውን አይቼ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የማልሁትን መሐላዬን አስባለሁ አለ፤ ይቅር እላቸዋለሁ ሲል ነው ፤

ወለምድርኒ እዜከራ ፤

ምድርንም አስባታለሁ አለ፤ ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር እሰጣታለሁ፤



፵፫፤ ወትትኃደግ ምድር እምኔሆሙ ፤

ከነሱ ኃጢአት የተነሣ ምድርም ትጠፋለች ፤

ወይእተ አሚረ ትትዌከፍ ምድር ሰናብቲሃ ሶበ ማሰነት በእንቲአሆሙ ፤

በነሱ ምክንያት ከጠፋች በኋላ ያን ጊዜ ምድር ዕረፍት ታደርጋለች ፤

ወእሙንቱኒ ይትዌከፉ ኃጣውኢሆሙ እስመ ተዓወሩ ኵነኔየ ወተቀጥዓት ነፍሶሙ ትእዛዝየ ፤

ሕጌን ቸል ብለዋልና፤ ልቡናቸውም ትእዛዜን ሰልችታለችና እነሱም የኃጢአታቸውን ፍዳ ይቀበላሉ ፤

፵፬፤ ወአኮ እንዘ ሀለዉ ውስተ ምድረ ጸላእቶሙ ዘተዓወርክዎሙ ወኢተቈጣዕክዎሙኒ ከመ አጥፍኦሙ ፤

አጠፋቸው ዘንድ ቸል ያልኋቸው የተቈጣሁባቸውም በጠላቶቻቸው አገር ሳሉ ብቻ አይደለም፤ በአገራቸውም ሳሉ ነው እንጂ ፤

እስመ ኀደጉ ኪዳንየ ዘነቤሆሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላኮሙ ፤

ፈጣሪያቸው እኔ እግዚአብሔር ስለሆንሁ በሳቸው ዘንድ ያለውን ሕጌን አፍርሰዋልና፤

፵፭፤ ተዘከርኩ ኪዳኖሙ ዘቀዳሚ ዘከመ አውፃእክዎሙ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት ፤

ቀድሞ የማልሁላቸውን መሐላ አስቤ ለፈርዖን ከመገዛት ከግብጽ ምድር ባወጣኋቸው ጊዜ፤

እንዘ ይሬእዩ አሕዛብ ከመ እኩኖሙ አምላኮሙ አነ እግዚአብሔር፤

ፈጣሪ እሆናቸው ዘንድ ማለት የፍቅር አባት እሆናቸው ዘንድ አሕዛብ እያዩ ከግብጽ ያወጣኋቸው እኔ እግዚአብሔር የሠራሁላቸውን ሕግ አፍርሰዋልና ፍዳ ኃጢአታቸውን ይቀበላሉ ፤

፵፮፤ ዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወሕግ ዘወሀበ ማዕከሌሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወማዕከሌሁ በደብረ ሲና በእደ ሙሴ ፤

እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆችና በርሱ መካከል በደብረ ሲና በሙሴ ቃል የሠራው ሕግ ይህ ነው፤ ‹‹ትእዛዝ ዘጠኙ ቃላት›› ኵነኔ ኢታም ልክ ሕግ የወል ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፯

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ እመቦ ዘበፅዓ ብፅዓተ ህየንተ ቤዛ ነፍሱ ለእግዚአብሔር ፤

ከእስራኤል አንዱም አንዱም ለራሱ መዳኛ ‹ቤዛ› ሊሆነው እግዚአብሔርን አገለግላለሁ ብሎ የተሳለ ሰው ቢኖር ፤

፫፤ ወይኩን ሤጡ ለተባዕት ዘእምእስራ ዓም እስከ ስሳ ዓም ዲድርክመ ብሩር በመዳልው ዘቅዱስ፤

ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ስድሳ ዘመን ያለው የወንዱ ዋጋ በተለየ (በከበረ) አዋቂ (ሚዛን) አምሳ ወቄት ይሁን ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው፤

፬፤ ወለአንስትሰ ይኩን ሤጣ ሠላሳ ዲድርክመ ብሩር ፤

‹‹እንስት ካለ ሤጦን›› ሤጣም ካለ ብእሲት ባለ በቀና ነበር፤ ልማደ መጽሐፍ ነው ፤ ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ስልሳ ዘመን ያለች ሴትም ብትሳል፤

አንድም እስከ ስልሳ ዘመን አገለግላለሁ ብላ የተሳለች ሴት ብትኖር ሠላሳ ወቄት ትስጥ፤ የወንዱን አብዝቶ የሴቲቱን አሳነሰ፤ ሴት ደካማ ናትና ፤

፭፤ ወእመሰ ዘእምሐምስቱ ዓም እስከ እስራ ዓም ይኩን ሤጡ ለተባዕት እስራ ዲድርክም ፤

ከአምስት ዘመን ጀምሮ እስከ ሃያ ዘመን ያለ የወንዱ ዋጋ ሃያ ወቄት ይሁን ፤

ወለአንስትሰ ዓሠርቱ ዲድርክመ ብሩር ፤

የሴቲቱ ግን ዓሥር ወቄት ይሁን ፤

፮፤ ወእመሰ ዘእምአሐዱ ወርኅ እስከ ሐምስቱ ዓም ይኩን ሤጡ ለተባዕት ሐምስተ ዲድርክሙ ብሩር፤

ካንድ ወር (ካንድ ዘመን) ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ አገለግላለሁ ብሎ የተሳለ ሰው አምስት ወቄት ይስጥ፤

ወለአንስትሰ ሠለስተ ዲድርክመ ብሩር፤

የሴቲቱ ግን ሦስት የብር ወቄት ይሁን ፤



፯፤ ወእመሰ ዘእምስሳ ዓም ወላዕሉ ለእመ ተባዕት ውእቱ ይኩን ሤጡ ዓሠርተ ወሐምስተ ዲድርክመ ብሩር ፤

ከስድሳ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለ ሰው የወንዱ ዋጋ ዐሥራ አምስት የብር ወቄት ይሁን ፤

ወለአንስትሰ ዐሠርቱ ዲድርክመ ብሩር ፤

የሴቲቱ ግን ዐሥር የብር ወቄት ይሁን ፤

፰፤ ወእመሰ ኅጡዕ ውእቱ ለአምጣነ ሤጡ ይቀውም ቅድመ ካህን ፤

ለዋጋው ልክ ያጣ ቢሆን ግን በሊቀ ካህናቱ ፊት ቆሞ ያስገምግም ፤

ወይበፅዖ ሤጦ ካህን በአምጣነ ቦቱ ውስተ እዴሁ በዘይክል ውእቱ ዘበፅዓ ከማሁ ይበፅዖ ካህን ሤጦ፤

ዘበፅዓና ይበፅዖ አንድ ወገን ነው፤ የተሳለውም ሰው በሚችል ገንዘብ በእጁ ባለው ገንዘብ ልክ ሊቀ ካህናቱ ዋጋውን ገምግሞ ያቆየው ፤

፱፤ ወእመሰ እምእንስሳ እምዘይክውን ለአብኦ ቍርባን ለእግዚአብሔር እምኔሁ ዘአምጽአ እምውስተ ቅዱስ ፤

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ከሚሆን ከእንስሳ ወገን ያመጣ ሰው ቢሆን ፤

፲፤ ኢይወልጥ ሠናዮ በእኩይ ወኢእኩዮ በሠናይ ፤

መልካሙን በክፉ አይለውጥ ማለት ደኅነኛውን በዕውር በአንካሳ አይለውጥ፤ አንድም ከቤት ያለውን ላሙን በሬውን ከበረሀ ታድኖ በመጣው በጎሽ፤ በአጋዘን፤ በድኩላ አይለውጥ፤

ወእመሰ ወልጦ ወለጠ እንስሳ በዘውጉ ይከውኖ ወተውላጡኒ ቅዱስ ውእቱ ፤

ከብቱንም ቢለውጠው በመሰሉ ይለውጠው፤ ለውጡም የከበረ ነው ፤

፲፩፤ ወእመሰ እምኵሉ እንስሳ ዘርኵስ ዘኢያበውኡ እምኔሁ ቍርባነ ለእግዚአብሔር ታቀውሞ ለውእቱ እንስሳ ቅድመ ካህን ፤

ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርገው ከማያቀርቡት ከርኩሱ እንስሳ ወገን ቢሆን ያን ከብት በካህኑ ፊት አቁመው፤

፲፪፤ ወያበፅዖ ካህን ማዕከለ ሠናይኒ ወማዕከለ እኩይኒ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሊቀ ካህናቱ በንጹሕና በርኵሱ መካከል ዋጋውን ይገምግመው ፤

ወበከመ በፅዖ ካህን ከማሁ ይከውን ሤጡ ፤

ዋጋውም ካህኑ እንደገመገመው ይሁን ፤

፲፫፤ ወእመሰ ቤዝዎ ቤዘወ ይዌስክ ሐምስተ እዴሁ ላዕለ ሤጡ ፤

ካህኑ ሳያይ ራሱ ቢገመግመው ግን በዋጋው ላይ አምስት እጅ ይጨምር ፤

፲፬፤ ወእመሰ በፅዓ ብእሲ ቤቶ ለእግዚአብሔር ወቀደሳ ወይበፅዓ ካህን ሤጣ ማዕከለ ሠናይት ወማዕከለ እኪት ፤

ቤቱን ለይቶ ለእግዚአብሔር የተሳለ ሰው ቢኖር ግን ካህኑ በእልፍኙና በአዳራሹ (በትልቁና በትንሹ) መካከል ሆኖ ዋጋውን ይገምግም ፤

ወበአምጣነ በፅዓ ሤጣ ካህን ከማሁ ትከውን ፤

ዋጋዋ ካህኑ በገመገመው ልክ ይሁን ፤

፲፭፤ ወእመሰ ውእቱ ዘበፅዓ ቤዘዋ ለቤቱ ይዌስክ ላዕለ ወርቀ ሤጡ ሐምስተ እዴሃ ወትገብእ ሎቱ ፤

የተሳለው ሰው ግን ካህኑ ሳያይ ራሱ ቤቱን ቢገመግም በዋጋዋ ላይ አምስት እጅ ይጨምር፤ ቤቱም ትመለስለት ፤

፲፮፤ ወእመሰ እምገራውሂሁ ዘዚአሁ በፅዓ ብእሲ ለእግዚአብሔር ወይሬስዩ ሤጦ በአምጣነ እትወተ እክሉ በመስፈርተ ቆሮስ ዘሰገም ሐምሳ ዲድርክመ ብሩር ፤

ሰው ከእርሻው ለእግዚአብሔር እሰጣለሁ ብሎ ቢሳል ገብስ በሚሰፍሩበት ቆሮስ በሚባል መስፈሪያ በእህሉ አገባብ መጠን ዋጋው አምሳ ወቄት ይሁን፤ ቆሮስ የሚባለው መስፈሪያ ዐሥራ ሁለት ጫን የሚይዝ ነው ፤

፲፯፤ ወእመሰ እምዓመተ ኀድገት በፅዓ ለገራህት ውእቱ በከመ ሐሳበ ሤጡ ፤

እርሻውን ከዓመተ ኀድገት ጀምሮ ቢሳል ግን በየዓመቱ እንደሚያወጣው እያስገመተ ይስጥ ፤

፲፰፤ ወእመሰ በዓመት ዘእምድኅረ ኀድገት በፅዓ ለገራህቱ ከመ ውእቱ የሐስብ ሎቱ ካህን ወርቆ ለዓመት ዘተርፈ እስከ ዓመተ ኀድገት ወይገድፍ ሎቱ እምሤጡ ፤

ከዓመተ ኀድገት በኋላ እርሻውን እሰጣለሁ ብሎ ቢሳል



ግን ካህኑ እስከ ዓመተ ኀድገት የቀረውን የዓመቱን ዋጋ ገምቶ ከዋጋው ይተውለት ፤

፲፱፤ ወእመሰ ለሊሁ ዘበፅዓ ለገራህቱ ቤዘዋ ይዌስክ ዲበ ወርቀ ሤጣ ሐምስተ እዴሃ ወትገብእ ሎቱ ገራህቱ ፤

ነገር ግን የተሳለው ሰው ለሊቀ ካህናቱ ሳያሳይ እርሻውን ራሱ ቢገመግማት በዋጋዋ ላይ አምስት እጅ ይጨምር እርሻው ትመለስለት ፤

፳፤ ወእመሰ እምድኅረ ቤዘዋ ለገራህቱ ሤጣ ኀበ ካልእ ብእሲ ኢይቤዝዋ እንከ ዳግመ ፤

ነገር ግን ከተቤዠት በኋላ እርሻውን ለሌላ ቢሸጣት ዳግመኛ ልቤዠት አይበል፤ አንድም ለካህን ካስጠመናት በኋላ ለጨዋ ቢያስጠምናት ተመልሳ ለሱ አትሁን ፤

፳፩፤ አላ ትከውን ገራህቱ ቅድስተ ወስብሕተ ለእግዚአብሔር ፤

ለእግዚአብሔር የተለየች የከበረች ናትና እርሻው ለካህኑ ትሁን እንጂ ፤

ወበዓመተ ኀድገትኒ ውፅእት ይእቲ እምኔሁ ወኢትገብእ ሎቱ ከመ ምድር እንተ ፍልጠት ለካህኑ በደወሉ ትከውን ፤

ዓመተ ኀድገትም በሚደረግበት ዘመን ከሱ የተለየች ናትና ለካህን እንደ ተለየች ምድር ለሱ አትመለስለትም፤ በአውራጃ እንዳለች ለካህኑ ትሁን እንጂ ፤

፳፪፤ ወእመሰ እምገራህት ዘተሣየጠ በፅዓ ለእግዚአብሔር እምዘኢኮነ ዘደወሉ ፤

አውራጃው ካይደለ እርሻ የገዛ ሰው ለእግዚአብሔር ቢሳል ግን ፤

፳፫፤ የሐስብ ሎቱ ካህን ክበበ ሤጡ እምዓመተ ኀድገት ወይሁብ ሤጦ በይእቲ ዕለት ብፅዓተ ለእግዚአብሔር ፤

‹‹ትልቁ ሤጡ ሲል ነው›› ከዓመተ ኀድገት ጀምሮ የዋጋውን ልክ ካህኑ ይገምግምለትና ለእግዚአብሔር እሰጣለሁ ብሎ የተሳለውን በዚያች ቀን ይስጥ ፤

፳፬፤ ወበዓመተ ኀድገት ይገብእ ውእቱ ገራህት ለዝክቱ ብእሲ ዘእምኀቤሁ ተሠይጠ እስመ ዚአሁ ውእቱ ምድሩ ፤

መሬቱ ርስቱ ነውና በዓመተ ኀድገት ለሸጠው ለዚያ ሰው እርሻው ይመለስለት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፭፤ ወኵሉ ሤጡ በመዳልው ቅዱስ ዕሥራ አቦሊ አሐዱ ዲድ ርክም ፤

ዋጋው ሁሉ በተለየ ዓዋቂ (በሚዛን) ሃያ አቦሊ አንድ ድሪም ይሁን አለ፤ ሃያው አቦሊ አንድ ድሪም፤ አንዱም ድሪም አንድ ወቄት ነው፤

፳፮፤ ወኵሉ በኵር ዘይትወለድ እምእንስሳከ ለእግዚአብሔር ውእቱ፤

ከመንጋህ መጀመሪያ የሚወለደው ሁሉ ለእግዚአብሔር ነው ፤

ወአልቦ ዘይዌልጥ መኑሂ እመኒ ላሕም ወእመኒ በግዕ ለእግዚአብሔር ውእቱ ፤

ላምም ቢሆን በግም ቢሆን መጀመሪያ የተወለደው ለእግዚአብሔር ነውና ማንም ማን የሚለውጥ አይኑር ፤

፳፯፤ ወእመሰ እምእንስሳ ዘርኵስ ይዌልጦ በሐሳበ ሤጡ ፤

ለእግዚአብሔር ከማይገባ ከብት ወገን ቢሆን ግን በዋጋው ልክ ይለውጠው ፤

ወእመሰ ለሊሁ ቤዘዎ ይዌስክ ሐምስተ እዴሁ ላዕሌሁ ወይገብእ ሎቱ ፤

እሱ ቢገመግመው ግን በዋጋው ላይ አምስት እጅ ጨምሮ ከብቱ ይመለስለት ፤

ወእመሰ ኢቤዘዎ ይሠይጥዎ በሐሳበ ሤጡ፤

ባይገመግመው ግን በዋጋው ልክ ይሸጡት ፤

፳፰፤ ወኵሉ ዘአብአ ሰብእ ለእግዚአብሔር እምኵሉ ዘቦ እምሰብእ እስከ እንስሳ ፤

ካለው ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ ለእግዚአብሔር ያገባ ሰው ሁሉ፤

ወእመኒ እምገራሁቱ ዘደወሉ ኢይሠይጥዎ ወኢይቤዝውዎ ፤

በአውራጃው ካለ ከእርሻም ቢሆን አይሸጡት አይቤዡት፤ (አይለውጡት)

ኵሉ መባእ ቅዱስ ዘቅዱሳን ለእግዚአብሔር ውእቱ ፤

እስራኤል ያቀረቡት የተለየ መባ ሁሉ ለእግዚአብሔር ነውና ፤

፳፱፤ ወኵሉ መባእ ዘአብአ ሰብእ ዘይከውን ኢይትቤዞ እስከ አመ ይመውት ፤

ሰው ያገባው ለእግዚአብሔር የሚገባው የሰው መባ ሁሉ



እስኪሞት ድረስ አይቤዥም ማለት አይለወጥም፤ እንደ ሳሙኤል እንደ እመቤታችን ያለው ነው ፤

፴፤ ወኵሉ ዓሥራታ ለምድር ዘእምዘርአ ምድር ወእመኒ ዘእምፍሬ ዕፅ ዘእግዚአብሔር ቅዱስ ውእቱ ለእግዚአብሔር ፤

ከምድር አዝመራ የተገኘ የምድር ዐሥራት ሁሉ እግዚአብሔር ካበቀለው ከእንጨት ፍሬም ቢሆን የተገኘው ለእግዚአብሔር የተለየ ነው ፤

፴፩፤ ወእመሰ ቤዝዎ ቤዘወ ሰብእ ዐሥራቲሁ ይዌስክ ላዕሌሁ ሐምስተ እዴሁ ፤

ነገር ግን ሰው ዐሥራቱን ለሊቀ ካህናቱ ሳያሳይ ራሱ ቢገመግም በዓይነቱ ላይ አምስት እጅ ጨምሮ ይስጥ፤

፴፪፤ ወኵሉ ዓሥራት ዘላሕም ወዘበግዕ ወኵሉ ዘይትኀዳዕ በበትር ለኈልቈ ቅዱስ ውእቱ ዓሥራቲሁ ለእግዚአብሔር ፤

የበግ፤ የላም ዓሥራት ሁሉ ለመቁጠርም በበትር የሚነዳው ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ዐሥራቱ ነው ፤

፴፫፤ ወኢይዌልጥዎ ሠናዮ በእኩይ ወኢእኩዮ በሠናይ ፤

መልካሙን በክፉ፤ ክፉውን በመልካም አይለውጡት ማለት ደኅነኛውን በዕውሩ፤ በአንካሳው አይለውጡት ፤

ወእመሰ ወልጦ ወለጠ ቅዱስ ውእቱ ተውላጡ ወኢይትቤዞ ፤

ቢለውጠው ግን ለውጡ (የተለየ) ንጹሕ ይሁን አይቤዥው ማለት በማይገባ አይለውጠው ፤

፴፬፤ ዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ከመ ይንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ለእስራኤል ልጆች ያስተምራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ያዘዘው ትእዛዝ የሠራው ሥራት ይህ ነው ፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘሌዋውያን ወስብሐት ለእግዚአብሔር ተውካፌ መሥዋዕት ወቍርባን ፤

አነሣሥቶ ላስጀመረን፤ አስጀምሮ ላስፈጸመን፤ መሥዋዕቱን፤ ቍርባኑን ለሚቀበል ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና የሌዋውያንን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ፤

ተፈጸመ ::

www.ethiopianorthodox.org